አዲስ ኪዳን

ማቴዎስ የጻፈው

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል

መግቢያ

የማቴዎስ ወንጌል ፥ ኢየሱስ የመምጣቱ ተስፋ አስቀድሞ የተነገረለት አዳኝ መሆኑንና እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ የሰጠውን የተስፋ ቃል የፈጸመውም በእርሱ አማካይነት መሆኑን የሚያበሥረውን የምሥራች ቃል የያዘ ነው ። ይህም የምሥራች ቃል ኢየሱስ በመካከላቸው ተወልዶ ላደገው ለአይሁዳውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጭምር ነው ።

የማቴዎስ ወንጌል በጥንቃቄ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው ፤ ከኢየሱስ መወለድ ይጀምርና ስለ ጥምቀቱና ስለ ፈተናው ካብራራ በኋላ በገሊላ የፈጸመውን የስብከት ፥ የማስተማርና የመፈወስ አገልግሎቱን ያቀርባል ፤ ከዚያም በመቀጠል ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ስላደረገው ጕዞና በዕድሜው መጨረሻ ሳምንት ስለሆኑት ነገሮች ይዘረዝራል ፤ እነዚህም ነገሮች ስቅለቱንና ትንሣኤውን ያጠቃልላሉ ።

ይህ ወንጌል ኢየሱስን ፥ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመተርጐም ሥልጣን ያለውና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስተምር ታላቅ መምህር እንደሆነ አድርጎ ያቀርበዋል ፤ ከትምህርቱ አብዛኛው ክፍል በተለያየ መልክ በተጠናቀሩ አምስት ክፍሎች ይመደባል ፦

1. የእግዚአብሔርን መንግሥት ዜጎች ጠባይ ፥ ሥራ ፥ መብትና የመጨረሻ ዕድል የሚያስረዳው የተራራው ስብከት (ከም. 5-7) ።
2. ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ለወንጌል ስብከት በተላኩበት ጊዜ የተሰጣቸው መመሪያዎች (ም. 10) ።
3. ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የቀረቡ ልዩ ልዩ ምሳሌዎች (ም. 13) ።
4. የደቀ መዛሙርትነትን ፍች የሚያስረዳ ትምህርት (ም. 18) ።
5. ስለ አሁኑ ዘመን ፍጻሜና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መምጣት የተሰጠ ትምህርት (ከም. 24-25) ።

ምዕራፍ 1

የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ
(ሉቃ. 3፥23-38)

1 የዳዊትና የአብርሃም ዘር የሆነው የኢየሱስ
ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ይህ ነው ፦-
2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ ፤ ይስሐቅ ያዕቆ
ብን ወለደ ፤ ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን
ወለደ ፤ 3 ይሁዳ ፋሬስንና ዛራሕን ትዕማር ከም
ትባል ሴት ወለደ ፤ ፋሬስ ሔጽሮንን ወለደ ፤
ሔጽሮንም ራምን ወለደ ፤ 4 ራም ዓሚናዳብን
ወለደ ፤ ዓሚናዳብ ነአሶንን ወለደ ፤ ነአሶን ሳል
ሞንን ወለደ ፤ 5 ሳልሞን በዔዝን ረዓብ ከምት
ባል ሴት ወለደ ፤ ቦዔዝ ኢዮቤድን ሩት ከምት
ባል ሴት ወለደ ፤ ኢዮቤድ እሴይን ወለደ ፤
6 እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ ።

ንጉሥ ዳዊት ሰሎሞንን ከእርዮን ሚስት
ወለደ ፤ 7 ሰሎሞን ሮብዓምን ወለደ ፤ ሮብዓም
አቢያን ወለደ ፤ አቢያ አሳፍን ወለደ ፤
8 አሳፍ ኢዮሣፍጥን ወለደ ፤ ኢዮሣፍጥ ኢዮ
ራምን ወለደ ፤ ኢዮራም ዖዝያንን ወለደ ፤
9 ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ ፤ ኢዮአታም አካ
ዝን ወለደ ፤ አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ ፤
10 ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ ፤ ምናሴ አሞንን
ወለደ ፤ አሞን ኢዮስያስን ወለደ ፤ 11 ኢዮስ
ያስ የእስራኤል ሕዝብ ወደ ባቢሎን ተማር
ከው በሄዱበት ዘመን ዮአኪንንና ወንድሞቹን
ወለደ ።

12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ዮአኪን ሰላትያልን
ወለደ ፤ ሰላትያል ዘሩባቤልን ወለደ ፤ 13 ዘሩባ
ቤል አብዩድን ወለደ ፤ አብዩድ ኤልያቂምን
ወለደ ፤ ኤልያቂም አዞርን ወለደ ፤ 14 አዞር ሳዶ
ቅን ወለደ ፤ ሳዶቅ አኪምን ወለደ ፤ አኪም
ኤልዩድን ወለደ ፤ 15 ኤልዩድ አልዓዛርን
ወለደ ፤ አልዓዛር ማታንን ወለደ ፤ ማታን ያዕቆ
ብን ወለደ ፤ 16 ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ ፤ ይህ

1፥1 ፡- ሙዝ. 132፥11 ፤ ኢሳ. 11፥1 ። 1፥1-11 ፡- 2ነገ. 24፥14-15 ፤ 2ዜ.መ. 36፥10 ፤ ኤር. 27፥20 ።
1፥6 ፡- ሩት 4፥18-22 ፤ 1ዜ.መ. 2፥13-15 ። 1፥11 ፡- 2ነገ. 24፥14 ፤ 1ዜ.መ. 3፥15-16 ።

ዮሴፍ መሲሕ[1] የተባለውን ኢየሱስን የወለደች
የማርያም እጮኛ ነበር ።
17 እንግዲህ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ፡ ፡ ፡

አነሣሣው ። [2]እዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
ከጾመ በኋላ ራበው ። [3]በዚህ ጊዜ ፈታኙ ዲያብ
ሎስ ወደ ኢየሱስ መጥቶ ፡ “አንተ የእግዚአብ
ሔር ልጅ ከሆንህ እስቲ እነዚህ ድንጋዮች እን
ጀራ እንዲሆኑ እዘዝ” አለው ።
[4]ኢየሱስም “‘ሰው የሚኖረው እግዚአብ
ሔር በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ
ብቻ አይደለም’ ተብሎ ተጽፎአል” አለው ።
[5]ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ ቅድ
ስት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው ፤ በቤተ
መቅደስ ጣራ ጫፍ ላይ አውጥቶም አቆመው ፤
[6]እንዲህም አለው ፥
“‘አንተን እንዲጠብቁ እግዚአብሔር
መላእክቱን ያዝልሃል ፤
እግርህም በድንጋይ እንዳይሰናከል
በእጆቻቸው ይዘው ይደግፉሃል’
ተብሎ ተጽፎአል ፤
ስለዚህ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ
እስቲ ከዚህ ወደታች ዘለህ ውረድ ።”
[7]ኢየሱስም “ደግሞ ‘እግዚአብሔር አምላክ
ህን አትፈታተነው’ ተብሎ ተጽፎአል” ሲል
መለሰለት ።
[8]ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን በጣም ከፍ
ወዳለ ተራራ ላይ አወጣው ፥ የዓለምን መንግሥ
ታት ሁሉ ከነክብራቸው አሳየውና ፥ [9]“ተንበር
ከክህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ”
አለው ።
[10]ኢየሱስም “ወዲያ ሂድ አንተ ሰይጣን ፥
‘ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ ፥ እርሱንም
ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአል” አለው ።
[11]ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ኢየሱስን ትቶት
ሄደ ፤ መላእክትም መጥተው ኢየሱስን አገለገ
ሉት ።

ኢየሱስ የማስተማር ሥራውን በገሊላ ጀመረ
(ማር. 1፡14-15፤ ሉቃ. 4፡14-15)

[12]ኢየሱስ የዮሐንስን መያዝና መታሰር
በሰማ ጊዜ ወደ ገሊላ ሄደ ፤ [13]የናዝሬትንም
ከተማ ትቶ ወደ ቅፍርናሆም ሄዶ ተቀመጠ ።
ቅፍርናሆም በዛብሎንና በንፍታሌም አውራጃ
በባሕር አጠገብ የምትገኝ ከተማ ናት ።
[14]ይህም የሆነው ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል
የተናገረው የትንቢት ቃል እንዲፈጸም ነው ፤
[15]“ወደ ባሕሩ በሚወስደው መንገድና
ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ
የሚገኙት የዛብሎን ምድር ፥
የንፍታሌም ምድር ፥
የአረማውያንም ገሊላ ፤
[16]እንዲሁም በጭለማ የሚኖር ሕዝብ
ታላቅ ብርሃን አየ ፤
ሞት ጥላውን በጣለበት ምድር
ለሚገኙትም ብርሃን ወጣላቸው ።”
[17]ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ “የእግዚአብ
ሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ” እያለ
ማስተማር ጀመረ ።

ኢየሱስ አራት ዓሣ አጥማጆችን ጠራ
(ማር. 1፡16-20፤ ሉቃ. 5፡1-11)

[18]ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ
ሁለት ወንድማማቾችን አየ ፤ እነርሱም ጴጥሮስ
የተባለው ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ ነበሩ ።
ዓሣ አጥማጆች ስለ ነበሩ መረባቸውን ወደ
ባሕር ይጥሉ ነበር ። [19]ኢየሱስም “ኑ ተከተ
ሉኝ ፤ እኔ ሰዎችን እንድታጠምዱ አደርጋችኋ
ለሁ” አላቸው ። [20]እነርሱም ወዲያውኑ መረባ
ቸውን ትተው ተከተሉት ።
[21]ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎች ሁለት ወንድ
ማማቾችን አየ ፤ እነርሱ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕ
ቆብና ዮሐንስ ነበሩ ። ከአባታቸው ከዘብዴዎስ
ጋር በጀልባ ላይ ሆነው መረባቸውን ያበጁ
ነበር ። ኢየሱስ እነርሱንም ጠራቸው ። [22]እነር
ሱም ወዲያውኑ ጀልባዋንና አባታቸውን
ትተው ተከተሉት ።

ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን እንዳስተማረና እንደፈወሰ
(ሉቃ. 6፡17-19)

[23]ኢየሱስ የአይሁድ ጸሎት ቤቶች በሆኑት
ምኩራቦች[3*] እያስተማረና የእግዚአብሔርን መን
ግሥት የምሥራች ቃል እያበሠረ ፥ በገሊላ ሁሉ
ይዘዋወር ነበር ። በልዩ ልዩ በሽታና ደዌ የተያ
ዙትንም ሰዎች ይፈውስ ነበር ። [24]ዝናው በሶ
ርያ አገር ሁሉ ስለተሰማ ፥ ሰዎች በልዩ ልዩ በሽ
ታና ደዌ የሚሠቃዩትን ሁሉ ወደ እርሱ
አመጡ ፤ ከበሽተኞችም መካከል ርኵሳን መናፍ
ስት ያደሩባቸው ፥ የሚጥል በሽታ ያለባቸውና
ሽባዎችም ይገኙባቸው ነበር ። ኢየሱስ ግን ሁሉ
ንም ፈወሳቸው ። [25]ከገሊላና ከዐሥሩ ከተሞች
ከኢየሩሳሌምና ከይሁዳ ፥ ከዮርዳኖስም ወንዝ
ማዶ የመጡ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉት ።

ምዕራፍ 5

ኢየሱስ በተራራ ላይ ሆኖ
ያስተማረው ትምህርት
(ከም. 5-7)

[1]ኢየሱስ ብዙ ሕዝብ ባየ ጊዜ ወደ ተራራ
ወጥቶ ተቀመጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ

3* 4፡23 ምኩራቦች ፡- በመሠረቱ መሰብሰቢያ ቦታዎች ሲሆኑ የአይሁድ ጸሎት ቤትም “ምኩራብ” ይባላል ።

4፡2 ፡- ዘጸ. 34፡28 ፤ 1ነገ. 19፡8 ። 4፡4 ፡- ዘዳ. 8፡3 ። 4፡5 ፡- ነህ. 11፡1 ፤ ዳን. 9፡24 ። 4፡6 ፡- መዝ. 91፡11-12 ።
4፡7 ፡- ዘዳ. 6፡16 ። 4፡10 ፡- ዘዳ. 6፡13 ። 4፡12 ፡- ማቴ. 14፡3 ፤ ማር. 6፡17 ፤ ሉቃ. 3፡19-20 ። 4፡13 ፡- ዮሐ. 2፡12 ።
4፡15-16 ፡- ኢሳ. 9፡1-2 ። 4፡17 ፡- ማቴ. 3፡2 ። 4፡23 ፡- ማቴ. 9፡35 ፤ ማር. 1፡39 ።

እርሱ ቀረቡ ። [2]እንዲህ እያለም ያስተምራቸው
ጀመር ፤

እውነተኛ ደስታ
(ሉቃ. 6፡20-23)

[3] “በመንፈስ ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ፥
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለ ሆነች
ደስ ይበላቸው ።
[4] የሚያዝኑ ፥ እግዚአብሔር መጽናናትን
ስለሚሰጣቸው
ደስ ይበላቸው ።
[5] የዋሆች ፥ ምድርን ስለሚወርሱ
ደስ ይበላቸው ።
[6] ጽድቅ እንደ እህል የሚርባቸውና እንደ
ውሃ የሚጠማቸው ፥
ጽድቅን አግኝተው ስለሚረኩ
ደስ ይበላቸው ።
[7] ምሕረትን የሚያደርጉ ፥ ምሕረትን
ስለሚያገኙ ደስ ይበላቸው ።
[8] ንጹሕ ልብ ያላቸው ፥ እግዚአብሔርን
ስለሚያዩት ደስ ይበላቸው ።
[9] በሰዎች መካከል እርቅና ሰላምን
የሚያደርጉ ፥
የእግዚአብሔር ልጆች ስለሚባሉ
ደስ ይበላቸው ።
[10] ስለ ጽድቅ ስደትና መከራን የሚቀበሉ ፥
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለ ሆነች
ደስ ይበላቸው ።
[11] “በእኔ ምክንያት ሰዎች ሲሰድቡአችሁና
ሲያሳድዱአችሁ ፥ በውሸትም ስማችሁን ሲያ
ጠፉ ደስ ይበላችሁ ። [12]በመንግሥተ ሰማይ
የምታገኙት ዋጋ ትልቅ ስለ ሆነ ደስ ይበላ
ችሁ ፤ በደስታም ፈንድቁ ። ምክንያቱም ከእና
ንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ ስደትና
መከራ አድርሰውባቸዋል ።”

ስለ ጨውና ስለ ብርሃን ምሳሌነት
(ማር. 9፡50፤ ሉቃ. 14፡34-35)

[13] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “እናንተ
የምድር ጨው ናችሁ ፤ ነገር ግን ጨው ጣዕ
ሙን ካጣ እንዴት ጣዕሙን መልሶ ሊያገኝ
ይችላል? ወደ ውጪ ከመጣልና በሰው እግር
ከመረገጥ በቀር ከእንግዲህ ወዲያ ለምንም አይ
ጠቅምም ። [14]እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ፤
በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላ
ትም ። [15]መብራት አብርቶ እንቅብ የሚደፋ
በት ማንም የለም ። ይልቅስ በቤት ውስጥ
ላሉት ሁሉ እንዲያበራ ብርሃኑ በሚታይበት
በከፍተኛ ቦታ ላይ ያደርገዋል ። [16]እንዲሁም
ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ
አባታችሁን እንዲያመሰግኑት የእናንተም ብር
ሃን በሰው ፊት ይብራ ።”

ስለ ሙሴ ሕግ

[17] ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “የሙሴን
ሕግና የነቢያትን ትምህርት ለመሻር የመጣሁ
አይምሰላችሁ ፤ እኔ ፍጹም እንዲሆኑ ላደርጋ
ቸው መጣሁ እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም ።
[18]በእውነት እላችኋለሁ ፥ ሰማይና ምድር እስ
ኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ
ከሕግ እንዴት ጭረት ወይም እንዴት ነጥብ
አትሻርም ። [19]ስለዚህ ከእነዚህ ትእዛዞች አነስ
ተኛ የሆነችውን አንድዋን እንኳ የሚያፈርስና
ሌሎችም ሰዎች እንዲህ እንዲያደርጉ የሚያስተ
ምር ሰው በመንግሥተ ሰማይ አነስተኛ ይሆ
ናል ። ነገር ግን ትእዛዞችን ሁሉ የሚፈጽምና
ሌሎችም ሰዎች እንዲሁ እንዲፈጽሙ የሚያስ
ተምር ሰው በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይሆ
ናል ። [20]የእናንተ ጽድቅ ከሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግ
ሥተ ሰማይ ከቶ አትገቡም እላችኋለሁ ።
[21]“በቀድሞ ጊዜ ለነበሩ ሰዎች የተባለውን
ሰምታችኋል ፤ ይኸውም ‘አትግደል ፤ ሰውን የገ
ደለ ይፈረድበታል’ የሚል ነው ። [22]እኔ የምላ
ችሁ ግን ይህ ነው ፤ ሰውን የሚቈጣ ሁሉ ይፈረ
ድበታል ፤ ደግሞም ማንንም ሰው ‘አንተ የማት
ረባ’ ብሎ የሚሳደብ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል ፤
‘ደደብ’ ብሎ የሚሳደብ ሁሉ ለገሃነመ እሳት
ፍርድ የተገባ ይሆናል ። [23]ስለዚህ መባህን በመ
ሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት
ጊዜ ያዘነብህ ሰው መኖሩን ብታስታውስ ፥
[24]መባህን በመሠዊያው ፊት አስቀምጥና ሄደህ
በመጀመሪያ ከዚያ ሰው ጋር ታረቅ ፤ ከዚህም
በኋላ ተመልሰህ መባህን አቅርብ ። [25]ባላጋራህ
ከሶህ ከእርሱ ጋር ወደ ፍርድ ቤት ስትሄድ በመ
ንገድ ላይ ሳለህ ቶሎ ብለህ ከባላጋራህ ጋር ተስ
ማማ ። አለበለዚያ ባላጋራህ ለዳኛ አሳልፎ ይሰጥ
ሃል ፤ ዳኛውም ለፖሊስ አሳልፎ ይሰጥህና ወደ
ወህኒ ቤት ትገባለህ ። [26]በእውነት እልሃለሁ ፥
መቀጮህን እስከ መጨረሻዋ ሳንቲም ከፍለህ እስ
ክትጨርስ ድረስ ከዚያ አትወጣም ።”

ማመንዘር አይገባም

[27] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “‘አታመ
ንዝር’ እንደተባለ ሰምታችኋል ። [28]እኔ ግን እን
ዲህ እላችኋለሁ ፥ ሴትን ተመልክቶ የተመኛት

5፡4 ፡- ኢሳ. 61፡2 ። 5፡5 ፡- መዝ. 37፡11 ። 5፡6 ፡- ኢሳ. 55፡1-2 ። 5፡8 ፡- መዝ. 24፡3-4 ። 5፡10 ፡- 1ጴጥ. 3፡14 ።
5፡11 ፡- 1ጴጥ. 4፡14 ። 5፡12 ፡- 2ዜ.መ. 36፡16 ፤ ሐሥ. 7፡52 ። 5፡13 ፡- ማቴ. 9፡50 ፤ ሉቃ. 14፡34-35 ።
5፡14 ፡- ዮሐ. 8፡12 ፤ 9፡5 ። 5፡15 ፡- ማር. 4፡21 ፤ ሉቃ. 8፡16 ፤ 11፡33 ። 5፡16 ፡- 1ጴጥ. 2፡12 ።
5፡18 ፡- ሉቃ. 16፡17 ። 5፡21 ፡- ዘጸ. 20፡13 ፤ ዘዳ. 5፡17 ፤ 16፡18 ። 5፡27 ፡- ዘጸ. 20፡14 ፤ ዘዳ. 5፡18 ።

ሁሉ ፥ ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር እንዳመነ
ዘረ ይቈጠራል ።' 29 ስለዚህ ቀኝ ዐይንህ የኃጢ
አት ምክንያት ቢሆንብህ አውጥተህ ጣለው ፤
ምክንያቱም ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚ
ጣል ይልቅ ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ
ይሻልሃል ። 30 ቀኝ እጅህ የኃጢአት ምክንያት
ቢሆንብህ ቈርጠህ ጣለው ፤ ምክንያቱም ሰውነ
ትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከሰው
ነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል ።"

መፋታት አይገባም
(ማቴ. 19፥9፤ ማር. 10፥11-12፤ ሉቃ. 16፥18)

31 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "እንዲ
ሁም 'ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የተፈታች ሆነን
ምክንያት የሚገልጽ ጽሑፍ ይስጣት' ተብሎ
አል ። 32 እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ፤ በዝሙት
ምክንያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ
እንድታመነዝር ምክንያት ይሆንባታል ። የተፈታ
ችውንም የሚያገባ ሁሉ አመንዝራ ይሆናል ።"

ስለ መሐላ

33 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "እንዲ
ሁም በቀድሞ ጊዜ ለነበሩት ሰዎች 'በመሐላ
ለእግዚአብሔር የሰጠኸውን ቃል ፈጽም እንጂ
የመሐላ ቃልህን አታፍርስ' እንደተባለ ሰም
ታችኋል ። 34 እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ፤ በጭ
ራሽ አትማሉ ፤ በሰማይም ቢሆን አትማሉ ፤ ምክ
ንያቱም ሰማይ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው ።
35 በምድርም ቢሆን አትማሉ ፤ ምክንያቱም
ምድር የእግዚአብሔር እግር ማሳረፊያ ናት ።
በኢየሩሳሌምም ቢሆን አትማሉ ፤ ምክንያቱም
ኢየሩሳሌም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናት ። 36 በራ
ስህም ቢሆን አትማል ፤ ምክንያቱም ከጠጕርህ
አንዱቱን እንኳ ነጭ ወይም ጥቁር ማድረግ አት
ችልም ። 37 ስለዚህ ንግግራችሁ 'አዎ' ከሆነ
'አዎ ፥' 'አይደለም' ከሆነ 'አይደለም' ይሁን ።
ከዚህ የተረፈ ቃል ግን ከሰይጣን ነው ።"

ቂም በቀል መያዝ አይገባም
(ሉቃ. 6፥29-30)

38 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "'ዐይን
ስለ ዐይን ፥ ጥርስ ስለ ጥርስ' እንደ ተባለ ሰም
ታችኋል ። 39 እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ፥ ክፉ
የሚያደርግባቸሁን ሰው አትበቀሉት ። ነገር ግን
ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ፥ ግራ ጉንጭህን
አዙርለት ። 40 እንድ ሰው ሸሚዝህን ለመውሰድ
ፈልጎ ቢከሰህ ፥ ኮትህንም እንዲወስድ ተው
ለት ። 41 አንድ ሰው 'ካእኔ ጋር ጥቂት መንገድ
ሂድ' ብሎ ቢያስገድድህ ፥ አንተ እጥፍ መንገድ
ሂድለት ። 42 ለሚለምንህ ስጥ ፤ ከአንተ መበደር
ለሚፈልግ አትከልክል ።"

ጠላትን ስለ መውደድ
(ሉቃ. 6፥27-36)

43 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "'ባልን
ጀራህን ውደድ ፤ ጠላትህን ጥላ' እንደተባለ
ሰምታችኋል ። 44 እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ ፥
ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ ስደትና መከራ ለሚያደ
ርሱባችሁም ጸልዩላቸው ።

45 "ይህን ብታደርጉ በሰማይ ላለው አባታ
ችሁ ልጆች ትሆናላችሁ ። እርሱ ለክፉዎችና
ለቅኖች ፀሐዩን ያወጣል ፤ እንዲሁም ለደጋግ
ሰዎችና ለኃጢአተኞች ዝናሙን ያዘንማል ።
46 የሚወዱአችሁን ሰዎች ብትወዱ ምን ዋጋ
አላችሁ? ኃጢአተኞችስ ይህንኑ ያደርጉ የለ
ምን? 47 ለወንድሞቻችሁ ብቻ ሰላምታ የምት
ሰጡ ከሆነ ምን ብልጫ ያለው ነገር ታደርጋላ
ችሁ? አረማውያንስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን?
48 "ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደ
ሆነ ፥ እናንተም ፍጹሞች ሁኑ ።"

ምዕራፍ 6

ስለ ምጽዋት አሰጣጥ

1 ኢየሱስ ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ ፥
"ሰዎች ይዩልን ብላችሁ መልካም ሥራችሁን
በሰው ፊት ከማድረግ ተጠንቀቁ ። አለበለዚያም
በሰማይ ካለው አባታችሁ ምንም ዋጋ አታገ
ኙም ። 2 ስለዚህ አንተ ለድኻ በምትመጽውትበት
ጊዜ ግብዞች ከሰዎች ምስጋና ለማግኘት ብለው
በየምኩራቡና በየመንገዱ እንደሚያደርጉት ለታ
ይታ አታድርግ ። በእውነት እላችኋለሁ ፥ እነርሱ
ዋጋቸውን በቅድሚያ አግኝተዋል ። 3 አንተ ግን
ለድኻ በምትመጽውትበት ጊዜ ፥ ቀኝ እጅህ የሚ
ሰጠውን ግራ እጅህ እንኳ አይወቅ ። 4 ምክንያ
ቱም ምጽዋትህ በስውር መሆን አለበት ፤ በስ
ውር የተሠራውን የሚያይ አባትህም የመልካም
ሥራህን ዋጋ ይከፍልሃል ።"

ስለ ጸሎት
(ሉቃ. 11፥2-4)

5 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "በምትጸል
ይበት ጊዜ እንደ ግብዞች አትሁኑ ፤ እነርሱ

5፥29 ፡- ማቴ. 18፥9፤ ማር. 9፥47 ። 5፥30 ፡- ማቴ. 18፥8፤ ማር. 9፥43 ። 5፥31 ፡- ዘዳ. 24፥1-4፤ ማቴ. 19፥7፤ ማር. 10፥4 ።
5፥32 ፡- ማቴ. 19፥9፤ ማር. 10፥11-12፤ ሉቃ. 16፥18፤ 1ቆሮ. 7፥10-11 ። 5፥33 ፡- ዘሌ. 19፥12፤ ዘኁ. 30፥2፤ ዘዳ. 23፥21 ።
5፥34 ፡- ያዕ. 5፥12፤ ኢሳ. 66፥1፤ ማቴ. 23፥22 ። 5፥35 ፡- ኢሳ. 66፥1፤ መዝ. 48፥2 ። 5፥37 ፡- ዘሌ. 19፥12፤ ዘኁ. 30፥2፤
ዘዳ. 23፥21 ። 5፥38 ፡- ዘጽ. 21፥24፤ ዘሌ. 24፥20፤ ዘዳ. 19፥21 ። 5፥42 ፡- ዘዳ. 15፥8፤ ምሳ. 24፥29 ።
5፥43 ፡- ዘሌ. 19፥18 ። 5፥44 ፡- ምሳ. 25፥21-22 ። 5፥48 ፡- ዘሌ. 19፥2፤18፤ ዘዳ. 18፥13 ። 6፥1 ፡- ማቴ. 23፥5 ።
6፥5 ፡- ሉቃ. 18፥10-14 ።

ሰው እንዲያይላቸው ብለው በየምኩራቡና በየመ
ንገዱ ዳር ቆመው መጸለይ ይወዳሉ ። በእውነት
እላችኋለሁ እነርሱ ዋጋቸውን በቅድሚያ አግኝ
ተዋል ። 6 አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ቤትህ ገብ
ተህ በርህን ዝጋና በስውር ወዳለው ወደማይታይ
አባትህ ጸልይ ፤ በስውር የተሠራውን የሚያይ
አባትህም የመልካም ሥራህን ዋጋ ይከፍልሃል ።
7 "እናንተ ስትጸልዩ እንደ አረማውያን ከንቱ
ቃል በመደጋገም አትለፍልፉ ፤ እነርሱ በልፍለ
ፋቸው ብዛት እግዚአብሔር የሚሰማቸው ይመስ
ላቸዋል ። 8 እናንተ ግን እንደ እነርሱ አትሁኑ ፤
ምክንያቱም አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ገና
ሳትሰምኑት አስቀድሞ ያውቃል ። 9 ስለዚህ እና
ንተ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ ፥
'በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ!
ስምህ ይቀደስ ፥
10 መንግሥትህ ትምጣ ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ ፥
እንዲሁም በምድር ይሁን ።
11 የዕለት እንጀራችንን በየቀኑ ስጠን ።
12 እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል ፥
በደላችንን ይቅር በልልን ፤
13 ከክፉ አድነን እንጂ ፥
ወደ ፈተና አታግባን ፤
[መንግሥት ፥ ኀይል ፥ ክብር ፤
ለዘላለም ያንተ ነው ፤ አሜን ።']
14 "የሰዎችን በደል ይቅር ብትሉላቸው እና
ንተንም የሰማዩ አባታችሁ ይቅር ይላችኋል ።
15 የሰዎችን በደል ይቅር ባትሉላቸው ግን የእና
ንተንም በደል የሰማዩ አባታችሁ ይቅር አይልላ
ችሁም ።"

ስለ ጾም

16 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "በምትጾ
ሙበት ጊዜ ግብዞች እንደሚያደርጉት የሐዘን
መልክ አታሳዩ ፤ እነርሱ ጾመኞች መሆናቸውን
ሰው እንዲያውቅላቸው የሐዘን መልክ ያሳያሉ ፤
በእውነት እላችኋለሁ ፥ እነርሱ ዋጋቸውን በቅድ
ሚያ ተቀብለዋል ። 17 አንተ ግን በምትጾምበት
ጊዜ ፊትህን ታጠብ ፤ ቅባትም ተቀባ ። 18 በዚህ
አኳኋን መጾምህን በስውር ካለው አባትህ በቀር
ሌላ ማንም አያየውም ። በስውር የተሠራውን
የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል ።"

በምድር ላይ ሀብት ማከማቸት አይገባም
(ሉቃ. 12፥33-34)

19 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "ለራሳ
ችሁ በዚህ ምድር ላይ ሀብት አታከማቹ ፤ ምክ
ንያቱም በዚህ ምድር ላይ ብልና ዝገት ያጠፋ
ዋል ፤ ሌቦችም ሰብረው ይሰርቁታል ፤ 20 ይል
ቅስ ለራሳችሁ በሰማይ ሀብት አከማቹ ፤ በዚያ
ያለውን ሀብት ብልና ዝገት ሊያጠፋው አይች
ልም ፤ ሌቦችም ቈፍረው ሊሰርቁት አይች
ሉም ። 21 ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያ ይገ
ኛል ።"

የሰውነት መብራት
(ሉቃ. 11፥34-36)

22 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "ዐይን
የሰውነት መብራት ነው ፤ ስለዚህ ዐይንህ
ጤናማ ከሆነ ሰውነትህ በሙሉ ብርሃን ይሆ
ናል ፤ 23 ዐይንህ ጤናማ ካልሆነ ግን ሰውነትህ
በሙሉ ጨለማ ይሆናል ። እንግዲህ በአንተ
ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ ፥ ጨለማው እን
ዴት የባሰ ይሆን!"

ስለ ኑሮ መጨነቅ አይገባም
(ሉቃ. 16፥13፤ 12፥22-31)

24 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "አንድ
ሰው የሁለት ጌታ አገልጋይ ሊሆን አይችልም ፤
አንዱን ይጠላል ፥ ሌላውንም ይወዳል ፤ አንዱን
ያክብራል ፥ ሌላውን ይንቃል ፤ እንዲሁም የገን
ዘብ ተገዥ የሆነ ሰው ፥ የእግዚአብሔር አገል
ጋይ መሆን ከቶ አይችልም ። 25 ስለዚህ እንዲህ
እላችኋለሁ ፥ 'ምን እንበላለን? ምን እንጠጣ
ለን? ምንስ እንለብሳለን?' በማለት ስለኑሮአችሁ
አትጨነቁ ፤ ከምግብ ሕይወት ፤ ከልብስም ሰው
ነት አይበልጥምን? 26 እስቲ በሰማይ የሚበሩ
ትን ወፎች ተመልከቱ ፤ እነርሱ አይዘሩም ፤
አያጭዱም ፤ በጐተራ አይከቱም ፤ ነገር ግን የሰ
ማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል ። ታዲያ እናንተ
ከወፎች እጅግ ትበልጡ የለምን? 27 ለመሆኑ
ከእናንተ በማሰብና በመጨነቅ በዕድሜው ላይ
አንድ ቀን* እንኳ መጨመር የሚችል ማን
ነው? 28 ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን ትጨነቃላ
ችሁ? የዱር አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ
እስቲ ተመልከቱ ፤ እነርሱ በሥራ አይደክ
ሙም ፤ አይፈትሉም ፤ 29 ነገር ግን ሰሎሞን
እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ ከእነርሱ እንደ አን
ዱቱ ፥ እንዲህ ያጌጠ ልብስ አልለበሰም እላችኋ
ለሁ ። 30 ታዲያ ዛሬ ታይቶ ነገ በእሳት ውስጥ
የሚጣለውን የሜዳ ሣር እግዚአብሔር እንዲህ
አስጊጦ የሚያለብስ ከሆነ ፥ እናንተ እምነት
የጐደላችሁ ፥ እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያ
ለብሳችሁም! 31 ስለዚህ 'ምን እንበላለን? ምን
እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?' እያላችሁ

4* 6፥27 በዕድሜው ላይ አንድ ቀን ፡- በአንዳንድ ትርጉም "በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ" የሚል ይገኛል ።
6፥7 ፡- ነገ. 18፥25-29 ። 6፥14-15 ፡- ማቴ. 11፥25-26 ። 6፥16 ፡- ኢሳ. 58፥5 ። 6፥19 ፡- ያዕ. 5፥2-3 ።
6፥27 ፡- መዝ. 39፥5-7 ። 6፥29 ፡- ነገ. 10፥4-7፤ 2ዜ.መ. 9፥3-6 ።

በማሰብ አትጨነቁ ። 32 ይህንን ለማግኘትማ አረ
ማውያንም ይጨነቁበታል ፤ እናንተ ይህ ሁሉ
እንደሚያስፈልጋችሁ የሰማይ አባታችሁ ያው
ቃል ። 33 እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብ
ሔርን መንግሥትና የእግዚአብሔርን ጽድቅ
ፈልጉ ፤ ሌላውም የቀረው ነገር ሁሉ ይጨመር
ላችኋል ፤ 34 የነገው ጭንቀት ለነገው ይበቃል ፤
ስለዚህ ለነገ በማሰብ አትጨነቁ ፤ እያንዳንዱ
ቀን በቂ የሆነ የራሱ ችግር አለው ።”

ምዕራፍ 7

በሌሎች ላይ መፍረድ አይገባም
(ሉቃ. 6፡37-42)

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በእናንተ
ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አት
ፍረዱ ፤ 2 ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈር
ዱበት ዐይነት በእናንተም ላይ ይፈረድባችኋል ፤
እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈር
ባችኋል ። 3 በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ ሳታይ
ስለምን በሌላ ሰው ዐይን ያለውን ጉድፍ ትመለ
ከታለህ? 4 ደግሞስ በአንተ ዐይን ያለውን ግንድ
ሳታይ ሌላውን ሰው ‘እስቲ በዐይንህ ያለውን
ጉድፍ ላውጣልህ’ እንዴት ትለዋለህ? 5 አንተ
ግብዝ! አስቀድመህ በአንተ ዐይን ያለውን
ግንድ አውጣ ፤ ከዚያም በኋላ በሌላ ሰው ዐይን
ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ ።
6 የተቀደሰውን ነገር ለውሾች አትስጡ ፤ ዕንቊ
አችሁንም በዐሣማዎች ፊት አትጣሉ ፤ ምክንያ
ቱም ዐሣማዎቹ ዕንቊአችሁን በእግራቸው ይረ
ግጡታል ፤ ውሾቹም ተመልሰው ይነክሱ
አችኋል ።”

የጸሎት ውጤት
(ሉቃ. 11፡9-13)

7 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ለምኑ ፥
ይሰጣችኋል ፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ ፤ በር አንኳኩ
ይከፈትላችኋል ፤ 8 ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ
ይሰጠዋል ፤ የሚፈልግ ያገኛል ፤ በር ለሚ
ያንኳኳ ይከፈትለታል ። 9 ከእናንተ አባት ሆኖ
ልጁ ዳቦ ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው
ማነው? 10 ዓሣ ቢለምነውስ እባብ ይሰጠዋልን?
11 እንግዲህ እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳለ ለል
ጆቻችሁ መልካም ነገር መስጠት ታውቃላ
ችሁ ፤ ታዲያ በሰማይ ያለው አባታችሁማ ለሚ
ለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገር አይሰ
ጣቸውም? 12 እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ
የምትፈልጉትን ሁሉ እናንተም ለእነርሱ እን
ዲሁ አድርጉላቸው ፤ የሙሴ ሕግና የነቢያት
ትምህርትም የሚሉት ይህንኑ ነው ።”

ስለ ጠባብዋ በር
(ሉቃ. 13፡24)

13 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በጠባ
ብዋ በር ግቡ ፥ ምክንያቱም ወደ ጥፋት የሚያ
ስገባው በር ሰፊ ፥ ወደ ጥፋት የሚወስደውም
መንገድ ትልቅ ነው ። ወደዚያ የሚገቡትም
ሰዎች ብዙዎች ናቸው ። 14 ወደ ሕይወት የም
ታስገባዋ በር ግን ጠባብ ናት ፤ መንገዱም አስ
ቸጋሪ ነው ፤ ስለዚህ እርስዋን የሚያገኙዋት
ሰዎች ጥቂቶች ናቸው ።”

ዛፍ በፍሬው ይታወቃል
(ሉቃ. 6፡43-44)

15 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ከሐሰተ
ኞች መምህራን ተጠንቀቁ ፤ እነርሱ በውጪያ
ቸው በግ መስለው ወደ እናንተ ይመጣሉ ፤
በውስጣቸው ግን እንደ ነጣቂ ተኩላ ናቸው ።
16 እነርሱንም የምታውቁአቸው በሥራቸው
ፍሬ ነው ። ከእሾኽ ቍጥቋጦ የወይን ፍሬ ይለ
ቀማልን? ከኮሽሽላስ የበለስ ፍሬ ይለቀማልን?
17 እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ ያፈ
ራል ፤ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል ።
18 ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ ማፍራት አይችልም ፤
መጥፎ ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም ።
19 ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ፤
ወደ እሳትም ይጣላል ። 20 ስለዚህ ሐሰተኞች
መምህራንን በሥራቸው ፍሬ ታውቁአቸዋላ
ችሁ ። 21 “ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ!” የሚለኝ ሁሉ
ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም ፤ ወደ መንግ
ሥተ ሰማይ የሚገባው በሰማይ ያለውን የአባቴን
ፈቃድ የሚፈጽም ነው ። 22 በፍርድ ቀን ብዙ
ዎች “ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት
አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣ
ንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግን
ምን?” ይሉኛል ። 23 እኔም በዚያ ቀን “በጭራሽ
አላውቃችሁም! እናንተ በመፀኞች ከእኔ ወዲያ
ራቁ!” እላቸዋለሁ ።”

በአለት ወይም በአሸዋ ላይ
የተሠሩ ቤቶች ምሳሌ
(ሉቃ. 6፡47-49)

24 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ይህን
ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የሚያውለው ሁሉ
ቤቱን በአለት ላይ የሠራውን ብልኅ ሰው ይመስ
ላል ። 25 ዝናም ዘነመ ፥ ጐርፍ ጐረፈ ፥ ነፋስም
ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ፤ ይህን እንጂ ቤቱ
በአለት ላይ ስለተመሠረተ አልወደቀም ። 26 ይህ
ንን ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለው ግን

7፡2 ፡- ማር. 4፡24 ። 7፡12 ፡- ሉቃ. 6፡31 ። 7፡14 ፡- ኤር. 21፡8 ፤ ዘዳ. 30፡19 ። 7፡15 ፡- ሕዝ. 22፡27 ።
7፡19 ፡- ማቴ. 3፡10 ፤ ሉቃ. 3፡9 ። 7፡20 ፡- ማቴ. 12፡33 ። 7፡23 ፡- መዝ. 6፡8 ።

ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራውን ሞኝ ሰው ይመስ
ላል ። 27 ዝናም ዘነመ ፥ ጐርፍም ጐረፈ ፥ ነፋ
ስም ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ፤ ቤቱም ወዲያ
ውኑ ወደቀ ፤ አወዳደቁም እጅግ የከፋ ሆነ ።”
28 ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሮ ባበቃ ጊዜ
ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ ። 29 ምክንያቱም
እርሱ እንደ ሕግ መምህሮቻቸው ሳይሆን እንደ
ባለሥልጣን ያስተምራቸው ስለነበረ ነው ።

ምዕራፍ 8

ኢየሱስ ለምጻሙን[5*] ሰው አነጻ
(ማር. 1፡40-45 ፤ ሉቃ. 5፡12-16)

1 ኢየሱስ ከተራራው በወረደ ጊዜ ብዙ
ሕዝብ ተከተለው ። 2 በዚህ ጊዜ አንድ ለምጻም
ሰው ወደ ኢየሱስ መጣ ፤ በግንባሩም ተደፍቶ
“ጌታ ሆይ! ብትፈቅድስ ልታነጻኝ ትችላለህ!”
አለ ። 3 ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና
“ፈቅጃለሁ ፥ ንጻ!” አለው ። ለምጻሙም ወዲያ
ውኑ ከለምጹ ነጻ ። 4 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከለ
ምጹ የዳነውን ሰው እንዲህ አለው ፥ “ይህን
ነገር ለማንም አትናገር ፤ ነገር ግን አሁን ሄደህ
መዳንህን ለካህን አሳይ ፤ ለሁሉም ምስክር እን
ዲሆን ስለ መዳንህ ሙሴ ያዘዘውን መባ ለእግዚ
አብሔር አቅርብ ።”

ኢየሱስ የመቶ አለቃውን አገልጋይ ፈወሰ
(ሉቃ. 7፡1-10)

5 ኢየሱስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ በገባ ጊዜ
አንድ ሮማዊ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ ፥
6 “ጌታ ሆይ! አገልጋዬ ሽባ ሆኖ እጅግ በመሠ
ቃየት በቤት ተኝቶአል” ብሎ ለመነው ። 7 ኢየ
ሱስም “እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ” አለው ።
8 የመቶ አለቃው ግን እንዲህ ሲል መለሰ ፥
“ጌታ ሆይ! አንተ ወደ ቤቴ እንድትገባ የበ
ቃሁ ሰው አይደለሁም ፤ ነገር ግን እንዲት ቃል
ብቻ ተናገር አገልጋዬም ይድናል ። 9 እኔ ራሴ
ለባለ ሥልጣኖች ታዛዥ ስሆን ከእኔ በታች የማ
ዛቸው ወታደሮች አሉኝ ፤ ከእነርሱ አንዱን
‘ሂድ!’ ስለው ይሄዳል ፤ ሌላውንም ‘ና!’ ስለው
ይመጣል ፤ አገልጋዬም ‘ይህን አድርግ!’ ስለው
ያደርጋል ።”
10 ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ ተደነቀ ፤ ይከተ
ሉት የነበሩትን ሰዎች እንዲህ አላቸው ፥ “በእ
ውነት እላችኋለሁ ይህን የሚያህል ትልቅ እም
ነት ያለው አንድም ሰው በእስራኤል አላገኘ
ሁም ። 11 ይህን አስተውሉ ፥ ብዙዎች ከምሥራ
ቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ፤ ከአብርሃም ፥ ከይስ
ሐቅ ፥ ከያዕቆብ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ይቀመ
ጣሉ ። 12 የዚህ መንግሥት ወራሾች መሆን ይገ
ባቸው የነበሩት ግን በውጪ ወደ ጨለማ ይጣ
ላሉ ። በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆ
ናል ።” 13 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ የመቶ አለቃውን
“ሂድ ፥ እንደ እምነትህ ይሁንልህ” አለው ።
አገልጋዩም በዚያኑ ሰዓት ተፈወሰ ።

ኢየሱስ ብዙ ሰዎችን ከበሽታቸው ፈወሰ
(ማር. 1፡29-34 ፤ ሉቃ. 4፡38-41)

14 ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት በገባ ጊዜ የጴ
ጥሮስ ዐማት አተኩሶአት ታማ እንደ ተኛች
አየ ። 15 እጅዋንም በዳሰሳት ጊዜ ወዲያው ትኩ
ሳቱ ለቀቃትና ዳነች ፤ ተነሥታም ኢየሱስን
ታገለግል ጀመር ። 16 በመሸም ጊዜ ሰዎች በአ
ጋንንት የተያዙ ብዙ በሽተኞችን ወደ ኢየሱስ
አመጡ ፤ ኢየሱስም በቃሉ ርኵሳን መናፍስትን
አስወጣ ፤ በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ ። 17 ይህን
ንም በማድረጉ በነቢዩ ኢሳይያስ ፥ “እርሱ ደዌ
አችንን ተቀበለ ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ” የተ
ባለው ትንቢት ተፈጸመ ።

የኢየሱስ ተከታዮች የሚገጥማቸው ችግር
(ሉቃ. 9፡57-62)

18 ኢየሱስ ብዙ ሰዎች በዙሪያው ተሰብስ
በው ባየ ጊዜ ወደ ባሕሩ ማዶ እንዲሻገሩ ደቀ
መዛሙርቱን አዘዘ ። 19 ከዚህ በኋላ አንድ
የሙሴ ሕግ መምህር ወደ ኢየሱስ መጥቶ
“መምህር ሆይ! ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተ
ልህ” አለው ። 20 ኢየሱስም “ቀበሮዎች
ጉድጓድ አላቸው ፤ በአየር ላይ የሚበሩ ወፎ
ችም የሚሰፍሩበት ጎጆ አላቸው ፤ የሰው ልጅ
ግን ራሱን እንኳ አስጠግቶ የሚያርፍበት ስፍራ
የለውም” ሲል መለሰለት ። 21 ከደቀ መዛሙር
ቱም አንዱ “ጌታ ሆይ! መጀመሪያ ሄጄ አባ
ቴን እንድቀብር[6*] ፍቀድልኝ” አለው ። 22 ኢየ
ሱስም “አንተ እኔን ተከተለኝ ፤ ሙታን ግን
ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው” አለው ።

ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ
(ማር. 4፡35-41 ፤ ሉቃ. 8፡22-25)

23 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር በጀልባ ተሳፍሮ ሄደ ። 24 ትልቅ ውሎ
ነፋስ በባሕሩ ላይ ስለ ተነሣ ማዕበሉ ጀልባዪ
ቱን ሸፈናት ፤ ኢየሱስ ግን ተኝቶ ነበር ።
25 ደቀ መዛሙርቱም ወደ ኢየሱስ ቀርበው
“ጌታ ሆይ! ልንጠፋ ነው ፤ አድነን!” ብለው
ቀሰቀሱት ።

5* 8፡1 ለምጽ ፡- እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ ቃሉ በሰውነት ላይ የሚታይን ልዩ ልዩ ዐይነት ተላላፊ የቆዳ በሽታ ሁሉ ያመለክታል (ዘሌ. 13 ተመልከት)። 6* 8፡21 እንድቀብር ፡- አባቴ እስኪሞት ድረስ ሙሮ ለመቅበር ያለውን ፍላጎት የሚያመለክት ይመስላል ።
7፡28-29 ፡- ማር. 1፡22 ፤ ሉቃ. 4፡32 ። 8፡4 ፡- ዘሌ. 14፡1-32 ። 8፡11 ፡- ሉቃ. 13፡29 ።
8፡12 ፡- ኢሳ. 49፡12 ፤ 59፡19 ፤ ሚል. 1፡11 ፤ መዝ. 107፡3 ፤ ማቴ. 22፡13 ፤ 25፡30 ፤ ሉቃ. 13፡28 ። 8፡17 ፡- ኢሳ. 53፡4 ።

[26]እርሱም “እናንተ እምነት የጐደላችሁ! ስለምን ትፈራላችሁ?” አላቸው ። ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ ። [27]ሰዎቹም እጅግ ተደነቁ “ነፋስና ባሕር እንኳ የሚታዘዙለት ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?” አሉ ።

ኢየሱስ በአጋንንት የተያዙ ሁለት ሰዎችን አዳነ
(ማር. 5፡1-20፡ ሉቃ. 8፡26-39)

[28]ኢየሱስ የገሊላን ባሕር ተሻግሮ ወደ ጌራ ሴኖን አገር መጣ ። በዚያም አጋንንት የያዛቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ቦታ ወጥተው ተገና ኙት ፥ እነርሱ በጣም አደገኞች ስለነበሩ ማንም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ አይችልም ነበር ። [29]እነርሱም በድንገት እንዲህ እያሉ መጮኽ ጀመሩ ፥ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ! እኛ ከእንተ ጋር ምን ግንኙነት አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን መጣህን?” [30]ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ባለ ስፍራ የብዙ ሠሃማዎች መንጋ ተሠማርቶ ነበር ። [31]አጋንንቱም “የምታስወ ጣን ከሆነ እባክህ ወደዚያ ወደ ሠሃማዎቹ መንጋ ስደደን!” ሲሉ ለመኑት ። [32]ኢየሱስም “ሂዱ!” አላቸው ። ስለዚህም ወጥተው ወደ ሠሃማዎቹ ሄዱና ገቡባቸው ። ሠሃማዎቹም በሙሉ ከገደሉ አፋፍ ላይ እየተንደረደሩ ወር ደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ ። [33]የዐሃማዎቹም እረኞች ሸሽተው ወደ ከተማ ገቡና ሁሉን ነገር አወሩ ፥ አጋንንት በያዙአቸው ሰዎች የሆነው ንም ነገር ተናገሩ ። [34]ከዚህ በኋላ የከተማው ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን ለማየት ወጡ ፤ ባዩትም ጊዜ ከአገራቸው ወጥቶ እንዲሄድላቸው ለመ ኑት ።

ምዕራፍ 9

ኢየሱስ ሽባውን ሰው ፈወሰ
(ማር. 2፡1-12፡ ሉቃ. 5፡17-26)

[1]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጀልባ ተሳፈረና ባሕ ሩን ተሻግሮ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ። [2]በዚያም ሰዎች በአልጋ ላይ የተኛ አንድ ሽባ ይዘው ወደ ኢየሱስ መጡ ። ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን “ልጄ ሆይ! አይዞህ ኃጢአትህ ተደምስሶልሃል” አለው ። [3]በዚህ ጊዜ አንዳንድ የሙሴ ሕግ መምህራን “ይህ ሰው በእግዚአብ ሔር ላይ የስድብ ቃል ይናገራል!” እያሉ በል ባቸው አሰቡ ። [4]ኢየሱስም አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላቸው ፡- “ስለምን ይህን ክፉ ነገር በልባችሁ ታስባላችሁ? [5]ለመሆኑ ‘ኃጢአትህ ተደምስሶሃል’ ከማለትና ‘ተነሥተህ ሂድ’ ከማለት የትኛው ይቀላል? [6]ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ለመደምሰስ ሥል ጣን እንዳለው ልታውቁ ይገባል” ብሎ ሽባውን ሰው “ተነሥና አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ” አለው ። [7]ተነሥቶም ወደ ቤቱ ሄደ ። [8]ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ ተገረመ ፥ እንዲህ ያለውንም ሥልጣን ለሰው በመስጠቱ እግዚአብ ሔርን አመሰገኑ ።

ኢየሱስ ማቴዎስን ጠራው
(ማር. 2፡13-17፡ ሉቃ. 5፡27-32)

[9]ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ሲሄድ ሳለ ማቴዎስ የተባለውን ቀራጭ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ አየውና “ተከተለኝ!” አለው ፥ ማቴዎስም ተነሥቶ ተከተለው ።

[10]ኢየሱስ በማቴዎስ ቤት በማእድ ተቀምጦ ሳለ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች ወደዚያ መጥተው ከእርሱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማ እድ ተቀመጡ ። [11]ፈሪሳውያንም ይህን አይ ተው ደቀ መዛሙርቱን “መምህራችሁ ከቀራ ጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ስለምን አብሮ ይበ ላል!” አሉአቸው ። [12]ኢየሱስም ይህን ሰምቶ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፡ “በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም ። [13]ሂዱ ‘እኔ የምፈልገው ምሕረትን እንጂ መሥዋዕትን አይደለም’ ተብሎ የተጻፈው ምን እንደሆነ መርምራችሁ አስተውሉ ። እኔ የመጣሁት ኃጢ አተኞችን ወደ ንስሐ ለመጥራት ነው እንጂ ፥ ጻድቃንን ወደ ንስሐ ለመጥራት አይደለም ።”

ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 2፡18-22፡ ሉቃ. 5፡33-39)

[14]በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ መጥተው “እኛና ፈሪሳውያን ዘወ ትር እንጾማለን ፥ የእንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድነው?” ሲሉ ጠየቁት ። [15]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፡ “ሙሽ ራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች ማዘን ይገባ ቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይ በት ጊዜ ይመጣል ፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ ። [16]በአረጀ ልብስ ላይ ውሃ ያልነካው አዲስ ዕራፊ የሚጥፍ ማንም የለም ፤ ምክንያቱም አዲሱ ዕራፊ አሮጌውን ልብስ ቦጭቆ ቀዳዳውን የባሰ ያሰፋዋል ። [17]እንዲሁም በአረጀ የውሃ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር ማንም የለም ፤ ይህን የሚያደርግ ቢኖር ግን አቁማዳው ይፈነዳል ፤ የወይን ጠጁም ይፈሳል ፤ አቁማዳ ውም ተበላሽቶ ከጥቅም ውጪ ይሆናል ። ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል ፤ በዚህም ዐይነት ሁለቱም በደ ኅና ተጠብቀው ይኖራሉ ።”

[8:29] ፡- መሳ. 11፡12 ፤ 2ሳሙ. 16፡10 ። 9፡10-11 ፡- ሉቃ. 15፡1-2 ። 9፡13 ፡- ሆሴዕ 6፡6 ፤ ማቴ. 12፡7 ።

ስለኢያኢሮስ ልጅና የኢየሱስን ልብስ ስለዳሰሰች ቤት
(ማር. 5፡21-43፡ ሉቃ. 8፡40-56)

[18]ኢየሱስ ይህን ሲነግራቸው ሳለ አንድ የምኩራብ አለቃ ወደ እርሱ መጣ ፤ በግንባሩም በኢየሱስ ፊት ተደፍቶ “እነሆ ልጄ አሁን ሞተችብኝ ፤ ነገር ግን አንተ መጥተህ እጅህን ብትጭንባት ትድናለች” አለው ። [19]ኢየሱስም ተነሣና ሰውየውን ተከትሎ ሄደ ፤ ደቀ መዛሙ ሮቱም አብረው ሄዱ ።

[20]እነሆ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም እየመታት ትሠቃይ የነበረች አንዲት ሴት በዚ ያን ጊዜ ከኢየሱስ በስተኋላ መጥታ የልብሱን ጫፍ በእጅዋ ነካች ። [21]ይህንንም ያደረገችው “ልብሱን ብቻ እንኳ በእጄ ብነካ እድናለሁ ብላ በልብዋ አስባ ስለነበር ነው ።” [22]ኢየሱ ስም መለስ ብሎ አያትና “እይዞሽ ልጄ ሆይ! እምነትሽ አድኖሻል” አላት ። ሴትዮዋም ወዲ ያውኑ ዳነች ።

[23]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ምኩራብ አለቃው ቤት በደረሰ ጊዜ የሐዘን እምቢልታ ነፊዎችንና እየተራወጡ በመጮኽ የሚያለቅሱትን ሰዎች አየ ። [24]እንዲህም አለ ፥ “ሁላችሁም ከዚህ ውጡ! ልጅትዋ አትቀላፍታለች እንጂ አልሞተ ችም!” እነርሱ ግን በማሾፍ ሳቁበት ። [25]ሰዎ ቹም ከወጡ በኋላ ኢየሱስ ልጅትዋ ወደምትገኝ በት ቤት ገባ ፤ እጅዋንም ሲይዛት ተነሣች ። [26]የዚህም ነገር ዝና በዚያ አገር ሁሉ ተሰማ ።

ኢየሱስ ሁለት ዐይነ ስውሮችን አዳነ

[27]ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ሲሄድ ሁለት ዐይነ ስውሮች ተከተሉት ፤ እነርሱም “የዳዊት ልጅ ሆይ! እባክህ ማረን” እያሉ ይጮኹ ነበር ። [28]ኢየሱስ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ዐይነ ስውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ ፤ ኢየሱስም “እኔ ይህን ማድረግ እንደምችል ታምናላችሁን?” አላቸው ። እነርሱም “አዎ ጌታ ሆይ!” ሲሉ መለሱ ። [29]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ዐይኖቻቸውን በእጁ ዳሰሰና “እንደ እምነታችሁ ይሁንላ ችሁ” አላቸው ። [30]ዐይኖቻቸውም ተከፈቱ ፤ ኢየሱስም “ለማንም እንዳትናገሩ!” ሲል በብ ርቱ አዘዛቸው ። [31]እነርሱ ግን ሄደው በዚያ አገር ሁሉ ስለ ኢየሱስ ዝና አወሩ ።

ኢየሱስ አንድ ድዳ ሰው ፈወሰ

[32]ዐይኖቻቸው የተከፈቱላቸው ሰዎች ወጥ ተው በሄዱ ጊዜ ፥ ሌሎች ሰዎች ጋኔን ያደረበ ትን ድዳ ወደ ኢየሱስ አመጡ ። [33]ጋኔኑም ከወ ጣለት በኋላ ድዳው ሰው ተናገረ ፤ ሕዝቡም “እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ከቶ ታይቶ አይ ታወቅም” እያሉ ተደነቁ ። [34]ፈሪሳውያን ግን “እርሱ አጋንንትን የሚያስወጣው በአጋንንት አለቃ አማካይነት ነው” አሉ ።

ኢየሱስ ለሕዝቡ ራራ

[35]እንዲሁም ኢየሱስ በምኩራቦቻቸው እያስ ተማረ ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት መልካም ዜና እያበሠረ ፥ ሕዝቡን ከበሽታና ከደዌ ሁሉ እየፈወሰ ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዘ ዋወር ነበር ። [36]ሕዝቡ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀውና ረዳት አጥተው ባያቸው ጊዜ ራራላቸው ። [37]ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ፥ “መከሩ ብዙ ነው ፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው ። [38]እንግዲህ ተጨማሪ ሠራተኞችን ወደ መከሩ ሥራ እንዲ ልክ የመከሩን ጌታ ለምኑት ።”

ምዕራፍ 10

ስለ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
(ማር. 3፡13-19፡ ሉቃ. 6፡12-16)

[1]ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ ርኵሳን መናፍስትን እንዲያስ ወጡ ፥ በሽታንና ደዌን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥል ጣን ሰጣቸው ። [2]የዐሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ነው ፡- መጀመ ሪያ ጴጥሮስ የተባለው ስምዖንና ወንድሙ እን ድርያስ ፥ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐ ንስ ፥ [3]ፊልጶስ ፥ በርቶሎሜዎስ ፥ ቶማስ ፥ ቀራጩ ማቴዎስ ፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ፥ ታዴዎስ ፥ [4]ተቀናቃኙ ስምዖን ፥ ኢየሱስን አሳ ልፎ የሰጠ አስቆሮታዊው ይሁዳ ።

ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለማስተማር እንደተላኩ
(ማር. 6፡7-13፡ ሉቃ. 9፡1-6)

[5]ኢየሱስ እነዚህን ዐሥራ ሁለት ሐዋርያት ላካቸው ፤ እንዲህም ብሎ አዘዛቸው ፥ “ወደ አረማውያን አትሂዱ ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ ፤ [6]ነገር ግን እንደ በጎች ወደ ጠፉት ወደ እስራኤል ሕዝቦች ሂዱ ። [7]ሄዳች ሁም ‘መንግሥተ ሰማይ ቀርባለች’ እያላችሁ ስበኩ ። [8]በሽተኞችን ፈውሱ ፤ ሙታንን አስ ነሡ ፤ ለምጻሞችን አድኑ ፤ አጋንንትን አስ ወጡ ፤ በነፃ የተቀበላችሁትን በነፃ ስጡ ። [9]ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በኪሳችሁ አት ያዙ ። [10]ከረጢትም ፤ ትርፍ እጅ ጠባብም ፥

9፡20 ፡- ዘኁ. 15፡38 ፤ ዘዳ. 22፡12 ። 9፡34 ፡- ማቴ. 10፡25 ፤ 12፡34 ፤ ማር. 3፡22 ፤ ሉቃ. 11፡15 ። 9፡35 ፡- ማቴ. 4፡23 ፤ ማር. 1፡39 ፤ ሉቃ. 4፡44 ። 9፡36 ፡- ዘኁ. 27፡17 ፤ 1ነገ. 22፡17 ፤ 2ዜ.መ. 18፡16 ፤ ሕዝ. 34፡5 ፤ ዘካ. 10፡2 ፤ ማር. 6፡34 ። 9፡37-38 ፡- ሉቃ. 10፡2 ። 10፡7-15 ፡- ሉቃ. 10፡4-12 ። 10፡10 ፡- 1ቆሮ. 9፡14 ፤ 1ጢሞ. 5፡18 ።

ትርፍ ጫማም በትርም ለመንገዳችሁ አትያዙ ፤ ምክንያቱም ለሠራተኛ የሚያስፈልገው ምግብ ይሰጠዋል ። [11] በምትገቡበት ከተማ ወይም መን ደር እናንተን ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ቢኖር መርምሩ ፤ ያንንም ስፍራ ለቅቃችሁ እስክ ትወጡ ድረስ ከዚያ ሰው ጋር ቆዩ ። [12] ወደ ሰው ቤት ስትገቡ ሰላምታ ስጡ ፤ [13] የቤቱ ጌታ ሰላም ታችሁን ቢቀበል ሰላምታችሁ ይድረሰው ፤ ባይቀ በል ግን ሰላምታችሁ ይመለስላችሁ ። [14] የማይቀ በላችሁና ቃላችሁንም የማይሰማ ቢኖር ያንን ቤት ወይም ከተማ ለቅቃችሁ ስትወጡ የእግራች ሁን ትቢያ አራግፋችሁ ሂዱ ። [15] በእውነት እላችኋለሁ ፥ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ ቅጣቱ ይቀልላቸዋል ።

ከጌታ መምጣት በፊት ስደትና መከራ ይሆናል
(ማር. 13፥9-13፤ ሉቃ. 21፥12-17)

[16] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "እነሆ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋ ለሁ ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ብልኆች ፥ እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ። [17] ሰዎች ለፍርድ አሳል ፈው ይሰጡአችኋል ፤ በየምኩራባቸውም ይገር ፉአችኋል ፤ ስለዚህ ተጠንቀቁ ። [18] በእኔ ምክን ያት ወደ ገዥዎችና ወደ ነገሥታት ለፍርድ ትወሰዳላችሁ ፤ በእነርሱና በአረማውያን ፊት ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ፤ [19] ሰዎች ለፍርድ ሲያ ቀርቡአችሁ የምትናገሩት በዚያን ሰዓት ስለሚ ሰጣችሁ 'እንዴት ወይም ምን እንናገራለን?' ብላችሁ በማሰብ አትጨነቁ ። [20] ምክንያቱም በእናንተ አድሮ የሚናገር የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁም ። [21] ሰው የገዛ ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰ ጣል ፤ እንዲሁም አባት የገዛ ልጁን ለሞት አሳ ልፎ ይሰጣል ፤ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ በጠላትነት ይነሣሉ ፤ ለሞትም አሳልፈው ይሰ ጡአቸዋል ። [22] እናንተም በእኔ ምክንያት በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ፤ ነገር ግን እስከ መጨረሻው በትዕግሥት የሚጸና ይድናል ። [23] በአንድ ከተማ መከራ ሲያስከፍ ችሁ ወደ ሌላ ከተማ ሽሹ ፤ በእውነት እላችኋ ለሁ የሰው ልጅ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ እስ ራኤልን ከተማዎች ሁሉ አታዳርሱም ። [24] ተማሪ ከአስተማሪው አይበልጥም ፤ አገልጋ ይም ከጌታው አይበልጥም ። [25] ስለዚህ ተማሪ እንደአስተማሪው ፥ አገልጋይም እንደጌታው ከሆነ ይበቃዋል ። የቤቱን ጌታ ፥ 'ብዔልዜቡል' ብለው ከጠሩት ቤተሰቦቹንማ ከዚህ በከፋ ስም እንዴት አይጠሩአቸውም!"

ማንን መፍራት እንደሚገባ
(ሉቃ. 12፥2-7)

[26] ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "እንግዲህ ሰዎችን አትፍሩ ፤ ምክንያቱም የተሸፈነ መገ ለጡ አይቀርም ፤ የተሰወረም መታወቁ አይቀ ርም ። [27] ስለዚህ እኔ በጨለማ የምነግራችሁን እናንተ በብርሃን ተናገሩት ፤ በጕክሹክታ የሰማች ሁትንም በከፍተኛ ቦታ ላይ በይፋ አስተምሩ ። [28] ሥጋን ከመግደል አልፈው ነፍስን መግደል የማይችሉትን ሰዎች አትፍሩ ፤ ይልቁንስ ነፍስ ንና ሥጋን በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን አም ላክ ፍሩ ። [29] ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ይሁን እንጂ የሰማይ አባታችሁ ሳይፈቅድ አንዷቷ ድንቢጥ እንኳ በምድር አትወ ድቅም ። [30] የእናንተማ የራስ ጠጕራችሁ እንኳ የተቈጠረ ነው ። [31] እንግዲህ እናንተ አትፍሩ ፤ ምክንያቱም ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ ።"

ስለ ክርስቶስ መመስከር ይገባል
(ሉቃ. 12፥8-9)

[32] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ ። [33] በሰው ፊት የሚክደኝን ሁሉ ግን እኔም በሰማይ አባቴ ፊት አክደዋለሁ ። [34] እኔ የመጣሁት ሰላምን በም ድር ላይ ለማምጣት አይምሰላችሁ ፤ እኔ ሰይ ፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ። [35] እኔ የመጣሁት ወንድ ልጅን በአባቱ ላይ ፥ ሴት ልጅን በእናትዋ ላይ ፥ ምራትን በወማትዋ ላይ ፥ በጠላትነት ለማስነሣት ነው ። [36] ስለዚህ የሰው ጠላቶች የገዛ ቤተሰቦቹ ይሆናሉ ። [37] ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ የእኔ ሊሆን አይገባውም ፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ የእኔ ሊሆን አይገባውም ። [38] የገዛ ራሱን መስቀል ተሸክሞ የማይከተለኝ ሰው የእኔ ሊሆን አይገባውም ። [39] ሕይወቱን ለማዳን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋ ታል ፤ ሕይወቱን ስለ እኔ የሚያጠፋት ሁሉ ግን ያድናታል ። [40] እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን አብን ይቀበላል ። [41] ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል

10፡14 ፡- ሐሥ. 13፡51 ። 10፡15 ፡- ማቴ. 11፡24 ፡ ዘፍ. 19፡24-28 ። 10፡16 ፡- ሉቃ. 10፡3 ።
10፡17-20 ፡- ማር. 13፡9-11 ፡ ሉቃ. 12፡11-12 ፡ 21፡12-15 ። 10፡21 ፡- ማር. 13፡12 ፡ ሉቃ. 21፡16 ።
10፡22 ፡- ማቴ. 24፡9 ፡ 13 ፡ ማር. 13፡13 ፡ ሉቃ. 21፡17 ። 10፡24 ፡- ሉቃ. 6፡40 ፡ ዮሐ. 13፡16 ፡ 15፡20 ።
10፡25 ፡- ማቴ. 9፡34 ፡ 12፡24 ፡ ማር. 3፡22 ፡ ሉቃ. 11፡15 ። 10፡26 ፡- ማር. 4፡22 ፡ ሉቃ. 8፡17 ።
10፡33 ፡- 2ጢሞ. 2፡12 ። 10፡35-36 ፡- ሚክ. 7፡6 ። 10፡38 ፡- ማቴ. 16፡24 ፡ ማር. 8፡34 ፡ ሉቃ. 9፡23 ።
10፡39 ፡- ማቴ. 16፡25 ፡ ማር. 8፡35 ፡ ሉቃ. 9፡24 ፡ 17፡33 ፡ ዮሐ. 12፡25 ። 10፡40 ፡- ማር. 9፡37 ፡ ሉቃ. 9፡48 ፡ 10፡16 ፡ ዮሐ. 13፡20 ።

የነቢይን ዋጋ ያገኛል ፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ። [42] በእውነት እላችኋለሁ ፥ የእኔ ደቀ መዝሙር በመሆኑ ከነ ዚህ ታናናሾች ለአንዱ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውሃ እንኳ የሚሰጥ ሰው ዋጋውን አያጣም ።"

ምዕራፍ 11

ከአጥማቂው ዮሐንስ የተላኩ መልእክተኞች
(ሉቃ. 7፡18-35)

[1] ኢየሱስ እነዚህን መመሪያ ትእዛዞች ለዐ ሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከሰጠ በኋላ ያንን ቦታ ትቶ በእቅራቢያው ወደሚገኙት ከተሞች ሊሰብክና ሊያስተምር ሄደ ።

[2] አጥማቂው ዮሐንስ በወህኒ ቤት ሳለ ፥ ስለ ክርስቶስ ሥራ ሰማ ፤ ስለዚህ ከራሱ ደቀ መዛ ሙርት መልእክተኞችን ወደ ኢየሱስ ልኮ ፥ [3] "ይመጣል የተባለው መሲሕ አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ?" ብለው ኢየሱስን እንዲ ጠይቁት አደረገ ። [4] ኢየሱስም እንዲህ ሲል መል ሰላቸው ፥ "ሂዱና ያያችሁትንና የሰማችሁትን ሁሉ ለዮሐንስ ንገሩት ። [5] እነሆ ዕውሮች ያያሉ ፤ አንካሶች ቀጥ ብለው ይሄዳሉ ፤ ለምጻ ሞች ይነጻሉ ፥ ደንቆሮዎች ይሰማሉ ፤ ሙታን ይነሣሉ ፤ ለድኾችም የምሥራች ቃል ይነገ ራል ፤ [6] በእኔ የማይሰናከል የተመሰገነ ነው ።"

[7] የዮሐንስ መልእክተኞች ከሄዱ በኋላ ኢየ ሱስ ስለ ዮሐንስ እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ ፥ "ለመሆኑ ፥ ምን ልታዩ ወደ በረሓ ወጣችሁ? በነፋስ የሚወዛወዘውን ሸንበቆ ለማየት ነውን? [8] ደግሞስ ምን ለማየት ወጣችሁ? ጥሩ የሐር ልብስ የለበሰውን ሰው ለማየት ነውን? ጥሩ የሐር ልብስ የሚለብሱማ በነገሥታት ቤት ይገ ኛሉ ። [9]ታዲያ ስለምን ወጣችሁ? ነቢይ ለማ የት ነውን? አዎ! እንዲያውም ከነቢይ የሚበል ጠውን ለማየት ነው እላችኋለሁ ። [10] እርሱ 'እነሆ እሌት እልተ ነቢያቴ ከፊትህ መንገድህን የሚያ ዘጋጅ መልእክተኛዬን ከእንተ በፊት እልካለሁ' ተብሎ የተጻፈለት ነው ። [11] በእውነት እላችኋ ለሁ ፥ በምድር ላይ ከተወለዱት ሰዎች ሁሉ ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ ከቶ የለም ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉ ያነ ሰው ይበልጠዋል ። [12] ከአጥማቂው ዮሐንስ ዘመን አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማይ በጣም ትገፋለች[7*] በብርቱ የሚጋደሉም ያገኙዋታል ።

[13] "መላው የነቢያት ትምህርትና የሙሴ ሕግ እስከ አጥማቂው ዮሐንስ ድረስ ሲነገሩ ቆይተዋል ። [14] እንግዲህ እነርሱ የተናገሩትን ለመቀበል ከፈቀዳችሁ ያ ይመጣል የተባለው ኤልያስ ፡ እነሆ ይህ ዮሐንስ ነው ። [15] እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!

[16] "ነገር ግን የዚህን ዘመን ሰዎች በምን እን ጻጽራቸዋለሁ? በአደባባይ ተቀምጠው ጓደኞች ቸውን እየጠሩ እንዲህ የሚሉትን ልጆች ይመስ ላሉ ፥ [17] 'የደስታ ሙዚቃ አሰማናችሁ ፤ እና ንተ ግን አልጨፈራችሁም ፤ የሐዘን እንጉርጉሮ አሰማናችሁ ፥ እናንተ ግን አላለቀሳችሁም ።' [18] እንዲሁም አጥማቂው ዮሐንስ እህል ሳይበላና የወይን ጠጅ ሳይጠጣ ቢመጣ 'ይህስ ጋኔን አለ በት!' አሉት ፤ [19] የሰው ልጅ ደግሞ እየበላና እየጠጣ ቢመጣ 'እነሆ ይህ መብልና መጠጥ የሚወድ ነው ፤ የቀራጮችና የኃጢአተኞችም ወዳጅ ነው!' አሉት ። እንግዲህ የጥበብ ትክክል ኝነት በሥራዋ ይገለጣል ።"

ባለማመናቸው የተወቀሱ ከተሞች
(ሉቃ. 10፡13-15)

[20] ቀጥሎም ኢየሱስ ከሌሎች ከተሞች ይበ ልጥ ብዙ ተአምራት ያደረገባቸው ከተሞች ንስሓ ስላልገቡ እንዲህ ሲል ይወቅሳቸው ጀመር ፥ [21] "ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ! በእናንተ የተደረጉት ተአምራት በጢሮ ስና በሲዶና ተደርገው ቢሆን ኖሮ ፥ በዚያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የሐዘን ልብስ ለብሰውና ዐመድ በላያቸው ላይ ነስንሰው ገና ዱሮ ንስሓ በገቡ ነበር ። [22] ስለዚህ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀልላቸዋል እላችኋለሁ ። [23] አንቺም ቅፍርናሆም እስከ ሰማይ ከፍ ብሽ የሉምን? ታዲያ እኮ ወደ ሲኦል አዘቅት ትወርጃለሽ ፤ በአንቺ የተደረጉት ተአምራት በሰዶም ተደርገው ቢሆን ፥ ያች ከተማ ሳትጠፋ እስከ ዛሬ በኖረች ነበር ። [24] ስለ ዚህ በእውነት እልሻለሁ ፥ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም ቅጣቱ ይቀልላታል ።"

በክርስቶስ ዕረፍት ማግኘት
(ሉቃ. 10፡21-22)

[25] በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "የሰማ ይና የምድር ጌታ የሆንህ አባት ሆይ! ይህን ነገር ከጥበበኞችና ከወቂቂዎች ሰውረህ ለሕፃ ናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ ፤ [26] አዎ! አባት ሆይ! ይህን ለማድረግ የአንተ በጎ ፈቃድ ሆኖአል ። [27] አባቴ ሁሉን ነገር ሰጥቶኛል ፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ ማንም የለም ።

7* 11፡12 ትገፋለች ፡- የአማዚአብሔር መንግሥት በመማፋትና በመገፋት ላይ መሆንዋን ያመለክታል ።
11፡5 ፡- ኢሳ. 35፡5-6 ፡ 61፡1 ። 11፡10 ፡- ሚል. 3፡1 ። 11፡12-13 ፡- ሉቃ. 16፡16 ። 11፡14 ፡- ሚል. 4፡5 ፡ ማቴ. 17፡10-13 ፡ ማር. 9፡11-13 ። 11፡21 ፡- ኢሳ. 23፡1-18 ፡ ሕዝ. 26፡1-28፡26 ፡ ኢዩ. 3፡4-8 ፡ አሞጽ 1፡9-10 ፡ ዘኁ. 9፡2-4 ። 11፡23 ፡- ኢሳ. 14፡13-15 ፡ ዘፍ. 19፡24-28 ። 11፡24 ፡- ማቴ. 10፡15 ፡ ሉቃ. 10፡12 ።
11፡27 ፡- ዮሐ. 3፡35 ፡ 1፡18 ፡ 10፡5 ።

እንዲሁም ከወልድ በቀር አብን የሚያውቅ
የለም ፤ ማንም ወልድ ሊገልጥለት ካልፈቀደለት
በቀር አብን ሊያውቅ አይችልም ።
28 “ሸክማችሁ የከበደባችሁ እናንተ ደካ
ሞች ሁሉ ፥ ወደ እኔ ኑ! እኔም ዕረፍት እሰ
ጣችኋለሁ ። 29 ቀንበሬን በጫንቃችሁ ተሸ
ከሙ ፤ ከእኔም ተማሩ ፤ እኔ የዋህና ትሑት
ነኝ ፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ ።
30 ቀንበሬ ልዝብ ነው ፤ ሸክሜም ቀላል
ነው ።”

ምዕራፍ 12

ስለ ሰንበት የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 2፡23-28፡ ሉቃ. 6፡1-5)

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በስንዴ
እርሻ መካከል ያልፍ ነበር ፤ ደቀ መዛሙርቱ
ርቦአቸው ስለነበረ የስንዴ እሸት እየቀጠፉ
ይበሉ ጀመር ። 2 ፈሪሳውያን ይህን አይተው
ኢየሱስን “እነሆ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት
ቀን ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ!” አሉት ።
3 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “ዳዊትና አብረ
ውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ ዳዊት ያደረ
ገውን ከቶ አላነበባችሁምን? 4 ወደ እግዚአብ
ሔር ቤት ገብቶ ከካህናት በስተቀር እርሱም
ሆነ አብረውት የነበሩት ሰዎች ሊበሉት ያልተ
ፈቀደውን የተቀደሰ የመባ ኅብስት በላ ። 5 ደግ
ሞስ ካህናት በሰንበት ቀን በቤተ መቅደስ ሰንበ
ትን ሲሽሩ በደል ሆኖ እንደማይቈጠርባቸው
በሙሴ ሕግ የተጻፈውን አላነበባችሁምን?
6 ነገር ግን ከቤተ መቅደስ የሚበልጥ እነሆ
እዚህ አለ እላችኋለሁ ። 7 ደግሞም ‘እኔ የምፈ
ልገው ምሕረትን እንጂ መሥዋዕትን አይደለም’
የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ምን እንደሆነ ብታ
ስተውሉ ኖሮ በደል በሌለባቸው ሰዎች ላይ
ባልፈረዳችሁም ነበር ። 8 ምክንያቱም የሰው
ልጅ የሰንበት ጌታ ነው ።”

እጁ ሽባው ሰው
(ማር. 3፡1-6፡ ሉቃ. 6፡6-11)

9 ኢየሱስ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ወደ ምኩራ
ባቸው ገባ ፤ 10 በዚያም አንድ እጁ ሽባ ሰው
ነበረ ፤ ኢየሱስን ሊከሱት የፈለጉ አንዳንድ
ሰዎች “በሰንበት ቀን በሽተኛን መፈወስ ተፈቅ
ዶልን?” ሲሉ ጠየቁት ። 11 ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው ፥ “ከእናንተ መካከል አንድ በግ
ያለው ፥ በጉ በሰንበት ቀን በጉድጓድ ውስጥ
ቢወድቅበት ስቦ የማያወጣው ማነው? 12 ታዲያ
ከበግ ይልቅ ሰው እንዴት አይበልጥም? ስለዚህ
በሰንበት ቀን መልካም ነገር ማድረግ የተፈቀደ
ነው ።” 13 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እጁ ሽባውን
“እጅህን ዘርጋ!” አለው ። እርሱም በዘረጋው
ጊዜ እጁ ዳነለትና ልክ እንደ ደኅንኛው እጅ
ሆነለት ። 14 ፈሪሳውያን ግን ከዚያ ወጥተው
ኢየሱስን እንዴት አድርገው እንደሚገድሉት
ተማከሩ ።

የእግዚአብሔር ምርጥ አገልጋይ

15 ኢየሱስ ግን ምክራቸውን ዐውቆ ከዚያ
ቦታ ገለል አለ ፤ ብዙ ሰዎችም ተከትለውት
ሄዱ ፤ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሳቸው ። 16 ስለ
እርሱ ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው ፤
17 ይህም የሆነው በነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ
ተብሎ የተጻፈው የትንቢት ቃል እንዲፈጸም
ነው ፥

18 “የመረጥሁት አገልጋዬ እነሆ ይህ ነው!
እርሱ እኔ የምወደውና የምደሰትበት
ነው ፤
መንፈሴን በእርሱ ላይ አደርጋለሁ ፤
እርሱም ቅን ፍርድን ለአረማውያን
ያውጃል ።
19 እርሱ አይከራከርም ወይም አይጮኽም ፤
በየመንገዱ ድምፁን አያሰማም ።
20 የተቀጠቀጠ ሸንበቆ እንኳ አይሰብርም ፤
የሚጤሰውንም የጥዋፍ ክር
አያጠፋም ፤
ይህንንም የሚያደርገው ቅን ፍርድ
ድል እስኪነሣ ድረስ ነው ።
21 አረማውያን በእርሱ ተስፋ ያደርጋሉ ።”

ስለ ኢየሱስና ስለ ብዔልዜቡል
(ማር. 3፡20-30፡ ሉቃ. 11፡14-23)

22 ከዚህ በኋላ ሰዎች ጋኔን ያደረበትን ዐይነ
ስውርና ድዳ ሰው ወደ ኢየሱስ አመጡ ፤ ኢየሱ
ስም ፈወሰው ፤ ሰውየውም መናገርና ማየት
ቻለ ። 23 ሕዝቡም ሁሉ ተገርመው ፥ “ይህ የዳ
ዊት ልጅ ይሆንን?” አሉ ።
24 ፈሪሳውያን ግን ይህን በሰሙ ጊዜ “እርሱ
አጋንንትን የሚያስወጣው ‘ብዔልዜቡል’ በተባ
ለው በአጋንንት አለቃ ነው” አሉ ።
25 ኢየሱስም አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው ፥ “አንድ መንግሥት ተከፋፍሎ እርስ በእ
ርሱ የሚጋጭ ከሆነ ያ መንግሥት ይወድቃል ።
እንዲሁም አንድ ከተማ ወይም አንድ ቤተሰብ
እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ መኖር አይችልም ።
26 ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ እርስ
በርሱ ተለያየ ማለት ነው ፤ ታዲያ መንግሥቱ
እንዴት ጸንቶ ሊኖር ይችላል? 27 ደግሞ እኔ
አጋንንትን የማስወጣቸው በብዔልዜቡል ከሆነ

11፡29 ፡- ኤር. 6፡16 ። 12፡1 ፡- ዘፍ. 23፡25 ። 12፡3-4 ፡- 1ሳሙ. 21፡1-6 ። 12፡4 ፡- ዘሌ. 24፡9 ።
12፡5 ፡- ዘኁ. 28፡9-10 ። 12፡7 ፡- ማቴ. 9፡13 ፤ ሆሴዕ 6፡6 ። 12፡11 ፡- ሉቃ. 14፡5 ። 12፡18-21 ፡- ኢሳ. 42፡1-4 ።
12፡24 ፡- ማቴ. 9፡34 ፤ 10፡25 ።

ልጆቻችሁስ በምን ያስወጡአቸዋል? ስለዚህ
ልጆቻችሁ በእናንተ ላይ ይፈርዱባችኋል ።
28 እኔ አጋንንትን የማስወጣ በእግዚአብሔር
መንፈስ ከሆነ ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግ
ሥት ወደ እናንተ መጥታለች ማለት ነው ።
29 ደግሞስ አንድ ሰው አስቀድሞ ኀይለኛውን
ሳያስር ወደ ኀይለኛው ቤት ገብቶ ንብረቱን
መዝረፍ እንዴት ይችላል? ኀይለኛውን ካሰረው
በኋላ ግን ንብረቱን ሊዘርፍ ይችላል ። 30 ከእኔ
ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል ፤ ከእኔም ጋር
የማይሰበስብ ይበትናል ። 31 ስለዚህ ሰው የሚያ
ደርገው ማናቸውም በደል ወይም የስድብ ቃል
ሁሉ ይቅር ይባልለታል እላችኋለሁ ፤ በመንፈስ
ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሰው ግን
በደሉ ይቅር አይባልለትም ። 32 በሰው ልጅ ላይ
የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባል
ለታል ። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚ
ናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው
ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም ።”

ጥሩ ዛፍ በፍሬው ይታወቃል
(ሉቃ. 6፡43-45)

33 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ዛፍ
ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ ፥ ጥሩ ዛፍ ቢኖራ
ችሁ ጥሩ ፍሬ ታገኛላችሁ ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራ
ችሁ ግን መጥፎ ፍሬ ታገኛላችሁ ፤ 34 እናንተ
የእባብ ልጆች! ክፉዎች ስትሆኑ መልካም
ነገር መናገር እንዴት ትችላላችሁ? ምክንያ
ቱም ሰው በአፉ የሚናገረው በልቡ ሞልቶ የተ
ረፈው ነው ።
35 “መልካም ሰው ከመልካም መዝገቡ
መልካም ነገርን ያወጣል ፤ ክፉ ሰውም ከክፉ
መዝገቡ ክፉ ነገርን ያወጣል ። 36 በእውነት
እላችኋለሁ ፥ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም
በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ
ይሰጡበታል ። 37 ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ
ይፈረድልሃል ፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብ
ሃል ።”

ተአምራት ለማየት የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 8፡11-12፡ ሉቃ. 11፡29-32)

38 በዚያን ጊዜ አንዳንድ የሙሴ ሕግ መምህ
ራንና ፈሪሳውያን ኢየሱስን ፥ “መምህር ሆይ!
አንተ ተአምር ስታደርግ ማየት እንፈልጋለን!”
አሉት ። 39 እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰላ
ቸው ፥ “ክፉና እምነተቢስ የሆኑ የዚህ ዘመን
ሰዎች ተአምር ለማየት ይፈልጋሉ ፤ ነገር ግን
ከነቢዩ ከዮናስ ተአምር በቀር ሌላ ተአምር አይ
ሰጣቸውም ። 40 ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ
ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንዳሳለፈ እንዲሁ
የሰው ልጅ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀንና
ሦስት ሌሊት ያሳልፋል ። 41 የነነዌ ከተማ
ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን ሰዎች ጋር ተነ
ሥተው በእነርሱ ላይ ይፈርዱባቸዋል ፤ ምክንያ
ቱም የነነዌ ሰዎች የዮናስን ስብከት በሰሙ ጊዜ
በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሓ ገብተዋል ።
ታዲያ እኮ ከዮናስ የሚበልጥ እነሆ እዚህ አለ ።
42 የደቡብ ንግሥት በፍርድ ቀን ከዚህ ዘመን
ሰዎች ጋር ተነሥታ በእነርሱ ላይ ትፈርድባቸ
ዋለች ፤ ምክንያቱም እርስዋ የሰሎሞንን ጥበብ
ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለች ፤ ታዲያ
እኮ ከሰሎሞን የሚበልጥ እነሆ እዚህ አለ ።”

የርኵስ መንፈስ በሰው ውስጥ ተመልሶ መግባት
(ሉቃ. 11፡24-26)

43 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ርኵስ
መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ የሚያርፍበት ቦታ
በመፈለግ ውሃ በሌለበት በደረቅ ቦታ ይዞራል ።
ነገር ግን አያገኝም ፤ 44 ስለዚህ ‘ወደ ወጣሁበት
ቤት ተመልሼ ልሂድ’ ይላል ። ተመልሶም
ሲመጣ ቤቱ ባዶ ሆኖ ጸድቶ ፥ ተዘጋጅቶ ያገኘ
ዋል ። 45 ከዚህ በኋላ ርኵሱ መንፈስ ይሄድና
ከእርሱ ይብስ የከፋ ሌሎች ሰባት አጋንንት ሰብ
ስቦ ያመጣል ። እርሱ ቀድሞ በነበረበት ሰው
ገብተው አብረው ይኖራሉ ። ስለዚህ የዚያ ሰው
የመጨረሻ ሁኔታ ከመጀመሪያው ይልቅ የባሰ
ይሆናል ። በዚህ ዘመን ክፉዎች ሰዎችም ላይ
የሚሆነው ይህንኑ የመሰለ ነገር ነው ።”

የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ
(ማር. 3፡31-35፡ ሉቃ. 8፡19-21)

46 ኢየሱስ ለሕዝቡ ገና ሲናገር ሳለ እናቱና
ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ
ቆመው ነበር ። [47 እዚያ ከነበሩት ሰዎች አንዱ
ኢየሱስን ፥ “እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ሊያነ
ጋግሩህ ፈልገው በውጪ ቆመዋል” አለው ።]*
48 ኢየሱስ ግን “እናቴ ማንናት? ወንድሞ
ቼስ እነማን ናቸው?” ሲል መለሰ ። 49 ከዚህ
በኋላ እጁን ዘርግቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያ
መለከተ እንዲህ አለ ፥ “እናቴና ወንድሞቼ
እነሆ እነዚህ ናቸው ፤ 50 በሰማይ ያለውን የአባ
ቴን ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ ወንድሜም ፡ እኅ
ቴም ፥ እናቴም እርሱ ነው ።”

8* 12፡47 አንዳንድ ቅጂዎች ቍጥር 47 የላቸውም ።
12፡30 ፡- ማር. 9፡40 ። 12፡32 ፡- ሉቃ. 12፡10 ። 12፡33 ፡- ማቴ. 7፡20 ፤ ሉቃ. 6፡44 ።
12፡34 ፡- ማቴ. 3፡7 ፤ 23፡33 ፤ 15፡18 ፤ ሉቃ. 3፡7 ፤ 6፡45 ። 12፡38 ፡- ማቴ. 16፡1 ፤ ማር. 8፡11 ፤ ሉቃ. 11፡16 ።
12፡39 ፡- ማቴ. 16፡4 ፤ ማር. 8፡12 ። 12፡40 ፡- ዮና 1፡17 ። 12፡41 ፡- ዮና 3፡5 ። 12፡42 ፡- 1ነገ. 10፡1-10 ፤
2ዜ.መ. 9፡1-12 ።

ምዕራፍ 13

የዘሪው ምሳሌ

(ማር. 4፡1-9፤ ሉቃ. 8፡4-8)

[1] በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕሩ
አጠገብ ተቀመጠ፤ [2] ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ
መጥተው በመሰብሰባቸው ምክንያት በጀልባ
ላይ ወጥቶ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕር
ዳር ቆመው ነበር። [3] ከዚያም በኋላ ብዙ ነገሮ
ችን በምሳሌ እንዲህ እያለ ይነግራቸው
ጀመር፥ “እነሆ ዘሪው ገበሬ ለመዝራት ወጣ።
[4] ሲዘራም አንዳንዱ ዘር በመንገድ ዳር ወደቀና
ወሮች መጥተው በሉት። [5] ሌላው ዘር ብዙ
ዐፈር በሌለበት በጭንጫማ መሬት ላይ ወደቀ፤
መሬቱም ብዙ ዐፈር ስላልነበረው ዘሩ ወዲያ
ውኑ በቀለ። [6] ይሁን እንጂ ፀሐይ በወጣ ጊዜ
ጠወለገ፤ ሥር ስላልነበረውም ደረቀ። [7] ሌላ
ውም ዘር በእሾኻማ ቍጥቋጦ መካከል ወደቀ፤
እሾኻማውም ቍጥቋጦ አደገና የዘሩን ቡቃያ
አንቆ አስቀረው። [8] ሌላውም ዘር በመልካም
መሬት ላይ ወድቆ በቀለና ብዙ ፍሬ አፈራ፤
አንዱ መቶ፥ አንዱ ስልሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ
ሰጠ። [9] ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!”

ኢየሱስ በምሳሌዎች ስለምን ይናገር እንደነበረ

(ማር. 4፡10-12፤ ሉቃ. 8፡9-10)

[10] ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ
ቀርበው “ስለምን ለሕዝቡ በምሳሌ ትናገራ
ለህ?” አሉት። [11] እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ
ላቸው፥ “ለእናንተ የመንግሥተ ሰማይን ምስ
ጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን
አልተሰጣቸውም። [12] ምክንያቱም ላለው ሰው
ይሰጠዋል፤ ይበዛለታልም፤ ከሌለው ሰው ግን
ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። [13] እያየ ከቶ
እንደማያዩ፥ እየሰሙ እንደማይሰሙ ወይም
እንደማያስተውሉ ስለሆኑ እነሆ እኔ በምሳሌ
እነግራቸዋለሁ። [14] ስለዚህ በነቢዩ በኢሳይያስ
እንዲህ ተብሎ የተጻፈው በእነርሱ ላይ ይፈጸ
ማል፥

‘መስማትንስ ትሰማላችሁ፥ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን ልብ
አታደርጉም።
[15] ምክንያቱም እነዚህ ሕዝብ ልባቸውን
አደንድነዋል፤
ጆሮአቸውን ደፍነዋል፤ ዐይናቸውን
ጨፍነዋል፤
እንዲህስ ባይሆን ኖሮ በዐይናቸው
ተመልክተው፥
በጆሮአቸው ሰምተው፥
በልባቸው አስተውለው፥
ወደ እኔ በተመለሱና በፈወስኋቸው
ነበር።’

[16] “እናንተ ግን ዐይኖቻችሁ ስለሚያዩ፥
ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ የታደላችሁ ናችሁ።
[17] በእውነት እላችኋለሁ፥ ብዙዎች ነቢያትና
ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየት ተመኝ
ተው ነበር፤ ነገር ግን አላዩም፤ እናንተ የምት
ሰሙትን ለመስማት ተመኝተው ነበር፤ ነገር
ግን አልሰሙም።”

ኢየሱስ የዘሪውን ምሳሌ አስረዳ

(ማር. 4፡13-20፤ ሉቃ. 8፡11-15)

[18] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “እንግ
ዲህ እናንተ የዘሪው ምሳሌ ምን እንደሆነ
ስሙ፤ [19] በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር የሚያ
መለክተው የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል
ሰምቶ የማያስተውለውን ሰው ነው፤ ወዲያውኑ
ሰይጣን መጥቶ በልቡ የተዘራውን ቃል ይወስድ
በታል፤ [20] በጭንጫማ መሬት ላይ የተዘራው
የሚያመለክተው ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደ
ስታ የሚቀበለውን ሰው ነው። [21] ነገር ግን ለጊ
ዜው ነው እንጂ ሥር የለውም፤ ስለዚህ በቃሉ
ምክንያት አንዳች ችግር ወይም ስደት በደረሰ
በት ጊዜ ቶሎ ይሰናከላል። [22] በእሾኻማ
ቍጥቋጦ መካከል የተዘራው የሚያመለክተው
ቃሉን ለጊዜው የሚሰማውን ሰው ነው፤ ይሁን
እንጂ የዚህ ዓለም አሳብና የሀብት ፍቅር ወደ
ልቡ ገብቶ ቃሉን ስለሚያንቀው ያለ ፍሬ ይቀ
ራል። [23] በመልካም መሬት የተዘራው የሚያመ
ለክተው ቃሉን ሰምቶ በማስተዋል የሚቀበለ
ውን ሰው ነው፤ እርሱ ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ
መቶ፥ አንዱ ስልሳ፥ አንዱ ሰላሳ ፍሬ ይሰ
ጣል።”

የእንክርዳድ ምሳሌ

[24] እንዲሁም ኢየሱስ ሌላ ምሳሌ እንዲህ
ሲል ነገራቸው፥ “መንግሥተ ሰማይ በእርሻው
መልካም ዘር የዘራውን ሰው ትመስላለች፤
[25] ነገር ግን ሰው ሁሉ በተኛበት ጊዜ ጠላት
መጣና በስንዴው ውስጥ እንክርዳድ ዘርቶ
ሄደ። [26] ስንዴው በቅሎ ባፈራ ጊዜ እንክርዳ
ዱም በዚያኑ ወቅት ታየ። [27] ስለዚህ የእርሻው
ባለቤት አገልጋዮች ወደ እርሱ ቀርበው ‘ጌታ
ሆይ! በእርሻህ መልካም ዘር ዘርተህ አልነበረ
ምን? ታዲያ እንክርዳዱ ከወዴት መጣ?’
አሉት። [28] እርሱም ‘ይህን ያደረገ ጠላት
ነው!’ አላቸው። አገልጋዮቹም ‘ታዲያ ሄደን
እንክርዳዱን እንድንነቅለው ትፈልጋለህን?’
አሉት። [29] እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው

13፡2 ፡- ሉቃ. 5፡1-3 ። 13፡12 ፡- ማቴ. 25፡29 ፤ ማር. 4፡25 ፤ ሉቃ. 8፡18 ፤ 19፡26 ። 13፡14-15 ፡- ኢሳ. 6፡9-10 ። 13፡16-17 ፡- ሉቃ. 10፡23-24 ።

‘አይሆንም! ምክንያቱም እንክርዳዱን ስትነቅሉ
ስንዴውን አብራችሁ ትነቅላላችሁ። [30] ስለዚህ
ተዉአቸው እስከ መከር ጊዜ ድረስ ስንዴውም
እንክርዳዱም አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜ
ዐጫጆችን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ፤
በእሳት እንዲቃጠልም በየጎራው እሰሩ፤ ስንዴ
ውን ግን ሰብስቡና በጐተራዬ ክተቱ’ እላቸዋ
ለሁ።”

የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ

(ማር. 4፡30-32፤ ሉቃ. 13፡18-19)

[31] ኢየሱስ ሌላ ምሳሌም እንዲህ ሲል ነገራ
ቸው፥ “መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ
ዘሪቱ የዘራችን የሰናፍጭ ዘር ትመስላለች።
[32] እርስዋ ከዘር ሁሉ ያነሰች ናት፤ ባደገች ጊዜ
ግን ከአትክልቶች ሁሉ ትበልጣለች፤ ዛፍም
ታህላለች፤ ወፎችም መጥተው በቅርንጫፎችዋ
ላይ ጎጆአቸውን ሠርተው ይሰፍሩባታል።”

የእርሾ ምሳሌ

(ሉቃ. 13፡20-21)

[33] ደግሞም ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራ
ቸው፥ “መንግሥተ ሰማይ አንዲት ሴት ወስዳ
ከሦስት መስፈሪያ ዱቄት ጋር የለወሰችውን
እርሾ ትመስላለች፤ እርሾውም ሊጡን ሁሉ
እንዲቦካ አደረገው።”

ኢየሱስ ለምን በምሳሌዎች እንዳስተማረ

(ማር. 4፡33-34)

[34] ኢየሱስ ይህን ሁሉ ነገር በምሳሌ ለሕዝቡ
ተናገረ፤ ያለ ምሳሌም ምንም ነገር አልተናገራ
ቸውም። [35] ይህም የሆነበት ምክንያት በነቢይ
እንዲህ ተብሎ የተጻፈው እንዲፈጸም ነው፥

“ንግግሬን በምሳሌ እገልጣለሁ፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውን
እናገራለሁ።”

ኢየሱስ የእንክርዳዱን ምሳሌ እንዳስረዳ

[36] ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ትቶ ወደ
ቤት ገባ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀር
ቡው “የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ትርጉ
ሙን አስረዳን” አሉት።

[37] ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥
“መልካሙን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤
[38] እርሻው ይህ ዓለም ነው፤ መልካሙ ዘር የእ
ግዚአብሔር መንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክር
ዳዱ የሰይጣን ልጆች ናቸው። [39] እንክርዳዱን
የዘራው ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩ የዓለም
መጨረሻ ነው፤ ዐጫጆቹ መላእክት ናቸው።
[40] ልክ እንክርዳዱ ተነቅሎና በየነዶው ታስሮ
እንደሚቃጠል ሁሉ በዓለም መጨረሻም እን
ዲሁ ይሆናል። [41] በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ መላ
እክቱን ይልካል፤ እነርሱም የኃጢአት ምክን
ያት የሆኑትንና ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ከእ
ርሱ መንግሥት ሰብስበው ያወጣሉ፤ [42] ወደ
እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ለቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። [43] ጻድቃን ግን በአባ
ታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ፤ ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ!”

የተሸሸገ ሀብት ምሳሌ

[44] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “መንግ
ሥተ ሰማይ በእርሻ ውስጥ የተሸሸገውን ሀብት
ትመስላለች አንድ ሰው ይህን ሀብት ባገኘው
ጊዜ መልሶ ደበቀው፤ ከደስታውም ብዛት የተ
ነሣ ሄደና ያለውን ሁሉ ሸጦ ያንን እርሻ
ገዛ።”

የዕንቊ ምሳሌ

[45] እንደገናም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “ደግሞ
መንግሥተ ሰማይ ጥሩ ዕንቊ ለመግዛት የሚፈ
ልግ ነጋዴን ትመስላለች፤ [46] ነጋዴውም አጅግ
ክቡር የሆነ ዕንቊ ባገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ
ሸጠና ያንን ዕንቊ ገዛ።”

የመረብ ምሳሌ

[47] ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፥ “እንዲ
ሁም መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር የተጣለች
መረብን ትመስላለች፤ እርስዋ በየዐይነቱ ዓሣ
የምትሰበስብ ናት፤ [48] በሞላች ጊዜ ዓሣ አጥማ
ጆቹ ወደ ባሕሩ ዳር ጐትተው ያወጡአታል፤
ተቀምጠውም ጥሩ ጥሩውን መርጠው በዕቃ
ያስቀምጣሉ፤ መጥፎ መጥፎውን ግን ወዲያ
ይጥላሉ። [49] በዓለም መጨረሻም እንዲህ ይሆ
ናል፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻ
ድቃን ይለዩዋቸዋል። [50] ወደ እቶን እሳትም
ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት
ይሆናል።”

[51] ደግሞም ኢየሱስ “ይህን ሁሉ አስተዋላች
ሁን?” አላቸው።

እነርሱም “አዎ” አሉ። [52] እርሱም “እንግ
ዲያውስ የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ጠንቅቆ
የሚያውቅ የሕግ መምህር ከመዝገብ አዲስ የሆ
ነውንና አሮጌ የሆነውን እንደሚያወጣ ባለቤት
ነው” ሲል መለሰላቸው።

ኢየሱስ በናዝሬት የደረሰበት ተቃውሞ

(ማር. 6፡1-6፤ ሉቃ. 4፡16-30)

[53] ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች ተናግሮ
ካበቃ በኋላ ከዚያ ስፍራ ሄደ። [54] ወደ ገዛ
አገሩ ወደ ናዝሬት ከተማም መጣ፤ እዚያም
በምኩራቦቻቸው ያስተምር ነበር፤ የሰሙትም

13፡35 ፡- መዝ. 78፡2 ።

ሁሉ በመደነቅ እንዲህ ይሉ ነበር ፥ “ይህ ሰው
ይህን ጥበብና ይህን ድንቅ ነገር ከወዴት አመ
ጣው? 55 እናቱስ ማርያም አይደለችምን? ወን
ድሞቹስ ያዕቆብና ዮሴፍ ፡ ስምዖንና ይሁዳ
አይደሉምን? 56 እኅቶቹስ ሁሉ ከእኛ ጋር አይ
ደሉምን? ታዲያ ይህ ሰው ይህን ሁሉ ጥበብ
ከየት አገኘው?” 57 በዚህም ምክንያት ተሰናክ
ለውበት ሳይቀበሉት ቀሩ ። ኢየሱስ ግን “ነቢይ
የሚናቀው በገዛ አገሩና በገዛ ቤተሰቡ ነው
እንጂ በሌላ ቦታስ ይከበራል” አላቸው ። 58 በለ
ማመናቸውም ምክንያት ኢየሱስ በዚያ ብዙ
ተአምር አላደረገም ።

ምዕራፍ 14

የአጥማቂው ዮሐንስ ሞት
(ማር. 6፡14-29፡ ሉቃ. 9፡7-9)

1 በዚያን ጊዜ የገሊላ ክፍለ ሀገር ገዥ የነበ
ረው ሄሮድስ ፡ የኢየሱስን ዝና ሰማ ። 2 ሎሌዎ
ቹንም “ይህ አጥማቂው ዮሐንስ ነው ፤ እርሱ
ከሞት ተነሥቶአል ፤ ይህ ሁሉ ድንቅ ኀይል
የሚደረገውም ስለዚህ ነው” አላቸው ።

3 ሄሮድስ የሐንስን አስይዞ በወህኒ ቤት አሳስ
ሮት ነበር ፤ ይህንንም ያደረገው የወንድሙ የፊ
ልጵስ ሚስት በነበረችው በሄሮዲያዳ ምክንያት
ነው ። 4 የሐንስ ሄሮድስን “የወንድምህን ሚስት
እንድታገባ ሕግ አይፈቅድልህም!” ብሎት
ነበር ። 5 ስለዚህ ሄሮድስ የሐንስን ሊገድለው
ይፈልግ ነበር ፤ ነገር ግን አይሁዳውያን እንደ
ነቢይ ያዩት ስለነበር ሕዝቡን ፈራ ። 6 የሄሮድስ
ልደት ቀን በሚከበርበት ጊዜ የሄሮድያዳ ልጅ
መጥታ በተጋባዥዎች መካከል እየዘፈነች ባሳየ
ችው ውዝዋዜ ሄሮድስን አስደሰተች ። 7 ስለዚህ
ሄሮድስ “የምትፈልጊውን ነገር ጠይቂኝ ፥
እኔም እሰጥሻለሁ” ሲል በመሐላ ቃል ገባላት ።

8 እርስዋም በእናቷ ተመክራ “የአጥማቂውን
የዮሐንስን ራስ በሳሕን አውጥኑ ስጠኝ” አለ
ችው ።

9 ንጉሡ በዚህ ነገር አዘነ ፤ ይሁን እንጂ ስለ
መሐላውና ከእርሱ ጋር በማእድ ተቀምጠው ስለ
ነበሩት ሰዎች ይሉኝታ ብሎ የዮሐንስ ራስ እን
ዲሰጣት አዘዘ ። 10 ስለዚህ ሰው ልኮ የዮሐንስን
ራስ በወህኒ ቤት አስቈረጠ ። 11 የተቈረጠውንም
ራስ በሳሕን አምጥተው ለልጅቱ ሰጡአት ፤ እር
ስዋም ለእናትዋ ወስዳ ሰጠች ። 12 የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትም መጡና አስከሬኑን ወስደው ቀበ
ሩት ፤ ሄደውም ይህን ነገር ለኢየሱስ ነገሩት ።

ኢየሱስ አምስት ሺ ሰዎችን መገበ
(ማር. 6፡30-44፡ ሉቃ. 9፡10-17፡ ዮሐ. 6፡1-14)

13 ኢየሱስ የዮሐንስን መሞት በሰማ ጊዜ
በጀልባ ተሳፈረና ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ
ብቻውን ለመሆን ሄደ ። ሕዝቡም ይህን በሰሙ
ጊዜ ከየከተሞቻቸው እየወጡ በእግር ተከተ
ሉት ። 14 ኢየሱስ ከጀልባው በወረደ ጊዜ ብዙ
ሰዎችን አይቶ ራራላቸው ፤ በሽተኞቻቸውንም
ፈወሰ ።

15 በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው ፥ “ይህ ቦታ በረሓ ነው ፤ ቀኑም መሽ
ቶአል ፤ ስለዚህ ሕዝቡ በአቅራቢያ ወዳሉት
መንደሮች ሄደው ምግባቸውን እንዲገዙ አሰና
ብታቸው” አሉት ።

16 ኢየሱስ ግን “እናንተ የሚበሉትን ስጡአ
ቸው እንጂ እነርሱ እንዲሁ ሊሄዱ አይገባም”
አላቸው ።

17 ደቀ መዛሙርቱም “እኛ ከአምስት እንጀ
ራና ከሁለት ዓሣ በቀር እዚህ ምንም የለንም”
ሲሉ መለሱለት ።

18 ኢየሱስም “እነርሱኑ ወደ እኔ አምጡ
ልኝ!” አላቸው ። 19 ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በሣሩ
ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ ፤ አምስቱን እንጀራና
ሁለቱን ዓሣ አንሥቶ ወደ ሰማይ አቸቅዶ አየና
የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ እንጀራውንም ቈርሶ
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ለሕ
ዝቡ አቀረቡ ። 20 ሁሉም በልተው ጠገቡ ፤ የተ
ረፈቸውን ፍርፋሪ ደቀ መዛሙርቱ በዐሥራ
ሁለት መሶብ ሞልተው አነሡ ። 21 የበሉትም
ሰዎች ሴቶችና ሕፃናት ሳይቈጠሩ አምስት ሺ
የሚያህሉ ነበሩ ።

ኢየሱስ በባሕር ላይ እየተራመደ ሄደ
(ማር. 6፡45-52፡ ዮሐ. 6፡15-21)

22 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
“እኔ ሕዝቡን እስካሰናብት ድረስ በጀልባ ተሳ
ፈሩና ቀድማችሁኝ ወደ ማዶ ተሻገሩ” ሲል
አዘዛቸው ። 23 ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ለመጸ
ለይ ብቻውን ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጣ ፤
በመሸም ጊዜ ኢየሱስ እዚያ ብቻውን ነበር ።
24 በዚያን ጊዜ ጀልባዋ ከባሕሩ ወደብ ብዙ
ርቃ ነበር ፤ ብርቱ ነፋስ ከወደ ፊትዋ ተነሥቶ
ስለነበር በማዕበሉ ወዲያና ወዲህ በማለት ትንገ
ላታ ነበር ። 25 ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በኋላ አያ
ሱስ በባሕር ላይ እየተራመደ ወደ ደቀ መዛሙ
ርቱ መጣ ። 26 ደቀ መዛሙርቱም በባሕሩ ላይ
እየተራመደ ሲሄድ ባዩት ጊዜ በጣም ፈርተው
ደነገጡ ፤ “ይህ ምትሐት ነው!” ብለውም በፍ
ርሐት ጮኹ ።

27 ኢየሱስም ወዲያውኑ አነጋገራቸውና
“አይዞአችሁ! እኔ ነኝ ፤ አትፍሩ!” አላቸው ።

28 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ “ጌታ ሆይ! አንተስ
ከሆንህ በባሕሩ ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ
መምጣት እንድችል አድርገኝ” አለው ።

13፡57 ፡- ዮሐ. 4፡44 ። 14፡3-4 ፡- ሉቃ. 3፡19-20 ። 14፡4 ፡- ዘሌ. 18፡16 ፡ 20፡21 ።

29 ኢየሱስም “ና” አለው ። ስለዚህ ጴጥሮስ
ከጀልባው ወርዶ ወደ ኢየሱስ ለመሄድ በባሕሩ
ላይ ተራመደ ። 30 ነገር ግን የነፋሱን ኀይል
አይቶ ፈራ ፤ ወደ ባሕሩ ውስጥ ለመስጠም በተ
ቃረበ ጊዜ “ጌታ ሆይ! አድነኝ!” ሲል ጮኸ ።
31 ኢየሱስ ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ ያዘውና
“አንተ እምነት የጐደለህ! ስለምን ተጠራጠ
ርህ?” አለው ።
32 ኢየሱስና ጴጥሮስ ወደ ጀልባው በገቡ
ጊዜ ነፋሱ ጸጥ አለ ። 33 በጀልባውም ውስጥ የነ
በሩት ሁሉ “በእርግጥ አንተ የእግዚአብሔር
ልጅ ነህ!” ብለው ለኢየሱስ ሰገዱለት ።

ኢየሱስ በጌንሴሬት ሕመምተኞችን ፈወሰ
(ማር. 6፡53-56)

34 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ባሕሩን ተሻግ
ረው ወደ ጌንሴሬት ምድር ደረሱ ። 35 በዚያም
አገር የነበሩ ሰዎች ኢየሱስ መሆኑን ባወቁ ጊዜ
በዙሪያ ወዳሉት አገሮች ተላልከው በሽተኞችን
ወደ እርሱ አስመጡ ። 36 በሽተኞቹም የልብ
ሱን ጫፍ ብቻ እንዲነኩ ለመኑት ። የነኩትም
ሁሉ ከበሽታቸው ተፈወሱ ።

ምዕራፍ 15

ስለ አባቶች ወግ
(ማር. 7፡1-13)

1 ከዚህ በኋላ ከኢየሩሳሌም የመጡ ፈሪሳው
ያንና የሙሴ ሕግ መምህራን ወደ ኢየሱስ ቀር
ቡው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት ፤ 2 “ደቀ መዛሙር
ትህ የሽማግሌዎችን ወግ ስለምን ያፈርሳሉ?
እጃቸሁ ምግብ የሚበሉት እጃቸውን ሳይታጠቡ
ነው ።”
3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እናንተስ ወጋችሁን ለመጠበቅ ብላችሁ የእግ
ዚአብሔርን ትእዛዝ ስለምን ታፈርሳላችሁ?
4 ምክንያቱም እግዚአብሔር ‘አባትህንና እናት
ህን አክብር ፤ በአባቱ ወይም በእናቱ ላይ የስ
ድብ ቃል የተናገረ በሞት ይቀጣል’ ብሎ አዝዞ
አል ። 5 እናንተ ግን ፥ አንድ ሰው አባቱን
ወይም እናቱን ‘ከእኔ የምታገኙትን ዕርዳታ ለእ
ግዚአብሔር መባ አድርጌ አቅርቤአለሁ’ ቢላ
ቸው ፤ 6 ያ ሰው ፥ አባቱን [ወይም እናቱን]9*
ማክበር አያስፈልገውም ትላላችሁ ፤ ስለዚህ
ወጋችሁን ለማጥበቅ ብላችሁ የእግዚአብሔርን
ሕግ ታፈርሳላችሁ ፤ 7 እናንተ ግብዞች! ኢሳይ
ያስ ስለ እናንተ እንዲህ ሲል የተናገረው ትን
ቢት ልክ ነው ፥

8 ‘ይህ ሕዝብ በአፉ ያከብረኛል ፤
ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው ፤
9 ሰው ሠራሽ ወግና ሥርዓትን
እንደ ሕግ አድርጎ እያስተማረ በከንቱ
ያመልከኛል ።’”

ሰውን የሚያረክስ ነገር
(ማር. 7፡14-23)

10 ቀጥሎም ኢየሱስ ሕዝቡን ወደ እርሱ
ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ “ስሙ ፡ አስተውሉ ፤
11 ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው
እንጂ ወደ አፍ የሚገባው አይደለም ።”
12 ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው ፥ “ፈሪሳውያን ይህን የተናገርኸውን
ሰምተው እንደተሰናከሉ ዐውቀሃልን?” ሲሉ
ጠየቁት ። 13 እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰላ
ቸው ፥ “የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ
ይነቀላል ፤ 14 እነርሱ የታውሩና የዕውራን መሪ
ዎች ስለሆኑ ተዉአቸው ፤ ዕውር ዕውርን
ቢመራ ሁለቱም በጉድጓድ ውስጥ ይወድ
ቃሉ ።”
15 ጴጥሮስ ኢየሱስን “የምሳሌውን ትርጉም
አስረዳን” አለው ። 16 ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥
“እናንተም እስከ አሁን ገና የማታስተውሉ ናች
ሁን? 17 ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ
ወርዶ ወደ ውጪ እንደሚጣል አታስተውሉ
ምን? 18 ከአፍ የሚወጣው ግን ከልብ ይወ
ጣል ፤ ሰውን የሚያረክሰውም እርሱ ነው ።
19 ምክንያቱም ክፉ ማሰብ ፤ ሰው መግደል ፥
ማመንዘር ፥ ዝሙት ማድረግ ፥ መስረቅ ፥ ሐሰት
መናገር ፥ የሰው ስም ማጥፋት ፤ ይህ ሁሉ
ከሰው ልብ ይወጣል ። 20 ሰውን የሚያረክሰው
ይህን የመሳሰለው ነገር ነው እንጂ ባልታጠበ
እጅ መብላትስ አያረክሰውም ።”

የአንዲት ከነዓናዊት ሴት እምነት
(ማር. 7፡24-30)

21 ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና ወደ
ሲዶና አገር ሄደ ፤ 22 ከዚያም አገር አንዲት ከነ
ዓናዊት ሴት ወደ ኢየሱስ መጥታ “የዳዊት
ልጅ ጌታ ሆይ! ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ
ትሠቃያለችና እባክህ ራራልኝ” እያለች
ጮኸች ።
23 እርሱ ግን አንድም ቃል ሳይመልስላት
ዝም አለ ፤ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
እርሱ ቀርበው “ይህች ሴት እየተከተለችን ስለ
ምትጮኽ እባክህ አሰናብታት” ሲሉ ለመኑት ።
24 እርሱም “እኔ የተላክሁት ከእስራኤል ቤት
እንደ በጎች ለጠፉት ብቻ ነው” ሲል መለሰ ።

9* 15፡6 አባቱን ፡- አንዳንድ ቅጂዎች “አባቱን ወይም እናቱን” ይላሉ ።

15፡4 ፡- ዘጽ. 20፡12 ፡ 21፡17 ፤ ዘዳ. 5፡16 ፤ ዘሌ. 20፡9 ። 15፡8-9 ፡- ኢሳ. 29፡13 ። 15፡14 ፡- ሉቃ. 6፡39 ።
15፡18 ፡- ማቴ. 12፡34 ።

25ሴትዮዋ ግን ቀርባ በእግሩ ሥር ተንበረከ
ከችና “ጌታ ሆይ! እባክህ እርዳኝ!” አለችው ።
26ኢየሱስም “የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለው
ሾች መጣል የተገባ አይደለም” አለ ።
27እርስዋም “ጌታ ሆይ! እርግጥ ነው ፤
ነገር ግን ውሾችም እኮ ከጌቶቻቸው ማእድ የወ
ደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ” አለች ።
28በዚያን ጊዜ ኢየሱስ “እንቺ ሴት! እምነ
ትሽ ትልቅ ነው ፤ ስለዚህ እንደፍላጎትሽ ይሁን
ልሽ!” አላት ። የሴትዮዋም ልጅ በዚያኑ ሰዓት
ዳነች ።

ኢየሱስ ብዙ
ሕመምተኞችን ፈወሰ

29ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ገሊላ ባሕር
አጠገብ መጣ ፤ ወደ ተራራ ላይም ወጥቶ እዚያ
ተቀመጠ ። 30ብዙ ሰዎች አንካሶችን ፥ ዕውሮ
ችን ፥ ሽባዎችን ፥ ድዳዎችንና ሌሎችንም በሽ
ተኞች ይዘው ወደ ኢየሱስ መጡ ፤ በእግሩም
ሥር አስቀመጡአቸው ፤ እርሱም ፈወሳቸው ።
31ስለዚህ ሕዝቡ ድዳዎች ሲናገሩ ፥ ሽባዎች
ሲድኑ ፥ አንካሳዎች በደኅና ሲራመዱ ፥ ዕይነ
ስውሮች ሲያዩ ፥ በተመለከቱ ጊዜ ተደንቀው
የእስራኤልን አምላክ አመሰገኑ ።

ኢየሱስ አራት ሺ ሰዎች መገበ
(ማር. 8፡1-10)

32ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እንዲህ
አላቸው ፥ “ሕዝቡ ከእኔ ጋር ሦስት ቀናቸው
ስለሆነና የሚበሉት ስለሌላቸው እራራላቸዋ
ለሁ ፤ ሲጐዱ በመንገድ ዝለው እንዳይወድቁ
ምንም ሳይመገቡ ላሰናብታቸው አልፈቅ
ድም ።”
33ደቀ መዛሙርቱም “ታዲያ ለዚህ ሁሉ
ሰው የሚበቃ ምግብ በዚህ በረሓ ከየት እናገኛ
ለን?” አሉት ። 34ኢየሱስም “ስንት እንጀራ
አላችሁ?” ሲል ጠየቃቸው ። እነርሱም “ሰባት
እንጀራና ጥቂት ትናንሽ ዓሣ አለን” አሉት ።
35ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡ በመሬት ላይ
እንዲቀመጡ አዘዘ ፤ 36ሰባቱን እንጀራና ዓሣው
ንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ ቈርሶም
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ለሕ
ዝቡ አቀረቡ ። 37ሁሉም በልተው ጠገቡ ፤ የተ
ረፈውንም ደቀ መዛሙርቱ ሰብስበው ሰባት
መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ አነሡ ። 38የበሉትም
ሰዎች ሴቶችና ሕፃናት ሳይቈጠሩ አራት ሺ
የሚያህሉ ነበሩ ።
39ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን አሰናበተ ፤
በጀልባም ተሳፍሮ ወደ መጊዶን አገር ሄደ ።

ምዕራፍ 16

ተአምር ለማየት የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 8፡11-13፤ ሉቃ. 12፡54-56)

1ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ ኢየሱስ
መጡ ፤ ሊፈትኑትም ፈልገው “ከሰማይ ተአ
ምር አሳየን” ሲሉ ጠየቁት ። 2እርሱ ግን እን
ዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ [“ሲመሽ ‘ሰማዩ ቀል
ቶአልና አይዘንምም’ ትላላችሁ ፤ 3ጠዋት በማ
ለዳ ደግሞ ‘ሰማዩ ደመና ሆኖ ቀልቶአልና ዛሬ
ይዘንማል’ ትላላችሁ ፤ የሰማዩንስ መልክ መለ
የት ታውቃላችሁ ፤ ነገር ግን የዘመኑን ምልክት
መለየት አትችሉም ።]10* 4ክፉና እምነተ ቢስ
የሆኑ የዚህ ዘመን ሰዎች ምልክት ለማየት ይፈ
ልጋሉ ፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት በቀር
ሌላ ምልክት አይሰጣቸውም ።” ከዚህ በኋላ
ኢየሱስ ትቶአቸው ወደ ሌላ ስፍራ ሄደ ።

የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እርሾ
(ማር. 8፡14-21)

5ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ማዶ በተሻገሩ
ጊዜ ረስተው እንጀራ አልያዙም ነበር ፤ 6ኢየሱስ
ደቀ መዛሙርቱን “ልብ አድርጉ! ከፈሪሳውያንና
ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁ!” አላቸው ።
7እነርሱም “ይህን ማለቱ ምናልባት እንጀራ
ስላልያዝን ይሆናል” በማለት እርስ በርሳቸው
ተነጋገሩ ።
8ኢየሱስ ግን አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው ፥ “እናንተ እምነት የጐደላችሁ ፤ ‘እን
ጀራ ስላልያዝን ነው’ ብላችሁ ስለምን እርስ
በርሳችሁ ትነጋገራላችሁ? 9ገና የማታስተውሉ
ናችሁን? አምስት እንጀራ ለአምስት ሺ ሰው
እንደበቃና የተረፈውን ፍርፋሪ ምን ያህል
መሶብ ሙሉ እንዳነሣችሁ አታስታውሉምን?
10እንዲሁም ሰባት እንጀራ ለአራት ሺ ሰው
እንደበቃና የተረፈውን ፍርፋሪ ምን ያህል
መሶብ ሙሉ እንዳነሣችሁ አታስታውሉምን?
11እንግዲህ ‘ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ
ተጠንቀቁ’ ብዬ ስነግራችሁ ፥ ስለ እንጀራ አለ
መሆኑን እንዴት አታስተውሉም?”
12ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ተጠንቀቁ ያላ
ቸው ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት
እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዳልሆነ ተገነዘቡ ።

የጴጥሮስ እምነትና ምስክርነት
(ማር. 8፡27-30፤ ሉቃ. 9፡18-21)

13ኢየሱስ ወደ ፊልጵስ ቂሳርያ አገር በደረሰ
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን “ሰዎች የሰውን ልጅ
ማን ነው ይሉታል?” ሲል ጠየቃቸው ።

10* 16፡3 አንዳንድ ቅጂዎች በቍ. 2 እና 3 የኢየሱስን ቃል አይጠቅሱም ።
16፡1 ፡- ማቴ. 12፡38 ፤ ሉቃ. 11፡16 ። 16፡4 ፡- ማቴ. 12፡39 ፤ ሉቃ. 11፡29 ። 16፡6 ፡- ሉቃ. 12፡1 ።
16፡9 ፡- ማቴ. 14፡17-21 ። 16፡10 ፡- ማቴ. 15፡34-38 ።

14እነርሱም “አንዳንዶች ‘አጥማቂው ዮሐ
ንስ ነው’ ይላሉ ፤ ሌሎች ‘ኤልያስ ነው’
ይላሉ ፤ ሌሎች ደግሞ ‘ኤርምያስ ወይም ከነቢ
ያት አንዱ ነው’ ይላሉ” አሉት ።
15ኢየሱስም “እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላ
ችሁ?” አላቸው ።
16በዚያን ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ “አንተ የሕ
ያው እግዚአብሔር ልጅ የሆንህ መሲሕ ነህ!”
ሲል መለሰለት ።
17ኢየሱስም እንዲህ አለው ፥ “የዮና ልጅ
ስምዖን ሆይ! የተባረክህ ነህ! ምክንያቱም
ይህን የገለጠልህ በሰማይ ያለው አባቴ ነው
እንጂ ሰው አይደለም ። 18እኔም እንዲህ እልሃ
ለሁ ፤ ጴጥሮስ ፡ አንተ አለት ነህ ፤ በዚህችም
የመሠረት ድንጋይ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራ
ለሁ ፤ ይህችንም ቤተ ክርስቲያን የሞት ኀይል
እንኳ አያሸንፋትም ። 19እነሆ ለአንተ የመንግ
ሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ ፤ በም
ድር ያሰርከው በሰማይ የታሰረ ይሆናል ፤ በም
ድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል ።”
20ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ
ክርስቶስ መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛ
ቸው ።

ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት
ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረ
(ማር. 8፡31-33፤ ሉቃ. 9፡22-27)

21ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ ደቀ መዛሙ
ርቱን እንዲህ ይላቸው ጀመር ፥ “ወደ ኢየሩሳ
ሌም መሄድ አለብኝ ፤ እዚያም ከሽማግሌዎች ፥
ከካህናት አለቆችና ከሙሴ ሕግ መምህራን
መከራ እቀበላለሁ ፤ ከሞትሁም በኋላ በሦስት
ኛው ቀን እነሣለሁ ።”
22ጴጥሮስ ግን ኢየሱስን ለብቻ ገለል አድ
ርጎ “ጌታ ሆይ! ከቶ አይሆንም! ይህ ነገር በአ
ንተ ላይ አይድረስብህ!” እያለ ይከለክለው
ጀመር ።
23ኢየሱስ ግን ዞር ብሎ ጴጥሮስን “ከእኔ
ወዲያ ሂድ ሰይጣን! አንተ የሰውን እንጂ የእግ
ዚአብሔርን ነገር ስለማታስብ መሰናክል ትሆን
ብኛለህ” አለው ።

ኢየሱስን የመከተል ሁኔታ
(ማር. 8፡34-9፡1፤ ሉቃ. 9፡23-27)

24ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው ፥ “እኔን መከተል የሚፈልግ
ራሱን ይካድ ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተ
ለኝ ። 25ሕይወቱን ለማዳን የሚፈልግ ሁሉ
ያጠፋታል ፤ ሕይወቱን ስለእኔ የሚያጠፋት ግን
ያገኛታል ። 26ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ ቢሆ
ንና ነፍሱን ግን ቢያጠፋ ምን ይጠቅመዋል?
ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ዋጋ ሊከፍል
ይችላል? 27የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ሆኖ
ከመላእክቱ ጋር ይመጣል ፤ በዚያን ጊዜም ለእ
ያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ይከፍለ
ዋል ። 28በእውነት እላችኋለሁ ፥ የሰው ልጅ
በመንግሥቱ ክብር ሲመጣ እስከሚያዩ ድረስ
በዚህ ከቆሙት መካከል የማይሞቱ ሰዎች
አሉ ።”

ምዕራፍ 17

የኢየሱስ መልክ መለወጥ
(ማር. 9፡2-13፤ ሉቃ. 9፡28-36)

1ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን ፥
ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን ብቻ
አስከትሎ ወደ አንድ ከፍተኛ ተራራ ላይ
ወጣ ። 2እዚያ በፊታቸው መልኩ ተለወጠ ፤
ፊቱም እንደ ፀሐይ አበራ ፤ ልብሱም ነጭ ሆኖ
እንደ ብርሃን አንጸባረቀ ። 3እነሆ ሙሴና ኤል
ያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው ። 4በዚ
ያን ጊዜ ጴጥሮስ ኢየሱስን “ጌታ ሆይ! እዚህ
መኖር ለእኛ መልካም ነው ፤ ስለዚህ ብትፈቅ
ድስ አንድ ለአንተ ፥ አንድ ለሙሴ ፥ አንድ ለኤ
ልያስ የሚሆኑ ሦስት ዳሶች ልሥራ” አለው ።
5ጴጥሮስ ገና ይህንን ሲናገር ሳለ ብሩህ
ደመና ጋረዳቸው ፤ ከደመናውም ውስጥ “በእ
ርሱ ደስ የሚሰኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤
እርሱን ስሙት” የሚል ድምፅ መጣ ።
6ደቀ መዛሙርቱም ይህን ድምፅ በሰሙ
ጊዜ እጅግ ስለደነገጡ በግንባራቸው በመሬት
ላይ ተደፉ ። 7ኢየሱስ ግን ወደእነርሱ ቀርቦ
በእጁ ዳሰሳቸውና “ተነሡ ፥ አይዞአችሁ ፥ አት
ፍሩ!” አላቸው ። 8እነርሱም ቀና ብለው
ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም ።
9ከተራራው ሲወርዱ ሳሉ ኢየሱስ “የሰው
ልጅ ከርስቶስ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ይህን ያያ
ችሁትን ለማንም አትንገሩ” ሲል ደቀ መዛሙር
ቱን አዘዛቸው ።
10ደቀ መዛሙርቱም “ታዲያ የሙሴ ሕግ
መምህራን አስቀድሞ መምጣት ያለበት ኤልያስ
ነው ለምን ይላሉ?” ሲሉ ኢየሱስን ጠየቁት ።
11ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “እር
ግጥ ነው ፥ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ፤
እርሱ ሁሉንም ያስተካክላል ። 12ነገር ግን ኤል
ያስ ገና ድሮ መጥቶአል እላችኋለሁ ፤ ሰዎች

16፡14 ፡- ማቴ. 14፡1-2 ፤ ማር. 6፡14-15 ፤ ሉቃ. 9፡7-8 ። 16፡16 ፡- ዮሐ. 6፡66-69 ። 16፡19 ፡- ማቴ. 18፡18 ፤
ዮሐ. 20፡23 ። 16፡24 ፡- ማቴ. 10፡38 ፤ ሉቃ. 14፡27 ። 16፡25 ፡- ማቴ. 10፡39 ፤ ሉቃ. 17፡33 ፤ ዮሐ. 12፡25 ።
16፡27 ፡- ማቴ. 25፡31 ፤ መዝ. 62፡12 ፤ ሮም 2፡6 ። 17፡1-5 ፡- 2ጴጥ. 1፡17-18 ። 17፡5 ፡- ዘፍ. 22፡2 ፤ ዘጻ. 18፡15 ፤
መዝ. 2፡7 ፤ ኢሳ. 42፡1 ፤ ማቴ. 3፡17 ፤ 12፡18 ፤ ማር. 1፡11 ፤ ሉቃ. 3፡22 ። 17፡10 ፡- ሚል. 4፡5 ።
17፡12 ፡- ማቴ. 11፡14 ።

ግን አላወቁትም ፤ ስለዚህ የፈለጉትን ሁሉ አደ
ረጉበት ። እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከርስ
ቶስ በእነርሱ እጅ መከራን መቀበል አለበት ።”
13 በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የተ
ናገረው ስለ አጥማቂው ዮሐንስ መሆኑ ገባ
ቸው ።

ኢየሱስ ጋኔን ያደረበትን ልጅ ፈወሰ
(ማር. 9፡14-29፤ ሉቃ. 9፡37-43)

14 ኢየሱስና ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ወደ
ሕዝቡ በተመለሱ ጊዜ አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ
መጥቶ በእግሩ ሥር ተንበረከከና እንዲህ አለ ፥
15 “ጌታ ሆይ! እባክህ ለልጄ ራራለት ፤ የሚ
ጥል የጋኔን በሽታ ክፉኛ ያሠቃየዋል ፤ በእሳት
ላይና በውሃ ውስጥ ብዙ ጊዜ ይወድቃል ።
16 ወደ ደቀ መዛሙርትህም አምጥቸው ነበር ፤
ነገር ግን ሊፈውሱት አልቻሉም ።” 17 ኢየሱ
ስም “እናንተ የማታምኑ ጠማማ ሰዎች ፡ እስከ
መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ
እታገሣችኋለሁ? እስቲ ልጁን ወደ እኔ አም
ጡት!” አላቸው ። 18 ኢየሱስ ጋኔኑን ገሠጸው ፤
ጋኔኑም ከልጁ ወጣ ፤ ልጁም በዚያኑ ሰዓት
ተፈወሰ ።
19 ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን
ወደ ኢየሱስ ቀርበው “እኛ ጋኔኑን ለማውጣት
ያልቻልነው ስለምንድን ነው?” ሲሉ ጠየቁት ።
20 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፡ “እምነታችሁ
ጐደሎ ስለሆነ ነው ፤ በእውነት እላችኋለሁ ፡
የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራ
ችሁ ይህን ተራራ ‘ከዚህ ተነሥተህ ወዲያ
ሂድ!’ ብትሉት ይሄዳል ፤ የሚሳናችሁም
ምንም ነገር አይኖርም ። [21 እንዲህ ዐይነቱ
ጋኔን ግን በጸሎትና በጾም ካልሆነ በቀር ከቶ
አይወጣም ።”]11*

ኢየሱስ ስለ ሞቱ ሁለተኛ ጊዜ ተናገረ
(ማር. 9፡30-32፤ ሉቃ. 9፡43-45)

22 በገሊላ ደቀ መዛሙርቱ በተሰበሰቡ ጊዜ
ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፡ “የሰው ልጅ በሰዎች
እጅ ተላልፎ ይሰጣል ፤ 23 እነርሱ ይገድሉ
ታል ፤ ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነ
ሣል ።” ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር እጅግ
አዘኑ ።

የቤተ መቅደስ ግብር ስለመክፈል

24 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቅፍርና
ሆም በደረሱ ጊዜ የቤተ መቅደስ ግብር ተቀባ
ዮች ወደ ጴጥሮስ ቀረቡና ፥ “መምህራችሁ
የቤተ መቅደስ ግብር ይከፍላልን?” ሲሉ ጠየ
ቁት ። 25 ጴጥሮስም “አዎ ፤ ይከፍላል” አላ
ቸው ። ጴጥሮስ ወደ ቤት በገባ ጊዜ ኢየሱስ
በመጀመሪያ “ስምዖን ጴጥሮስ ሆይ! ምን ይመ
ስልሃል ፥ የዚህ ዓለም መንግሥታት ቀረጥና
ግብር የሚቀበሉት ከማን ነው? ከሕዝባቸው
ነውን ወይስ ከውጭ አገር ሰዎች?” ሲል ጠየ
ቀው ። 26 ጴጥሮስም “ከውጭ አገር ሰዎች
ነው” ሲል መለሰ ። ኢየሱስም እንዲህ አለ ፥
“እንግዲያውስ የአገሩ ሕዝብ ግብር ከመክፈል
ነፃ ናቸው ማለት ነዋ! 27 ነገር ግን እነርሱ እን
ዳይሰናከሉ ወደ ባሕር ሂድና መንጠቆ ጣል ፤
በመጀመሪያ የሚወጣውን ዓሣ ያዝ ፤ አፉንም
ስትከፍት ሁለት ብር የሚያህል ገንዘብ ታገኛ
ለህ ፤ ያንንም ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ
ፈንታ ክፈል ።”

ምዕራፍ 18

ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?
(ማር. 9፡33-37፤ ሉቃ. 9፡46-48)

1 በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ
ቀርበው “በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ
ማን ነው?” ሲሉ ጠየቁት ። 2 ኢየሱስም አንድ
ሕፃን ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ ፤ 3 እንዲህም
አለ ፥ “በእውነት እላችኋለሁ ካልተለወጣችሁና
እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ፡ ወደ መንግሥተ
ሰማይ ከቶ አትገቡም ። 4 እንደዚህ ሕፃን ራሱን
ዝቅ የሚያደርግ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይሆ
ናል ። 5 እንደዚህ ያለውን ሕፃን በስሜ የሚቀ
በል እኔን ይቀበላል ። 6 በእኔም ከሚያምኑት ከነ
ዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያስት ሰው ከባድ
የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ላይ ታስሮ ወደ
ጥልቅ ባሕር ቢጣልና ቢሰጥም ይሻለዋል ።”

የመሰናከያ ምክንያት
(ማር. 9፡42-48፤ ሉቃ. 17፡1-2)

7 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “የኃጢ
አት ምክንያት በሚሆኑ ነገሮች ለተሞላች
ዓለም ወዮላት! መቼም የመሰናከያ ምክንያት
መምጣቱ አይቀርም ፤ ነገር ግን የመሰናከያ
ምክንያት ለሚሆነው ለዚያ ሰው ወዮለት! 8 ስለ
ዚህ እጅህ ወይም እግርህ የኃጢአት ምክንያት
ቢሆንብህ ቁርጠህ ወዲያ ጣለው ፤ ሁለት እጅ
ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት
ከምትጣል ይልቅ ጉንጭሽ ወይም አንካሳ ሆነህ
ወደ ዘላለም ሕይወት መግባት ይሻልሃል ።
9 ዐይንህም የኃጢአት ምክንያት ቢሆንብህ አው
ጥተህ ወዲያ ጣለው ፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ
ገሃነም እሳት ከምትጣል ይልቅ አንድ ዐይና

11* 17፡21 አንዳንድ ቅጂዎች ቁ. 21 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በማር. 9፡29 ያለውን ይመስላል ።
17፡20 ፡- ማቴ. 21፡21 ፤ ማር. 11፡23 ፤ ፡ቆሮ. 13፡2 ። 17፡24 ፡- ዘጸ. 30፡13 ፤ 38፡26 ። 18፡1 ፡- ሉቃ. 22፡24 ።
18፡3 ፡- ማር. 10፡15 ፤ ሉቃ. 18፡17 ። 18፡8 ፡- ማቴ. 5፡30 ። 18፡9 ፡- ማቴ. 5፡29 ።

ሆነህ ወደ ዘላለም ሕይወት መግባት ይሻል
ሃል ። 10 ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱንም እንዳት
ንቁ ተጠንቀቁ ፤ በሰማይ ያሉት የእነርሱ መላእ
ክት በሰማይ ባለው ባባቴ ፊት ሁልጊዜ ይገ
ኛሉ ። [11 የሰው ልጅም የመጣው የጠፋውን
ለማዳን ነው ።”]12*

የጠፋው በግ ምሳሌ
(ሉቃ. 15፡3-7)

12 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “እስቲ
ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው መቶ በጎች
ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋበት ዘጠና ዘጠ
ኙን በተራራ ጥግ ትቶ የጠፋውን ለመፈለግ
አይሄድም? 13 ባገኘው ጊዜ ፥ በእውነት እላችኋ
ለሁ ፥ ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ
በተገኘው በግ ደስ ይለዋል ። 14 እንዲሁም በሰ
ማይ ያለው አባታችሁ ከነዚህ ከታናናሾች አን
ዱም እንዲጠፋ አይፈልግም ።”

ለበደልኛ ሰው ምን ማድረግ እንደሚገባ

15 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “ወንድ
ምህ ቢበድልህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆና
ችሁ በደሉን ንገረው ፤ ቢሰማህ እንደገና ወንድ
ምህ እንዲሆን ታደርገዋለህ ፤ 16 ባይሰማህ ግን
የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ምስክርነት ስለ
ሚጸና ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ይዘህ ወደ
እርሱ ሂድ ። 17 እነርሱንም አልሰማም ቢል
ለቤተ ክርስቲያን ንገር ፤ ቤተ ክርስቲያንንም
የማይሰማ ከሆነ እንደ አረመኔና ተጸጽቶ እንደ
ማይመለስ ኃጢአተኛ ቍጠረው ።
18 “በእውነት እላችኋለሁ ፥ በምድር የምታ
ስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል ፤ በምድር የምት
ፈቱትም በሰማይ የተፈታ ይሆናል ። 19 ደግ
ሞም እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር ላይ
ማናቸውንም ነገር ለመለመን በጸሎት ቢተባበሩ
በሰማይ ያለው አባቴ ይፈጽምላቸዋል ። 20 ምክ
ንያቱም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ
በሚሰበሰቡበት ስፍራ እኔ በመካከላቸው እገኛ
ለሁ ።”

ይቅርታ ስለማድረግ

21 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ
“ጌታ ሆይ! ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ
ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?” ሲል
ጠየቀው ።
22 ኢየሱስም እንዲህ አለው ፥ “እስከ ሰባ
ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልል
ሃም ፤ 23 ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ ከአገልጋዮቹ
ጋር ሊተሳሰብ የፈለገውን ንጉሥ ትመስላለች ፤
24 ንጉሡ መተሳሰብ በጀመረ ጊዜ በሚሊዮን
የሚቈጠር ብር ዕዳ ያለበት አንድ አገልጋይ
ተይዞ መጣ ። 25 ይህ አገልጋይ ዕዳውን መክፈል
ስላልቻለ እርሱም ፥ ሚስቱም ፥ ልጆቹም ያለ
ውም ንብረት ሁሉ ተሽጦ ዕዳው እንዲከፈል
ጌታው አዘዘ ። 26 አገልጋዩ ግን በጌታው እግር
ሥር ተንበርክኮ ፥ ‘ጌታ ሆይ! እባክህ ታገሠኝ ፤
ሁሉንም እከፍልሃለሁ!’ ሲል ለመነው ።
27 ጌታውም ራራለትና ለቀቀው ፤ ዕዳውንም
ተወለት ።
28 “ነገር ግን ያ አገልጋይ ከዚያ ወጥቶ
ሲሄድ ሳለ መቶ ብር ያበደረውን የሥራ ጓደኛ
ውን አገኘና አንገቱን አንቆ ይዞ ‘ያበደርከህን
ገንዘብ ክፈለኝ!’ አለው ። 29 ጓደኛውም በእግሩ
ሥር ወድቆ ‘እባክህ ታገሠኝ ፤ እከፍልሃለሁ!’
ሲል ለመነው ። 30 አበዳሪው ግን እምቢ
አለው ። እንዲያውም ይዞት ሄደና ዕዳውን እስ
ኪከፍል ድረስ በወህኒ ቤት አሳሰረው ።
31 ሌሎች የሥራ ጓደኞቹ ይህን ባዩ ጊዜ እጅግ
አዘኑ ፤ ሄደውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ነገ
ሩት ። 32 ጌትዮውም ያን አገልጋይ አስጠራቸ
እንዲህ አለው ፡ ‘አንተ ክፉ አገልጋይ ፤ ስለ
ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ ፤ 33 ታዲያ
እኔ ዕዳህን እንደተውሁልህ አንተስ ባልንጀራህ
ለሆነው አገልጋይ ዕዳውን ልትተውለት አይገባ
ህም ነበርን?’ 34 ስለዚህ ጌታው ተቆጥቶ ዕዳ
ውን ሁሉ እስኪከፍል ድረስ ለሚያሠቃዩት
ሰዎች አሳልፎ ሰጠው ።
35 “እንግዲህ እናንተም እያንዳንዳችሁ ወን
ድማችሁን ከልብ ይቅር ባትሉ በሰማይ ያለው
አባቴም እንዲሁ ያደርግባችኋል ።”

ምዕራፍ 19

ኢየሱስ ስለ ጋብቻ አስተማረ
(ማር. 10፡1-12)

1 ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ካበቃ በኋላ ከገሊላ
ተነሥቶ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ወደምትገኝ
ወደ ይሁዳ ክፍለ ሀገር ሄደ ። 2 ብዙ ሰዎችም
ተከተሉት ፤ እነርሱንም እዚያ ፈወሳቸው ።
3 በዚያን ጊዜ ፈሪሳውያን ወደ እርሱ ቀረ
ቡና ሊፈትኑት ፈልገው “ሰው ሚስቱን በማን
ኛውም ምክንያት እንዲፈታ ተፈቅዶለታልን?”
ሲሉ ጠየቁት ።
4 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እግዚአብሔር በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድ
ርጎ እንደፈጠራቸው ከቶ አላነበባችሁምን?

12* 18፡11 አንዳንድ ቅጂዎች ቁ. 11 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በሉቃ. 19፡10 ያለውን ይመስላል ።
18፡11 ፡- ሉቃ. 19፡10 ። 18፡15 ፡- ሉቃ. 17፡3 ። 18፡16 ፡- ዘዳ. 19፡15 ። 18፡18 ፡- ማቴ. 16፡19 ፤ ዮሐ. 20፡23 ።
18፡21-22 ፡- ሉቃ. 17፡3-4 ። 18፡22 ፡- ዘፍ. 4፡24 ። 19፡4 ፡- ዘፍ. 1፡27 ፤ 5፡2 ።

5 ደግሞም ‘በዚህ ምክንያት ሰው አባትና እና
ቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም
አንድ አካል ይሆናሉ’ ያለውን አላነበባችሁ
ምን? 6 ስለዚህ እነርሱ ከአንግዲህ ወዲህ አንድ
አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይሆኑም ። እንግ
ዲህ እግዚአብሔር አጣምሮ አንድ ያደረገውን፥
ሰው አይለየው ።”
7 ፈሪሳውያንም “ታዲያ ሙሴ ስለምን ‘ባል
የፍቺዋን የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ይፋታት’
ይላል?” አሉት ።
8 እርሱም እንዲህ አላቸው ፥ “ሙሴማ ሚስ
ቶቻችሁን እንድትፈቱ የፈቀደላችሁ ልባችሁ
ደንድኖ አስቸጋሪዎች በመሆናችሁ ምክንያት
ነው ፤ ከጥንት ጀምሮ ግን እንዲህ አልነበረም ።
9 “እኔ ግን ፥ ‘አንድ ሰው በዝሙት ምክን
ያት ካልሆነ በቀር ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ቤት
ቢያገባ አመንዝራ ነው ፤ [ባልዋ የፈታትንም
ቤት የሚያገባ ሰው እንዲሁ አመንዝራ ነው]
እላችኋለሁ ።”
10 ደቀ መዛሙርቱም “የባልና የሚስት
ሁኔታ እንዲህ ከሆነ አለማግባት የተሻለ ነው”
አሉት ።
11 ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው ፥ “ልዩ
ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ይህ ነገር ሰሁ
ሉም አይሆንም ። 12 ምክንያቱም ስልቦች
ሆነው የተወለዱ አሉ ፤ ሰው የሰለባቸውም
አሉ ፤ ለመንግሥተ ሰማይ ሲሉ ራሳቸውን እንደ
ስልብ ያደረጉ አሉ ፤ ስለዚህ ይህን ሊቀበል
የሚችል ይቀበለው ።”

ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ
(ማር. 10፡13-16፡ ሉቃ. 18፡15-17)

13 በዚያን ጊዜ እጁን በላያቸው ላይ ጭኖ
እንዲጸልይላቸው ሰዎች ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ
አመጡ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ሰዎቹን ገሠጹአ
ቸው ። 14 ኢየሱስም “መንግሥተ ሰማይ እንደነ
ዚህ ላሉት ስለሆነች ሕፃናትን ተዉአቸው ፥
ወደ እኔ ይምጡ ፥ አትከልክሉአቸው” አለ ።
15 እጁንም ጫነባቸውና ከዚያ ስፍራ አልፎ
ሄደ ።

የሀብታሙ ወጣት ጥያቄ
(ማር. 10፡17-31፡ ሉቃ. 18፡18-30)

16 አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ
መጥቶ “መምህር ሆይ! የዘላለምን ሕይወት
ለማግኘት ምን መልካም ነገር ማድረግ ይገባ
ኛል?” ሲል ጠየቀው ።
17 ኢየሱስም “ስለ መልካም ነገር ለምን
ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ አምላክ
ብቻ ነው ፤ ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ
ግን ትእዛዞችን ፈጽም” አለው ።
18 ሰውየውም “የትኞቹን ትእዛዞች?” ብ
ለው ።
ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “አትግ
ደል ፥ አታመንዝር ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት አትመ
ስክር ፥ 19 አባትና እናትህን አክብር ፥ ሰውን
እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚሉት ትእዛዞች
ናቸው” አለው ። 20 ወጣቱም “እነዚህንማ ትእ
ዛዞች ፈጽሜአለሁ ፤ ሌላስ የሚጐድለኝ ምንድን
ነው?” አለ ።
21 ኢየሱስም “ፍጹም መሆን ብትፈልግ
ሂድና ያለህን ሽጠህ ገንዘቡን ለድኻ ስጥ ፤ በሰ
ማይ ሀብት ታገኛለህ ፤ መጥተህም ተከተለኝ”
አለው ።
22 ወጣቱ ግን ብዙ ሀብት ስለነበረው ይህን
በሰማ ጊዜ እየተከዘ ሄደ ።
23 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እን
ዲህ አላቸው ፥ “በእውነት እላችኋለሁ ፤ ለሀብ
ታም ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት
በጣም አስቸጋሪ ነው ። 24 ደግሞም እላችኋ
ለሁ ፥ ሀብታም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግ
ሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያ
ልፍ ይቀላል ።”
25 ደቀ መዛሙርቱ ይህን በሰሙ ጊዜ በጣም
ተገረሙና “ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?”
አሉ ።
26 ኢየሱስ ወደ እነርሱ ተመልክቶ “ይህ
ነገር ለሰው የማይቻል ነው ፤ ለእግዚአብሔር
ግን ሁሉ ይቻለዋል” አለ ።
27 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ “እነሆ እኛ ሁሉን
ትተን ተከትለንሃል ፤ ታዲያ የምናገኘው ምን
ይሆን?” አለ ።
28 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “በእውነት
እላችኋለሁ ፤ የሰው ልጅ በክብር ዙፋን ላይ
በሚቀመጥበት በአዲሱ ዘመን የእኔ ተከታዮች
የሆናችሁ እናንተም በዐሥራ ሁለት ዙፋን ላይ
ትቀመጣላችሁ ፤ በዐሥራ ሁለቱም የእስራኤል
ነገዶች ላይ ተሾማችሁ ትፈርዳላችሁ ። 29 ስለ
እኔ ብሎ ቤቶችን ፥ ወይም ወንድሞችን ፥
ወይም እኅቶችን ፥ ወይም አባትን ወይም እና
ትን ፥ ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ
ሁሉ ፥ መቶ እጥፍ ይቀበላል ፤ የዘላለም ሕይወ
ትንም ያገኛል ። 30 ነገር ግን አሁን ፊተኞች
የሆኑ ብዙዎች ኋለኞች ይሆናሉ ፤ ኋለኞች የሆ
ኑትም ፊተኞች ይሆናሉ ።”

19፡5 ፡- ዘፍ. 2፡24 ። 19፡7 ፡- ዘዳ. 24፡1-4 ፤ ማቴ. 5፡31 ። 19፡9 ፡- ማቴ. 5፡32 ፤ 1ቆሮ. 7፡10-11 ።
19፡18 ፡- ዘጽ. 20፡13-16 ፤ ዘዳ. 5፡17-20 ። 19፡19 ፡- ዘጽ. 20፡12 ፤ ዘዳ. 5፡16 ፤ ዘሌ. 19፡18 ። 19፡28 ፡- ማቴ. 25፡31 ፤ ሉቃ. 22፡30 ። 19፡30 ፡- ማቴ. 20፡16 ፤ ሉቃ. 13፡30 ።

ምዕራፍ 20

የወይን አትክልት ሠራተኞች ምሳሌ

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “መንግ
ሥተ ሰማይ በወይኑ አትክልት የሚሠሩ ሠራተ
ኞችን ለመቅጠር ጠዋት በማለዳ የወጣውን የአ
ትክልት ባለቤት ትመስላለች ። 2 እርሱ ለእያንዳ
ንዱ በቀን አንድ ብር ሊከፍል ተዋውሎ ሠራተ
ኞችን ወደ ወይኑ አትክልት ላካቸው ። 3 በሦ
ስት ሰዓት ገደማም ወጥቶ ሥራ ፈትተው በአደ
ባባይ የቆሙትን ሌሎች ሰዎች አየና ፥ 4 “እናን
ተም ወደ ወይኑ አትክልት ሂዳችሁ ሥሩ ፤
የሚገባችሁንም ዋጋ እከፍላችኋለሁ” አላቸው ።
5 እነርሱም ወደ ወይኑ አትክልት ሄዱ ፤ ደግ
ሞም የአትክልቱ ባለቤት በስድስት ሰዓትና በዘ
ጠኝ ሰዓት ገደማ ወጥቶ እንዲሁ አደረገ ። 6 በዐ
ሥራ አንድ ሰዓትም ወጥቶ ሌሎች ሰዎች
ቆመው አገኘና ‘እናንተስ ቀኑን ሙሉ ሥራ
ፈትታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው?’
ሲል ጠየቃቸው ። 7 እነርሱም ‘የሚቀጥረን ሰው
አጥተን ነው’ አሉት ፤ እርሱም ‘እንግዲያውስ ፥
እናንተም ወደ ወይኑ አትክልት ሂዱና ሥሩ’
እላቸው ።
8 “በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ጌታ አዛ
ዥን ‘ሠራተኞቹን ጥራና በመጨረሻ ከተቀጠ
ሩት ጀምረህ በፊት እስከ ተቀጠሩት ድረስ
የሥራ ዋጋቸውን ክፈላቸው’ አለው ። 9 ስለዚህ
በዐሥራ አንድ ሰዓት የተቀጠሩት ቀርበው እያን
ዳንዳቸው አንድ ብር ተቀበሉ ። 10 በፊት የተቀ
ጠሩት በቀረቡ ጊዜ ይበልጥ የሚቀበሉ መስሎአ
ቸው ነበር ፤ ነገር ግን እነርሱም እያንዳንዳቸው
አንድ ብር ተቀበሉ ። 11 ገንዘቡን ተቀበሉና በወ
ይኑ አትክልት ባለቤት ላይ እንዲህ እያሉ አጉ
ረመረሙ ፤ 12 “እነዚህ በመጨረሻ መጥተው
የሠሩት ለአንድ ሰዓት ብቻ ነው ፤ ነገር ግን
ቀኑን ሙሉ በፀሐይ መቃት እየተቃጠልን
በሥራ ስንደክም ከዋልነው ከእኛ ጋር እኩል
አደረግሃቸው ።” 13 የወይኑ አትክልት ባለቤትም
ከሠራተኞቹ ለአንዱ እንዲህ ሲል መለሰለት ፥
‘ወዳጄ ሆይ! ምንም አልበደልኩህም ፤ የተዋዋ
ልነው በቀን አንድ ብር ልከፍልህ አይደለምን?
14 ስለዚህ ድርሻህን ይዘህ ሂድ ፤ ለአንተ የሰጠሁ
ትን ያህል ለዚህ ለኋለኛውም ልሰጠው ፈቀ
ድሁ ። 15 በገዛ ገንዘቤ የፈለግሁትን ማድረግ
መብት የለኝምን? ወይስ እኔ ለጋሥ ስለሆንኩ
ትመቀኛለህን?’”
16 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ “እንዲሁም ፊተኞች
የሆኑ ኋለኞች ይሆናሉ ፤ ኋለኞችም የሆኑ ፊተ
ኞች ይሆናሉ” አለ ።

ኢየሱስ ስለ ሞቱ ሦስተኛ ጊዜ ተናገረ
(ማር. 10፡32-34፡ ሉቃ. 18፡31-34)

17 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
ይሄድ ነበር ፤ በመንገድም ሳሉ ዐሥራ ሁለቱን
ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ
እንዲህ አላቸው ፥ 18 “እነሆ አሁን ወደ ኢየሩሳ
ሌም መሄዳችን ነው ፤ በዚያም የሰው ልጅ ለካ
ህናት አለቆችና ለሙሴ ሕግ መምህራን ተላልፎ
ይሰጣል ፤ እነርሱም የሞት ፍርድ ይፈርዱበ
ታል ። 19 ለአረማውያንም አሳልፈው ይሰጡ
ታል ፤ አረማውያንም ያላግጡበታል ፤ ይገርፉ
ታል ፤ ይሰቅሉታልም ፤ ግን በሦስተኛው ቀን
ከሞት ይነሣል ።”

የዘብዴዎስ ልጆች እናት ልመና
(ማር. 10፡35-45)

20 ከዚህ በኋላ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከል
ጆችዋ ጋር ወደ ኢየሱስ ቀረበችና በፊቱ እጅ
ነሣች ፤ አንድ ነገር እንዲያደርግላትም ለመነ
ችው ። 21 ኢየሱስም “ምን ትፈልጊያለሽ?”
አላት ። እርስዋም “በመንግሥትህ እነዚህ
ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ ፥ አንዱ በግራህ
እንዲቀመጡ አድርግልኝ!” አለችው ።
22 ኢየሱስ ግን “የምትለምኑትን አታው
ቁም ፤ እኔ በቅርብ ጊዜ የምጠጣውን (የመከራ)
ጽዋ መጠጣት ትችላላችሁን? (እኔስ የምጠመቀ
ውን ጥምቀት መጠመቅ ትችላላችሁን?”) አላ
ችው ። እነርሱም “አዎ እንችላለን” አሉ ።
23 ኢየሱስም “በእርግጥ እኔ የምጠጣውን
የመከራ ጽዋ ትጠጣላችሁ ፤ ነገር ግን በቀኜና
በግራዬ እንድትቀመጡ የማደርገው እኔ አይደለ
ሁም ፤ ይህ ቦታ የሚሰጠው አባቴ ላዘጋጀላቸው
ሰዎች ነው ።”
24 የቀሩት ዐሥር ደቀ መዛሙርት ይህን
ልመና በሰሙ ጊዜ በሁለቱ ወንድማማቾች ላይ
ተቆጡ ። 25 ኢየሱስ ግን ሁሉንም ወደ እርሱ
ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ “የአረማውያን አለ
ቆች የሕዝቦቻቸው ገዥዎች ናቸው ፤ መሪዎቻ
ቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣን እንዳላቸው
ታውቃላችሁ ። 26 በእናንተስ መካከል እንዲህ
መሆን አይገባም ። ነገር ግን ከእናንተ አለቃ
መሆን የሚፈልግ ፥ ከእናንተ በታች ሆኖ ያገል
ግል ። 27 እንዲሁም ከእናንተ የበላይ መሆን
የሚፈልግ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ። 28 የሰው
ልጅም ለማገልገልና ብዙዎችን ለማዳን ሕይወ
ቱን አሳልፎ ለመስጠት መጣ እንጂ እንዲያገለግ
ሉት አልመጣም ።”

20፡8 ፡- ዘሌ. 19፡13 ፤ ዘዳ. 24፡15 ። 20፡16 ፡- ማቴ. 19፡30 ፤ ማር. 10፡31 ፤ ሉቃ. 13፡30 ።
20፡25-26 ፡- ሉቃ. 22፡25-26 ። 20፡26-27 ፡- ማቴ. 23፡11 ፤ ማር. 9፡35 ፤ ሉቃ. 22፡26 ።

ኢየሱስ ሁለት ዐይነ ስውሮችን ፈወሰ
(ማር. 10፡46-52፤ ሉቃ. 18፡35-43)

29 ከዚህ በኋላ ከኢያሪኮ ወጥተው ሲሄዱ
ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ተከተሉት ። 30 እነሆ በመ
ንገድ ዳር የተቀመጡት ሁለት ዐይነ ስውሮች
በዚህ በኩል የሚያልፈው ኢየሱስ መሆኑን
በሰሙ ጊዜ "የዳዊት ልጅ የሆንህ ጌታ ሆይ!
እባክህ ማረን" እያሉ ጮኹ ።
31 ሰዎቹም "ዝም በሉ!" ብለው ገሠጹአ
ቸው ፤ እነርሱ ግን "የዳዊት ልጅ የሆንህ ጌታ
ሆይ! እባክህ ማረን" እያሉ አብዝተው ጮኹ ።
32 ኢየሱስም ቆሞ ጠራቸውና "ምን እንዳደ
ርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?" አላቸው ።
33 እነርሱም "ጌታ ሆይ! ዐይኖቻችን እንዲ
ከፈቱ እንፈልጋለን" አሉት ።
34 ኢየሱስም ራራላቸውና ዐይኖቻቸውን
ዳሰሰ ፤ ወዲያውኑ ዐይኖቻቸው ተከፈቱ ፤ ኢየሱ
ስንም ተከተሉት ።

ምዕራፍ 21

ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ
(ማር. 11፡1-11፤ ሉቃ. 19፡28-40፤
ዮሐ. 12፡12-19)

1 ኢየሱስና ተከታዮቹ ወደ ኢየሩሳሌም በቀ
ረቡ ጊዜ በደብረ ዘይት ወደምትገኘው ቤተ
ፋጌ ወደምትባለው መንደር ደረሱ ። ከዚያም
በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ
ሲል ላካቸው ፥ 2 "በፊታችሁ ወዳለችው መን
ደር ቀድማችሁ ሂዱ ፤ እዚያም አንዲት የታሰ
ረች አህያ ከነውርንጫዋ ወዲያውኑ ታገኛላ
ችሁ ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ ። 3 ማንም ሰው
አንዳች ነገር ቢላችሁ 'ጌታ ስለሚፈልጋቸው
ነው' በሉት ። እርሱም አህዮቹን ወዲያውኑ
ይልካቸዋል ።"
4 ይህም የሆነው በነቢይ እንዲህ ተብሎ የተ
ነገረው እንዲፈጸም ነው ፥
5 "የጽዮን ከተማ ለምትባለው
ለኢየሩሳሌም
'እነሆ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ ፥
በአህያይቱ ላይ ተቀምጦ ፥
በውርንጫ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ
ይመጣል' በሉአት ።"
6 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ሄደው ልክ ኢየ
ሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ ። 7 አህያዋንም ከነ
ውርንጫዋ አመጡለት ፤ ልብሳቸውንም በአህ
ዮቹ ጀርባ ላይ አደረጉና ኢየሱስ ተቀመጠባ
ቸው ። 8 ከሕዝቡም ብዙዎቹ ልብሳቸውን በመ
ንገድ ላይ አነጠፉ ፤ ሌሎች ደግሞ የዛፍ ቅርን
ጫፍ እየቀጠፉ በመንገድ ላይ ይጐዘጉዙ
ነበር ። 9 እፊት እፊት ይሄዱ የነበሩትና ከኋላ
ይከተሉ የነበሩት "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ምስ
ጋና ይሁን! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ
ነው! ሆሳዕና! ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር
ይሁን!" እያሉ ይጮኹ ነበር ። 10 ኢየሱስ ወደ
ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ የከተማው ሰዎች በሙሉ
"ይህ ማን ነው?" በማለት ታወኩ ። 11 ሕዝ
ቡም "ይህ በገሊላ ከፍል ሀገር ከምትገኝ ከናዝ
ሬት ከተማ የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው" አሉ ።

ኢየሱስ በቤተ መቅደስ
(ማር. 11፡15-19፤ ሉቃ. 19፡45-48፤
ዮሐ. 2፡13-22)

12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ገባ ፤ በዚያም የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሰዎች
ሁሉ አስወጣ ። የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛዎ
ችና የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠ ።
13 እንዲህም አላቸው ፥ "'ቤቴ የጸሎት ቤት
ይባላል' ተብሎ ተጽፎአል ፤ እናንተ ግን የሌ
ቦች ዋሻ አደረጋችሁት ።"
14 ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሳለ ዐይነ ስውሮ
ችና አንካሶች ወደ እርሱ መጡና ፈወሳቸው ።
15 ነገር ግን የካህናት አለቆችና የሙሴ ሕግ
መምህራን ኢየሱስ ያደረገውን ድንቅ ነገር በማ
የታቸውና ሕፃናትም በቤተ መቅደስ "ለዳዊት
ልጅ ሆሳዕና! ምስጋና ይሁን!" እያሉ ሲጮኹ
በመስማታቸው ተቆጡ ። 16 ስለዚህ ኢየሱስን
"እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን ትሰማለህን?"
አሉት ፤ እርሱም "አዎ እሰማለሁ ፤ 'ከልጆችና
ከሚጠቡት ሕፃናት አፍ ምስጋናን ለአንተ አዘ
ጋጀህ' የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?" አላ
ቸው ፤ 17 ትቶአቸውም ከከተማ ወጥቶ ቢታንያ
ወደምትባል መንደር ሄደ ፤ በዚያም አደረ ።

ያለ ፍሬ የተገኘች የበለስ ዛፍ
(ማር. 11፡12-14፡20-24)

18 ኢየሱስ ጠዋት በማለዳ ወደ ከተማ ተመ
ልሶ ሲሄድ ራበው ፤ 19 አንዲት የበለስ ዛፍ በመ
ንገድ ዳር አየና ወደ እርስዋ ሄደ ፤ ነገር ግን
ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም ። ስለዚህ
"ከእንግዲህ ወዲህ ኩቶ ፍሬ አይገኝብሽ!"
አላት ። ዛፊቱም ወዲያውኑ ደረቀች ። 20 ደቀ
መዛሙርቱ ይህን ባዩ ጊዜ "ይህች የበለስ ዛፍ
በአንድ አፍታ እንዴት ደረቀች!" በማለት ተገ
ረሙ ። 21 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"በእውነት እላችኋለሁ ፥ እምነት ቢኖራችሁና
ባትጠራጠሩ ፥ በበለሲቱ ዛፍ ላይ እኔ እንዳደረግ
ሁት ማድረግ ብቻ ሳይሆን ፤ ይህንን ተራራ
እንኳ 'ከዚህ ተነሥተህ ወደ ባሕር ተወርወር!'
ብትሉት ይሆንላችኋል ። 22 አምናችሁ በጸሎት
የምትለምኑትን ሁሉ ታገኛላችሁ ።"

የኢየሱስ ሥልጣን ከየት እንደሆነ
(ማር. 11፡27-33፤ ሉቃ. 20፡1-8)

23 ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ያስተ
ምር ነበር ። በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆችና
የሕዝብ ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀረቡና ፥
"ይህን ሁሉ የምታደርገው በምን ሥልጣን
ነው? ይህን ሥልጣን የሰጠህስ ማን ነው?"
ሲሉ ጠየቁት ። 24 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ
ላቸው ፥ "እኔም አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ ፤
ለጥያቄዬ መልስ ከሰጣችሁኝ ፥ እኔም ይህን
ሁሉ በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋ
ለሁ ። 25 የዮሐንስ ጥምቀት ከየት መጣ? ከእግ
ዚአብሔር ነበረ ወይስ ከሰው?" እነርሱም
እርስ በርሳቸው እንዲህ ሲሉ ተመካከሩ ፥
"'ከእግዚአብሔር ነው' ብንል 'ታዲያ ለምን
አላመናችሁትም' ይለናል ፤ 26 'ከሰው ነው'
ብንል ደግሞ ፥ ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ
ስለሚያዩት ሕዝቡን እንፈራለን ።" 27 ስለዚህ
ለኢየሱስ "እናውቅም" ሲሉ መለሱለት ። እር
ሱም "እንግዲያውስ እኔም በምን ሥልጣን
ይህን ሁሉ እንደማደርግ አልነግራችሁም" አላ
ቸው ።

የሁለቱ ልጆች ምሳሌ

28 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥
"ታዲያ ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው ሁለት
ልጆች ነበሩት ፤ ከእነርሱ ወደ አንደኛው ቀርቦ
'ልጄ ሆይ! ዛሬ ወደ ወይን አትክልቴ ሄደህ
እንድትሠራ ይሁን' አለው ። 29 ልጁም 'እምቢ
አልሄድም' አለ ። ይሁን እንጂ በኋላ ተጸጸተና
ሊሠራ ሄደ ። 30 አባትየው ወደ ሁለተኛው ልጁ
ደግሞ ሄዶና እርሱንም እንዲሁ እንዲሠራ አዘ
ዘው ፤ ልጁም 'እሺ አባቴ እሄዳለሁ' አለ ።
ነገር ግን ወደ ሥራ አልሄደም ። 31 እንግዲህ
ከነዚህ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው የት
ኛው ነው?"
እነርሱም "የመጀመሪያው ነዋ!" አሉ ።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ "በእውነት
እላችኋለሁ ፤ ኃጢአተኞችና ዘማውያን ወደ
መንግሥተ ሰማይ በመግባት ይቀድሙአችኋል ።
32 ምክንያቱም አጥማቂው ዮሐንስ የጽድቅን
መንገድ ሊያሳያችሁ ቢመጣ አላመናችሁትም ፤
ኃጢአተኞችና ዘማውያን ግን አመኑት ፤ ይህን
ንም አይታችሁ እንኳ ንስሓ ገብታችሁ አላመና
ችሁትም ።"

የወይኑ አትክልት ገበሬዎች ምሳሌ
(ማር. 12፡1-12፤ ሉቃ. 20፡9-19)

33 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ "ሌላም
ምሳሌ ስሙ ፤ የወይን አትክልት የተከለ አንድ
ሰው ነበረ ፤ እርሱ በወይኑ አትክልት ዙሪያ
አጥር አጠረ ፤ የወይን መጭመቂያ የሚሆን
ጉድጓድ ቁፍሮ አበጀ ፤ ለወይኑ ጥበቃ የሚያገ
ለግል ረዥም ማንብ ሠራ ፤ ከዚህ በኋላ የአትክ
ልቱን ቦታ ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር
ሄደ ። 34 የፍሬ ወራት በደረሰ ጊዜ ድርሻውን
እንዲቀበሉለት አገልጋዮቹን ወደ ገበሬዎቹ
ላከ ። 35 ገበሬዎቹ ግን አገልጋዮቹን ይዘው አን
ዱን ደበደቡት ፤ አንዱን ገደሉት ፤ አንዱንም
ደግሞ በድንጋይ ወገሩት ። 36 የወይኑ አትክልት
ጌታ እንደገና ቀጥሮራቸው ከፊተኞቹ የሚበልጥ
ሌሎችን አገልጋዮች ደግሞ ላከ ። ገበሬዎቹ በእ
ነርሱም ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸሙባቸው ።
37 በመጨረሻም የወይኑ አትክልት ጌታ 'ልጄ
ንስ ያክብሩታል!' በማለት ልጁን ወደ ገበሬ
ዎቹ ላከ ። 38 ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ
'ይህማ ወራሹ ነው ፤ ኑ እንግደለውና ርስቱን
እንውሰድ' ተባባሉ ። 39 ልጁንም ይዘው ከአትክ
ልቱ ውጪ ወሰዱና ገደሉት ።
40 "ታዲያ የወይኑ አትክልት ጌታ በመጣ
ጊዜ በእነዚህ ገበሬዎች ላይ ምን የሚያደርግ
ይመስላችኋል?" 41 እነርሱም "እነዚህን ክፉ
ሰዎች ያለ ርኅራኄ ይገድላቸዋል ፤ የወይኑንም
አትክልት ፥ ፍሬውን በየጊዜው ለሚሰጡት ለሌ
ሎች ገበሬዎች ያከራያል" አሉት ።
42 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥
"'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ
እርሱ ዋና የማእዘን ድንጋይ ሆነ ፤
ይህም የእግዚአብሔር ሥራ ነው ፤
ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው'
ተብሎ የተጻፈውን ከቶ አላነበባችሁምን?
43 "ስለዚህ እንዲህ እላችኋለሁ ፥ የእግዚአብ
ሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬ ለሚያ
ፈራ ሕዝብ ትሰጣለች ። [44 በዚህ ድንጋይ ላይ
የሚወድቅ ይሰበራል ፤ ድንጋዩ በላዩ ላይ የሚ
ወድቅበት ሰው ግን ይጨፈለቃል ።"]13*
45 የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን እነዚህን
ምሳሌዎች በሰሙ ጊዜ ኢየሱስ የተናገረው ስለ
እነርሱ መሆኑን ተገነዘቡ ። 46 ስለዚህ ሊይዙት
ፈልገው ነበር ፤ ነገር ግን ሕዝቡ እንደ ነቢይ
ያየው ስለነበር ፈሩ ።

21፡5 ፡- ዘካ. 9፡9 ። 21፡9 ፡- መዝ. 118፡25-26 ። 21፡13 ፡- ኢሳ. 56፡7 ፤ ኤር. 7፡11 ። 21፡16 ፡- መዝ. 8፡2 ።
21፡21 ፡- ማቴ. 17፡20 ፤ 1ቆሮ. 13፡2 ።

13* 21፡44 አንዳንድ ቅጂዎች ቁ. 44 ይጨምራሉ ፥ ቃሉም በሉቃ. 20፡18 ያለውን ይመስላል ።
21፡32 ፡- ሉቃ. 3፡12 ፤ 7፡29-30 ። 21፡33 ፡- ኢሳ. 5፡1-2 ። 21፡42 ፡- መዝ. 118፡22-23 ።

ምዕራፍ 22

የሠርጉ ግብዣ ምሳሌ
(ሉቃ. 14፡15-24)

[1]እንደገናም ኢየሱስ በምሳሌ እንዲህ እያለ
ይነግራቸው ነበር ፥ [2]“መንግሥተ ሰማይ ለልጁ
የሠርግ ግብዣ ያደረገውን ንጉሥ ትመስላለች ።
[3]ንጉሡ የተጠሩትን ሰዎች ወደ ሠርጉ እንዲ
መጡ ለማሳሰብ አገልጋዮቹን ወደ እነርሱ ላከ ፥
ሰዎቹ ግን ወደ ግብዣው ሊመጡ አልፈለጉም ።
[4]“ንጉሡ ሌሎች አገልጋዮችን እንደገና እን
ዲህ ሲል ላከ ፥ ‘ወደ ተጠሩት ሰዎች ሂዱና ፦
እነሆ የሠርግ ድግሴን አዘጋጅቻለሁ ፥ ሰንጋዎ
ቼና የሰቡት ፍሪዳዎቼ ታርደዋል ፤ ሁሉም ነገር
ተዘጋጅቶአል ፤ ስለዚህ ወደ ሠርጉ ግብዣ ኑ’
ብላችሁ ንገሩዋቸው ። [5]እነርሱ ግን ነገሩን ችላ
ብለው አንዱ ወደ እርሻው ፥ ሌላውም ወደ
ንግዱ ሄደ ፤ [6]የቀሩትም ደግሞ አገልጋዮቹን
ይዘው በማዋረድ ደበደቡና ገደሉአቸው ፤
[7]በዚህ ጊዜ ንጉሡ ተቈጣና ወታደሮቹን ልኮ
እነዚያን ገዳዮች አስገደለ ፤ ከተማቸውንም በእ
ሳት እንዲያቃጥሉ አደረገ ፤ [8]ከዚህ በኋላ አገልጋ
ዮቹን እንዲህ አላቸው ፥ ‘እነሆ የሠርጉ ድግስ
ተዘጋጅቶአል ፤ የተጠሩት ግን ለግብዣው የተ
ገቡ አልሆኑም ። [9]ስለዚህ በየአደባባዩ ሂዱና ያገ
ኛችሁትን ሰው ሁሉ ወደ ሠርጉ ግብዣ ጥሩ ።’
[10]አገልጋዮቹም በየመንገዱ ሄደው ያገኙትን
ሰው ሁሉ ክፉዎችንም ደጎችንም ሰበሰቡ ፤ የሠ
ርጉንም አዳራሽ ተጋባዥዎች ሞሉት ።
[11]“ነገር ግን ንጉሡ ተጋባዥዎቹን ለማየት
ወደ አዳራሽ በገባ ጊዜ የሠርግ ልብስ ያልለበሰ
አንድ ሰው በዚያ አየ ። [12]እንዲህም አለው ፥
‘ወዳጄ ሆይ! የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት
ወደዚህ ገባህ?’ ሰውየው ግን ዝም አለ ። [13]ንጉ
ሡም አገልጋዮቹን ‘እጅና እግሩን እሰሩና አው
ጥታችሁ በውጪ ወዳለው ጨለማ ጣሉት ፤ በዚ
ያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል’ አለ ።”
[14]ቀጥሎም ኢየሱስ “ስለዚህ የተጠሩ ብዙዎች
ናቸው ፤ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው” አለ ።

ግብር ስለ መክፈል የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 12፡13-17፤ ሉቃ. 20፡20-26)

[15]ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ሄዱና እንዴት
አድርገው ኢየሱስን በንግግሩ እንደሚያጠም
ዱት ተማከሩ ፤ [16]የእነርሱንም ደቀ መዛሙርት
ከሄሮድስ ሰዎች ጋር ወደ ኢየሱስ ልከው እን
ዲህ ብለው እንዲጠይቁት አደረጉ ፥ “መምህር
ሆይ! አንተ እውነተኛ መሆንህና የእግዚአብ
ሔርን መንገድ በእውነት የምታስተምር መሆን
ህን እናውቃለን ፤ ሰውንም በመፍራት የምታደ
ርገው ነገር የለም ፤ ምክንያቱም አንተ ለሰው
አታዳላም ። [17]በል እስቲ ንገረን ምን ይመስል
ሃል? ለቄሳር ግብር መክፈል ተገቢ ነውን
ወይስ ተገቢ አይደለም?” [18]ኢየሱስ ግን ክፋታ
ቸውን ዐውቆ “እናንተ ግብዞች! ስለምን ትፈት
ኑኛላችሁ? [19]ለግብር የሚከፈለውን ገንዘብ
እስቲ አሳዩኝ” አላቸው ። እነርሱም አንድ ብር
አመጡለት ። [20]እርሱም “በዚህ ገንዘብ ላይ
የተቀረጸው መልክና የተጻፈው ስም የማን
ነው!” ሲል ጠየቃቸው ፤ [21]እነርሱም “የቄሳር
ነው” አሉት ፤ እርሱም “እንግዲያውስ የቄሳርን
ለቄሳር ፥ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር
ስጡ” አላቸው ። [22]እነርሱም በዚህ አነጋገሩ
ተደንቀው ትተውት ሄዱ ።

ስለ ሙታን መነሣት
(ማር. 12፡18-27፤ ሉቃ. 20፡27-40)

[23]በዚያኑ ቀን “የሙታን ትንሣኤ የለም”
የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ ኢየሱስ መጥተው እን
ዲህ ሲሉ ጠየቁት ፥ [24]“መምህር ሆይ! ሙሴ
‘አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ከሚስቱ በሞት
ቢለይ ወንድሙ የሚቹን ሚስት አግብቶ ለሚቹ
ዘር ይተካለት’ ብሎአል ። [25]ሰባት ወንድማማ
ቾች በእኛ ዘንድ ነበሩ ፤ የሁሉም ታላቅ ሚስት
አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ፤ ስለዚህ ታናሽ
ወንድሙ የሚቹን ሚስት አገባ ። [26]እንዲሁ
ሁለተኛውም ፥ ሦስተኛውም እስከ ሰባተኛው
ድረስ በየተራ አግብተዋት ሞቱ ። [27]ከሁሉም
በኋላ ሴትዮዋ ሞተች ። [28]ታዲያ ሰባቱም ስለእ
ገሁኑት ሙታን በሚነሡበት ጊዜ ለየትኛው
ሚስት ትሆናለች?”
[29]ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እናንተ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔ
ርን ኀይል ባለማወቃችሁ ትሳሳታላችሁ ።
[30]ምክንያቱም ሰዎች ከሞት በተነሡ ጊዜ በሰ
ማይ እንዳሉት መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገ
ቡም ፥ አይጋቡም ። [31]ደግሞ ስለሙታን መነ
ሣት እግዚአብሔር ለእናንተ የነገራችሁን አላነ
በባችሁምን? [32]እርሱም ያለው እንዲህ ነው ፥
‘እኔ የአብርሃም አምላክ ፥ የይስሐቅ አምላክ ፥
የያዕቆብ አምላክ ነኝ ፤’ ስለዚህ እግዚአብሔር
የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ
አይደለም ።” [33]ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ
በትምህርቱ ተደነቁ ።

ከሁሉ የሚበልጥ ትእዛዝ
(ማር. 12፡28-34፤ ሉቃ. 10፡25-28)

[34]ኢየሱስ ሰዱቃውያንን መልስ አሳጥቶ
ዝም እንዳሰኛቸው ፈሪሳውያን በሰሙ ጊዜ በአ
ንድነት ተሰበሰቡ ። [35]ከእነርሱም አንድ የሙሴ
ሕግ መምህር ፥ ኢየሱስን ሊፈትነው ፈልጎ እን
ዲህ ሲል ጠየቀው ፤ [36]“መምህር ሆይ! ከሁሉ
የሚበልጥ ትእዛዝ የትኛው ነው?” [37]ኢየሱ
ስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥ “እግዚአብሔር
አምላክህን በፍጹም ልብህ ፥ በፍጹም ነፍስህ ፥
በፍጹም አሳብህ ውደድ ፤ [38]ከሁሉም የሚበል
ጡውና የመጀመሪያው ትእዛዝ ይህ ነው ።
[39]ይህንንም የሚመስለው ሁለተኛው ትእዛዝ
ደግሞ ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ ፣
የሚለው ነው ። [40]የሙሴ ሕግና የነቢያት ትም
ህርት ሁሉ የተመሠረቱት በእነዚህ በሁለቱ
ትእዛዞች ላይ ነው ።”

ስለ መሲሕ የቀረበ ጥያቄ
(ማር. 12፡35-37፤ ሉቃ. 20፡41-44)

[41]ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ እን
ዲህ ሲል ጠየቃቸው ፥ [42]“ስለ መሲሕ ምን
ትላላችሁ? የማንስ ልጅ ይመስላችኋል?” እነር
ሱም “የዳዊት ልጅ ነው” ሲሉ መለሱለት ።
[43]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “ታዲያ ዳዊት
በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንዲህ ሲል ጌታ
ብሎ እንዴት ይጠራዋል?
[44]‘እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለመሲሑ)
ጠላቶችህን በሥልጣንህ ሥር
እስከ ደርግልህ ድረስ
በቀኜ ተቀመጥ! አለው ።’
[45]እንግዲህ ዳዊት ራሱ ‘ጌታ’ ብሎ ከጠራው ፥
ታዲያ መሲሕ እንዴት ልጁ ሊሆን ይችላል?”
[46]አንድ ቃል እንኳ ሊመልስለት የቻለ ማንም
ሰው አልነበረም ፤ ከዚያን ቀን ጀምሮም ጥያቄ
ሊያቀርብለት የደፈረ ማንም አልነበረም ።

ምዕራፍ 23

ስለ ሙሴ ሕግ መምህራንና ስለ ፈሪሳውያን ክፋት
(ማር. 12፡38-39፤ ሉቃ. 11፡43-46፤ 20፡45-46)

[1]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛ
ሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ ፤ [2]“የሙሴ ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን ፥ ለማስተማር በሙሴ
ወንበር ተቀምጠዋል ። [3]ስለዚህ እነርሱ የሚሉ
አችሁን ሁሉ አድርጉ ፤ ጠብቁም ፤ እነርሱ
የሚያደርጉትን ግን አታድርጉ ፤ ምክንያቱም
እነርሱ የሚናገሩትን በሥራ ላይ አያውሉትም ፤
[4]ከባድና አስቸጋሪ ሸክም አስረው ለሰው ያሸክ
ማሉ ፤ ራሳቸው ግን በጣታቸው እንኳ ሊነኩት
አይፈልጉም ። [5]ሥራቸውን ሁሉ የሚያደርጉት
ሰው እንዲያይላቸው ብለው ነው ፤ አሸንክታባቸ
ውን ያሰፋሉ ፤ የልብሳቸውን ዘርፍ ያስረዝ
ማሉ ፤ [6]በግብዣ ላይ የከበሬታ ቦታን ፥ በምኩ
ራብም የመጀመሪያ ስፍራን መያዝ ይወዳሉ ።
[7]በየአደባባዩም ሰው ሁሉ እጅ እንዲነሣቸውና
‘መምህር ሆይ!’ ብሎ እንዲጠራቸው ይፈል
ጋሉ ፤ [8]እናንተ ግን መምህራችሁ አንድ ብቻ
ስለሆነና ሁላችሁም ወንድማማቾች ስለሆናችሁ
‘መምህር’ ተብላችሁ አትጠሩ ። [9]ደግሞም በሰ
ማይ ያለው አባታችሁ አንድ ብቻ ስለሆነ በም
ድር ላይ ማንንም ‘አባት’ ብላችሁ አትጥሩ ።
[10]ሊቃችሁ መሲሑ ብቻ ስለሆነ ‘ሊቃውንት’
ተብላችሁ አትጠሩ ። [11]ከእናንተ መካከል የበ
ላይ ሹም የሆነው የእናንተ አገልጋይ ይሁን ።
[12]ራሱን ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል ፤ ራሱን
ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል ።”

የሙሴ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ተወቀሱ
(ማር. 12፡40፤ ሉቃ. 11፡39-42፤44፤52፤ 20፡47)

[13]“ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገባ
በሩን የምትዘጉ እናንተ ግብዞች ፤ የሙሴ ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን! ወዮላችሁ! እናንተ
ራሳችሁ አትገቡበትም ፤ መግባት የሚፈልጉት
ንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ ።
[14“ለታይታ በምታቀርቡት ረዥም ጸሎት
እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት የምትበዘ
ብዙ ፥ እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ስለዚህ እናንተ
የባሰ ፍርድ ይደርስባችኋል ።][14*]
[15“እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! አንድን ሰው ወደ
ሃይማኖታችሁ ለማስገባት በባሕርና በየብስ ትዞ
ራላችሁ ፤ ባስገባችሁትም ጊዜ ከእናንተ በሁ
ለት እጥፍ ይብስ ለገሃነም የተዘጋጀ ታደርጉታ
ላችሁ ።
[16“እናንተ የታወራችሁ መሪዎች ወዮላ
ችሁ! ‘ሰው በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም አይ
ደለም’ ትላላችሁ ፤ ‘በቤተ መቅደሱ ወርቅ
ቢምል ግን በመሐላው ይያዛል’ ትላላችሁ ፤
[17]እናንተ ሞኞችና ዕውሮች! ከወርቁና ወርቁን
ከሚቀድሰው ቤተ መቅደስ የቱ ይበልጣል?
[18]እንዲሁም ‘ሰው በመሠዊያው ቢምል ምንም
አይደለም’ ትላላችሁ ፤ ‘በመሠዊያው ላይ
ባለው መባ ቢምል ግን በመሐላው ይያዛል’
ትላላችሁ ። [19]እናንተ ዕውሮች! ከመባውና
መባውን ከሚቀድሰው መሠዊያ የቱ ይበል
ጣል? [20]ስለዚህ በመሠዊያው የሚምል ፥ በመ
ሠዊያውና በመሠዊያው ላይ ባለው ነገር ሁሉ
ይምላል ። [21]በቤተ መቅደስም የሚምል ፥

22፡13 ፡- ማቴ. 8፡12 ፡ 25፡30 ፡ ሉቃ. 13፡28 ። 22፡23 ፡- ሐ.ሥ. 23፡8 ። 22፡24 ፡- ዘፍ. 25፡5 ። 22፡32 ፡- ዘፍ. 3፡6 ። 22፡35-40 ፡- ሉቃ. 10፡25-28 ።

[14*] 23፡14 አንዳንድ ቅጂዎች ቁ. 14 ይጨምራሉ ፡ ቃሉም በማር. 12፡40 ያለውን ይመስላል ።

22፡37 ፡- ዘፍ. 6፡5 ። 22፡39 ፡- ዘሌ. 19፡18 ። 22፡44 ፡- መዝ. 110፡1 ። 23፡5 ፡- ማቴ. 6፡1 ፡ ዘኁ. 15፡38 ፡ ዘፍ. 6፡8 ። 23፡11 ፡- ማቴ. 20፡26-27 ፡ ማር. 9፡35 ፡ 10፡43-44 ፡ ሉቃ. 22፡26 ። 23፡12 ፡- ሉቃ. 14፡11 ፡ 18፡14 ።

በቤተ መቅደሱና በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሚኖ
ረው ይምላል ። 22 በሰማይ የሚምልም በእግዚአ
ብሔር ዙፋንና በዙፋኑ ላይ በሚቀመጠው
ይምላል ።

23 “እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ከአዝሙድ ፡ ከእንስ
ላል ፡ ከከሙን ዐሥራት ትሰጣላችሁ ፤ ነገር ግን
በሕግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ነገሮች ትተዋላ
ችሁ ፤ እነርሱም ፍርድ ፡ ምሕረትና ታማኝነት
ናቸው ፤ ያንን ሳትተዉ ይህንንም ማድረግ ይገባ
ችሁ ነበር ። 24 እናንተ የታወራችሁ መሪዎች ፡
ከምትጠጡት ሁሉ እንደ ትንኝ ትንሽ የሆነች
ውን ነገር አውጥታችሁ ትጥላላችሁ ፤ እንደ
ግመል ትልቅ የሆነውን ግን ትውጣላችሁ ።

25 “እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! ብርጭቆውንና ሳሕ
ኑን ከውጪ በኩል ታጠራላችሁ ፤ ውስጡ ግን
ቅሚያና ስስት የሞላበት ነው ፤ 26 አንተ ዕውር
ፈሪሳዊ! አስቀድመህ ብርጭቆውንና ሳሕኑን
ከውስጥ በኩል አጥራ ፤ በዚያን ጊዜ በውጪም
በኩል ንጹሕ ይሆናል ።

27 “እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! በውስጣቸው በሞቱ
ሰዎች አጥንትና በርኩስ ነገር ሁሉ የተሞሉ ፡
በውጪ ግን በኖራ ተለስነው የሚያምሩ የመቃ
ብር ግንቦችን ትመስላላችሁ ። 28 እንዲሁም እና
ንተ በውጪ ሰለው ጻድቃን መስላችሁ ትታያላ
ችሁ ፤ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ክፋት ሞል
ቶባችኋል ።

29 “እናንተ ግብዞች የሙሴ ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ! የነቢያትን መቃብር
ትገነባላችሁ ፤ የጻድቃንንም ሐውልት ታስጌጣላ
ችሁ ። 30 እናንተ ‘በእባቶቻችን ዘመን ተገኝተን
ብንሆን ኖሮ የነቢያትን ደም በማፍሰስ ከእነርሱ
ጋር ባልተባበርንም ነበር’ ትላላችሁ ። 31 እንግ
ዲህ ነቢያትን ለገደሉ ሰዎች ልጆቻቸው መሆና
ችሁን ራሳችሁ ትመሰክራላችሁ ። 32 ታዲያ አባ
ቶቻችሁ የጀመሩትን ሥራ እናንተም መፈጸም
ነዋ! 33 እናንተ እባቦች ፡ የእባብ ልጆች! እና
ንተ ከገሃነም ቅጣት ማምለጥ እንዴት ትችላላ
ችሁ? 34 ስለዚህ እነሆ እኔ ነቢያትን ፡ ጥበበኞ
ችን ፡ መምህራንን ወደ እናንተ እልካለሁ ፤ ከእ
ነርሱ አንዳንዶችን ትገድላላችሁ ፤ አንዳንዶቹን
ትሰቅላላችሁ ፤ አንዳንዶቹንም በምኩራባችሁ
ትገርፋላችሁ ፤ ከከተማ ወደ ከተማም ታሳድዱ
አቸዋላችሁ ፤ 35 በዚህም ምክንያት ከጻድቁ ከአ
ቤል ደም ጀምሮ በመቅደሱና በመሠዊያው
መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ
እስከ ዘካርያስ ደም በምድር ላይ ስለ ፈሰሰው
የጻድቅ ደም ቅጣቱ በእናንተ ላይ ይደርሳል ።
36 በእውነት እላችኋለሁ ፤ ይህ ሁሉ ቅጣት
በዚህ ዘመን ሰዎች ላይ ይደርሳል ።”

ለኢየሩሳሌም የተሰጠ ማስጠንቀቂያ
(ሉቃ. 13፡34-35)

37 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “ኢየሩሳ
ሌም ፡ ኢየሩሳሌም ሆይ! አንቺ ነቢያትን የም
ትገድዪ ፡ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ
የምትወግሪ! ዶሮ ጫጩቶቹዋን በክንፎችዋ
ሥር እንደምትሰበስብ ፡ እኔም የአንቺን ልጆች
በአንድነት ልሰበስብ ስንት ጊዜ ወደድሁ! እና
ንተ ግን አልፈለጋችሁም ። 38 እንግዲህ እነሆ
ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀራል ። 39 ስለዚህ ‘በጌታ
ስም የሚመጣ የተባረከ ነው’ እስክትሉ ድረስ
ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም እላችኋለሁ ።”

ምዕራፍ 24

ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ የኢየሱስ ትንቢት
(ማር. 13፡1-2፡ ሉቃ. 21፡5-6)

1 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሲሄድ ደቀ
መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ሊያሳዩት
ወደ እርሱ ቀረቡ ። 2 እርሱ ግን “ይህን ሁሉ
ታያላችሁን? በእውነት እላችኋለሁ ፤ ድንጋይ
በድንጋይ ላይ ተነባብሮ ሳይፈርስ የሚቀር
የለም” አላቸው ።

ስለ ዓለም መጨረሻ
(ማር. 13፡3-13፡ ሉቃ. 21፡7-19)

3 ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ
ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ እርሱ ቀር
በው ፡ “ይህ ሁሉ ነገር የሚሆነው መቼ ነው?
የመምጫህና የዓለም መጨረሻ ምልክትስ ምን
ድን ነው?” ሲሉ ጠየቁት ።

4 ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፡
“ማንም ሰው እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ!
5 ምክንያቱም ብዙዎች ‘እኔ መሲሕ ነኝ!’
እያሉ በስሜ ይመጣሉ ፤ ብዙ ሰዎችንም ያሳስ
ታሉ ። 6 የጦርነትን ድምፅና የጦርነትን ወሬ
ትሰማላችሁ ፤ ይህ ሁሉ መሆን ስላለበት አትደ
ንግጡ ፤ መጨረሻው ግን ገና ነው ። 7 ሕዝብ
በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ
በመርኃት ይነሣል ፤ በዚህ ልዩ ስፍራ ረሀብና
የምድር መናወጥ ይሆናል ። 8 ይህም ሁሉ እንደ
ምጥ ጣር ያለ የጭንቅ መጀመሪያ ይሆናል ።

9 “በዚያን ጊዜ ሰዎች ለመከራ አሳልፈው
ይሰጡአችኋል ፤ ይገድሉአችኋል ፤ በስሜም
ምክንያት በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ

23:22 ፡- ኢሳ. 66:1 ፡ ማቴ. 5:34 ። 23:23 ፡- ዘሌ. 27:30 ። 23:27 ፡- ሐሥ. 23:3 ። 23:33 ፡- ማቴ. 3:7 ፡ 12:34 ፡ ሉቃ. 3:7 ። 23:35 ፡- ዘፍ. 4:8 ፡ 2ዜ.መ. 24:20-21 ። 23:38 ፡- ኤር. 22:5 ። 23:39 ፡- መዝ. 118:26 ። 24:9 ፡- ማቴ. 10:22 ።

ትሆናላችሁ ። 10 በዚያን ጊዜ ብዙዎች ሃይማኖ
ታቸውን በመካድ ይሰናከላሉ ፤ አንዱ ሌላውን
አሳልፎ ይሰጣል ፤ ሰዎችም እርስ በርሳቸው ይጣ
ላሉ ። 11 ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ ፤ ብዙ
ዎችንም ያሳስታሉ ፤ 12 ከክፋት ብዛት የተነሣ
የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች ። 13 እስከ
መጨረሻ በትዕግሥት የሚጸና ግን ይድናል ።
14 ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚ
አብሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰ
በክል ፤ በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል ።”

አሠቃቂው መከራ
(ማር. 13፡14-23፡ ሉቃ. 21፡20-24)

15 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “ነቢዩ ዳን
ኤል በተናገረው መሠረት የሚያረክሰውን አጸያፊ
ነገር በተቀደሰ ስፍራ ቆሞ ታያላችሁ ፤ ይህንንም
አንባቢው ያስተውል ። 16 በዚያን ጊዜ በይሁዳ
አገር ያሉ ወደ ተራራዎች ይሽሹ ፤ 17 በጣራ ላይ
ያለ ከቤቱ አንዳች ነገር ለመውሰድ አይውረድ ።
18 በእርሻም ያለ ልብሱን ለመውሰድ ወደ ኋላው
አይመለስ ፤ 19 በዚያን ጊዜ ለነፍሰ ጡሮችና ለሚ
ያጠቡ እመጫቶች ወዮላችሁ! 20 ሽሽታችሁ በክ
ረምት ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን ጸልዩ ።
21 በዚያን ጊዜ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ
ድረስ ያልሆነ ፡ ወደፊትም እርሱን የሚመስል
ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይመጣል ። 22 እነዚያ
ቀኖች ባያጥሩማ ኖሮ አንድም ሰው መዳን ባል
ቻለ ነበር ፤ ነገር ግን ስለ ተመረጡት ሰዎች እነ
ዚያ ቀኖች ያጥራሉ ።

23 “በዚያን ጊዜ ማንም ሰው ‘እነሆ መሲሕ
እዚህ አለ! ወይም እዚያ አለ!’ ቢላችሁ አት
መኑ ። 24 ምክንያቱም ሐሰተኞች መሲሖችና
ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ ፤ እነርሱ ቢቻላቸ
ውስ የእግዚአብሔርን ምርጦች እንኳ ለማሳሳት
ታላላቅ ተአምራትንና ድንቅ ነገሮችን ያሳያሉ ።
25 “እንግዲህ ይህን ሁሉ አስቀድሜ ነግሬ
አችኋለሁ ፤ 26 ስለዚህ ‘እነሆ በበረሓ አለ’ ቢሉ
አትሁ አትሂዱ ፤ ‘እነሆ በስውር ቦታ አለ’ ቢሉ
አትሁ አትመኑ ። 27 ምክንያቱም መብረቅ በሰ
ማይ ብልጭ ብሎ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ
እንደሚታይ ፡ የሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ
ይሆናል ። 28 በድን ወዳለበት ቦታ አሞራዎች
ይሰበሰባሉ ።”

የሰው ልጅ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት
(ማር. 13፡24-27፡ ሉቃ. 21፡25-28)

29 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “ከነዚያ
ከመከራ ቀኖች በኋላ ወዲያውኑ ፀሐይ ትጨል
ማለች ፤ ጨረቃም ብርሃንዋን አታሳይም ፤ ከዋክ
ብትም ከሰማይ ይወድቃሉ ፤ የሰማያት ኀይሎ
ችም ይናወጣሉ ። 30 ከዚህም በኋላ የሰው ልጅ
ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል ፤ በዚያን ጊዜ
በዓለም ላይ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ ደረታቸውን እየ
መቱ ያለቅሳሉ ። የሰው ልጅም በኀይልና በታ
ላቅ ክብር በደመና ላይ ሆኖ ሲመጣ ያዩታል ፤
31 ታላቅ የመለከት ድምፅ የሚያሰሙ መላእክ
ቱን ይልካል ፤ እነርሱ በአራቱም የዓለም ማእዘ
ኖች ሄደው ከሰማይ ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ
ለእርሱ የተመረጡትን ሰዎች ይሰበስባሉ ።”

የጌታ መምጫ ጊዜ ምልክት
(ማር. 13፡28-31፡ ሉቃ. 21፡29-33)

32 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “የበለስ
ዛፍ ምሳሌ ትምህርት ይሁናችሁ ፤ ቅርንጫፎ
ችዋ ሲያቆጠቁጡና ቅጠሎችዋም ሲለመልሙ
ያን ጊዜ ጸደይ መቅረቡን ታውቃላችሁ ። 33 እን
ዲሁም እናንተ ይህን ሁሉ ስታዩ ፡ የሰው ልጅ
የሚመጣበት ጊዜ እንደቀረበ ዕወቁ ። 34 በእው
ነት እላችኋለሁ ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ
ይህ ትውልድ አያልፍም ። 35 ሰማይና ምድር
ያልፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ይኖራል ።”

ጌታ የሚመጣበትን ቀን ማንም አያውቅም
(ማር. 13፡32-37፡ ሉቃ. 17፡26-30፡34-36)

36 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “ስለዚ
ያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአብ በቀር የሰ
ማይ መላእክት ቢሆኑ ወልድም ቢሆን ማንም
የሚያውቅ የለም ። 37 በኖኅ ዘመን እንደነበረው
ዐይነት በሰው ልጅ መምጣትም ጊዜ እንዲሁ
ይሆናል ። 38 በዚያን ዘመን ከጥፋት ውሃ በፊት
ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች
ሲበሉና ሲጠጡ ፤ ሲያገቡና ሲያጋቡ ነበር ።
39 የጥፋት ውሃ መጥቶ ሁሉንም ጠራርጎ እስከ
ወሰዳቸው ድረስ እነዚህ ሰዎች ፡ የሰው ልጅ
አመጣጥም ልክ እንዲሁ ይሆናል ። 40 በዚያን
ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ አብረው ይሠራሉ ፤
አንደኛው ይወሰዳል ፤ ሌላው ይቀራል ።
41 ሁለት ሴቶች አብረው ይፈጫሉ ፤ አንደኛዋ
ትወሰዳለች ፤ ሌላይቱ ትቀራለች ። 42 እንግዲህ
ጌታችሁ በየትኛው ቀን እንደሚመጣ አታውቁ
ምና ተግታችሁ ጠብቁ ። 43 ነገር ግን ይህን
ዕወቁ ፤ ባለ ቤት ከሌሊቱ በየትኛው ሰዓት ሌባ
እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ ነቅቶ በጠበቀ
ነበር ፤ ቤቱም እንዲቆፈር ባልተወም ነበር ።
44 እንዲሁም የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ስለ
ሚመጣ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ።”

24:13 ፡- ማቴ. 10:22 ። 24:15 ፡- ዳን. 9:27 ፡ 11:31 ፡ 12:11 ። 24:17-18 ፡- ሉቃ. 17:31 ። 24:21 ፡- ዳን. 12:1 ፡ ሉቃ. 7:14 ። 24:26-27 ፡- ሉቃ. 17:23-24 ። 24:28 ፡- ሉቃ. 17:37 ። 24:29 ፡- ኢሳ. 13:10 ፡ 34:4 ፡ ሕዝ. 32:7 ፡ ኢዩ. 2:10 ፡ 3:1 ፡ 3:15 ፡ ራእ. 6:12-13 ። 24:30 ፡- ዳን. 7:13 ፡ ዘካ. 12:10-14 ፡ ራእ. 1:7 ። 24:37 ፡- ዘፍ. 6:5-8 ። 24:39 ፡- ዘፍ. 7:6-24 ። 24:43-44 ፡- ሉቃ. 12:39-40 ።

የደጉና የክፉው አገልጋይ ምሳሌ
(ሉቃ. 12፡41-48)

45 “ለቤተሰቦቹ ምግባቸውን በጊዜው እንዲ
ሰጣቸው ጌታው በቤተሰቦቹ ላይ የሚሾመው
ታማኝና ብልኅ አገልጋይ ማን ነው? 46 ጌታው
በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ
አገልጋይ የተመሰገነ ነው ። 47 በእውነት
እላችኋለሁ ፥ ያን አገልጋይ ጌታው በንብረቱ
ሁሉ ላይ ይሾመዋል ። 48 ያ ክፉ አገልጋይ ግን
‘ጌታዬ አሁን አይመጣም ይዘገያል’ ብሎ ቢያስ
ብና ፥ 49 የሥራ ጓደኞቹንም መደብደብ ቢጀ
ምር ፥ ከሰካራሞችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ ፥
50 የዚያ አገልጋይ ጌታ ባልጠበቀው ቀንና ባላወ
ቀው ሰዓት ይመጣል ፤ 51 ያንን አገልጋይ
ጌታው በብርቱ ይቀጣዋል ፤ ዕጣ ክፍሉንም ከግ
ብዞች ጋር ያደርግበታል ፤ በዚያም ለቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል ።”

ምዕራፍ 25

የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በዚያን
ጊዜ መንግሥተ ሰማይ የመግባት ሁኔታ መብራ
ታቸውን ይዘው ሙሽራ ለመቀበል የወጡ የዐ
ሥር ልጃገረዶችን ታሪክ ይመስላል ። 2 ከእነርሱ
አምስቱ ሞኞች ፥ አምስቱ ብልኆች ነበሩ ።
3 ሞኞቹ ልጃገረዶች መብራታቸውን ይዘው ፥
ለመብራቱ የሚሆን ትርፍ ዘይት አልያዙም
ነበር ። 4 ብልኆቹ ልጃገረዶች ግን ከመብራታ
ቸው ጋር ትርፍ ዘይት በዕቃ ይዘው ነበር ፤
5 ሙሽራው በመዘግየቱ ሁሉም በእንቅልፍ ተሸ
ንፈው ተኙ ።

6 “እኩለ ሌሊት ሲሆን ግን ‘እነሆ ሙሽራው
መጣ! ውጡና ተቀበሉት!’ የሚል ሁካታ
ተሰማ ። 7 በዚያን ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሡና
መብራታቸውን አዘጋጁ ። 8 ሞኞቹ ልጃገረዶች
ብልኆቹን ‘መብራታችን መጥፋቱ ስለሆነ እባካ
ችሁ ከዘይታችሁ ስጡን’ አሉአቸው ። 9 ብል
ኆቹ ልጃገረዶች ግን ‘ለእኛና ለእናንተ የሚበቃ
ዘይት የለንም ፤ ይልቅስ ወደ ሱቅ ሂዱና ለእና
ንተ የሚሆን ዘይት ግዙ’ ሲሉ መለሱላቸው ።
10 ሞኞቹ ልጃገረዶች ዘይት ለመግዛት በሄዱበት
ወቅት ሙሽራው መጣ ፤ ተዘጋጅተው የነበሩ
ትም ልጃገረዶች ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ
ግብዣ አዳራሽ ገቡ ፤ በሩም ተዘጋ ።

11 “በኋላም የቀሩት ልጃገረዶች መጡና
‘ጌታ ሆይ! እባክህ ክፈትልን!’ አሉት ።
12 እርሱ ግን ‘በእውነት እላችኋለሁ ፥ እኔ አላው
ቃችሁም!’ ሲል መለሰላቸው ። 13 ስለዚህ ቀኑ
ንና ሰዓቱን ስለማታውቁ ተግታችሁ ጠብቁ ።”

የሦስቱ አገልጋዮች ምሳሌ
(ሉቃ. 19፡11-27)

14 ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “በዚያን
ጊዜ ወደ መንግሥተ ሰማይ የመግባት ሁኔታ
እንዲህ ይሆናል ፦ ወደ ሌላ አገር የሚሄድ
አንድ ሰው አገልጋዮቹን ጠርቶ ንብረቱን አስረ
ከባቸው ፤ 15 ለእያንዳንዱ እንደ ችሎታው በማ
ካፈል ፥ ለአንዱ አምስት ሺ ብር ፥ ለአንዱ
ሁለት ሺ ብር ፥ ለአንዱ አንድ ሺ ብር
ሰጠና ወደ ሌላ አገር ሄደ ። 16 አምስት ሺ ብር
የተቀበለው ወዲያውኑ ሄዶ ነገደበትና ሌላ አም
ስት ሺ ብር አተረፈ ። 17 ሁለት ሺ ብር የተቀበ
ለውም እንዲሁ ነገሥ ሌላ ሁለት ሺ ብር አተ
ረፈ ። 18 አንድ ሺ ብር የተቀበለው ግን ሄደና
መሬት ቈፍሮ የጌታውን ገንዘብ ቀበረ ።

19 “ከብዙ ጊዜ በኋላ የነዚያ አገልጋዮች
ጌታ መጣና ከአገልጋዮቹ ጋር መተሳሰብ
ጀመረ ። 20 አምስት ሺ ብር የተቀበለው አገል
ጋይ ወደ ጌታው መጣና ሌላም አምስት ሺ
ብር አቅርቦ ፥ ‘ጌታ ሆይ! አምስት ሺ ብር ሰጥ
ተኸኝ ነበር ፤ እነሆ ሌላ አምስት ሺ ብር አትር
ፈአለሁ!’ አለ ። 21 ጌታውም ‘መልካም አደረ
ግህ ፥ አንተ ታማኝና ደግ አገልጋይ! በጥቂት
ነገር ታማኝ ሆነህ ስለተገኘህ በብዙ ነገር ላይ
እሾምሃለሁ ፥ ና! የጌታህን ደስታ ለመካፈል
ግባ!’ አለው ። 22 ሁለት ሺ ብር የተቀበለውም
ቀርቦ ‘ጌታ ሆይ! ሁለት ሺ ብር ሰጥተኸኝ
ነበር ፤ እነሆ ሌላ ሁለት ሺ ብር አትርፈአለሁ’
አለ ። 23 ጌታውም ‘መልካም ነው! አንተ ታማ
ኝና ደግ አገልጋይ ፥ በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ
ስለተገኘህ በብዙ ነገር እሾምሃለሁ ፤ ና የጌታ
ህን ደስታ ለመካፈል ግባ!’ አለው ። 24 አንድ
ሺ ብር የተቀበለውም ቀርቦ ‘ጌታ ሆይ! ካልዘ
ራህበት የምታጭድ ፥ ካልበተንህበት የምትሰበ
ስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቃለሁ ፤ 25 ስለ
ዚህ ፈራሁና ሄጄ ገንዘብህን በመሬት ውስጥ
ቀበርሁት ፥ ይኸውልህ ገንዘብህ’ አለው ።
26 ጌታው ግን እንዲህ አለው ፥ ‘አንተ ክፉና
ሰነፍ አገልጋይ! ካልዘራሁበት እንደማጭድ ፥
ካልበተንሁበት እንደምሰበስብ የምታውቅ
ከሆነ ፥ 27 ገንዘቤን በባንክ ማስቀመጥ ነበረብህ ፤
እኔም በመጣሁ ጊዜ ገንዘቤን ከነወለዱ እወስድ
ነበር ።’ 28 በሉ ገንዘቡን ተቀበሉና ዐሥር ሺ
ብር ላለው ስጡት ። 29 ምክንያቱም ላለው ሰው
ይጨመርለታል ፤ ይበዛለታልም ፤ ከሌለው ሰው
ግን ያው ያለውም እንኳ ይወሰድበታል ።
30 ይህን የማይረባ አገልጋይ ግን በውጪ ወዳ
ለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት ፤ በዚያ ለቅ
ሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል ።”

25፡1 ፡- ሉቃ. 12፡35 ። 25፡11-12 ፡- ሉቃ. 13፡25 ። 25፡14-30 ፡- ሉቃ. 19፡11-27 ። 25፡29 ፡- ማቴ. 13፡12 ፡ ማር. 4፡25 ፡ ሉቃ. 8፡18 ። 25፡30 ፡- ማቴ. 8፡12 ፡ 22፡13 ፡ ሉቃ. 13፡28 ።

በዓለም መጨረሻ የሚሆነው ፍርድ

31 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “የሰው
ልጅ በመላእክቱ ሁሉ ታጅቦ በክብር ሲመጣ
በክብር ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል ፤ 32 ሕዝቦች
ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛ በጎችን ከፍየ
ሎች እንደሚለይ እርሱም ሕዝቦችን ይለያል ።
33 በጎቹን በቀኙ ፥ ፍየሎቹን በግራው ያቆማቸ
ዋል ። 34 በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉ
ትን እንዲህ ይላቸዋል ፥ ‘እናንተ አባቴ የባረካ
ችሁ ፥ ኑ! ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ የተዘጋጀላች
ሁን መንግሥት ውረሱ ፤ 35 ምክንያቱም ተርቤ
አብልታችኋል ፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል ፤
እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል ፤ 36 ታርዤ አልብ
ሳችሁኛል ፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛል ፤ ታስሬ
ጐብኝታችሁኛል ።’ 37 በዚያን ጊዜ ጻድቃን
እንዲህ ሲሉ ይመልሱለታል ፥ ‘ጌታ ሆይ! መቼ
ቸርበህ አየንህና አበላንህ? መቼ ተጠምተህ አየ
ንህና አጠጣንህ? 38 መቼ እንግዳ ሆነህ አየንህና
ቀቀበልንህ? መቼ ታርዘህ አየንህና አለበስንህ?
39 መቼ ታመህ ወይም ታስረህ አየንህና ጠየቅ
ንህ?’ 40 ንጉሡም ‘በእውነት እላችኋለሁ ፥ ከእ
ነዚህ ከወንድሞቼ አነስተኛ ለሆነው ለአንዱ
እንኳ ያደረጋችሁት ሁሉ ለእኔ እንዳደረጋች
ሁት ነው’ ሲል ይመልስላቸዋል ።

41 “ከዚህ በኋላ በግራው በኩል ያሉትንም
እንዲህ ይላቸዋል ፥ ‘እናንተ የተረገማችሁ!
ከእኔ ወዲያ ራቁ! ለሰይጣንና ለተከታዮቹ መላ
እክት ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ ።
42 ምክንያቱም ተርቤ አላበላችኋኝም ፤ ተጠ
ምቼ አላጠጣችኋኝም ። 43 እንግዳ ሆኜ አልተቀ
በላችሁኝም ፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝም ፥ ታም
ሜና ታስሬ አልጠየቃችሁኝም ፤’ 44 እነርሱም
‘ጌታ ሆይ! ተርበህ ወይም ተጠምተህ ፥ እንግዳ
ሆነህ ወይም ታርዘህ ፥ ታመህ ወይም ታስረህ
መቼ አየንህና ሳንረዳህ ቀረን?’ ሲሉ ይመልሱለ
ታል ። 45 ንጉሡም ‘በእውነት እላችኋለሁ ፥
ከእነዚህ ከወንድሞቼ አነስተኛ ለሆነው ለአንዱ
እንኳ ያላደረጋችሁት ሁሉ ለእኔ እንዳላደረጋች
ሁት ነው’ ይላቸዋል ። 46 ስለዚህ እነዚህ ወደ
ዘላለም ቅጣት ሲሄዱ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም
ሕይወት ይሄዳሉ ።”

ምዕራፍ 26

በኢየሱስ ላይ የተደረገ ሴራ
(ማር. 14፡1-2፡ ሉቃ. 22፡1-2፡ ዮሐ. 11፡45-53)

1 ኢየሱስ ይህን ሁሉ ትምህርት አስተምሮ
ባበቃ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ፥
2 “ከሁለት ቀን በኋላ የፋሲካ በዓል እንደሚሆን
ታውቃላችሁ ፤ የሰው ልጅ ለመሰቀል ተላልፎ
ይሰጣል ።”

3 በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕዝብ
ሽማግሌዎች በሊቀ ካህናቱ በቀያፋ ግቢ ተሰበ
ሰቡ ። 4 እዚያም ኢየሱስን በተንኮል ለመያዝና
ለመግደል ተማከሩ ። 5 ነገር ግን “ሕዝቡ ሁከት
እንዳያስነሣ በበዓል ቀን አይሁን” አሉ ።

አንዲት ሴት ኢየሱስን ሽቶ እንደቀባች
(ማር. 14፡3-9፡ ዮሐ. 12፡1-8)

6 እነሆ ኢየሱስ በቢታንያ ለምጻም በነበረው
በስምዖን ቤት ነበረ ። 7 ኢየሱስ በማእድ ተቀ
ምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ ውድ
የሆነ ሽቶ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ
ወደ እርሱ ቀረበች ፤ ሽቶውንም በራሱ ላይ አፈ
ሰሰች ። 8 ደቀ መዛሙርቱ ይህን አይተው ተቈ
ጡና እንዲህ አሉ ፥ “ይህ ሽቶ በከንቱ ባከነ!
9 ሽቶው እኮ በውድ ዋጋ ተሸጦ ገንዘቡ ለድ
ኾች ይሆን ነበር!” 10 ኢየሱስም ይህን ማለታች
ውን ዐውቆ እንዲህ አላቸው ፥ “ይህችን ሴት
ለምን ታስቸግሩአታላችሁ? እርስዋ ለእኔ መል
ካም ነገር አድርጋለች ፤ 11 ድኾች ሁልጊዜ ከእ
ናንተ ጋር ናቸው ፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ
ጋር እዚህ አልገኝም ። 12 እርስዋ ይህን ሽቶ
በእኔ ላይ ማፍሰስዋ እኔን ለቀብር ለማዘጋጀት
ነው ። 13 በእውነት እላችኋለሁ በዓለም ሁሉ
ይህ ወንጌል በሚሰበክበት በማናቸውም ስፍራ
ይህ እርስዋ ያደረገችው ለመታሰቢያዋ ይነገርላ
ታል ።”

ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ
(ማር. 14፡10-11፡ ሉቃ. 22፡3-6)

14 በዚያን ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
አንዱ የሆነው አስቆሮታዊው ይሁዳ ወደ ካህ
ናት አለቆች ሄደና ፥ 15 “ኢየሱስን አሳልፌ ብሰ
ጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ?” አለ ። እነርሱም
ሠላሳ ጥሬ ብር ሰጡት ። 16 እርሱም ከዚያ ቀን
ጀምሮ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጥበትን ምቹ
ጊዜ ይፈልግ ነበር ።

ኢየሱስ የአይሁድን የፋሲካ ራት ከሐዋርያቱ ጋር እንደበላ
(ማር. 14፡12-21፡ ሉቃ. 22፡7-14፡21-23፡ ዮሐ. 13፡21-30)

17 በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙ
ርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው “የፋሲካን ራት የት
እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” ሲሉ ጠየቁት ።
18 እርሱም “በከተማ ወደሚኖረው ወደ እንትና
ቤት ሂዱና ‘መምህር ጊዜዬ ቀርቦአልና ከደቀ

25፡31 ፡- ማቴ. 16፡27 ፡ 19፡28 ። 25፡46 ፡- ዳን. 12፡2 ። 26፡2 ፡- ዘጽ. 12፡1-27 ። 26፡7 ፡- ሉቃ. 7፡37-38 ። 26፡11 ፡- ዘዳ. 15፡11 ። 26፡15 ፡- ዘካ. 11፡12 ።

መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት የምበላው በአ
ንተ ቤት ነው ይላል’ በሉት” አለ ። 19 ደቀ
መዛሙርቱም ኢየሱስ እንዳዘዘቸው አደረጉ ፥
የፋሲካውንም ራት አዘጋጁ ፤ 20 በመሽም ጊዜ
ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር በማእድ ተቀ
መጠ ። 21 ሲበሉም ኢየሱስ “በእውነት እላችኋ
ለሁ ፥ ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል”
አለ ። 22 ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር በጣም
አዝነው እያንዳንዳቸው “እኔ እሆን?” እያሉ
ይጠይቁት ጀመር ። 23 ኢየሱስም እንዲህ ሲል
መለሰላቸው ፥ “እኔን አሳልፎ የሚሰጥ ከእኔ
ጋር በሳሕኑ ውስጥ የሚያጠቅሰው ነው ። 24 የሰው ልጅ ስለ እርሱ በተጻፈው መሠረት
ይሞታል ፤ ነገር ግን የሰው ልጅን አሳልፎ ለሚ
ሰጥ ሰው ወዮለት! ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው
ነበር ።” 25 አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም “መም
ህር ሆይ! እኔ እሆንን?” አለ ። ኢየሱስም
“አንተ እንዳልከው ነው” አለው ።

የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት (የጌታ ራት)
(ማር. 14፡22-26፤ ሉቃ. 22፡15-20፤
1 ቆሮ. 11፡23-25)

26 (ራት) ሲበሉም ኢየሱስ ኅብስት አንሥቶ
የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛ
ሙርቱ “እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው”
ብሎ ሰጣቸው ።
27 ጽዋውንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደ
ረገ በኋላ እንዲህ ሲል ሰጣቸው ፥ “ሁላችሁም
ከዚህ ጽዋ ጠጡ ፤ 28 ይህ ስለ ብዙዎች ለኃጢ
አት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው ፤
29 በአባቴ መንግሥት አዲሱን የወይን ፍሬ
ጭማቂ ከእናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀን
ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ የወይን ፍሬ
ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም እላችኋለሁ ።”
30 ከዚህ በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ ደብረ
ዘይት ተራራ ወጡ ።

ኢየሱስ የጴጥሮስን መካድ አስቀድሞ ተናገረ
(ማር. 14፡27-31፤ ሉቃ. 22፡31-34፤
ዮሐ. 13፡36-38)

31 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
እንዲህ አላቸው ፥ “‘እረኛውን መትቼ እገድላ
ለሁ ፤ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ’ ተብሎ
ተጽፎአልና በዚህች ሌሊት ሁላችሁም ትክዱ
ኛላችሁ ። 32 ነገር ግን ከሞት ከተነሣሁ በኋላ
ወደ ገሊላ ቀድሜአችሁ እሄዳለሁ ።”
33 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ “ሌሎቹ ሁሉ እንኳ
ቢክዱህ ፥ እኔ ከቶ አልክድህም” ብሎ ተናገረ ።
34 ኢየሱስም “በእውነት እልሃለሁ ፥ ዛሬ በዚ
ህች ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት አንተ ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ” አለው ። 35 ጴጥሮስ ግን
“መሞት እንኳ የሚያስፈልግ ቢሆን ከአንተ
ጋር እሞታለሁ እንጂ ከቶ አልክድህም”
አለው ። የቀሩትም ደቀ መዛሙርት ሁሉ እን
ዲሁ ይሉ ነበር ።

ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ
(ማር. 14፡32-42፤ ሉቃ. 22፡39-46)

36 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ ሄደ ፤ እዚያም
እንደ ደረሱ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “እኔ
እዚያ ሄጄ እስክጸልይ ፥ እናንተ እዚህ ቆዩ”
አላቸው ። 37 ከእርሱ ጋር ጴጥሮስንና የዘብዴዎ
ስን ልጆች አስከትሎ ሄደ ፤ ማዘንና መጨነቅም
ጀመረ ። 38 እንዲህም አላቸው ፥ “ለመሞት እስ
ክደርስ አዝኛለሁ ፤ እናንተ እዚህ ቆዩ ፤ ከእኔም
ጋር ንቁ ።” 39 ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ብሎ ሄደና
በመሬት ላይ በግንባሩ ተደፍቶ እንዲህ ሲል
ጸለየ ፥ “አባት ሆይ! የሚቻልህ ከሆነ ይህ የመ
ከራ ጽዋ ከእኔ ወዲያ ይለፍ ፤ ነገር ግን እንደ
አንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ
አይሁን ።”
40 ከዚህ በኋላ ወደ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት
ተመልሶ በመጣ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው ፤ ስለ
ዚህ ጴጥሮስን እንዲህ አለው ፥ “ከእኔ ጋር አን
ዲት ሰዓት እንኳ መንቃት አልቻላችሁምን?
41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ ፤
የሰው መንፈስ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው ፤ ሥጋ ግን
ደካማ ነው ።”
42 እንደገናም ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ርቆ
ሄዶና “አባቴ ሆይ! ይህ የመከራ ጽዋ ሳልጠ
ጣው ሊያልፍ የማይቻል ከሆነ እንደ አንተ
ፈቃድ ይሁን” ሲል ጸለየ ። 43 ደግሞም ወደ
ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ በመጣ ጊዜ ዐይኖቻ
ቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገ
ኛቸው ። 44 እንደገናም ትቶአቸው ሄዶና ያንኑ
የፊተኛውን ቃል በመናገር ሦስተኛ ጊዜ ጸለየ ።
45 ከዚህ በኋላ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ
መጣና እንዲህ አላቸው ፥ “አሁንም ገና ተኝ
ታችኋልን? አሁንም ዕረፍት ታደርጋላችሁን?
እነሆ ሰዓቱ ደርሶአል ፤ የሰው ልጅ በኃጢአተ
ኞች እጅ ተላልፎ ይሰጣል ፤ 46 ተነሡ እን
ሂድ ፤ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል ።”

ኢየሱስ በጠላቶቹ ተያዘ
(ማር. 14፡43-50፤ ሉቃ. 22፡47-53፤
ዮሐ. 18፡3-12)

47 ኢየሱስ ገና ሲናገር ሳለ እነሆ ከዐሥራ
ሁለቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ መጣ ፤ ከእርሱም
ጋር ሰይፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎች መጡ ፤ እነ
ርሱ ከካህናት አለቆችና ከሕዝብ ሽማግሌዎች
የተላኩ ነበሩ ። 48 ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጠው
ይሁዳ ለሰዎቹ “የምትፈልጉት እኔ የምስመው
ነውና እርሱን ያዙት” ሲል ምልክት ሰጥቶአ
ቸው ነበር ።
49 ይሁዳ ወዲያውኑ መጥቶ ወደ ኢየሱስ
ቀረበና “መምህር ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን”
ብሎ ሳመው ። 50 ኢየሱስም “ወዳጄ ሆይ! እን
ግዲህ የመጣህበትን ጉዳይ ፈጽም”[15*] አለው ፤
ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ወደ ኢየሱስ ቀረቡና
ያዙት ። 51 በዚህ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት
አንዱ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ
መትቶ ጆሮውን ቈረጠው ። 52 ኢየሱስ ግን እን
ዲህ አለ ፥ “ሰይፍን የሚያነሡ በሰይፍ ይጠፋ
ሉና ሰይፍህን ወደ ስገባው መልሰህ ክተተው ።
53 ለመሆኑ እኔ አባቴን ብለምን እርሱ በብዙ ሺ
የሚቈጠሩ የመላእክት ሠራዊት ሊልክልኝ የማ
ይችል ይመስልሃልን? 54 እንዲህማ ቢሆን ኖሮ
‘መከራ መቀበል አለበት’ የሚለው የመጽሐፍ
ቅዱስ ቃል እንዴት ይፈጸማል?”
55 በዚያን ሰዓት ኢየሱስ ለሕዝቡ እንዲህ
አለ ፥ “ወንበዴን እንደምትይዙ ፥ እኔን ለመያዝ
ሰይፍና ዱላ ይዛችሁ መጣችሁን? በየቀኑ በቤተ
መቅደስ እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ሳለሁ አልያ
ዛችሁኝም ነበር ፤ 56 ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው
በነቢያት የተጻፈው እንዲፈጸም ነው ።” በዚያን
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ ።

ኢየሱስ ወደ ፍርድ ሸንጎ ቀረበ
(ማር. 14፡53-65፤ ሉቃ. 22፡54-55፤63-71፤
ዮሐ. 18፡13-14፤19-24)

57 ከዚህ በኋላ ኢየሱስን የያዙት ሰዎች ወደ
ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት ፤ በዚያም
የሕግ መምህራንና ሽማግሌዎች ተሰብስበው
ነበር ። 58 ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ
ድረስ ኢየሱስን በሩቅ ተከተለው ፤ ወደ ውስጥ
ገብቶም የነገሩን ፍጻሜ ለማየት ከሌሎች ጋር
ተቀመጠ ። 59 የካህናት አለቆችና የሸንጎውም
አባሎች ሁሉ በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ ለማስ
ፈረድ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር ።
60 ምንም እንኳ ብዙ የሐሰት ምስክሮች ቢቀር
ቡም ፥ ሞት የሚያስፈርድበት ምስክርነት አላገ
ኙም ፤ በመጨረሻ ሁለት ምስክሮች ቀርበው ፥
61 “ይህ ሰው ‘የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ
አፍርሼ በሦስት ቀን ልሠራው እችላለሁ’ ብሎ
አል” ሲሉ ተናገሩ ።
62 ሊቀ ካህናቱም ተነሣና “እነዚህ ሰዎች
ለሚመሰክሩብህ ሁሉ ምንም መልስ አትሰጥ
ምን?” ሲል ጠየቀው ። 63 ኢየሱስ ግን ዝም
አለ ። ሊቀ ካህናቱም እንደገና ኢየሱስን “በሕ
ያው እግዚአብሔር ስም ይገዘሃለሁ! የእግዚአብ
ሔር ልጅ መሲሕ አንተ እንደሆንህ ንገረን?”
አለው ። 64 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥
“አንተ እንዳልኸው ነው ፤ ነገር ግን ከአንግዲህ
ወዲህ የሰው ልጅ በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ
ተቀምጦ ታዩታላችሁ ፤ እንዲሁም በሰማይ
ደመና ሆኖ ሲመጣ ታዩታላችሁ እላችኋለሁ ።”
65 በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ በቍጣ ልብሱን ቀደ
ደና እንዲህ አለ ፥ “እነሆ በእግዚአብሔር ላይ
የስድብ ቃል ተናግሮአል ፤ እናንተም ስድቡን
ሰምታችኋል ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር
ያስፈልጋል? 66 ታዲያ ምን ይመስላችኋል?”
እነርሱም “ሞት ይገባዋል!” ሲሉ መለሱ ።
67 በዚያን ጊዜ ምራቃቸውን ተፉበት ፤ ጎሽ
ሙት ፤ በጥፊም እየመቱት ፥ 68 “መሲሕ ሆይ!
ማን ነው የመታህ እስቲ ዕወቅ” ይሉት ነበር ።

ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ
(ማር. 14፡66-72፤ ሉቃ. 22፡56-62፤
ዮሐ. 18፡15-18፡25-27)

69 ጴጥሮስ ከቤት ውጪ በሊቀ ካህናቱ ግቢ
ውስጥ ተቀምጦ ነበር ፤ በዚያን ጊዜ አንዲት
ገረድ ወደ እርሱ ቀርባ “አንተም እኮ ከገሊላ
ዊው ኢየሱስ ጋር ነበርህ!” አለችው ። 70 እርሱ
ግን “የምትዪውን አላውቅም!” ሲል በሁሉም
ፊት ካደ ። 71 ሊወጣ ወደ በሩ ሲሄድ አንዲት
ሌላ ገረድ አየችውና እዚያ ለነበሩት ሰዎች
“ይህ ሰው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበር”
አለች ። 72 ጴጥሮስም “ይህን የምትዪውን ሰው
አላውቀውም” ሲል በመማል እንደገና ካደ ።
73 ከጥቂት ጊዜ በኋላ እዚያ ቆመው የነበሩት
ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ጠጋ ብለው “እነጋገርህ
ያስታውቃልና በእርግጥ አንተም ከእርሱ ወገን
ነህ” አሉት ። 74 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ “እኔ
ይህን ሰው አላውቀውም!” እያለ ራሱን መራገ
ምና መማል ጀመረ ። ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ ።
75 ጴጥሮስም “ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ” ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ቃል
ትዝ አለው ። ወደ ውጪም ወጣና ምርር ብሎ
አለቀሰ ።

ምዕራፍ 27

ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ለፍርድ ቀረበ
(ማር. 15፡1፤ ሉቃ. 23፡1-3፤ ዮሐ. 18፡28-32)

1 ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆችና የሕዝብ
ሽማግሌዎች ሁሉ በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ

26፡23 ፡- መዝ. 41፡9 ። 26፡28 ፡- ዘጸ. 24፡8 ፤ ኤር. 31፡31-34 ። 26፡31 ፡- ዘካ. 13፡7 ። 26፡32 ፡- ማቴ. 28፡16 ።

15* 26፡50 አንዳንድ ቅጂዎች “ወዳጄ ሆይ! እዚህ ምን ልታደርግ መጣህ?” ይላሉ ።
26፡55 ፡- ሉቃ. 19፡47 ፤ 21፡37 ። 26፡61 ፡- ዮሐ. 2፡19 ። 26፡64 ፡- ዳን. 7፡13 ። 26፡65-66 ፡- ዘሌ. 24፡16 ።
26፡67 ፡- ኢሳ. 50፡6 ።

ለማስፈረድ ተማከሩ ። 2 ከዚህ በኋላ ኢየሱስን
አስረው ወሰዱና ለገዥው ለጲላጦስ አሳልፈው
ሰጡት ።
3 ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ፡ ኢየሱስ
እንደተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ ፤ ሠላሳውንም
ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች እን
ዲህ በማለት መልሶ ሰጣቸው ፡ 4 “ንጹሑን
ሰው ለሞት አሳልፌ በመስጠቴ በድዬአለሁ ።”
እነርሱ ግን “ታዲያ እኛ ምን ቸገረን! የራስህ
ጕዳይ ነው!” አሉት ። 5 እርሱም ሠላሳውን
ጥሬ ብር በቤተ መቅደስ ውስጥ በትኖ ትቶአ
ቸው ወጣ ፤ ሄዶም ታንቆ ሞተ ።
6 የካህናት አለቆች ሠላሳውን ጥሬ ብር አን
ሥተው “ይህ ገንዘብ የደም ዋጋ ስለሆነ ከቤተ
መቅደስ መባ ጋር ልንቀላቅለው አይፈቀድም”
አሉ ። 7 ስለዚህ ከተመካከሩ በኋላ ለእንግዶች
የመቃብር ቦታ እንዲሆን የሸክላ ሠሪውን
መሬት ገዙበት ። 8 በዚህ ምክንያት ያ መሬት
እስከ ዛሬ ድረስ “የደም መሬት” እየተባለ ይጠ
ራል ።
9 በዚህ ሁኔታ “የእስራኤል ልጆች የገመቱ
ትን ለእርሱ ዋጋ የሚሆን ሠላሳ ጥሬ ብር
ወሰዱ ፤ 10 ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪው
መሬት ከፈሉ” ተብሎ በነቢዩ ኤርምያስ የተነ
ገረው ትንቢት ተፈጸመ ።

ጲላጦስ ኢየሱስን መረመረ
(ማር. 15፡2-5፤ ሉቃ. 23፡3-5፤ ዮሐ. 18፡33-38)

11 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ወደ ገዥው ወደ
ጲላጦስ ፊት ቀረበ ፤ ገዥውም “አንተ የአይ
ሁድ ንጉሥ ነህን?” ሲል ጠየቀው ፤ ኢየሱስም
“አንተ እንዳልኸው ነኝ” ሲል መለሰ ። 12 ነገር
ግን የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሲወነጅ
ሉት ምንም መልስ አልሰጠም ።
13 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ “በስንት ነገር ሲወነ
ጅሉህ አትሰማምን?” አለው ። 14 ኢየሱስ ግን
ገዥው እስኪደነቅ ድረስ አንዴት ቃል እንኳ
አልመለሰለትም ።

ኢየሱስ የሞት ፍርድ ተፈረደበት
(ማር. 15፡6-15፤ ሉቃ. 23፡13-25፤
ዮሐ. 18፡39-40፤ 19፡1-16)

15 ሮማዊው ገዥ በየዓመቱ በአይሁድ ፋሲካ
በዓል ጊዜ እንዲፈታላቸው ሕዝቡ የጠየቁትን
አንድ እስረኛ ፈትቶ መልቀቅ አስለምዶ ነበር ።
16 በዚያን ጊዜ “በርባን” የተባለ በዐመፀኛነቱ
የታወቀ እስረኛ ነበራቸው ። 17 ስለዚህ ሕዝቡ
በተሰበሰቡ ጊዜ ጲላጦስ “ማንን እንድፈታላ
ችሁ ትፈልጋላችሁ? በርባንን ነውን ወይስ
መሲሕ የተባለውን ኢየሱስን?” ሲል ጠየቃ
ቸው ። 18 ይህንን ያለበት ምክንያት ኢየሱስን
በቅንአት አሳልፈው እንደሰጡት ያውቅ ስለነበር
ነው ።
19 ጲላጦስ በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ
ሚስቱ “በእርሱ ምክንያት ዛሬ ሌሊት በሕልም
ብዙ ተሠቃይቻለሁና በዚያ በንጹሕ ሰው ላይ
ምንም እንዳታደርግ” ስትል ላከችበት ።
20 በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆችና ሽማግሌ
ዎች “በርባን ይለቀቅ! ኢየሱስ ይገደል!”
ብለው እንዲጠይቁ ሕዝቡን አግባቡ ። 21 ገዥ
ውም “ከሁለቱ የትኛውን እንድፈታላችሁ ትፈ
ልጋላችሁ” ሲል ሕዝቡን እንደገና ጠየቀ ። እነ
ርሱም “በርባንን እንድትፈታልን እንፈልጋለን”
ሲሉ መለሱ ። 22 ጲላጦስም “ታዲያ መሲሕ
የተባለውን ኢየሱስን ምን ላድርገው” አላ
ቸው ። ሁሉም “ይሰቀል!” ሲሉ መለሱ ።
23 ገዥውም “እርሱ ያደረገው በደል ምንድን
ነው?” አላቸው ። እነርሱ ግን “ይሰቀል!”
እያሉ አብዝተው ጮኹ ። 24 ስለዚህ ጲላጦስ
ይህ ነገር ሁከት እንደሚያስነሣ እንጂ ሌላ
ምንም እንደማይጠቅም ባየ ጊዜ ውሃ አስመጥቶ
“እኔ ለዚህ ሰው ሞት ኀላፊ አይደለሁም ፤ እና
ንተ እንደፈለጋችሁ አድርጉት” ብሎ በሕዝቡ
ፊት እጁን ታጠበ ።
25 ሕዝቡም ሁሉ “በእርሱ ሞት ምክንያት
የሚመጣው ቅጣት በእኛና በልጆቻችን ላይ
ይሁን” አሉ ።
26 በዚያን ጊዜ ጲላጦስ በርባንን ፈትቶ ለቀ
ቀላቸው ፤ ኢየሱስን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲ
ሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው ።

ወታደሮች በኢየሱስ አፌዙበት
(ማር. 15፡16-20፤ ዮሐ. 19፡2-3)

27 በዚያን ጊዜ የገዥው ወታደሮች ወደ
ገዥው ግቢ ወሰዱት ፤ ወታደሮቹንም ሁሉ በእ
የሱስ ዙሪያ ሰበሰቡ ። 28 ልብሱንም ገፈው ቀይ
ልብስ አለበሱት ። 29 የእሾኽ አክሊልም ጐንጉተ
ነው በራሱ ላይ ደፉበት ፤ በቀኝ እጁም መቃ
አስያዙት ፤ በፊቱም እየተንበረከኩ “የአይሁድ
ንጉሥ ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን” እያሉ ያፌ
ዙበት ነበር ፤ 30 ምራቃቸውንም ይተፉበት
ነበር ፤ መቃውንም ከእጁ ወስደው ራስ ራሱን
በመቃው ይመቱት ነበር ። 31 ካፌዙበት በኋላ
ቀዩን ልብስ አውልቀው የራሱን ልብስ አለበ
ሱት ፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት ።

ኢየሱስ ተሰቀለ
(ማር. 15፡21-32፤ ሉቃ. 23፡25-43፤
ዮሐ. 19፡17-27)

32 ከገዥው ግቢ ሲወጡ ሳሉ ስምዖን የተባለ
ውን የቀሬና አገር ሰው አገኙና የኢየሱስን መስ
ቀል እንዲሸከም አስገደዱት ። 33 ከዚህ በኋላ

27፡3-8 ፡- ሐሥ. 1፡18-19 ። 27፡9-10 ፡- ዘካ. 11፡12-13 ። 27፡24 ፡- ዘዳ. 21፡6-9 ።

ቀቀራንዮ” ወይም “የራስ ቅል” እየተባለ ወደ
ሚጠራው ስፍራ ወደ ጎልጎታ ደረሱ ። 34 በዚ
ያም ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እን
ዲጠጣ ለኢየሱስ አቀረቡለት ፤ እርሱ ግን ቀመስ
እድርጎ ሊጠጣው አልፈለገም ። 35 ኢየሱስን ከሰ
ቀሉት በኋላ ልብሱን ዕጣ ተጣጥለው ተካፈሉ ።
36 በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር ።
37 ወንጀሉንም የሚያመለክት “ይህ የአይሁድ
ንጉሥ ኢየሱስ ነው” የሚል ጽሑፍ በኢየሱስ
ራስጌ በመስቀሉ ላይ አኖሩ ። 38 በዚያን ጊዜ
ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኝ ፡ አንዱ በግራ
ክኢየሱስ ጋር ተሰቀሉ ።
39 በአጠገቡ ያልፉ የነበሩትም ሰዎች በን
ቀት ራሳቸውን እየነቀነቁ ፡ 40 “አንተ ቤተ
መቅደስን የምታፈርስና በሦስት ቀን የምትሠ
ራው! እስቲ ራስህን አድን! የእግዚአብሔር
ልጅ ከሆነህ እስቲ ከመስቀል ውረድ!” በማለት
ያላግጡብት ነበር ።
41 በዚሁ ዐይነት የካህናት አለቆች ከመሴ
ሕግ መምህራንና ከሽማግሌዎች ጋር እንዲህ
እያሉ ያፌዙበት ነበር ፡ 42 “ሌሎችን አዳነ ፡
ራሱን ግን ማዳን አይችልም ፤ እርሱ የእስራኤል
ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ ፤
እኛም እንመንበት ። 43 እርሱ በእግዚአብሔር
ታምኖአል ፡ ‘የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ’ ብሎ
ኣል ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሚወደው ከሆነ
እስቲ አሁን ያድነው!” 44 እንዲሁም ከእርሱ
ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎች ይሰድቡት ነበር ።

ኢየሱስ ሞተ
(ማር. 15፡33-41፤ ሉቃ. 23፡44-49፤
ዮሐ. 19፡28-30)

45 ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት
ድረስ በምድር ሁሉ ጨለማ ሆነ ። 46 ዘጠኝ
ሰዓት ሲሆን ኢየሱስ “ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበ
ቅታኒ?” ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ ፤ ትርጓሜ
ውም “አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውኸኝ?”
ማለት ነው ። 47 በዚያም ቆመው ከነበሩት
ሰዎች አንዳንዶቹ “ይህስ ኤልያስን ይጠራል!”
አሉ ። 48 በዚያን ጊዜ ከእነርሱ አንዱ ስፖንጅ
አምጥቶ ሆምጣጤ ሞላበት ፤ በመቃ ላይ አድር
ጎም ኢየሱስ እንዲጠማ አቀረበለት ። 49 ሌሎ
ችም “ቆይ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እን
ደሆነ እንይ!” አሉ ። 50 ኢየሱስ እንደገና በታ
ላቅ ድምፅ ጮኸና ሞተ ።
51 በዚያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ
እስከ ታች ተቀዶ ከሁለት ተከፈለ ፤ ምድርም
ተናወጠች ፤ አለቶችም ተሰነጠቁ ፤ 52 መቃብሮ
ችም ተከፍተው ሞተው ከነበሩት ብዙ ቅዱሳን
ሰዎች ከሞት ተነሡ ። 53 ከመቃብርም ወጡና
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ወደ ቅድስት
ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ ፤ በዚያም ለብዙ
ሰዎች ታዩ ።
54 የመቶ አለቃውና ከእርሱም ጋር ኢየሱ
ስን ይጠብቁ የነበሩት የምድርን መናወጥና
ሌላውንም ነገር ባዩ ጊዜ እጅግ ፈርተው
“በእውነት ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ!”
አሉ ። 55 በሩቅ ሆነው የሚመለከቱት ብዙ
ሴቶችም በዚያ ነበሩ ፤ እነርሱ ከገሊላ ጀም
ረው ኢየሱስን እያገለገሉ ይከተሉት የነበሩ
ናቸው ። 56 ከእነርሱም መካከል መግደላዊት
ማርያም ፡ የያዕቆብና የዮሴፍ እናት ማር
ያም ፡ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ይገኙባቸው
ነበር ።

ኢየሱስ ተቀበረ
(ማር. 15፡42-47፤ ሉቃ. 23፡50-56፤
ዮሐ. 19፡38-42)

57 በመሸ ጊዜ የአርማትያስ ሰው የሆነ
ዮሴፍ የሚባል አንድ ሀብታም ሰው ወደዚያ
መጣ ፤ እርሱም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ ፤
58 ይህ ሰው ወደ ጲላጦስ ሄዶና የኢየሱስን አስ
ከሬን ለመነ ፤ ጲላጦስም አስከሬኑ እንዲሰጠው
አዘዘ ። 59 ስለዚህ ዮሴፍ አስከሬኑን አውርዶ በን
ጹሕ ጨርቅ ከፈነው ። 60 ከአለት ተወቅሮ በተዘ
ጋጀው በራሱ አዲስ መቃብር ውስጥ ቀበረው ፤
ከዚህ በኋላ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ የመቃብ
ሩን በር ዘጋና ሄደ ። 61 መግደላዊት ማርያምና
ሌላይቱ ማርያም እዚያ በመቃብሩ ፊት ለፊት
ተቀምጠው ነበር ።
62 በማግሥቱ ቅዳሜ የካህናት አለቆችና ፈሪ
ሳውያን በአንድነት ወደ ጲላጦስ ሄዱና እንዲህ
አሉት ፡ 63 “ጌታ ሆይ! ያ አሳሳች ገና በሕይ
ወቱ ሳለ ‘ከሦስት ቀን በኋላ ከሞት እነሣለሁ’
ያለው ትዝ አለን ። 64 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ
ሄደው እንዳይሰርቁትና ለሕዝቡም ‘እነሆ
ከሞት ተነሥቶአል’ እንዳይሉ መቃብሩ እስከ
ሦስት ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ ፤ አለበለዚ
የመጨረሻው ማሳሳት ከመጀመሪያው ይልቅ
የባሰ ይሆናል ።” 65 ጲላጦስም “እነሆ ጠባቂ
ዎች አሉላችሁ ፤ ሂዱና በምትፈልጉት ዐይነት
አስጠብቁ” አላቸው ። 66 ስለዚህ ሄደው ድንጋ
ዩን በማኅተም አሸጉና መቃብሩን በወታደሮች
አስጠበቁ ።

27፡34 ፡- መዝ. 69፡21 ። 27፡35 ፡- መዝ. 22፡18 ። 27፡39 ፡- መዝ. 22፡7 ፤ 109፡25 ። 27፡40 ፡- ማቴ. 26፡61 ፤
ዮሐ. 2፡19 ። 27፡43 ፡- መዝ. 22፡8 ። 27፡46 ፡- መዝ. 22፡1 ። 27፡48 ፡- መዝ. 69፡21 ። 27፡51 ፡- ዘጸ. 26፡31-33 ።
27፡55-56 ፡- ሉቃ. 8፡2-3 ። 27፡63 ፡- ማቴ. 16፡21 ፤ 17፡23 ፤ 20፡19 ፤ ማር. 8፡31 ፤ 9፡31 ፤ 10፡33-34 ፤
ሉቃ. 9፡22 ፤ 18፡31-33 ።

ምዕራፍ 28

ኢየሱስ ከሞት ተነሣ
(ማር. 16፥1-10፤ ሉቃ. 24፥1-12፤
ዮሐ. 20፥1-10)

[1] ሰንበት ካለፈ በኋላ እሑድ ጠዋት በማለዳ
መሣደላዊቷ ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃ
ብሩን ለማየት ሄዱ ። [2] እነሆ በድንገት ታላቅ
የምድር መናወጥ ሆነ ፤ የእግዚአብሔር መል
አክ ከሰማይ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድን
ጋይ አንከባለለና በላዩ ተቀመጠ ። [3] የመልአኩ
ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር ፤ ልብሱም
እንደ በረዶ ነጭ ነበረ ። [4] ጠባቂዎቹ መልአኩን
ከመፍራት የተነሣ በመንቀጥቀጥ እንደ በድን
ሆኑ ፤ [5] መልአኩ ግን ሴቶቹን እንዲህ አላ
ቸው ፥ “እናንተስ አትፍሩ ፤ የተሰቀለውን ኢያ
ሱስን እንደምትፈልጉ ዐውቃለሁ ፤ [6] እርሱ
‘ከሞት እነሣለሁ’ ብሎ እንደተናገረው ተነሥቶ
አልና በዚህ የለም ፤ ተኝቶበት የነበረውን ስፍራ
ኑና እዩ ። [7] እንግዲህ በፍጥነት ሄዳችሁ ለደቀ
መዛሙርቱ ‘ከሞት ተነሥቶአል ፤ እነሆ ወደ
ገሊላ ቀድሞአችሁ ይሄዳል ፤ በዚያ ታገኙታላ
ችሁ’ ብላችሁ ንገሩአቸው ፤ እነሆ ነግሬአችኋ
ለሁ ።”

[8] ከዚህ በኋላ ሴቶቹ በፍርሃትና በታላቅ
ደስታ ከመቃብሩ በፍጥነት ሄዱ ፤ ለደቀ መዛ
ሙርቱም ሊነግሩ ሮጡ ።

[9] ኢየሱስ በመንገድ አገኛቸውና “ሰላም ለእ
ናንተ ይሁን” አላቸው ። እነርሱም ወደ እርሱ
ቀረቡና እግሮቹን ይዘው ሰገዱለት ። [10] በዚያን
ጊዜ ኢየሱስ “አትፍሩ! ሂዱና ወደ ገሊላ እን
ዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሩአቸው ፤ የሚያዩኝም
በዚያ ነው” አላቸው ።

[11] ሴቶቹም ሲሄዱ ሳለ ከወታደሮቹ አንዳን
ዶቹ ወደ ከተማ ሄደው የሆነውን ነገር ሁሉ
ለካህናት አለቆች ነገሩ ። [12] የካህናት አለቆች
ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብስበው ከተማከሩ
በኋላ ለወታደሮቹ ብዙ ገንዘብ ሰጡአቸውና
እንዲህ አሉዋቸው ፥ [13] “‘እኛ ተኝተን ሳለ
ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት’
ብላችሁ ለሕዝቡ ንገሩ ። [14] ይህን ነገር
ገዥው የሰማ እንደሆነ እኛ ጕዳዩን አስረድ
ተን በእናንተ ላይ ችግር እንዳይደርስባችሁ
እናደርጋለን ።”

[15] ስለዚህ ወታደሮቹ ገንዘቡን ተቀብለው
ልክ እንደተነገራቸው አደረጉ ፤ ይህም ነገር
እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁዳውያን ዘንድ ይነገ
ራል ።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ
(ማር. 16፥14-18፤ ሉቃ. 24፥36-49፤
ዮሐ. 20፥19-23፤ ሐ.ሥ. 1፥6-8፤
1 ቆሮ. 15፥3-8)

[16] ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ
እንዲሄዱ ወደ አመለከታቸው ፥ በገሊላ ወደሚ
ገኘው ተራራ ሄዱ ። [17] ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት ፤
አንዳንዶቹ ግን ተጠራጠሩ ፤ [18] ኢየሱስ ወደ
እነርሱ ቀረበና እንዲህ አላቸው ፥ “ሥልጣን
ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል ፤ [19] እንግ
ዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱ ፤ በአብና በወ
ልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋ
ቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጉአቸው ፤
[20] ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አስተምሩ
አቸው ፤ እነሆ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ።”

28፥16 ፡- ማቴ. 26፥32 ፤ ማር. 14፥28 ። 28፥19 ፡- ሐ.ሥ. 1፥8 ።

ማርቆስ የጻፈው

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል

መግቢያ

የማርቆስ ወንጌል “ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ቃል መጀመሪያ ነው” በማለት ይነግል ፤ በዚህ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ የሥራና የሥልጣን ሰው በመሆን ቀርቦ አል ፤ ሥልጣኑም በትምህርቱ ፤ በአጋንንት ላይ ባለው ኀይልና የሰውን ኃጢአት ይቅር በማለቱ ታይቶአል ፤ ኢየሱስ “ሰዎችን ከኃጢአት ባርነት ነፃ በማውጣት ሕይወቱን ቤዛ አድርጌ ለመስ ጠት የመጣሁ የሰው ልጅ ነኝ” በማለት ራሱ ተናግሮአል ።

ማርቆስ የኢየሱስን ታሪክ ያቀረበው ቀጥተኛና ኀይልን በተሞላ መንገድ ሲሆን ያተኰረውም በኢየሱስ ቃልና ትምህርት ላይ ሳይሆን ባከናወናቸው ድንቅ ሥራዎች ላይ ነበር ፤ ስለ አጥማ ቂው ዮሐንስ ታሪክ ፥ ስለ ኢየሱስ ጥምቀትና ፈተና አጠር ያለ መግቢያ ከሰጠ በኋላ ጸሐፊው ስለ ኢየሱስ የማስተማርና የመፈወስ አገልግሎቱ ይተነትናል ። ከጊዜ በኋላ የኢየሱስ ተከታዮች ኢየሱስን በበለጠ ሁኔታ እያወቁ በሄዱ መጠን ፥ የኢየሱስ ተቃዋሚዎችም ይበልጡን እየጠሉት ሄዱ ፥ የመጨረሻዎቹ ምዕራፎች በኢየሱስ ሕይወት በመጨረሻው ሳምንት ውስጥ ስለተፈጸ ሙት ድርጊቶች ፤ በተለይም ስለ ስቅለቱና ስለ ትንሣኤው የሚተርኩ ናቸው ።

በወንጌሉ መጨረሻ ላይ በቅንፍ የተመለከቱት ሁለት ክፍሎች በአንዳንድ ቅጂዎች ብቻ የሚገኙ ናቸው ።

ምዕራፍ 1

የአጥማቂው ዮሐንስ ወዋጅ
(ማቴ. 3፥1-12፤ ሉቃ. 3፥1-18፤ ዮሐ. 1፥19-28)

[1] ይህ የእግዚአብሔር ልጅ[1*] የኢየሱስ ክርስ
ቶስ የምሥራች ቃል መጀመሪያ ነው ፤ [2] እንዲ
ሁም በነቢዩ ኢሳይያስ ፥

“እነሆ መንገድህን የሚጠርግ
መልእክተኛዬን በፊትህ አስቀድሜ
እልካለሁ ፤

[3] ይህም ፥
‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ ፤
ጥርጊያውንም አቅኑ’ እያለ
በበረሓ የሚጮኽ ሰው ድምፅ”

ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።

[4] ስለዚህ አጥማቂው ዮሐንስ[2*] “የኃጢአትን
ይቅርታ እንድታገኙ ንስሓ ገብታችሁ ተጠ
መቁ” በማለት በበረሓ እያወጀ መጣ ። [5] የይ
ሁዳ አገር ሰዎችና የኢየሩሳሌም ከተማ ነዋሪ
ዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር ፤ ኃጢአታ
ቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ
እጅ ይጠመቁ ነበር ።

[6] ዮሐንስ ከግመል ጠጕር የተሠራ ልብስ
ይለብስ ነበር ፤ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ
ነበር ፤ ምግቡም አንበጣና የበረሓ ማር ነበር ።
[7] እንዲህም ይል ነበር ፥ “ጐንበስ ብዬ የጫማ
ውን ማሠሪያ ለመፍታት እንኳን የማልበቃ ፥
ከእኔ የሚበልጥ ከእኔ በኋላ ይመጣል ፤ [8] እኔ
በውሃ አጠምቃችኋለሁ ፤ እርሱ ግን በመንፈስ
ቅዱስ ያጠምቃችኋል ።”

የኢየሱስ መጠመቅና መፈተን
(ማቴ. 3፥13-17፤ 4፥1-11፤
ሉቃ. 3፥21-22፤ 4፥1-13)

[9] በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በገሊላ አገር ከምት
ገኝ ከናዝሬት ከተማ መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ። [10] ኢየሱስ ከውሃው
እንደወጣ ወዲያውኑ ሰማይ ሲከፈትና መንፈስ
ቅዱስም በርግብ አምሳል ሆኖ በእርሱ ላይ ሲወ
ርድ አየ ። [11] በዚያን ጊዜ “አንተ የተወደድህ
ልጄ ነህ ፤ በአንተ ደስ ይለኛል” የሚል ድምፅ
ከሰማይ መጣ ።

[12] ወዲያውኑ ወደ በረሓ እንዲሄድ መንፈስ
ቅዱስ አነሣሣው ። [13] በዚያም በረሓ በሰይጣን

1* 1፥1 አንዳንድ ቅጂዎች “የእግዚአብሔር ልጅ” የሚል ቃል አይጨምሩም ። 2* 1፥4 አንዳንድ ቅጂዎች “አጥማቂው ዮሐንስ” በማለት ፈንታ “ዮሐንስ እያጠመቀ” ይላሉ ።
1፥2 ፡- ሚል. 3፥1 ። 1፥3 ፡- ኢሳ. 40፥3 ። 1፥6 ፡- 2ነገ. 1፥8 ። 1፥11 ፡- ዘፍ. 22፥2 ፤ መዝ. 2፥7 ፤ ኢሳ. 42፥1 ፤ ማቴ. 3፥17 ፤ 12፥18 ፤ ማር. 9፥7 ፤ ሉቃ. 3፥22 ።

እየተፈተነ እርባ ቀን ቆየ ፤ ከአራዊትም ጋር ነበረ ፤ መላእክትም አገለገሉት ።

ኢየሱስ አራት ዓሣ አጥማጆችን ጠራ
(ማቴ. 4፡12-22፤ ሉቃ. 4፡14-15፤ 5፡1-11)

14 ዮሐንስም ተይዞ ወደ እስር ቤት ከገባ
በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የምሥራች ቃል
እያስሠረ ወደ ገሊላ መጣ ። 15 ሲያስሠርም
“ጊዜው ደረሰ ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀር
ባለችና ንስሓ ግቡ ፤ በዚህ የምሥራች ቃል
እመኑ” ይል ነበር ።
16 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ
ያልፍ ነበር ፤ ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ
ዓሣ አጥማጆች ስለነበሩ መረባቸውን ወደ ባሕር
ሲጥሉ አያቸው ። 17 ኢየሱስም “ኑ ተከተሉኝ ፤
እኔ ሰዎችን እንድታጠምዱ አደርጋችኋለሁ!”
አላቸው ። 18 እነርሱም ወዲያውኑ መረባቸውን
ትተው ተከተሉት ።
19 ከዚያም ጥቂት አለፍ እንዳለ ሌሎች
ሁለት ወንድማማቾችን አየ ፤ እነርሱም የዘብዴ
ዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ነበሩ ፤ እነርሱ
በጀልባ ላይ ሆነው መረባቸውን ያበጁ ነበር ፤
20 ኢየሱስ ወዲያውኑ ጠራቸው ፤ እነርሱም አያ
ሱስን ለመከተል አባታቸውን ዘብዴዎስን ከሠራ
ተኞቹ ጋር በጀልባው ላይ ትተውት ሄዱ ።

ርኵስ መንፈስ ያደረበት ሰው ዳነ
(ሉቃ. 4፡31-37)

21 አልፈውም ወደ ቅፍርናሆም ከተማ
ደረሱ ፤ በሚቀጥለውም ሰንበት ኢየሱስ የአይ
ሁድ ጸሎት ቤት ወደ ሆነው ወደ ምኵራብ
ገብቶ ማስተማር ጀመረ ። 22 ኢየሱስ ፥ የሙሴ
ሕግ መምህራን እንደሚያስተምሩት ዐይነት
ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው
ነበር ፤ ስለዚህ የሰሙት ሁሉ በትምህርቱ ተደ
ነቁ ።
23 በምኵራባቸው ርኵስ መንፈስ ያደረበት
ሰው ነበረ ፤ እርሱ እንዲህ ሲል ጮኸ ፥ 24 “የና
ዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! እኛ ከእንተ ጋር ምን ግን
ኙነት አለን? ልታጠፋን መጣህን? አንተ ማን
እንደሆንህ እኔ ዐውቃለሁ ፤ አንተ እኮ የእግዚአ
ብሔር ቅዱስ ነህ ።”
25 ኢየሱስም ርኵሱን መንፈስ “ዝም በል!
ከእርሱ ውጣ!” ብሎ ገሠጸው ።
26 ርኵሱ መንፈስ ሰውየውን ጥሎ ካንፈራገ
ጠው በኋላ በታላቅ ድምፅ እየጮኸ ከእርሱ
ወጣ ። 27 ሰዎቹም ሁሉ ተደንቅው “ይህ ነገር
ምንድን ነው? ርኵሳን መናፍስትን በሥልጣን
ያዛል ፤ እነርሱም ይታዘዙለታል ፤ ይህ አዲስ
ትምህርት አይደለምን?” እያሉ እርስ በርሳ
ቸው ተጠያየቁ ።
28 ወዲያውኑ የኢያሱስ ዝና በየስፍራው በገ
ሊላ ዙሪያ ሁሉ ተሰማ ።

ኢየሱስ ብዙ ሕመምተኞችን ፈወሰ
(ማቴ. 8፡14-17፤ ሉቃ. 4፡38-41)

29 በዚያኑ ጊዜ ኢየሱስ ከምኵራብ ወጥቶ
ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና እንድ
ያስ ቤት ገባ ። 30 በቤት ውስጥ የስምዖን ዐማት
በንዳድ ሕመም አተኩሶአት ተኝታ ነበር ፤ ስለ
እርስዋም መታመም ነገሩት ። 31 ኢየሱስም
ወደ እርስዋ ቀረበና እጅዋን ይዞ አስነሣት ፤
ትኩሳቱ ወዲያው ለቀቃት ፤ ተነሥታም አስተና
ገደቻቸው ።
32 ፀሐይ ጠልቃ በመሸ ጊዜ ሰዎች በሽተኞ
ችንና በአጋንንት የተያዙትን ሁሉ ወደ ኢየሱስ
ማምጣት ጀመሩ ። 33 የከተማው ሰዎች ሁሉ
በደጅ ተሰብስበው ነበር ። 34 ኢየሱስ በልዩ ልዩ
በሽታ የሚሠቃዩትን ብዙ ሰዎች ፈወሰ ፤ ብዙ
አጋንንትንም አስወጣ ፤ አጋንንቱም እርሱ ማን
እንደሆነ ያውቁ ነበር ፤ ይሁን እንጂ እንዲናገሩ
አልፈቀደላቸውም ።

ኢየሱስ በገሊላ አስተማረ
(ሉቃ. 4፡42-44)

35 ሊነጋ ሲል ኢየሱስ በማለዳ ተነሥቶ
ወጣና ለመጸለይ ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ
ሄደ ፤ 36 ስምዖንና ጓደኞቹ ተከትለው እርሱን
ፍለጋ ሄዱ ። 37 ባገኙትም ጊዜ “ሰዎች ሁሉ
ይፈልጉሃል እኮ” አሉት ።
38 ኢየሱስም “እኔ የመጣሁት ለማስተማር
ስለሆነ እንዳስተምር በቅርብ ወዳሉት መንደ
ሮች እንሂድ” አላቸው ።
39 ስለዚህ በየምኵራቦቻቸው እያስተማረና
አጋንንትን እያስወጣ በገሊላ ሁሉ ይዘዋወር
ነበር ።

ኢየሱስ ለምጻሙን* ሰው አነጻ
(ማቴ. 8፡1-4፤ ሉቃ. 5፡12-17)

40 አንድ ለምጻም ወደ ኢየሱስ መጣና በእ
ግሩ ሥር ተንበርክኮ “ብትፈቅድስ ልታነጻኝ
ትችላለህ” ሲል ለመነው ።
41 ኢየሱስም ራራለትና እጁን ዘርግቶ እየዳሰ
ሰው “ፈቅጃለሁ ፥ ንጻ” አለው ። 42 ሰውየውም
ከለምጹ ወዲያውኑ ነጻ ። 43 ኢየሱስ ሲያሰናብ
ተው እንዲህ ብሎ በብርቱ አዘዘው ፥ 44 “ይህ
ንን ነገር ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ ፤ ነገር
ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ፤ ለሕዝቡም

3* 1:40 ለምጽ ፡- እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ ቃሉ በሰውነት ላይ የሚታይን ልዩ ልዩ ዐይነት ተላላፊ የቆዳ በሽታ ሁሉ ያመለክታል (ዘሌ. 13 ተመልከት) ።

1:15 ፡- ማቴ. 3:2 ። 1:22 ፡- ማቴ. 7:28-2 ። 1:39 ፡- ማቴ. 4:23 ፡ 9:35 ። 1:44 ፡- ዘሌ. 4:1-32 ።

ምስክር እንዲሆን ስለ መዳንህ ሙሴ ያዘዘውን
መሥዋዕት አቅርብ ።”
45 ይሁን እንጂ ሰውየው ከዚያ ወጥቶ ይህን
ነገር ለሰው ሁሉ ማውራት ጀመረ ። በዚህም
ምክንያት ኢየሱስ ወደ ማናቸውም ከተማ በግ
ልጥ መግባት አልቻለም ። ነገር ግን ከከተማ
ውጪ ሰው በሌለበት ቦታ ይኖር ነበር ፤ ሰዎ
ችም ከየስፍራው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር ።

ምዕራፍ 2

ኢየሱስ ሽባውን ሰው ፈወሰ
(ማቴ. 9፡1-8፤ ሉቃ. 5፡17-26)

1 ከጥቂት ቀን በኋላ ኢየሱስ ወደ ቅፍርና
ሆም ተመልሶ መጣ ፤ እዚያ በቤት ውስጥ
መሆኑ ተሰማ ። 2 በደጅ ያለው ስፍራ እንኳ እስ
ኪጠብ ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ ፤ ቃሉንም
ይነግራቸው ነበር ። 3 በዚያን ጊዜ አራት ሰዎች
አንድ ሽባ ሰው ተሸክመው ወደ እርሱ
አመጡ ። 4 ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ሽባውን
ወደ ኢየሱስ ማቅረብ ቢያቅታቸው የቤቱን
ጣራ ኢየሱስ ባለበት በኩል ሸንቆረው ሽባውን
ከነአልጋው አወረዱት ። 5 ኢየሱስም እምነታቸ
ውን አይቶ ሽባውን “አንተ ልጅ ኃጢአትህ
ተደምስሶልሃል” አለው ።
6 ከሙሴ ሕግ መምህራን አንዳንዶቹ በዚያ
ተቀምጠው ነበር ፤ እነርሱ በልባቸው እንዲህ
አሉ ፥ 7 “ይህ ሰው ለምን እንዲህ ያለ ስድብ
በእግዚአብሔር ላይ ይናገራል? ከአንዱ እግዚአ
ብሔር በቀር ኃጢአትን መደምሰስ የሚችል
ማን ነው?”
8 ወዲያውኑ ኢየሱስ የልባቸውን አሳብ በመ
ንፈሱ ዐውቆ እንዲህ አላቸው ፥ “ስለምን በልባ
ችሁ ይህን ታስባላችሁ? 9 ሽባውን ፣ ‘ኃጢአትህ
ተደምስሶልሃል’ ከማለትና ፥ ‘ተነሥተህ አልጋ
ህን ተሸክምና ሂድ’ ከማለት የትኛው ይቀላል?
10 ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን
ለመደምሰስ ሥልጣን ያለው መሆኑን እንድታ
ውቁ” ብሎ ሽባውን ፥ 11 “ተነሥ ፥ አልጋህን
ተሸክምና ወደ ቤትህ ሂድ እልሃለሁ” አለው ።
12 ሽባውም ወዲያውኑ ተነሣና አልጋውን
ተሸክሞ በሰዎቹ ሁሉ ፊት ወጣ ። ስለዚህም
ሰዎቹ ሁሉ ተደንቀው “እንዲህ ያለ ነገር ኩቶ
እይተን እናውቅም” እያሉ እግዚአብሔርን
አመሰገኑ ።

ኢየሱስ ሌዊን ጠራ
(ማቴ. 9፡9-13፤ ሉቃ. 5፡27-32)

13 ኢየሱስም እንደገና ወደ ባሕሩ አጠገብ
ሄደ ፤ ሕዝቡም ሁሉ ተሰብስበው ወደ እርሱ
መጡና አስተማራቸው ። 14 በዚያም ሲያልፍ
ሳለ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ የነበረውን
የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን አይቶ “ተከተለኝ”
አለው ፤ እርሱም ተነሥቶ ተከተለው ።
15 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሌዊ ቤት በማእድ
ተቀምጦ ነበር ፤ ብዙ ሰዎችም ተከትለውት ስለ
ነበር ፥ ከእነርሱ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች
ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በገበታ ቀር
በው ነበር ። 16 ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ የሙሴ
ሕግ መምህራን ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተ
ኞች ጋር ሲበላ አይተው “ከቀራጮችና ከኃጢ
አተኞች ጋር የሚበላውና የሚጠጣው ስለምን
ድን ነው?” በማለት ደቀ መዛሙርቱን ጠየቁአ
ቸው ።
17 ኢየሱስም ይህን ሰምቶ “ለበሽተኞች
እንጂ ለጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም ፤
እኔም የመጣሁት ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ
ለመጥራት እንጂ ጻድቃንን ወደ ንስሓ ለመጥ
ራት አይደለም” አላቸው ።

ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 9፡14-17፤ ሉቃ. 5፡33-39)

18 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን
ይጾሙ ነበር ። ስለዚህ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥ
ተው “የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት
ይጾማሉ ፤ የእንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾ
ሙት ስለምንድን ነው?” አሉት ።
19 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “ሙሽራው
ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች መጾም ይገባቸዋ
ልን? አይደለም ፤ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ
መጾም አይገባቸውም ። 20 ነገር ግን ሙሽራው
ከእነርሱ የሚለይበት ቀን ይመጣል ፤ በዚያን
ጊዜ ይጾማሉ ።
21 “ባረጀ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ የሚጥፍ
የለም ፤ ይህ ቢደረግ ግን አዲሱ ዕራፊ አሮጌውን
ልብስ ይቀደዋል ፤ ቀዳዳውም ከበፊቱ የባሰ ይሆ
ናል ። 22 እንዲሁም በአረጀ የወይን ጠጅ አቁ
ማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም ፤ ቢደ
ረግ ግን የወይን ጠጁ አቁማዳውን ያፈነዳዋል ፤
የወይን ጠጁም ይፈሳል ፥ አቁማዳውም ከንቱ
ይሆናል ። ስለዚህ ለአዲስ የወይን ጠጅ ፥ አዲስ
አቁማዳ ያስፈልገዋል ።”

ስለ ሰንበት የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 12፡1-8፤ ሉቃ. 6፡1-5)

23 በሰንበት ቀን ኢየሱስ በስንዴ እርሻ መካ
ከል ያልፍ ነበር ። ደቀ መዛሙርቱ ሲሄዱ የስ
ንዴ እሸት መቅጠፍ ጀመሩ ። 24 ፈሪሳውያንም
“ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ያልተፈቀደውን
ስለምን ያደርጋሉ?” ሲሉ ጠየቁት ።
25 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“ዳዊት ከተከታዮቹ ጋር በተራበና በተቸገረ

2:23 ፡- ዘጸ. 23:25 ። 2:25-26 ፡- 1ሳሙ. 21:1-6 ።

ጊዜ ምን እንዳደረገ አላነበባችሁምን? [26]አብያ
ታር ሊቀ ካህናት በነበረበት ዘመን እርሱ ወደ
እግዚአብሔር ቤት ገብቶ ከካህናት በቀር ለሌ
ሎች መብላት ያልተፈቀደውን የተቀደሰውን
የመባ ኅብስት በላ ፤ ከእርሱም ጋር ለነበሩት
ሰዎች ሰጣቸው ።”
[27]ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፡ “ሰን
በት እኮ ስለ ሰው ተሠራ እንጂ ሰው ስለ ሰን
በት አልተፈጠረም ። [28]የሰው ልጅ ለሰንበትም
ጌታዋ ነው ።”

ምዕራፍ 3

እጁ ሽባው ሰው

(ማቴ. 12፡9-14፤ ሉቃ. 6፡6-11)

[1]ኢየሱስ ወደ ምኵራብ እንደገና ገባ ፤ እዚ
ያም አንድ እጁ ሽባ ሰው ነበር ። [2]ኢየሱስን
ሊከሱት የፈለጉ ሰዎች “እስቲ በሰንበት ቀን
ይፈውሰው እንደሆን እንይ” ብለው ይጠባበቁት
ነበር ። [3]ኢየሱስም እጁ ሽባውን ሰው “ና በመ
ካከል ቁም!” አለው ። [4]ከዚያም በኋላ እንዲህ
አላቸው ፡ “ለመሆኑ በሰንበት ቀን የተፈቀደው
መልካም ማድረግ ነውን ወይስ ክፉ? ነፍስን
ማዳን ነውን ወይስ ማጥፋት?” እነርሱ ግን
ዝም አሉ ። [5]ኢየሱስም ስለ ልባቸው ድንዝዝ
አዝኖ በዙሪያው ያሉትን በቍጣ ተመለከተና
ሰውየውን “እጅህን ዘርጋ” አለው ። እርሱም
በዘረጋ ጊዜ እጁ ዳነለት ። [6]ወዲያውኑ ፈሪሳው
ያን ወጥተው እንዴት አድርገው ኢየሱስን እን
ደሚያጠፉት ከሄሮድስ ሰዎች ጋር ተማከሩ ።

ሕዝቡ በባሕሩ አጠገብ ወደ ኢየሱስ ተሰበሰቡ

[7]ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ገሊላ
ባሕር ሄደ ። [8]ያደርገው የነበረውንም ነገር
ሁሉ በሰሙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተከተሉት ፤ እነ
ርሱ ግን ከገሊላ ፡ ከይሁዳ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ከኤዶምያስ ፡ በዮርዳኖስ ማዶ ካለው አገርና
እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና ከተሞች የመጡ
ነበሩ ። [9]ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሰዎች እንዳይ
ጋፉት ጀልባ እንዲያቀርቡለት ደቀ መዛሙር
ቱን አዘዛቸው ። [10]ብዙ ሰዎችን ከበሽታ ፈውሷ
ቸው ነበርና በሕመም የሚሠቃዩ ሁሉ ሊነኩት
ፈልገው ይረባረቡበት ነበር ። [11]ርኵሳን መናፍ
ስትም ሲያዩት በፊቱ እየተደፉ ፡ “አንተ የእግ
ዚአብሔር ልጅ ነህ!” እያሉ ይጮኹ ነበር ።
[12]እርሱ ግን ማንነቱን እንዳይገልጹ በብርቱ
ገሠጻቸው ።

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መረጠ

(ማቴ. 10፡1-4፤ ሉቃ. 6፡12-16)

[13]ኢየሱስ ወደ ተራራ በወጣ ጊዜ የፈለጋቸ
ውን ወደ እርሱ ጠራ ፤ እነርሱም ወደ እርሱ
ቀረቡ ። [14]ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ፡ ለማስተማ
ርም እንዲልካቸው ዐሥራ ሁለቱን መርጦ
“ሐዋርያት” ብሎ ሰየማቸው ። [15]አጋንንትን
እንዲያስወጡም ሥልጣን ሰጣቸው ።
[16]የተመረጡትም ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
እነዚህ ናቸው ፡- ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው ስም
ዖን ፡ [17]ቦአኔርጌስ ወይም የነጐድጓድ ልጆች
ብሎ የሰየማቸው የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና
ዮሐንስ ፡ [18]እንድርያስ ፡ ፊልጶስ ፡ በርቶሎሜ
ዎስ ፡ ማቴዎስ ፡ ቶማስ ፡ የአልፍዮስ ልጅ ያዕ
ቆብ ፡ ታዴዎስ ፡ ተቀናቃኙ ስምዖን ፡ [19]ኢየሱ
ስን አሳልፎ የሰጠውም አስቆሮታዊው ይሁዳ ።

ኢየሱስና ብዔልዜቡል

(ማቴ. 12፡22-32፤ ሉቃ. 11፡14-23፤ 12፡10)

[20]ከዘዚህም በኋላ ኢየሱስ ወደ ቤት ገባ ።
ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ እህል መብላት እንኳ
እስኪያቅታቸው ድረስ እንደገና ብዙ ሰዎች
ተሰበሰቡ ። [21]“ኢየሱስ አብዶአል” ሲባል በመ
ስማታቸው ዘመዶቹ ሊይዙት ወደ እርሱ
መጡ ።
[22]ከኢየሩሳሌም የወረዱ የሙሴ ሕግ መምህ
ራን “እርሱ ብዔልዜቡል አለበት ፡ አጋንንት
ንም የሚያወጣው በዚሁ የአጋንንት አለቃ በሆ
ነው በብዔልዜቡል ነው” እያሉ ያወሩበት
ነበር ።
[23]ኢየሱስም እነርሱን ወደ እርሱ ጠርቶ
በምሳሌ እንዲህ አላቸው ፡ “ሰይጣን እንዴት
ሰይጣንን ሊያስወጣ ይችላል? [24]አንድ መንግ
ሥት ተከፋፍሎ እርስ በርሱ የሚጋጭ ከሆነ ያ
መንግሥት ጸንቶ መቆም አይችልም ። [25]እንዲ
ሁም አንድ ቤተሰብ እርስ በርሱ ከተለያየ ጸንቶ
መኖር አይችልም ፤ [26]ስለዚህ ሰይጣን እርስ
በርሱ ከተለያየ ይወድቃል እንጂ መቆም አይች
ልም ።
[27]“እንዲሁም ወደ አንድ ኀይለኛ ሰው
ቤት ገብቶ አስቀድሞም ኀይለኛውን ሰው ሳያስር
ንብረቱን መዝረፍ የሚችል የለም ።
[28]“በእውነት እላችኋለሁ ፡ ሰዎች የሚሠ
ሩት ኃጢአትና የሚናገሩት ስድብ ሁሉ ይቅር
ይባልላቸዋል ። [29]ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ
ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ የዘላለም ዕዳ
ይሆንበታል እንጂ ከቶ ኃጢአቱ ይቅር አይባልለ
ትም ።” [30]ኢየሱስ ይህን የተናገረው “ርኵስ
መንፈስ አለበት” በማለታቸው ነበር ።

የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

(ማቴ. 12፡46-50፤ ሉቃ. 8፡19-21)

[31]የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ ወደ እርሱ
መጡ ፤ በውጪም ቆመው ወደ እርሱ ሰው
ላኩና አስጠሩት ። [32]በዙሪያውም ተቀምጠው

2፡26 ፡- ዘሌ. 24፡9 ። 3፡9-10 ፡- ማር. 4፡1 ፡ ሉቃ. 5፡1-3 ። 3፡22 ፡- ማቴ. 9፡34 ፡ 10፡25 ። 3፡29 ፡- ሉቃ. 12፡10 ።

የነበሩ ሰዎች “እነሆ እናትህና ወንድሞችህ እኅ
ቶችህም በውጪ ቆመው ይፈልጉሃል” ብለው
ነገሩት ።
[33]እርሱም “እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ
እነማን ናቸው?” ሲል መለሰ ። [34]በዙሪያው
ተቀምጠው ወደነበሩት እየተመለከተ “እነሆ
እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው ፤ [35]የእግዚአ
ብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ ፡ እርሱ ወንድ
ሜም ፡ እኅቴም እናቴም ነው” አለ ።

ምዕራፍ 4

የዘሪው ምሳሌ

(ማቴ. 13፡10-17፤ ሉቃ. 8፡4-8)

[1]ኢየሱስ እንደገና በባሕሩ አጠገብ ማስተ
ማር ጀመረ ። እጅግ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ
መጥተው በመሰብሰባቸው እርሱ በባሕሩ ላይ
በነበረው ጀልባ ገብቶ ተቀመጠ ፤ ሕዝቡም
ሁሉ በባሕሩ ዳርቻ ነበሩ ። [2]ብዙ ነገሮችንም
በምሳሌ አስተማራቸው ፤ ሲያስተምራቸውም
እንዲህ አላቸው ፡ [3]“ስሙ ፤ እነሆ ገበሬው
ዘሩን ለመዝራት ወጣ ፤ [4]ሲዘራ ሳለ አንዳንዱ
ዘር በመንገድ ዳር ወደቀ ፤ ወፎችም መጥተው
በሉት ። [5]ሌላው ዘር ብዙ ዐፈር በሌለበት በጭ
ንጫማ ቦታ ላይ ወደቀ ፤ ቦታውም ብዙ ዐፈር
ስላልነበረው ወዲያው በቀለ ፤ [6]ይሁን እንጂ
ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጠወለገ ፤ ሥር ስላልነበረ
ውም ደረቀ ። [7]ሌላው ዘር በእሾኽ ቍጥቋጦ
መካከል ወደቀ ፤ እሾኹም ባደገ ጊዜ ስላነቀው
ያለ ፍሬ ቀረ ። [8]ሌላው ዘር በመልካም መሬት
ላይ ወድቆ በቀለ ፤ ቡቃያውም አድጎ ፍሬ
ሰጠ ፤ አንዱ ሠላሳ አንዱ ስልሳ ፡ አንዱም መቶ
አፈራ ።”
[9]ቀጥሎም ኢየሱስ “ሰሚ ጆሮ ያለው
ይስማ” አለ ።

ኢየሱስ በምሳሌዎች የተናገረበት ምክንያት

(ማቴ. 13፡10-17፤ ሉቃ. 8፡9-10)

[10]ኢየሱስ ብቻውን በሆነ ጊዜ ፡ ይከተሉት
የነበሩ ሰዎችና ዐሥራ ሁለቱም ስለ ምሳሌዎቹ
ትርጕም ጠየቁት ። [11]እርሱም እንዲህ አላ
ቸው ፡ “ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት
ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል ፤ በውጪ
ላሉት ግን ፡ ሁሉ ነገር በምሳሌ ይነገራቸዋል ።
[12]ምክንያቱም ፡
‘እነርሱ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው
ኃጢአታቸው ይቅር
እንዳይባልላቸው ፡
እያዩ ልብ እንዳያደርጉ ፡
እየሰሙም እንዳያስተውሉ ነው ።’”

የዘሪው ምሳሌ ትርጕም

(ማቴ. 13፡18-23፤ ሉቃ. 8፡11-15)

[13]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፡ “እናንተም
ይህ ምሳሌ አይገባችሁምን? ታዲያ ሌሎችን
ምሳሌዎች ሁሉ እንዴት ልትረዱ ትችላላችሁ?
[14]ዘሪው ቃልን ይዘራል ፤ [15]ቃሉ በተዘራ ጊዜ
በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር የሚያመለክተው ፡
ቃሉን በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ ሰይጣን መጥቶ
በልባቸው የተዘራውን ቃል የሚወስድባቸውን
ሰዎች ነው ። [16]እንዲሁም በጭንጫማ ቦታ ላይ
የተዘራው የሚያመለክተው ፡ ቃሉን ሲሰሙ
ወዲያው በደስታ የሚቀበሉትን ሰዎች ነው ፤
[17]ግን እነርሱ ስጊዜው ነው እንጂ ሥር የላች
ውም ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በቃሉ ምክንያት
ችግር ወይም ስደት በደረሰባቸው ጊዜ ወዲያ
ውኑ ተሰናክለው ይወድቃሉ ። [18]በእሾኽ መካ
ከል የተዘራው ደግሞ የሚያመለክተው ፡ ቃሉን
የሚሰሙትን ሰዎች ነው ፤ [19]ይሁን እንጂ ፡
የዚህ ዓለም አሳብ ፡ የሀብት ፍቅርና ሌላውም
ከንቱ ምኞት ወደ ልባቸው ገብቶ ቃሉን ስለሚ
ያንቀው ያለ ፍሬ ይቀራል ። [20]በመልካም
መሬት የተዘራው ግን የሚያመለክተው ፡ ቃሉን
ሰምተው በማስተዋል የሚቀበሉትን ሰዎች
ነው ። እንዲህ ዐይነቱ አንዱ ሠላሳ አንዱ
ስልሳ ፡ አንዱም መቶ ፍሬ ያፈራል ።”

ስውር መብራት

(ሉቃ. 8፡16-18)

[21]ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፡
“ሰው መብራትን አብርቶ በእንቅብ ውስጥ
ወይም በአልጋ ሥር ያስቀምጠዋልን? የሚያስ
ቀምጠው ብርሃኑ በሚታይበት በመቅረዝ ላይ
አይደለምን? [22]እንዲሁም የተሸሸገ ሳይገለጥ ፡
የተሰወረም ሳይታወቅ አይቀርም ። [23]እንግዲህ
ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ ።”
[24]ደግሞም እንዲህ አላቸው ፡ “ስለምትሰ
ሙት ነገር ተጠንቀቁ ፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ
ለእናንተም ይሰፈርላችኋል ፤ በይበልጥም ይጨመ
ርላችኋል ። [25]ምክንያቱም ላለው ይሰጠዋል ፤
ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል ።”

የሚያድግ ዘር ምሳሌ

[26]ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፡ “የእግዚ
አብሔር መንግሥት በምድር ላይ ዘር የሚዘራ
ውን ሰው ትመስላለች ። [27]ሰውየው ሌሊት ይተ
ኛል ፤ ቀንም ይነቃል ፤ እንዴት እንደሆነም
ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ፤ ያድጋልም ። [28]ምድሪ
ቱም በገዛ ራስዋ በመጀመሪያ ቡቃያውን ፤ ቀጥ
ሎም ዛላውን ታሳያለች ፤ በኋላም በዛላው ፍሬ

4፡1 ፡- ሉቃ. 5፡1-3 ። 4፡12 ፡- ኢሳ. 6፡9-10 ። 4፡21 ፡- ማቴ. 5፡15 ፡ ሉቃ. 11፡33 ። 4፡22 ፡- ማቴ. 10፡26 ፡ ሉቃ. 12፡2 ። 4፡24 ፡- ማቴ. 7፡2 ፡ ሉቃ. 6፡38 ። 4፡25 ፡- ማቴ. 13፡12 ፡ 25፡29 ፡ ሉቃ. 19፡26 ።

ይገኛል ። [29] ሰብሉም በደረሰ ጊዜ መከር በመ
ሆኑ ሰውየው ወዲያውኑ ማጭድ ያዘጋጃል ።”

የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ
(ማቴ. 13፡31-34፤ ሉቃ. 13፡18-19)

[30] ኢየሱስ እንዲህ አለ ፥ “የእግዚአብሔርን
መንግሥት ከምን ጋር እናነጻጽራታለን? ወይስ
በምን ምሳሌ እንገልጻታለን? [31] የሰናፍጭን ዘር
ትመስላለች ፤ እርስዋ ስትዘራ በምድር ላይ
ካለው ዘር ሁሉ ያነሰች ናት ። [32] ከተዘራች
በኋላ ግን አድጋ ከአዝርዕት ሁሉ ትበልጣለች ፤
የሰማይ ወፎችም በሥርዋ መጠለል እስኪችሉ
ድረስ ታላላቅ ቅርንጫፎችን ታወጣለች ።”

[33] ኢየሱስም ሕዝቡ ማስተዋል በሚችልበት
መጠን እነዚህን በመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች
ቃሉን ይነግራቸው ነበር ። [34] ያለ ምሳሌም አያ
ስተምራቸውም ነበር ፤ ብቻቸውን ሲሆኑ ግን
ሁሉን ነገር ለደቀ መዛሙርቱ ያስረዳቸው
ነበር ።

ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ
(ማቴ. 8፡23-27፤ ሉቃ. 8፡22-25)

[35] በዚያኑ ቀን ማታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
“ወደ ባሕሩ ማዶ እንሻገር” አላቸው ። [36] ከሕዝ
ቡም ተለይተው ተሳፍርበት በነበረው ጀልባ ኢየ
ሱስን ይዘውት ሄዱ ፤ ሌሎችም ጀልባዎች አብ
ረው ነበሩ ። [37] ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ተነሥቶ
ውሃው በጀልባው እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ ጀልባ
ውን ይመታ ጀመር ። [38] በዚህ ጊዜ ኢየሱስ በጀል
ባው በኋለኛው ክፍል ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ
ነበር ፤ ደቀ መዛሙርቱ ቀስቀሱትና “መምህር
ሆይ! ስንጠፋ ዝም ትላለህን?” አሉት ።

[39] እርሱም ነቅቶ ነፋሱን ገሠጸው ፤ ባሕሩ
ንም “ዝም በል! ጸጥ በል!” አለው ፤ ነፋሱም
ወዲያውኑ ዝም አለ ፤ ታላቅ ጸጥታም ሆነ ።
[40] ኢየሱስም “እንዲህ የምትፈሩት ለምንድን
ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም?” አላ
ቸው ።

[41] እነርሱም በጣም ፈርተው “ኧረ ለመሆኑ
ነፋስና ባሕር እንኳ የሚታዘዙለት ይህ ማን
ነው?” ተባባሉ ።

ምዕራፍ 5

ርኵስ መንፈስ ያለበትን ሰው ኢየሱስ ፈወሰው
(ማቴ. 8፡28-34፤ ሉቃ. 8፡26-39)

[1] የገሊላን ባሕር በጀልባ ተሻግረው ወደ
ጌራሴኖን አገር ደረሱ ። [2] ኢየሱስ ከጀልባው
እንደወረደ በርኵስ መንፈስ የተያዘ አንድ ሰው
ወዲያውኑ ከመቃብር ቦታ ወጥቶ ተገናኘው ።
[3] ይህ ሰው በመቃብር ቦታ ይኖር ነበር ፤ ማንም
በሰንሰለት እንኳ አስሮ ሊያቆየው አይችልም
ነበር ። [4] ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት
ይታሰር ነበር ፤ ነገር ግን ሰንሰለቱን እየበጣጣ
ሰና እግር ብረቱንም እየሰባበረ ይዋል ነበር ፤
ስለዚህ ይዞ ሊያቆመው የሚችል ማንም አልነበ
ረም ። [5] ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን ባለማቋረጥ
በየመቃብር ቦታና በየተራራው ላይ እየተዘዋ
ወረ ይጮኽ ነበር ፤ ሰውነቱን በድንጋይ እየቈራ
ረጠ ያቆስል ነበር ።

[6] እርሱም ኢየሱስን በሩቅ ባየው ጊዜ ወደ
እርሱ ሮጦና በጉልበቱ ተንበርክኮ ሰገደለት ።
[7] በታላቅ ድምፅም እየጮኸ “አንተ የልዑል
እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ! እኔ ከአንተ
ጋር ምን ግንኙነት አለኝ? በእግዚአብሔር ስም
እለምንሃለሁ ፤ እባክህ አታሠቃየኝ” አለው ።
[8] ይህንንም ያለበት ምክንያት “አንተ ርኵስ
መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ!” ብሎ አዝዞት ስለነ
በር ነው ።

[9] ኢየሱስም “ስምህ ማን ነው?” ብሎ ጠየ
ቀው ፤ እርሱም “ብዙዎች ስለሆንን ስሜ ሠራ
ዊት ነው” ሲል መለሰለት ።

[10] ከዚያም አገር እንዳያባርራቸው አጥብቆ
ለመነው ።

[11] በዚያም ስፍራ በኮረብታዎች ጥግ ብዙ
የዐሳማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር ፤ [12] ስለዚህ “እባ
ክህ ወደ ዐሳማዎቹ ሄደን እንድንገባ ፍቀድ
ልን” ብለው ለመኑት ፤ [13] ኢየሱስም ፈቀደላ
ቸው ፤ ርኵሳን መናፍስቱም ከዚያ ሰው ወጥ
ተው በዐሳማዎቹ ውስጥ ገቡ ፤ ሁለት ሺ የሚያ
ህሉ ዐሳማዎች ከገደሉ በመንደርደር ወርደው
በባሕሩ ውስጥ ሰጠሙ ።

[14] የዐሳማዎቹ እረኞች ሸሽተው ሄዱ ፤ በከተ
ማና በገጠር ወሬውን ነዙት ፤ ሰዎቹ የሆነውን
ነገር ለማየት ከየቤታቸው ወጡ ፤ [15] ወደ ኢየሱ
ስም መጥተው ያ በርኵሳን መናፍስት ተይዞ የነ
በረው ሰው ከአእምሮው ሕመም ድኖ ፥ ልብ
ሱን ለብሶ ፥ ተቀምጦም ባዩት ጊዜ ደነገጡ ።
[16] ይህንንም ቀደም ብለው ያዩ ሰዎች ርኵስ
መንፈስ ባደረበት ሰውና በዐሳማዎቹ የሆነውን
ሁሉ አወሩላቸው ።

[17] የአገሩው ሰዎችም ኢየሱስ ከአገራቸው
ወጥቶ እንዲሄድላቸው ለመኑት ።

[18] ኢየሱስ ወደ ጀልባው በመግባት ላይ ሳለ
አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው “እባክህ
ልከተልህ” ብሎ ለመነው ።

[19] ኢየሱስ ግን አልፈቀደለትም ፤ ነገር ግን
“ወደ ቤትህ ሂድና ጌታ ምን ያህል ታላቅ ነገር
እንዳደረገልህና እንዴትስ እንደማረህ ለቤተሰ
ብህ አውራላቸው” አለው ።

[20] ሰውየውም ኢየሱስ ያደረገለትን ነገር
“ዐሥር ከተሞች” በሚባል አገር ማውራት
ጀመረ ፤ የሰሙትም ሁሉ ይደነቁ ነበር ።

የኢያኢሮስ ልጅና የኢየሱስን
ልብስ የነካች ሴት
(ማቴ. 9፡18-26፤ ሉቃ. 8፡40-56)

[21] ኢየሱስ በጀልባ ወደ ባሕሩ ማዶ በተመ
ለሰ ጊዜ ብዙ ሰዎች እንደገና ወደ እርሱ ተሰበ
ሰቡ ፤ በዚያ ጊዜ እርሱ በባሕሩ አጠገብ ነበር ።
[22] እዚያም ኢያኢሮስ የተባለ ሰው መጣ ፤
እርሱ ከምኵራብ አለቆች አንዱ ነበር ፤ ኢየሱ
ስን ባየው ጊዜ ከእግሩ ሥር ወድቆ ፤ [23] “ትን
ሽዋ ልጄ በሞት አፋፍ ላይ ናት ፤ እንድትድ
ንና በሕይወት እንድትኖር እባክህ መጥተህ እጅ
ህን ጫንባት” ሲል አጥብቆ ለመነው ።

[24] ኢየሱስም አብሮት ሄደ ፤ ብዙ ሰዎችም
ተከትለውት በዙሪያው ይጋፉት ነበር ።

[25] ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም እየመታት የም
ትውቃይ አንዲት ሴት ነበረች ። [26] ከሐኪም
ወደ ሐኪም በመሄድ ብዙ ተሠቃይታና ገንዘብ
ዋንም ሁሉ ጨርሳ ነበር ። ነገር ግን እየባሰባት
ሄደ እንጂ ምንም አልተሻላትም ። [27] እርስዋም
የኢየሱስን ዝና ሰምታ ስለነበር በሕዝቡ መካ
ከል በስተኋላው መጥታ ልብሱን ነካች ። [28] ይህ
ንንም ያደረገችው “ልብሱን እንኳ ብነካ እድና
ለሁ” በሚል እምነት ነበረ ።

[29] የሚፈሰው ደምዋም ወዲያውኑ ቆመ ፤
ከሕመምዋም እንደዳነች በሰውነትዋ ተሰማት ።
[30] ኢየሱስም ወዲያውኑ ኀይል ከእርሱ እንደ
ወጣ ዐወቀ ፤ ወደ ሕዝቡም ዘወር ብሎ “ልብ
ሴን የነካ ማን ነው?” ሲል ጠየቀ ።

[31] ደቀ መዛሙርቱም “ሕዝቡ እየተጋፋ
ሲከተልህ እያየህ ‘ማን ነው የነካኝ’ ትላለህን?”
ሲሉ መለሱለት ።

[32] እርሱም ይህንን ያደረገው ማን እንደሆነ
ለማየት ዘወር ብሎ ተመለከተ ። [33] ሴትዮዋ ግን
በእርስዋ የሆነውን በማወቅዋ በፍርሃት እየተን
ቀጠቀጠች በፊቱ ወድቃ እውነቱን ሁሉ ነገረ
ችው ። [34] እርሱም “ልጂ ሆይ! እምነትሽ አድ
ኖሻል ፤ በሰላም ሂጂ ፤ ከሥቃይሽም ተፈወሺ”
አላት ።

[35] ኢየሱስ ገና ይህን በመናገር ላይ ሳለ
ከምኵራብ አለቃው ቤት የመጡ ሰዎች የምኵ
ራብ አለቃውን “ልጅህ ሞታለች ፤ እንግዲህ
ስለምን መምህሩን ታደክመዋለህ?” አሉት ።

[36] ኢየሱስ ግን ይህን ሰምቶ የምኵራቡን
አለቃ “እመን ብቻ እንጂ አትፍራ” አለው ።
[37] ኢየሱስ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ፥ ከያዕቆብም
ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም እንዲከተለው
አልፈቀደም ። [38] ወደ ምኵራብ አለቃው ቤት
በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ ሰዎቹ ሲንጫጩና ሲያለ
ቅሱ ሲጮኹም ተመለከተ ። [39] ወደ ውስጥ ገብ
ቶም “ይህ ሁሉ ጫጫታና ለቅሶ ስለምንድን
ነው? ልጅትዋ እንቀላፍታለች እንጂ አልሞተ
ችም እኮ” አላቸው ።

[40] ሰዎቹም በማፌዝ ሳቁበት ፤ ኢየሱስ ግን
ሁሉንም ከቤት አስወጣ ፤ የልጅትዋን አባትና
እናት ከእርሱም ጋር የነበሩትን አስከትሎ ልጅ
ትዋ ወደተኛችበት ክፍል ገባ ። [41] የልጅትዋ
ንም እጅ ይዞ ፥ “ጣሊታ ኩም!” አላት ፤ ፍች
ውም “አንቺ ልጅ ተነሺ! እልሻለሁ” ማለት
ነው ።

[42] እርስዋ የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበ
ረች ። ወዲያውኑ ተነሥታ ወዲያና ወዲህ
ማለት ጀመረች ፤ ይህም በሆነ ጊዜ ሰዎቹ
እጅግ ተደነቁ ። [43] ኢየሱስ ግን ይህን ነገር
ማንም እንዳያውቅ አዘዛቸውና “የምትበላውን
ስጡአት” አላቸው ።

ምዕራፍ 6

ኢየሱስ በናዝሬት ተቃውሞ ደረሰበት
(ማቴ. 13፡53-58፤ ሉቃ. 4፡16-30)

[1] ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ፤
ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት ። [2] በሰንበት ቀን
በምኵራብ ማስተማር ጀመረ ፤ ብዙ ሰዎች
በዚያ ተገኝተው ይሰሙት ነበር ፤ እነርሱም
“ይህ ሰው ይህን ሁሉ ነገር ከየት አገኘው?
ምን ዐይነት ጥበብ ተሰጥቶታል? እነዚህንስ
ተአምራት የሚያደርገው እንዴት ነው?”
እያሉ ይደነቁ ነበር ። [3] ቀጥለውም “ለመሆኑ
ይህ እንጨት ጠራቢው የማርያም ልጅ አይደለ
ምን? የያዕቆብ ፥ የዮሴፍ የይሁዳና የስምዖንም
ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ እዚህ ከእኛ
ጋር አይደሉምን?” እያሉ በመናቅ ሳይቀበሉት
ቀሩ ።

[4] ኢየሱስም “ነቢይ በሌሎች ዘንድ ይከበ
ራል ፤ በገዛ አገሩ ፥ በዘመዶቹና በቤተ ሰቡ
መካከል ግን ይናቃል” ሲል መለሰላቸው ።

[5] በዚያም በጥቂት ሕመምተኞች ላይ እጁን
ጭኖ ከመፈወስ በቀር ሌላ ተአምር ማድረግ
አልተቻለውም ። [6] ስለ አለማመናቸውም እጅግ
ተገረመ ፤ ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በየመንደሩ እየ
ተዘዋወረ ያስተምር ነበር ።

ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት
ለወንጌል ሥራ ላከ
(ማቴ. 10፡5-15፤ ሉቃ. 9፡1-6)

[7] ዐሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ ጠርቶ ሁለት
ሁለት አድርጎ ላካቸው ፤ በርኵሳን መናፍስትም
ላይ ሥልጣን ሰጣቸው ፤ [8] ለመንገዳቸው ከበትር
በቀር እንጀራም ሆነ ከረጢት ፥ ገንዘብም በመ
ቀነታቸው እንዳይዙ አዘዛቸው ። [9] እንዲህም
አላቸው ፥ “በእግራችሁ ጫማ አድርጉ እንጂ
ሁለት ቀሚ

ሁለት እጀጠባብ እንኳ አትልበሱ ፤ 10 በማናቸ
ውም ስፍራ ወደ ሰው ቤት ስትገቡ ያንን
ነፍራ እስከትለቁ ድረስ በዚያው ቆዩ ፤
11 ሰዎች በማይቀበሉዋችሁና በማይሰሙአችሁ
በታ ሁሉ የእግራችሁን አቧራ አራግፉና ከዚያ
ወጥታችሁ ሂዱ ፤ ይህም ለእነርሱ የማስጠንቀ
ቂያ ምስክር ይሆንባቸዋል ።"
12 እነርሱም ከዚያ ወጥተው ሰዎች ሁሉ
ንስሓ እንዲገቡ አስተማሩ ። 13 ብዙ አጋንንት
ንም አስወጡ ፤ ብዙ ሰዎችንም ዘይት እየቀቡ
ፈወሱ ።

የአጥማቂው ዮሐንስ ሞት
(ማቴ. 14፡1-12፤ ሉቃ. 9፡7-9)

14 የኢየሱስ ዝና በሁሉም ዘንድ በመሠራ
ጨቱ ንጉሡ ሄሮድስ ስለ እርሱ ሰማ ። አንዳ
ንድ ሰዎች "አጥማቂው ዮሐንስ ከሞት ተነሥ
ቶአል ፤ ስለዚህ ይህ ሁሉ ኀይል በእርሱ ይደሪ
ጋል" ይሉ ነበር ።
15 ሌሎችም "ኤልያስ ነው" ይሉ ነበር ፤
የቀሩትም ደግሞ "ከቀድሞዎቹ ነቢያት እንደ
አንዱ ነው" ይሉ ነበር ።
16 ሄሮድስ ግን ይህን ሁሉ ሰምቶ "ይህ እኔ
አንገቱን ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ነው ፤ እነሆ
እርሱ ከሞት ተነሥቶአል" አለ ። 17 ሄሮድስ
የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮዲያዳን ስለአ
ገባ ዮሐንስን በእርስዋ ምክንያት በጭፍሮች
አስይዞ በወህኒ ቤት አስሮት ነበር ። 18 ምክንያ
ቱም ዮሐንስ ሄሮድስን "የወንድምህን ሚስት
ማግባትህ ተገቢ አይደለም" ብሎት ስለነበር
ነው ።
19 ሄሮዲያዳ በዚህ ተቀይማ ዮሐንስን ልታስ
ገድለው ትፈልግ ነበር ፤ ነገር ግን አልቻለ
ችም ። 20 ምክንያቱም ሄሮድስ ዮሐንስን ጻድ
ቅና ቅዱስ አድርጎ ስለሚያየው ይፈራውና ይጠ
ብቀው ነበር ። ሄሮድስ የዮሐንስን ንግግር
በሰማ ቍጥር ይታወክ ነበር ፤ ይሁን እንጂ በደ
ስታ ይሰማው ነበር ።
21 ሄሮድስ የተወለደበትን ቀን ለማክበር ለመ
ንግሥት ባለሥልጣኖች ፥ ለጦር ሹማምንትና
ለአንዳንድ የታወቁ የገሊላ ነዋሪዎች ታላቅ
ግብዣ አደረገ ፤ ይህም ለሄሮዲያዳ ጥሩ አጋ
ጣሚ ሆነላት ፤ 22 ስለዚህም የሄሮዲያዳ ልጅ
ወደ ግብዣው አዳራሽ ገብታ እየዘፈነች በውዝ
ዋዜዋ ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ተጋል
ዥዎች አስደሰተች ፤ ንጉሡም ልጅትዋን "የም
ትፈልጊውን ማንኛውንም ነገር ጠይቂኝ ፥ እሰ
ጥሻለሁ ፤ 23 የመንግሥቴንም እኩሌታ እንኳ
ቢሆን የምትጠይቂኝን ሁሉ እሰጥሻለሁ" ሲል
ማለላት ።

24 እርስዋም ወደ እናትዋ ሄዳ "ምን ልጠ
ይቅ?" አለቻት ፤ እናትዋም "የአጥማቂው
ዮሐንስ ራስ ይሰጠኝ" ብለሽ ጠይቂ" አለቻት ።
25 ልጅትዋም ወዲያውኑ በፍጥነት ወደ
ንጉሡ ተመልሳ "የአጥማቂው ዮሐንስ ራስ በሳ
ሕን ሆኖ አሁን እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ"
ስትል ጠየቀች ።
26 ንጉሡ በዚህ ነገር በጣም አዘነ ፤ ይሁን
እንጂ በተጋባዥዎች ፊት ስላደረገው መሐላ
የጠየቀችውን ሊከለክላት አልቻለም ። 27 ስለዚህ
ንጉሡ ወዲያውኑ ከወታደሮቹ አንዱን የዮሐን
ስን ራስ ቈርጦ እንዲያመጣ ላከው ፤ ወታደሩም
ወደ ወህኒው ቤት ሄዶ የዮሐንስን ራስ ቈረጠ ፤
28 የተቈረጠውንም ራስ በሳሕን አድርጎ አመ
ጣና ለልጅትዋ ሰጣት ፤ ልጅትዋም ለእናትዋ
ሰጠች ። 29 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ይህን
በሰሙ ጊዜ መጡና ሬሳውን ወስደው ቀበሩ ።

ኢየሱስ አምስት ሺ ሰዎች መገበ
(ማቴ. 14፡13-21፤ ሉቃ. 9፡10-17፤
ዮሐ. 6፡1-14)

30 ሐዋርያት ከተላኩበት ተመልሰው መጥ
ተው በኢየሱስ ፊት ተሰበሰቡ ፤ ያደረጉትንና
ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት ። 31 እርሱም "እና
ንተ ብቻችሁን ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ
ሂዱና ዋቂት ዕረፉ" አላቸው ፤ ይህንንም ያለ
በት ምክንያት ወደ እነርሱ የሚመጡና የሚ
ሄዱ ብዙዎች ስለነበሩ ፥ ለመመገብ እንኳ ጊዜ
ሊኖራቸው ስላልቻለ ነው ። 32 ስለዚህ ወደ
አንድ ገለልተኛ ስፍራ ብቻቸውን ለመሆን በጀ
ልባ ተሳፍረው ሄዱ ።
33 ይሁን እንጂ እነርሱ ሲሄዱ ብዙ ሰዎች
አይተው ወመቁአቸው ፤ ከየከተማውም ወጥተው
በእግር እየሮጡ ቀደሙአቸውና ወደ እነርሱ
ተሰበሰቡ ። 34 ኢየሱስ ከጀልባው ሲወርድ ብዙ
ሕዝብ አየ ፤ እረኛ እንደሌላቸው በጎች በመሆና
ቸውም አዘነላቸው ፤ ብዙ ነገርም ያስተምራ
ቸው ጀመር ። 35 ጊዜው እየመሸ በመሄዱ ደቀ
መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው እንዲህ
አሉት ፥ "ቦታው በረሓ ነው ፤ ጊዜውም መሸቶ
አል ፤ 36 የሚበሉት የላቸውምና በአካባቢው
ወዳሉት ገጠሮችና መንደሮች ሄደው ምግብ
እንዲገዙ እነዚህን ሰዎች አሰናብታቸው ።"
37 ኢየሱስ ግን "የሚበሉትን እናንተ ስጡአ
ቸው" ሲል መለሰ ። እነርሱም "ታዲያ ሄደን
የሚበሉትን እንጀራ በሁለት መቶ ብር ገዝተን
እንስጣቸውን?" አሉ ።
38 እርሱም "ስንት እንጀራ አላችሁ? እስቲ
ሂዱና እዩ" አላቸው ፤ አይተውም "አምስት
እንጀራና ሁለት ዓሣ አለ" አሉት ።

6፡11 ፡- ሐመ. 13፡51 ። 6፡13 ፡- ያዕ. 5፡14 ። 6፡14-15 ፡- ማቴ. 16፡14 ፡ ማር. 8፡28 ፡ ሉቃ. 9፡19 ።
6፡17-18 ፡- ሉቃ. 3፡19-20 ። 6፡34 ፡- ዘኍ. 27፡17 ፡ 1ነገ. 22፡17 ፡ 2ዘመ. 18፡16 ፡ ሕዝ. 34፡5 ፡ ማቴ. 9፡36 ።

39 ኢየሱስም ሕዝቡን በቡድን ከፋፍለው
በለመለመው መስክ ላይ እንዲያስቀምጡአቸው
ደቀ መዛሙርቱን አዘዘ ። 40 ስለዚህ ሕዝቡ በመ
ቶና በጎሳሳ ተከፋፍለው በተርታ ተቀመጡ ።
41 ኢየሱስም አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ
አንሥቶ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና እግዚአብሔ
ርን አመሰገነ ፤ እንጀራውንም ቈርሶ ለሰዎቹ
እንዲያድሉ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ፤ እንዲሁም
ሁለቱን ዓሣ ለሁሉም አከፋፈለ ። 42 ሁሉም
በልተው ጠገቡ ። 43 የተረፈላቸውንም ቁርስራሽ
እንጀራና ዓሣ ደቀ መዛሙርቱ ዐሥራ ሁለት
መሶብ ሙሉ ሰበሰቡ ። 44 እንጀራውን የበሉ
ወንዶች ብቻ ቍጥራቸው አምስት ሺ ነበር ።

ኢየሱስ በባሕር ላይ እየተራመደ ሄደ
(ማቴ. 14፡22-33፤ ዮሐ. 6፡15-21)

45 ኢየሱስ ወዲያውኑ ሕዝቡን ሲያሰናብት
ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ሆነው ወደ ማዶ
ወደ ቤተ ሳይዳ ተሻግረው እንዲቀድሙት አዘዛ
ቸው ። 46 ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ተለይቶ ለመጸ
ለይ ወደ ኮረብታ ወጣ ። 47 በመሸም ጊዜ ጀል
ባዋ በባሕሩ መካከል ነበረች ፤ እርሱ ግን ብቻ
ውን በምድር ላይ ነበረ ። 48 ደቀ መዛሙርቱ
ከወደፊታቸው በሚነፍሰው ነፋስ ምክንያት
መቅዘፍ ተቸግረው ሲጨነቁ አየ ፤ ከሌሊቱም
በዘጠኝ ሰዓት ገደማ በባሕሩ ላይ እየተራመደ
ወደ እነርሱ መጣ ፤ አልፎአቸውም ሊሄድ
ነበር ። 49 ነገር ግን እነርሱ በባሕሩ ላይ እየተራ
መደ ሲሄድ አይተው መንፈስ መስሎአቸው
ጮኹ ። 50 ሁሉም ባዩት ጊዜ ደነገጡ ።
እርሱ ግን ወዲያውኑ "አይዞአችሁ ፥ እኔ
ነኝ እኮ ፥ አትፍሩ" ብሎ አበረታታቸው ፤
51 ወደ ጀልባውም ገብቶ ከእነርሱ ጋር በሆነ
ጊዜ ነፋሱ ቆመ ፤ ደቀ መዛሙርቱ በጣም ተደ
ነቁ ። 52 ታዲያ ልባቸው ደንዝዞ የእንጀራውን
ተአምር ሳያስተውሉ ቀርተው ነው እንጂ ይህ
ነገር ባላስገረማቸውም ነበር ።

ኢየሱስ በጌንሴሬጥ በሽተኞችን አዳነ
(ማቴ. 14፡34-36)

53 ባሕሩን ተሻግረው ወደ ጌንሴሬጥ ደረሱ ፤
ጀልባዋን ወደ ምድር አስጠግተው አሰሩ ፤
54 ከጀልባ እንደወረዱ ወዲያውኑ ሰዎች ኢየሱ
ስን ዐወቁት ፤ 55 እነርሱም በዚያ አገር ዙሪያ
እየተራወጡ ኢየሱስ ወዳለበት ስፍራ ሁሉ በሽ
ተኞችን በአልጋ ተሸክመው ያመጡ ጀመር ።
56 በየሄደበትም ስፍራ ሁሉ በመንደር ፥ በከ
ተማ ፥ በገጠርም በሽተኞችን ወደ አደባባይ እያ
ወጡ በእርሱ ፊት ያቀርቡአቸው ነበር ፤ የልብ
ሱንም ጫፍ እንኳ እንዲነኩ ይለምኑት ነበር ፤
የነኩትም ሁሉ ይድኑ ነበር ።

ምዕራፍ 7

ኢየሱስ ሰው ሠራሽ ሥርዓትን ተቃወመ
(ማቴ. 15፡1-9)

1 ፈሪሳውያንና ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳ
ንድ የሙሴ ሕግ መምህራን ወደ ኢየሱስ ቀር
በው በዙሪያው ተሰበሰቡ ። 2 ከኢየሱስ ደቀ መዛ
ሙርት አንዳንዶቹ እጃቸውን ሳይታጠቡ እን
ጀራ ሲበሉ አዩአቸው ።
3 ፈሪሳውያንና የቀሩትም አይሁዳውያን የሽ
ማግሌዎችን ወግ በመጠበቅ እጃቸውን ደኅና
አድርገው ካልታጠቡ አይበሉም ነበር ። 4 እንዲ
ሁም ከገበያ ሲመለሱ ካልታጠቡ አይበሉም
ነበር ፤ ዋንጫን ፥ ማሰሮን ፥ ሳሕንና አልጋን ፥
እንደማጠብ ያለ ሌላም ብዙ ወግ ይጠብቁ
ነበር ።
5 ስለዚህ ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህ
ራን "ደቀ መዛሙርትህ የሽማግሌዎችን ወግ
በመጣስ ስለምን እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ
ይበላሉ?" ሲሉ ኢየሱስን ጠየቁት ።
6 እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"እናንተ ግብዞች ፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ ፥
'ይህ ሕዝብ በአፉ ብቻ ያከብረኛል እንጂ
ልቡ ከእኔ በጣም የራቀ ነው ፤
7 የሰውንም ሥርዓት እያስተማሩ በከንቱ
ያመልኩኛል'
ሲል የተናገረው ቃል እውነት ነው ።
8 "ስለዚህ እናንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ
ትታችሁ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ ።"
9 ቀጥሎም እንዲህ አላቸው ፥ "ወጋችሁን
ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተ
ዋላችሁ ፤ 10 ለምሳሌ ሙሴ 'አባትህንና እናት
ህን አክብር ፤ ደግሞ በአባቱ ወይም በእናቱ ላይ
ክፉ የሚናገር ሰው በሞት ይቀጣ' ይላል ።
11 እናንተ ግን እንዲህ ትላላችሁ ፥ 'አንድ ሰው
አባቱን ወይም እናቱን በመርዳት ፈንታ ለአባ
ቱና ለእናቱ ማድረግ የሚገባውን ነገር ሁሉ
ለእግዚአብሔር ያቀረብሁት መባ ነው' ቢላ
ችሁ ፥ 12 አባትና እናቱን ከመርዳት ነፃ ታደር
ጉታላችሁ ፤ 13 በዚህም ሁኔታ የራሳችሁን ወግ
ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራ
ላችሁ ፤ እንዲሁም ይህንን የመሳሰለ ብዙ ነገር
ታደርጋላችሁ ።"

ሰውን የሚያረክስ ነገር
(ማቴ. 15፡10-20)

14 ሰዎቹንም እንደገና ወደ እርሱ ጠርቶ እን
ዲህ አላቸው ፥ "እናንተ ሁላችሁም በማስተ
ዋል አዳምጡኝ ፤ 15 ሰውን የሚያረክሰው ከሰው
የሚወጣው ነገር ነው እንጂ ከውጪ ወደ ሰው

7፡6-7 ፡- ኢሳ. 29፡13 ። 7፡10 ፡- ዘጸ. 20፡12 ፡ 21፡17 ፡ ዘሌ. 20፡9 ፡ ዘዳ. 5፡16 ።

የሚገባውስ አያረክሰውም ። [16 እንግዲህ ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ ።”]*
17 ኢየሱስ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት በገባ
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ምሳሌው ጠየቁት ።
18 እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “እናን
ተም ደግሞ ይህን አታስተውሉምን? ከውጪ
ወደ ሰው የሚገባ ነገር ሰውን ምንም እንደማ
ያረክሰው አይገባችሁምን? 19 ምክንያቱም
በሆድ በኩል ተላልፎ ወደ ውጪ ይወጣል
እንጂ ወደ ልብ አይሄድም ፤” ስለዚህ ኢየሱስ
ምግብ ሁሉ ንጹሕ መሆኑን በዚህ ሁኔታ
ገለጸ ።
20 ቀጥሎም እንዲህ አለ ፥ “ሰውን የሚያረክ
ሱት ከሰው ልብ የሚወጡት ነገሮች ናቸው ።
21 እነርሱም ፥ ክፉ አሳብ ፥ ዝሙት ፥ ስርቆት ፥
ሰው መግደል ፥ 22 ምንዝር ፥ ስግብግብነት ፥
ክፋት ፥ አታላይነት ፥ ስድነት ፥ ምቀኝነት ፥ የሰ
ውን ስም ማጥፋት ፥ ትዕቢት ፥ አእምሮቢስነት
ናቸው ። 23 ይህ ሁሉ ክፉ ነገር ከሰው ልብ
ይወጣል ፥ ሰውንም ያረክሰዋል ።”

የአንዲት ግሪካዊት ሴት እምነት
(ማቴ. 15፡21-28)

24 ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ በጢሮስ ከተማ
አጠገብ ወዳለው መንደር ሄደ ፤ ወደ አንድ
ቤትም ገብቶ እዚያ መኖሩን ማንም ሰው እን
ዳያውቅ ፈለገ ፤ ይሁን እንጂ ሊሰወር አልተቻ
ለውም ። 25 ልጅዋ በርኩስ መንፈስ የተያዘች
ባት አንዲት ሴት ስለ ኢየሱስ ሰምታ ወዲያ
ውኑ መጣችና በእግሩ ሥር ወደቀች ። 26 ሴት
ዮዋም ከሲሮፊኒቃውያን ወገን የሆነች ግሪካ
ዊት ነበረች ፤ እርስዋ ከልጅዋ ጋኔን እንዲያወ
ጣላት ኢየሱስን ለመነችው ። 27 ኢየሱስ ግን
“የልጆችን ምግብ ወስዶ ለውሾች መስጠት
አይገባምና እስቲ ልጆቹ አስቀድመው ይዋ
ገቡ” አላት ።
28 እርስዋም “እርግጥ ነው ጌታዬ ፤ ታዲያ
እኮ ውሾችም በገበታ ሥር ሆነው ከልጆች የወ
ደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ” ስትል መለሰችለት ።
29 ስለዚህ ኢየሱስ “ይህን በማለትሽ ጋኔኑ
ከልጅሽ ወጥቶአል ፤ እንግዲህ ወደ ቤትሽ
ሂጂ” አላት ።
30 እርስዋም ወደ ቤትዋ በተመለሰች ጊዜ
ልጅዋን ጋኔኑ ለቅቶ በአልጋ ላይ በደኅና
ተኝታ አገኘችት ።

ኢየሱስ ደንቆሮና ድዳ
የነበረውን ሰው ፈወሰ

31 ኢየሱስ የጢሮስን አገር ትቶ ሄደ ፤ በሲ
ዶና በኩልም አድርጎ ዐሥር ከተሞች በሚባ
ለው አገር ወደ ገሊላ ባሕር መጣ ። 32 በዚያ
አንድ ደንቆሮና ድዳ የሆነ ሰው ወደ እርሱ
አመጡ ፤ እጁንም እንዲጭንበት ለመኑት ።
33 ኢየሱስም ሰውየውን ከሕዝቡ ለይቶ ለብቻው
ወሰደና ጣቶቹን በሰውየው ጆሮዎች ውስጥ
አገባ ፤ ምራቁንም እንትፍ ብሎ የሰውየውን
ምላስ ዳሰሰ ፤ 34 ወደ ሰማይም አሻቅቦ አይቶ
ቃተተና ሰውየውን “ኤፋታህ” አለው ፤ ፍቺ
ውም “ተከፈት” ማለት ነው ።
35 ወዲያውኑ ጆሮዎቹ ተከፈቱ ፤ እንደበቱም
ተፈታ ፤ ያለአንዳች ችግርም አጥርቶ መናገር
ጀመረ ። 36 ኢየሱስ ይህን ነገር ለማንም እንዳይ
ናገሩ ሰዎቹን አዘዛቸው ፤ ይሁን እንጂ እንዳይና
ገሩ ባዘዛቸው መጠን በብዙ ያወሩ ነበር ።
37 የሰሙትም ሁሉ እጅግ በመደነቅ “ሁሉን
ነገር በመልካም አደረገ ፤ ደንቆሮዎች እንዲ
ሰሙ ፤ ድዳዎችም እንዲናገሩ ያደርጋል”
አሉ ።

ምዕራፍ 8

ኢየሱስ አራት ሺ ሰዎች መገበ
(ማቴ. 15፡32-39)

1 በዚያን ጊዜ እንደገና ብዙ ሰዎች ተሰበ
ሰቡ ፤ የሚበሉትም አልነበራቸውም ፤ ስለዚህ
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ እንዲህ አላ
ቸው ፥ 2 “እነዚህ ሰዎች እነሆ ከእኔ ጋር ሦስት
ቀን ቆይተዋል ፤ የሚበሉት ምንም ስለሌላቸው
እራራላቸዋለሁ ፤ 3 እንዲሁ እንደተራቡ ወደ
ቤታቸው ባሰናብታቸው በመንገድ ይደክማሉ ፤
እንዲያውም ከእነርሱ አንዳንዶቹ ከሩቅ የመጡ
ናቸው ።”
4 ደቀ መዛሙርቱም “ታዲያ በዚህ በረሓ
ለእነዚህ ሁሉ ሰዎች የሚበቃ እንጀራ ማግ
ኘት ማን ይችላል?” ሲሉ መለሱለት ። 5 ኢየ
ሱስም “ስንት እንጀራ አላችሁ?” ብሎ ጠየ
ቃቸው ፤
እነርሱም “ሰባት እንጀራ አለ” አሉት ።
6 እርሱም በመሬት ላይ እንዲቀመጡ ሕዝ
ቡን አዘዘ ፤ ሰባቱንም እንጀራ ይዞ እግዚአብሔ
ርን አመሰገነ ቈርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ
ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው ፤ እነርሱም ለሕዝቡ
አቀረቡ ። 7 ጥቂት ትናንሽ ዓሣዎችም ነበሩአ
ቸው ፤ ስለ ዓሣዎቹም እግዚአብሔርን ካመሰገነ
በኋላ ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ደቀ መዛሙርቱን
አዘዘ ። 8 ሰዎቹም ሁሉ በልተው ጠገቡ ፤ የተረ
ፈውንም ቁርስራሽ ሰብስበው ሰባት መሶብ
ሙሉ አነሡ ። 9 የተመገቡት ሰዎች አራት ሺ
ያህል ነበሩ ፤ ኢየሱስ እነርሱን ካሰናበተ በኋላ ፥
10 ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጀልባ ሆኖ ወደ ዳል
ማኑታ አገር ሄደ ።

4* 7፡16 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 16 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በ4፡23 ያለውን ይመስላል ።

ፈሪሳውያን ተአምር እንዲደረግላቸው ጠየቁ
(ማቴ. 16፡1-4)

11 ፈሪሳውያን ወደ ኢየሱስ መጡና ከእርሱ
ጋር መከራከር ጀመሩ ፤ ሊፈትኑትም አስበው
ከሰማይ አንድ ተአምር እንዲያሳያቸው ጠየ
ቁት ። 12 ኢየሱስ በመንፈሱ በመቃተት “የዚህ
ትውልድ ሰዎች ተአምር እንዲደረግላቸው ስለምን
ይፈልጋሉ? በእውነት እላችኋለሁ ፥ ምንም ተአ
ምር አይደረግላቸውም” አላቸው ። 13 ትቶአቸ
ውም እንደገና በጀልባ ሆኖ ወደ ማዶ ተሻገረ ።

የፈሪሳውያንና የሄሮድስ እርሾ
(ማቴ. 16፡5-12)

14 ደቀ መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ስለ ረሱ
በጀልባው ውስጥ ከአንድ እንጀራ በቀር ምንም
አልነበራቸውም ። 15 ኢየሱስም “ከፈሪሳውያንና
ከሄሮድስ እርሾ ተጠንቀቁ” ብሎ አዘዛቸው ።
16 እነርሱም “ይህን ማለቱ ምናልባት እን
ጀራ ስለሌለን ይሆናል” ብለው እርስ በርሳቸው
ተነጋገሩ ።
17 ኢየሱስም ይህንኑ አሳባቸውን ዐውቆ እን
ዲህ አላቸው ፥ “እንጀራ ስለሌለን ነው ብላችሁ
ስለምን ታስባላችሁ? ገና ምንም የማታስተው
ሉና የማይገባችሁ ናችሁን? ልባችሁስ ገና
እንደ ደነዘዘ ነውን? 18 ዐይን እያላችሁ አታዩ
ምን? ጆሮስ እያላችሁ አትሰሙምን? እንዴትስ
ትዝ አይላችሁም? 19 ለመሆኑ አምስቱን እን
ጀራ ለአምስት ሺ ሰዎች በቈረስኩ ጊዜ ትራፊ
ውን ስንት መሶብ ሙሉ አነሣችሁ?”
እነርሱም “ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ”
አሉት ።
20 “እንዲሁም ሰባቱን እንጀራስ ለአራት ሺ
ሰዎች በቈረስኩ ጊዜ ትራፊውን ስንት መሶብ
ሙሉ አነሣችሁ?” ሲል ጠየቃቸው ።
እነርሱም “ሰባት መሶብ ሙሉ” አሉት ።
21 እርሱም “ታዲያ ገና አታስተውሉምን?”
አላቸው ።

ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ አንድ
ዐይነ ስውር ፈወሰ

22 ወደ ቤተ ሳይዳም በደረሱ ጊዜ ሰዎች
አንድ ዐይነ ስውር ወደ ኢየሱስ አመጡ ፤ እንዲ
ዳስሰውም ለመኑት ። 23 እርሱም የዐይነ ስውሩን
እጅ ይዞ እየመራ ከመንደር ወደ ውጪ አወ
ጣው ፤ በሰውየውም ዐይኖች ላይ ምራቁን እን
ትፍ ብሎ እጁን ጫነበትና “አንዳች ነገር ታያ
ለህን?” ሲል ጠየቀው ።
24 ዐይነ ስውሩም ቀና ብሎ “አዎ ሰዎች
ይታዩኛል ፤ ግን እንደሚራመዱ ዛፎች ይመስ
ላሉ” አለ ።
25 እንደገናም ኢየሱስ በሰውየው ዐይኖች
ላይ እጁን ጫነ ፤ በዚህ ጊዜ ሰውየው ትኩር
ብሎ አየ ፤ ድኖም ሁሉን ነገር አጥርቶ ማየት
ጀመረ ። 26 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ “ወደ መን
ደሩ አትግባ” ብሎ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አሰናበ
ተው ።

የጴጥሮስ እምነትና ምስክርነት
(ማቴ. 16፡13-20፡ ሉቃ. 9፡18-21)

27 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በፊልጵስ ቂሳ
ርያ ወረሱት መንደሮች አመሩ ፤ በመንገድም
ላይ ሳሉ ኢየሱስ “ሰዎች ፡ እኔን ማን ይሉ
ኛል?” ሲል ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው ።
28 እነርሱም “እንዳንዶች አጥማቂው ዮሐ
ንስ ነው ፥ ሌሎች ኤልያስ ነው ፤ ሌሎችም
ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል” ሲሉ
መለሱለት ።
29 “እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?”
ብሎ ጠየቃቸው ። ጴጥሮስም “አንተ መሲሕ
ነህ” ሲል መለሰለት ።
30 ኢየሱስም “ስለ እኔ ለማንም እንዳትና
ገሩ” ብሎ አስጠነቀቃቸው ።

ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት
ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረ
(ማቴ. 16፡21-28፡ ሉቃ. 9፡22-27)

31 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ሲል
ማስተማር ጀመረ ፥ “የሰው ልጅ ብዙ መከራ
መቀበል ይገባዋል ፤ በሽማግሌዎች ፡ በካህናት
አለቆችና በሙሴ ሕግ መምህራን ዘንድ ይና
ቃል ፤ ይገደላልም ፤ ይሁን እንጂ ከሦስት ቀን
በኋላ ይነሣል ።” 32 ይህን ነገር በግልጥ ነገራ
ቸው ፤ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ለብቻው ገለል አድር
ጎት ፥ “እንዲህ አትበል” ሲል ከለከለው ።
33 ኢየሱስ ግን ዘወር ብሎ ደቀ መዛሙርቱን
ተመለከተና ጴጥሮስን “አንተ ሰይጣን ከእኔ
ወዲያ ሂድ ፤ አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔ
ርን ነገር አታስብም” ሲል ገሠጸው ።

ኢየሱስን መከተል የሚጠይቀው መሥዋዕትነት
(ማቴ. 10፡38-39፡ 16፡24-28፡
ሉቃ. 9፡23-27፡ 14፡26-27)

34 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ከደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ “ሊከተ
ለኝ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ ፤ መስቀሉ
ንም ተሸክሞ ይከተለኝ ፤ 35 ሕይወቱን ለማዳን

8፡11 ፡- ማቴ. 12፡38 ፡ ሉቃ. 11፡16 ። 8፡12 ፡- ማቴ. 12፡39 ፡ ሉቃ. 11፡29 ። 8፡15 ፡- ሉቃ. 12፡1 ።
8፡18 ፡- ኤር. 5፡21 ፡ ሕዝ. 12፡2 ፡ ማር. 4፡12 ። 8፡28 ፡- ማር. 6፡14-15 ፡ ሉቃ. 9፡7-8 ። 8፡29 ፡- ዮሐ. 6፡68-69 ።
8፡34 ፡- ማቴ. 10፡38 ፡ ሉቃ. 14፡27 ። 8፡35 ፡- ማቴ. 10፡39 ፡ ሉቃ. 17፡33 ፡ ዮሐ. 12፡25 ።

የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል ፤ ስለ እኔና ስለ ወን
ጌል ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያድና
ታል ፤ 36 ሰው የዓለምን ሀብት ሁሉ አግኝቶ
ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? 37 ወይስ
ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ዋጋ ሊከፍል ይች
ላል? 38 በዚህ በከሐዲና በኃጢአተኛ ትውልድ
ፊት በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ ፥ የሰው
ልጅ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር
ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል ።"

ምዕራፍ 9

የኢየሱስ መልክ መለወጥ

(ማቴ. 17፡1-13፤ ሉቃ. 9፡28-36)

1 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፥ "በእ
ውነት እላችኋለሁ ፥ አሁን እዚህ ካሉት መካ
ከል አንዳንዶች የእግዚአብሔር መንግሥት በታ
ላቅ ኀይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ የማይሞቱ
አሉ ።"
2 ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን ፥
ያዕቆብንና ዮሐንስን ብቻ አስከትሎ ወደ ከፍ
ተኛ ተራራ ላይ ወጣ ፤ በፊታቸውም መልኩ
ተለወጠ ። 3 ልብሱ እጅግ አንጸባረቀ ፥ በዓለም
ላይ ማንም አጣቢ ፥ ያን ያህል ሊያነጣ እስከማ
ይችል ድረስ ነጭ ሆነ ። 4 በዚያን ጊዜ ኤልያ
ስና ሙሴ ተገልጠው ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ
ታዩአቸው ። 5 ጴጥሮስም ኢየሱስን "መምህር
ሆይ! እዚህ መኖር ለእኛ መልካም ነው ፤ ስለ
ዚህ አንድ ለእንተ ፥ አንድ ለሙሴ ፥ አንድ ለኤ
ልያስ የሚሆኑ ሦስት ዳሶች እንሥራ" አለው ።
6 ሦስቱ ደቀ መዛሙርት እጅግ ደንግጠው ስለነ
በር ጴጥሮስ የሚናገረውን አያውቅም ነበር ።
7 ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው ፤ ከደመናውም
ውስጥ "የምወደው ልጄ ይህ ነው ፤ እርሱን
ስሙት" የሚል ድምፅ መጣ ። 8 ወዲያውም
ዞር ብለው ሲመለከቱ ከእነርሱ ጋር ከኢየሱስ
ብቻ በቀር ማንንም አላዩም ።
9 ከተራራውም ሲወርዱ ኢየሱስ "የሰው
ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ይህን ያያችሁትን
ለማንም አትንገሩ" ሲል አዘዛቸው ።
10 ቃሉንም ሰምተው ተቀበሉት ፤ ይሁን
እንጂ "ይህ ከሞት መነሣት ምን ማለት ይሆን"
እያሉ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ ። 11 እነርሱም
"የሙሴ ሕግ መምህራን መጀመሪያ መምጣት
ያለበት ኤልያስ ነው ስለምን ይላሉ" ሲሉ ጠየ
ቁት ።
12 እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው ፥
"እርግጥ ነው ፤ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመ
ጣል ፤ ሁሉንም ያስተካክላል ፤ ይሁን እንጂ
የሰው ልጅ መከራ እንደሚቀበልና እንደሚናቅ
የተጻፈው እንዴት ነው? 13 እኔ ግን እላችኋ
ለሁ ፥ ኤልያስ ቀደም ብሎ መጥቶአል ፤ ሰዎ
ችም ስለ እርሱ እንደተጻፈው የፈለጉትን ሁሉ
አድርገውበታል ።"

ኢየሱስ ርኵስ መንፈስ ያደረበትን ልጅ ፈወሰ

(ማቴ. 17፡14-21፤ ሉቃ. 9፡37-43)

14 ኢየሱስና ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ወደቀ
ሩት ደቀ መዛሙርት ተመልሰው በመጡ ጊዜ
ብዙ ሕዝብ በዙሪያቸው ተሰብስቦ አየ ፤ የሙሴ
ሕግ መምህራን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ይከራ
ከሩ ነበር ። 15 ሰዎችም ሁሉ ኢየሱስን ባዩት
ጊዜ በመገረም ተደናገጡ ፤ ወደ እርሱም
ሮጠው እጅ ነሡት ። 16 ኢየሱስም ደቀ መዛሙ
ርቱን "ከእነርሱ ጋር የምትከራከሩት በምን
ጉዳይ ነበር?" ሲል ጠየቃቸው ።
17 ከሕዝቡም መካከል አንዱ እንዲህ ሲል
መለሰ ፥ "መምህር ሆይ! በማያናግር ርኵስ መን
ፈስ የተያዘውን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼው
ነበር ፤ 18 በተነሣበትም ጊዜ ይጥለዋል ፤ አፉም
አረፋ እየደፈቀ ጥርሶቹን ያፋጫል ፤ ሰውነቱም
ደርቆ እንደ በድን ይሆናል ፤ ርኵሱንም መንፈስ
እንዲያስወጡለት ደቀ መዛሙርትህን ጠይቄአ
ቸው ነበር ፤ ነገር ግን አልቻሉም ።"
19 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ "እናንተ
የማታምኑ ሰዎች ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር
እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? እስቲ
ልጁን ወደ እኔ አምጡት ።" 20 እነርሱም
ልጁን አመጡለት ፤ ርኵሱም መንፈስ ኢየሱስን
ባየ ጊዜ ወዲያው ልጁን ጥሎ እንፈራገጠው ፤
ልጁም በመሬት ላይ እየተንከባለለ አረፋ ይደ
ፍቅ ጀመር ። 21 ኢየሱስም የልጁን አባት "ይህ
በሽታ ከጀመረው ምን ያህል ጊዜ ነው?" ሲል
ጠየቀው ።
አባትየውም እንዲህ አለ ፥ "ከሕፃንነቱ
ጀምሮ ነው ። 22 ሊገድለውም እየፈለገ ብዙ
ጊዜ በእሳትና በውሃ ውስጥ ይጥለው ነበር ፤ ግን
ቢቻልህ እባክህ እዘንልን ፥ እርዳንም ።"
23 ኢየሱስም "ቢቻልህ ትላለህን? ለሚያም
ን ሁሉ ነገር ይቻላል" አለው ።
24 ወዲያውኑ የልጁ አባት "ማመንስ አምና
ለሁ ፤ ግን አለማመኔ እንዲወገድልኝ እርዳኝ"
ብሎ ጮኸ ።
25 ኢየሱስም ሰዎቹ እየተራወጡ ሲመጡ
አየ ፤ ርኵሱንም መንፈስ "አንተ ድዳና ደንቆሮ
መንፈስ ፥ ከልጁ እንድትወጣ ፤ ወደ እርሱም
ተመልሰህ እንዳትገባ አዝሃለሁ" ብሎ ገሠጸው ።
26 ርኵሱም መንፈስ በታላቅ ድምፅ ጮኸ ፤
ልጁንም በጣም ካንፈራገጠው በኋላ ወጣ ፤
ልጁም ልክ እንደ በድን በመሆኑ ብዙዎቹ
የሞተ መሰላቸው ። 27 ኢየሱስ ግን የልጁን እጅ
ይዞ አስነሣው ፤ ልጁም ቆመ ።

9፡2-7 ፡- 2ጴጥ. 1፡17-18 ። 9፡7 ፡- ማቴ. 3፡17 ፡ ማር. 1፡11 ፡ ሉቃ. 3፡22 ። 9፡11 ፡- ሚል. 4፡5 ፡ ማቴ. 11፡14 ።

28 ኢየሱስም ወደ ቤት በገባ ጊዜ ደቀ መዛ
ሙርቱ "ለመሆኑ ይህን ርኵስ መንፈስ እኛ
ልናስወጣው ስለምን አልቻልንም?" ብለው
ጠየቁት ።
29 እርሱም "እንዲህ ዐይነቱ በጸሎትና
[በጾም] ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም አይወ
ጣም" ሲል መለሰላቸው ።

ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት ሁለተኛ ጊዜ ተናገረ

(ማቴ. 17፡22-23፤ ሉቃ. 9፡43-45)

30 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ያንን ስፍራ
ትተው በገሊላ በኩል ሄዱ ፤ ያለበትን ቦታም
ማንም ሰው እንዲያውቅ ኢየሱስ አልፈለገም ፤
31 ምክንያቱም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
ሞያሰው ልጅ በሰዎች እጅ ተላልፎ ይሰጣል ፤
እነርሱም ይገድሉታል ፤ ከተገደለ በኋላ ግን
በሦስተኛው ቀን ይነሣል" እያለ ያስተምራቸው
ስለነበር ነው ።
32 ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህ ነገር አልገባቸ
ውም ፤ እንዳይጠይቁትም ፈሩ ።

ከሁሉም የሚበልጥ ማን ነው?

(ማቴ. 18፡1-5፤ ሉቃ. 9፡46-48)

33 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቅፍርና
ሆም መጡ ፤ ኢየሱስ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱን "በመንገድ ሳላችሁ የተከራከራች
ሁበት ነገር ምን ነበር?" ሲል ጠየቃቸው ።
34 እነርሱ ግን ዝም አሉ ፤ ምክንያቱም በመ
ንገድ ሳሉ "ከሁላችን የሚበልጥ ማን ነው?"
እያሉ ይከራከሩ ስለነበረ ነው ። 35 እርሱም ከተ
ቀመጠ በኋላ ዐሥራ ሁለቱንም ጠርቶ "መጀመ
ሪያ መሆን የሚፈልግ ማናቸውም ሰው የሁሉ
መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ መሆን አለበት"
አላቸው ። 36 አንድ ሕፃን ልጅ አምጥቶ በመካከ
ላቸው አቆመው ፤ አቅፎትም እንዲህ አላቸው ፥
37 "እንደዚህ ካሉት ሕፃናት አንዱን በስሜ
የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፤ እኔንም የሚቀበል
ሁሉ እኔን ብቻ ሳይሆን የላከኝንም ይቀበ
ላል ።"

ኢየሱስ "የማይቃወመን ሁሉ ከእኛ ጋር ነው" አለ

(ሉቃ. 9፡49-50)

38 ዮሐንስ ኢየሱስን "መምህር ሆይ! አንድ
ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያስወጣ አየን ፤ ከእ
ኛም ጋር ስላልሆነ ከለከልነው" አለው ።
39 ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ ፥ "በስሜ ተአ
ምር እያደረገ ወዲያውኑ በእኔ ላይ ክፉ የሚና
ገር ስለሌለ ተዉት ፤ አትከልክሉት ፤ 40 ምክንያ
ቱም እኛን የማይቃወም ሁሉ ከእኛ ጋር ነው ፤
41 በእውነት እላችኋለሁ ፥ የክርስቶስ ስለሆና
ችሁ አንድ ብርጭቆ ውሃ እንኳ የሚሰጣችሁ
ዋጋውን አያጣም ።

የኃጢአት ምክንያት

(ማቴ. 18፡6-9፡ ሉቃ. 17፡1-2)

42 "በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከትንንሾቹ
አንዱን የሚያስት ሰው ከባድ የወፍጮ ድንጋይ
በአንገቱ ላይ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለ
ዋል ። 43 ስለዚህ እጅህ ቢያስትህ ቁርጠህ
ጣለው ፤ ሁለት እጅ እያለህ ወደ ገሃነም ከምት
ጣል ይልቅ ፥ ጕንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግ
ባት ይሻልሃል ። [44 ገሃነም ትሉ የማይሞት
በት ፥ እሳቱ የማይጠፋበት ስፍራ ነው ።]5*
45 እግርህም ቢያስትህ ቁርጠህ ጣለው ፤ ሁለት
እግር እያለህ ወደ ገሃነም ከምትጣል ይልቅ ፥
አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል ።
[46 ገሃነም ትሉ የማይሞትበት ፥ እሳቱ የማይጠ
ፋበት ስፍራ ነው ።]6* 47 ዐይንህም ቢያስትህ
አውጥተህ ጣለው ፤ ሁለት ዐይን እያለህ ወደ
ገሃነም ከምትጣል ይልቅ ፥ አንድ ዐይና ሆነህ
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻል
ሃል ። 48 ገሃነም ትሉ የማይሞትበት ፥ እሳቱም
የማይጠፋበት ስፍራ ነው ።
49 "ሰው ሁሉ በእሳት ተቀምሞ ይጠራል ።
50 "ጨው መልካም ነው ፤ ይሁን እንጂ
የጨውነቱን ጣዕም ካጣ በምን ታጣፍጡታላ
ችሁ?
"በእናንተም የጨው ጣዕም ይኑርባችሁ ፤
እርስ በርሳችሁ ተስማምታችሁ በሰላም ኑሩ ።"

ምዕራፍ 10

መፋታት አይገባም

(ማቴ. 19፡1-12፤ ሉቃ. 16፡18)

1 ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ወደ ይሁዳ አገርና
ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሄደ ፤ ብዙ ሰዎችም እንደ
ገና ወደ እርሱ ተሰበሰቡ ፤ እርሱም እንደ
ልማዱ ያስተምራቸው ነበር ።
2 አንዳንድ ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡ ፤
ሊፈትኑትም ፈልገው "ሰው ሚስቱን እንዲፈታ
በሕግ ተፈቅዶለታልን?" ሲሉ ጠየቁት ።
3 ኢየሱስም "ሙሴ ስለዚህ ነገር ምን አዘዛ
ችሁ" አላቸው ።

5* 9፡44 አንዳንድ ቅጂዎች ቊ. 44 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በቊ. 48 ያለውን ይመስላል ። 6* 9፡46 አንዳንድ ቅጂዎች ቊ. 46 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በቊ. 48 ያለውን ይመስላል ።
9፡34 ፡- ሉቃ. 22፡24 ። 9፡35 ፡- ማቴ. 20፡26-27 ፡ 23፡11 ፡ ማር. 10፡43-44 ፡ ሉቃ. 22፡26 ። 9፡37 ፡- ማቴ. 10፡40 ፡ ሉቃ. 10፡16 ፡ ዮሐ. 13፡20 ። 9፡40 ፡- ማቴ. 12፡30 ፡ ሉቃ. 11፡23 ። 9፡41 ፡- ማቴ. 10፡42 ። 9፡43 ፡- ማቴ. 5፡30 ። 9፡47 ፡- ማቴ. 5፡29 ። 9፡48 ፡- ኢሳ. 66፡24 ። 9፡50 ፡- ማቴ. 5፡13 ፡ ሉቃ. 14፡34-35 ።

4 እነርሱም “ሙሴማ የፍቺዋን የምስክር
ወረቀት ሰጥቶ እንዲፈታት ፈቅዶአል” አሉት ።
5 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“ሙሴስ ይህንን የፈቀደው የልባችሁን ደንዝዘ
በማየት ነው ፤ 6 ነገር ግን ከፍጥረት መጀመሪያ
አንሥቶ ‘እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ
ፈጠራቸው ፤ 7 በዚህ ምክንያት ሰው አባትና እና
ቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል ፤ 8 ሁለቱም
አንድ አካል ይሆናሉ ፣’ ከዚያም ወዲያ ሁለት
መሆናቸው ቀርቶ አንድ ይሆናሉ ። 9 እንግዲህ
እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው ።”
10 ወደ ቤት በተመለሱ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ
ስለዚህ ጕዳይ እንደገና ኢየሱስን ጠየቁት ፤
11 እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥ “ሚስ
ቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ በሚስቱ ላይ
አመንዝሮአል ማለት ነው ፤ 12 እንዲሁም ባል
ዋን ፈትታ ሌላ ወንድ የምታገባ ሴት አመን
ዝራ ሆናለች ማለት ነው ።”

ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ
(ማቴ. 19፡13-15፤ ሉቃ. 18፡15-17)

13 ኢየሱስ እንዲጸሰላቸው ሕፃናቱን ወደ
እርሱ አመጡ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃናቱን
ያመጡአቸውን ሰዎች ገሠጹአቸው ። 14 ኢየሱ
ስም ይህን በማየት ተቆጥቶ ደቀ መዛሙርቱን
እንዲህ አላቸው ፥ “የእግዚአብሔር መንግሥት
እንደነዚህ ላሉት ስለ ሆነች ሕፃናት ወደ እኔ
ይምጡ ፤ ተዉ ፡ አትከልክሉአቸው ፤ 15 በእው
ነት እላችኋለሁ ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት
እንደ ሕፃን ሆኖ የማይቀበላት ኩቱ አይገባባ
ትም ።” 16 ከዚህ በኋላ ሕፃናቱን አቀፋቸውና
እጁን ጭኖ ባረካቸው ።

የገንዘብ ፍቅር የሚያመጣው ጣጣ
(ማቴ. 19፡16-30፤ ሉቃ. 18፡18-30)

17 ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ እንደገና ጕዞ
ጀመረ ፤ በዚህም ጊዜ አንድ ሰው ወደ እርሱ
ሮጦ በፊቱ ተንበረከከና “ደግ መምህር ሆይ!
የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ ይገ
ባኛል?” ሲል ጠየቀው ። 18 ኢየሱስም እንዲህ
ሲል መለሰለት ፥ “ስለምን ደግ ትለኛለህ? ከአ
ንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ደግ የለም ፤
19 ትእዛዞችን ታውቃለህ ፤ እነርሱም ‘አትግ
ደል ፤ አታመንዝር ፤ አትስረቅ ፤ በሐሰት አትመ
ስክር ፤ አታታልል ፤ አባትህንና እናትህን አክ
ብር’ የተባሉት ናቸው ።”
20 ሰውየውም “መምህር ሆይ! እነዚህንማ
ትእዛዞች ከልጅነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ”
አለው ።

21 ኢየሱስም ተመለከተውና ወደደው ፤ እን
ዲህም አለው ፥ “አንድ ነገር ብቻ ቀርቶሃል ፤
ሂድ ፡ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ገንዘብህን ለድኾች
ስጥ ፤ የተከማቸ ሀብት በሰማይ ታገኛለህ ፡ ከዚ
ህም በኋላ ና ፡ ተከተለኝ ።” 22 ሰውየውም
ይህን በሰማ ጊዜ ፊቱ በሐዘን ጠቆረ ፤ ብዙ ንብ
ረትም ስለነበረው እያዘነ ሄደ ።
23 ኢየሱስ ዘወር ብሎ ተመለከተና ደቀ መዛ
ሙርቱን “ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መን
ግሥት መግባት እንዴት አስቸጋሪ ነው?” አላ
ቸው ።
24 ደቀ መዛሙርቱም በቃሉ ተደነቁ ፤ ኢየ
ሱስ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው ፥ “ልጆች
ሆይ! ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት
እንዴት አስቸጋሪ ነው ፤ 25 ሀብታም ሰው ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል
በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍና ይቀላል ።”
26 ደቀ መዛሙርቱም በጣም ተገረሙና
“ታዲያ በዚህ ሁኔታ ማን ሊድን ይችላል” ተባ
ባሉ ።
27 ኢየሱስም ወደ እነርሱ ተመልክቶ “እር
ግጥ ይህ ነገር በሰው ዘንድ አይቻልም ፤ በእግዚ
አብሔር ዘንድ ግን ይቻላል ፤ ለእግዚአብሔር
ሁሉ ይቻለዋል” አላቸው ።
28 ጴጥሮስም “እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከ
ትለንሃል” አለው ።
29 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ ፥ “በእው
ነት እላችኋለሁ ፡ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ብሎ
ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን
ወይም እናትን ወይም አባትን ወይም ልጆችን
ወይም ርስትን የሚተው ሰው ይበልጥ ያገኛል ፤
30 በዚህ ዘመን እንኳ ከስደት ጋር ቤቶችን ፥
ወንድሞችን ፥ እኅቶችን እናቶችን ፥ ልጆችን ፥
ርስትን በመቶ እጥፍ ይቀበላል ፤ በሚመጣውም
ዓለም የዘላለምን ሕይወት ያገኛል ። 31 ይሁን
እንጂ ፊተኞች የሆኑት ብዙዎች ኋለኞች ይሆ
ናሉ ፤ ኋለኞች የሆኑትም ፊተኞች ይሆናሉ ።”

ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት ሦስተኛ ጊዜ ተናገረ
(ማቴ. 20፡17-19፤ ሉቃ. 18፡31-34)

32 ወደ ኢየሩሳሌም በሚወስደው መንገድ
ላሉ ኢየሱስ እፊት እፊታቸው ይሄድ ነበር ፤
ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር ተገረሙ ፤
በስተኋላ የሚከተሉትም ፈርተው ነበር ። እንደ
ገናም ዐሥራሁለቱን ወደ እርሱ አቅርቦ ስለሚ
ደርስበት ነገር እንዲህ ሲል ገለጸላቸው ፤
33 “እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳችን ነው ፤
የሰው ልጅ ለካህናት አለቆችና ለሙሴ ሕግ

10፡4 ፡- ዘፍ. 24፡1-4 ፡ ማቴ. 5፡31 ። 10፡6 ፡- ዘፍ. 1፡27 ፡ 5፡2 ። 10፡7-8 ፡- ዘፍ. 2፡24 ። 10፡11-12 ፡- ማቴ. 5፡32 ፡ 1ቆሮ. 7፡10-11 ። 10፡15 ፡- ማቴ. 18፡3 ። 10፡19 ፡- ዘጽ. 20፡12-16 ፡ ዘፍ. 5፡16-20 ። 10፡31 ፡- ማቴ. 20፡16 ፡ ሉቃ. 13፡30 ።

መምህራን ተላልፎ ይሰጣል ፤ እነርሱም የሞት
ፍርድ ይፈርዱበታል ፤ ለአረማውያን አሳልፈው
ይሰጡታል ፤ 34 አረማውያንም ያፌዙበታል ፤
ይተፉበታል ፤ ይገርፉታል ፤ ይገድሉታልም ፤
ከዚ ግን ከሦስት ቀን በኋላ ይነሣል ።”

የያዕቆብና የዮሐንስ ልመና
(ማቴ. 20፡20-28)

35 የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ ወደ
ኢየሱስ ቀርበው “መምህር ሆይ! የምንለምን
ን እንድታደርግልን እንፈልጋለን” አሉት ።
36 እርሱም “ምን እንዳደርግላቸሁ ትፈልጋ
ለችሁ?” አላቸው ።
37 እነርሱም “በመንግሥትህ ክብር አንዳችን
በቀኝህ ፥ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድ
ልን” አሉት ።
38 ኢየሱስ ግን “የምትለምኑትን አታው
ቁም ፤ እኔ የምጠጣውን (የመከራ) ጽዋ መጠ
ጣት ትችላላችሁን? እኔስ የምጠመቀውን ጥም
ቀት መጠመቅ ትችላላችሁን?” አላቸው ።
39 እነርሱም “አዎ እንችላለን” አሉ ። ኢየ
ሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “በእርግጥ እኔ የምጠ
ጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ ፤ እኔም የምጠመቀ
ውን ጥምቀት ትጠመቃላችሁ ፤ 40 ነገር ግን
በቀኜና በግራዬ መቀመጥን የምፈቅድ እኔ አይ
ደለሁም ፤ ይህ የሚሰጠው ለተዘጋጀላቸው ብቻ
ነው ።”
41 የቀሩት ዐሥሩ ይህን ሰምተው በያዕቆብና
በዮሐንስ ላይ ተቆጡ ። 42 ኢየሱስ ሁሉንም
ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ “የአረማ
ውያን አለቆች የሕዝብ ገዥዎች ተብለው እንደ
ሚጠሩና መሪዎቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥል
ጣን እንዳላቸው ታውቃላችሁ ፤ 43 በእናንተ
ዘንድ ግን እንዲህ መሆን አይገባም ፤ ከመካከላ
ችሁ ትልቅ ሊሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ
መሆን አለበት ፤ 44 እንዲሁም ከመካከላችሁ የበ
ላይ ሊሆን የሚፈልግ የሁሉም አገልጋይ
ሆኑን ። 45 የሰው ልጅ እንኳ ለማገልገልና ሕይ
ወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጣ
እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም ።”

ኢየሱስ የዐይነ ስውሩን የበርጢሜዎስን ዐይን አዳነ
(ማቴ. 20፡29-34፤ ሉቃ. 18፡35-43)

46 ከዚህ በኋላ ወደ ኢያሪኮ ከተማ መጡ ።
ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱና ከብዙ ሕዝብ ጋር
ከኢያሪኮ ከተማ ሲወጣ ፡ ሳለ የጢሜዎስ ልጅ
ዐይነ ስውሩ በርጢሜዎስ ምጽዋት እየለመነ
በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር ። 47 በዚያም የሚ
ያልፈው የናዝሬቱ ኢየሱስ መሆኑን ባወቀ ጊዜ
“የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ! እባክህ ራራ
ልኝ!” እያለ ይጮኽ ጀመር ።
48 ብዙዎቹ “ዝም በል!” ብለው ገሠጹት ፤
እርሱ ግን “የዳዊት ልጅ ሆይ! እባክህ
ማረኝ!” እያለ ይበልጥ ጮኸ ።
49 ኢየሱስም ቆመና “ጥሩት” አለ ፤ እነር
ሱም ዐይነ ስውሩን “በል በርታ ተነሥ ፤ ኢየ
ሱስ ይጠራሃል” አሉት ።
50 እርሱም ሸማውን ጣለና ዘሎ ወደ ኢየሱስ
ሄደ ።
51 ኢየሱስም “ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋ
ለህ?” ሲል ጠየቀው ።
ዐይነ ስውሩም “መምህር ሆይ! እባክህ እን
ዳይ አድርገኝ” አለው ።
52 ኢየሱስም “በል ሂድ እምነትህ አድኖ
ሃል” አለው ።
ሰውየውም ወዲያውኑ ማየት ቻለ ፤ በመንገ
ድም ኢየሱስን ተከትሎ ሄደ ።

ምዕራፍ 11

ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ
(ማቴ. 21፡1-11፤ ሉቃ. 19፡28-40፤ ዮሐ. 12፡12-19)

1 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳ
ሌም በቀረቡ ጊዜ በቤተ ፋጌና በቢታንያ አድር
ገው ወደ ደብረ ዘይት ደረሱ ፤ ከዚያም ኢየሱስ
ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ ሲል ላካ
ቸው ፥ 2 “በፊታችሁ ወጥለው መንደር ቀድማ
ችሁ ሂዱ ፤ እዚያም እንደ ደረሳችሁ ወዲያውኑ
ማንም ሰው ገና ያልተቀመጠበት የአህያ ውር
ንጫ ታስሮ ታገኛላችሁ ፤ ፍቱትና ወዲህ አም
ጡት ። 3 ማንም ሰው ‘ለምን ይህን ታደርጋላ
ችሁ?’ ቢላችሁ ‘ጌታ ስለሚያስፈልገው ነው ፤
ወዲያውኑ መልሶ ይልከዋል’ በሉት ።”
4 እነርሱም ሄደው ውርንጫውን በመንገድ
ዳር በቤት ደጃፍ ታስሮ አገኙትና ፈቱት ።
5 በዚያም ጊዜ እዚያ ቆመው ከነበሩት ሰዎች
አንዳንዶቹ “ውርንጫውን የምትፈቱት ለምን
ድን ነው?” ሲሉ ጠየቁዋቸው ።
6 እነርሱም ኢየሱስ ያላቸውን ነገሩአቸው ፤
ሰዎቹም ተዉአቸው ። 7 ደቀ መዛሙርቱም የአ
ህያውን ውርንጫ ወደ ኢየሱስ አመጡ ፤ ልብሳ
ቸውን በውርንጫው ጀርባ ላይ አድርገው ኢየ
ሱስ ተቀመጠበት ። 8 ብዙ ሰዎች ሸማቸውን
በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር ፤ ሌሎችም ከዱር
የዛፍ ዝንጣፊ እየቈረጡ በመንገድ ላይ ይጐዘ
ጉዙ ነበር ። 9 ከፊት የቀደሙትና ከኋላ የሚከተ
ሉትም ሁሉ “ሆሳዕና! በጌታ ስም የሚመጣ

10፡38 ፡- ሉቃ. 12፡50 ። 10፡42-43 ፡- ሉቃ. 22፡25-26 ። 10፡43-44 ፡- ማቴ. 23፡11 ፡ ማር. 9፡35 ፡ ሉቃ. 22፡26 ። 11፡9 ፡- መዝ. 118፡25-26 ።

የተባረከ ነው ፤ [10]የምትመጣው የአባታችን የዳ
ዊት መንግሥት የተባረከች ናት ፤ ሆሳዕና በአር
ያም!” እያሉ ይጮኹ ነበር ።

[11]ኢየሱስም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ወደ
ቤተ መቅደስ ገባ ፤ በዙሪያውም ያለውን ነገር
ሁሉ ተመለከተ ፥ ቀኑም ስለነበር ከዐ
ሥራ ሁለቱ ጋር ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ቢታ
ንያ ሄደ ።

ኢየሱስ የረገማት የበለስ ዛፍ
(ማቴ. 21፡18-19)

[12]በማግሥቱም ከቢታንያ ሲመለሱ ኢየሱስ
ራበው ። [13]የለመለመች የበለስ ዛፍም በሩቅ
አይቶ ምናልባት ፍሬ ይገኝባት እንደሆነ በማ
ለት ወደ እርስዋ ሄደ ፤ ነገር ግን ወደ እርስዋ
በቀረበ ጊዜ በለስ የሚያፈራበት ወራት ስላልነ
በረ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም ። [14]ስለ
ዚህ ኢየሱስ የበለስዋን ዛፍ “ከእንግዲህ ወዲህ
ማንም ከአንቺ ፍሬ አይብላ” አላት ።

ይሁንም ሲናገር ደቀ መዛሙርቱ ሰሙ ።

ኢየሱስ በቤተ መቅደስ የሚገበያዩትን አስወጣ
(ማቴ. 21፡12-17፤ ሉቃ. 19፡45-48፤
ዮሐ. 2፡13-22)

[15]ወደ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ
ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በውስጡ የሚሸጡት
ንና የሚገዙትን ሰዎች አስወጣ ፤ የገንዘብ ለዋ
ጮችን ጠረጴዛዎችና የርግብ ሻጮችንም ወንበ
ሮች ገለበጠ ፤ [16]ማንም ሰው ምንም ዕቃ ተሸ
ክሞ በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ እንዲተላለፍ
አልፈቀደም ። [17]እንዲህም ሲል አስተማራ
ቸው ፥ “‘ቤቴ ለሕዝብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባ
ላል’ ተብሎ አልተጻፈምን? እናንተ ግን የሌ
ቦች ዋሻ አደረጋችሁት ።”

[18]የካህናት አለቆችና የሙሴ ሕግ መምህራን
ይህን ሲናገር ሰሙት ፤ ሕዝቡም ሁሉ በትምህ
ርቱ ይደነቁ ስለነበር ፈሩት ፤ ስለዚህ እንዴት
አድርገው እንደሚያጠፉት ዘዴ ይፈልጉ ነበር ።
[19]በመሸም ጊዜ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ
ከከተማ ወጡ ።

የበለሲቱ ዛፍ መድረቅ
(ማቴ. 21፡20-22)

[20]በማግሥቱ ማለዳ በመንገድ ሲያልፉ የበለ
ሲቱ ዛፍ ከነሥርዋ ደርቃ አዩአት ። [21]ጴጥሮ
ስም ነገሩ ትዝ ብሎት ኢየሱስን “መምህር
ሆይ! እነሆ የረገምሃት ዛፍ ደርቃለች” አለው ።
[22]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “በእግዚአብ
ሔር እመኑ ፤ [23]በእውነት እላችኋለሁ ፥ ማንም
ሰው በልቡ ሳይጠራጠር የሚፈልገው ነገር እን
ደሚፈጸምለት አምኖ ይህንን ተራራ ‘ከዚህ ተነ
ሥተህ ወደ ባሕር ተወርወር’ ቢል ይሆንለ
ታል ። [24]ስለዚህ በጸሎት ማናቸውንም ነገር
ብትለምኑ እንደሚፈጸምላችሁ እመኑ ፤ የምትለ
ምኑትም ሁሉ ይሰጣችኋል ። [25]በሰማይ ያለው
አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ
እናንተም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ በሰው
ላይ የያዛችሁትን ቂም ተዉ ። [26]ነገር ግን እና
ንተ የሌሎችን በደል ይቅር ባትሉ ፤ በሰማይ
ያለው አባታችሁ የእናንተንም ኃጢአት ይቅር
አይልላችሁም ።”]7*

ኢየሱስ በምን ሥልጣን
እንደሚሠራ የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 21፡23-27፤ ሉቃ. 20፡1-8)

[27]እንደገናም ወደ ኢየሩሳሌም መጡ ፤ ኢየ
ሱስም በቤተ መቅደስ ሲዘዋወር ሳለ የካህናት
አለቆች ፥ የሙሴ ሕግ መምህራንና ሽማግሌዎች
ወደ እርሱ መጡና ፤ [28]“እነዚህን ነገሮች የም
ታደርገው በምን ሥልጣን ነው? ወይስ እነዚ
ህን ነገሮች እንድታደርግ ሥልጣን የሰጠህ ማን
ነው?” ሲሉ ጠየቁት ።

[29]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፥ “እኔም
አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ ፤ እናንተ መልስ
ከሰጣችሁኝ እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥል
ጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ ። [30]የዮሐንስ
ጥምቀት ከእግዚአብሔር ነበረ ወይስ ከሰው?
እስቲ መልሱልኝ” አላቸው ።

[31]እነርሱም “እንግዲህ ምን እንበል?” በማ
ለት እርስ በርሳቸው ተመካከሩ ፤ “‘ከእግዚአብ
ሔር ነው’ብንል ፥ ‘ታዲያ ለምን አላመናችሁብ
ትም?’ ይለናል ፤ [32]‘ከሰው ነው’ብንልስ?”
ይህንን እንዳይሉ ሕዝቡ ሁሉ ዮሐንስን “በእር
ግጥ ነቢይ ነው” ይሉ ስለነበር ፈሩ ። [33]ስለዚህ
“እኛ እናውቅም” ሲሉ መለሱለት ።

ኢየሱስም “እንግዲያውስ እኔም በምን ሥል
ጣን እነዚህን ነገሮች እንደማደርግ አልነግራች
ሁም” አላቸው ።

ምዕራፍ 12

የወይን አትክልት ገበሬዎች ምሳሌ
(ማቴ. 21፡33-46፤ ሉቃ. 20፡9-19)

[1]ቀጥሎም ኢየሱስ ይህን በምሳሌ እንዲህ
ሲል ይነግራቸው ጀመር ፤ “አንድ ሰው የወይን
አትክልት ተከለ ፤ ዙሪያውንም ዐጠረ ፤ የወይን
መጭመቂያ የሚሆን ጉድጓድ ቈፍሮ አበጀ ፤
ለወይኑ ጥበቃ የሚያገለግል ከፍተኛ የማንብ
ማማ ሠራ ፤ ከዚህም በኋላ የአትክልቱን ቦታ
ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሩቅ አገር ሄደ ።
[2]ፍሬው በደረሰ ጊዜ ከወይኑ ፍሬ እንዲያመጣ
ለት አገልጋዩን ወደ ገበሬዎቹ ላከ ። [3]ገበሬዎቹ
ግን አገልጋዩን ይዘው ክደበደቡት በኋላ ባዶ
እጁን ሰደዱት ። [4]እንደገና ባለቤቱ ሌላ አገል
ጋይ ላከ ፤ ገበሬዎቹ ክወይንም በድንጋይ ፈንክ
ተውና አዋርደው ሰደዱት ። [5]ቀጥሎም ሌላውን
ቢልክ ገደሉት ፤ እንዲሁም ብዙዎችን ቢልክ
እንዳንዶቹን ደበደቡ ፤ ሌሎቹንም ገደሉ ።
[6]እሁን ማድረግ የቀረው የሚወደውን ልጁን
መላክ ብቻ ነበር ፤ ስለዚህ ‘ልጄንስ ያከብሩት
ይሆናል’ ብሎ በማሰብ በመጨረሻ አንድ ልጁን
ላከ ። [7]ነገር ግን ገበሬዎቹ እርስ በርሳቸው
‘ይህማ ወራሹ ነው ፤ ኑ እንግደለው ፤ርስቱም
ለእኛ ይሆናል’ ተባባሉ ። [8]ስለዚህ ልጁን
ይዘው ገደሉት ፤ ከወይኑ አትክልትም ውጪ
ጣሉት ።

[9]“እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን
ያደርጋል! ባለቤቱ ራሱ ይመጣል ፤ ገበሬዎቹ
ንም ይገድላል ፤ የወይኑንም አትክልት ለሌሎች
ይሰጣል ። [10]ለመሆኑ እንዲህ የሚለውን ጽሑፍ
አላነበባችሁምን?

‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ
የማእዘን ራስ ሆነ ፤
[11]ይህም የእግዚአብሔር ሥራ ነው ፤
ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው ።’”

[12]የአይሁድ አለቆች ኢየሱስ የተናገረው
ምሳሌ እነርሱን የሚመለከት መሆኑን ስለተገነ
ዘቡ ሊይዙት ፈልገው ነበር ፤ ነገር ግን ሕዝ
ቡን ፈርተው ትተውት ሄዱ ።

ግብር ስለመክፈል የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. 22፡15-22፤ ሉቃ. 20፡20-26)

[13]ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑ አንዳ
ንድ ሰዎች ኢየሱስን በንግግሩ ለማጥመድ ወደ
እርሱ ተላኩ ። [14]ቀርበውም እንዲህ አሉት ፥
“መምህር ሆይ! አንተ እውነተኛ መሆንህን
ስናውቃለን ፤ ሰውንም በመፍራትና በይሉኝታ
የማታደርገው ነገር የለም ፤ የእግዚአብሔርንም
መንገድ በእውነት ታስተምራለህ ፤ ታዲያ
ለሮም ቄሳር ግብር መክፈል ተፈቅዶአልን
ወይስ አልተፈቀደም? እንገብር? ወይስ አንገ
ብር?”

[15]ኢየሱስም ተንኰላቸውን ዐውቆ “ለምን
ልታጠምዱኝ ትፈልጋላችሁ? እስቲ ገንዘቡን
አምጡና አሳዩኝ” አላቸው ።

[16]እነርሱም ገንዘቡን አመጡለት ፤ እርሱም
“ፀዘሂ ገንዘብ ላይ ያለው መልክና የተጻፈው
ስም የማን ነው?” ሲል ጠየቃቸው ።

እነርሱም “የቄሳር ነው” አሉት ።

[17]ኢየሱስም “እንግዲያውስ የቄሳርን ለቄ
ሳር ፤ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ”
ሲል መለሰላቸው ። እነርሱም በመልሱ ተደነቁ ።

ስለ ሙታን መነሣት
(ማቴ. 22፡23-33፤ ሉቃ. 20፡27-40)

[18]“የሙታን መነሣት የለም” የሚሉ ሰዱቃ
ውያን ወደ ኢየሱስ መጡ ፤ እንዲህም ሲሉ ጠየ
ቁት ፤ [19]“መምህር ሆይ! ሙሴ አንድ ሕግ
ጽፎ ሰጥቶናል ፤ ይኸውም ‘አንድ ሰው ልጅ
ሳይወልድ ከሚስቱ በሞት ቢለይ ወንድሙ ሴት
ዮዋን አግብቶ ለሚቹ ዘር ይተካለት’ የሚል
ነው ። [20]ታዲያ ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ ፤
የሁሉም ታላቅ ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ
ሞተ ፤ [21]ሁለተኛውም ወንድሙ ያችኑ ሴት
አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ ፤ ሦስተኛውም
እንዲሁ ሆነ ፤ [22]በዚህ ሁኔታ ሰባቱም አግብተ
ዋት ዘር ሳይተኩ ሞቱ ፤ ከሁሉም በኋላ ደግሞ
ሴትዮዋ ሞተች ። [23]ሰባቱም ወንድማማቾች በየ
ተራ አግብተዋታልና እንግዲህ ሙታን በሚነሡ
በት ጊዜ ለየትኛው ሚስት ትሆናለች?”

[24]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
“እናንተ እንዲህ የምትሳሳቱት ቅዱሳት መጻሕ
ፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ባለማወቃችሁ
አይደለምን? [25]ሙታንስ ሲነሡ በሰማይ እንዳ
ሉት መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም ፥ አይ
ጋቡም ። [26]ስለ ሙታን መነሣት የሆነ እንደሆነ
ግን እግዚአብሔር ሙሴን በቍጥቋጦው እሳት
ውስጥ ምን እንደተናገረው ከሙሴ መጽሐፍ
አላነበባችሁምን? ይኸውም ‘እኔ የአብርሃም
አምላክ ፥ የይሥሐቅ አምላክ ፥ የያዕቆብ አምላክ
ነኝ’ ያለው ነው ። [27]ስለዚህ እግዚአብሔር የሕ
ያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይ
ደለም ፤ እናንተ ግን እጅግ ትሳሳታላችሁ ።”

ከሁሉ የሚበልጥ ትእዛዝ
(ማቴ. 22፡34-40፤ ሉቃ. 10፡25-28)

[28]ከሙሴ ሕግ መምህራን አንዱ ክርክራቸ
ውን ይሰማ ነበር ፤ ኢየሱስ በመልካም ሁኔታ
እንደመለሰላቸው የሙሴ ሕግ መምህሩ አስተ
ዋለ ፤ ወደ ኢየሱስ ቀርቦም “ከሁሉ የሚበልጥ
ትእዛዝ የትኛው ነው?” ሲል ጠየቀው ።

[29]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ፥
“ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ‘እስራኤል ሆይ!
ስማ ፤ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ አምላክ
ነው ፤ [30]እንተም እግዚአብሔር አምላክህን በፍ
ጹም ልብህ ፥ በፍጹም ነፍስህ ፥ በፍጹም አሳ
ብህ ፥ በፍጹም ኀይልህ ውደድ’ የሚል ነው ።
[31]ይህንንም የሚመስል ሁለተኛው ትእዛዝ
‘ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ’

7* 11፡26 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 26 ይጨምራሉ ፤ ቃሉም በማቴ. 6፡15 ያለውን ይመስላል ።

11፡17 ፡- ኢሳ. 56፡7 ፡ ኤር. 7፡11 ። 11፡23 ፡- ማቴ. 17፡20 ፡ 1ቆሮ. 13፡2 ። 11፡25-26 ፡- ማቴ. 6፡14-15 ።
12፡1 ፡- ኢሳ. 5፡1-2 ።

12፡10-11 ፡- መዝ. 118፡22-23 ። 12፡18 ፡- ሐሥ. 23፡8 ። 12፡19 ፡- ዘፍ. 25፡5 ። 12፡26 ፡- ዘጽ. 3፡6 ።
12፡28-34 ፡- ሉቃ. 10፡25-28 ። 12፡29-30 ፡- ዘዳ. 6፡4-5 ። 12፡31 ፡- ዘሌ. 19፡18 ።

የሚል ነው ። ከነዚህም ከሁለቱ የሚበልጥ ሌላ
ትእዛዝ የለም ።"
32 የሕግ መምህሩም ኢየሱስን እንዲህ
አለው ፥ "መምህር ሆይ! 'እግዚአብሔር አንድ
ነው ፤ ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ የለም'
ብለህ የተናገርከው ልክ ነው ፤ 33 ስለዚህ ሰው
በፍጹም ልቡ ፥ [በፍጹም ነፍሱ ፥] በፍጹም
አእምሮ ፥ በፍጹም ኀይሉ እግዚአብሔርን መው
ደድ ይገባዋል ፤ እንዲሁም ሰውን ሁሉ እንደ
ራሱ አድርጎ መውደድ ይገባዋል ፤ የሚቃጠል
መሥዋዕትና ሌላም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር
ከማቅረብ ይልቅ እነዚህን ሁለቱን ትእዛዛት
መጠበቅ ይበልጣል ።"
34 ኢየሱስም የሕግ መምህሩ በጥበብና በማስ
ተዋል እንደመለሰ አይቶ "አንተስ ከእግዚአብ
ሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም" አለው ።
ከዚህ በኋላ ለኢየሱስ ጥያቄ ሊያቀርብለት
የደፈረ ማንም የለም ።

ኢየሱስ ያቀረበው ጥያቄ
(ማቴ. 22፡41-46፤ ሉቃ. 20፡41-46)

35 ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲያስተምር እን
ዲህ ብሎ ጠየቀ ፥ "የሙሴ ሕግ መምህራን
'መሲሕ የዳዊት ልጅ ነው' ስለምን ይላሉ?
36 ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ፥
'እግዚአብሔር ለጌታዬ (ለመሲሑ) ፥
ጠላቶችህን በሥልጣንህ ሥር
እስካደርግልህ ድረስ
በቀኜ ተቀመጥ' ብሎታል ።
37 ዳዊት ራሱ 'ጌታ' ብሎ ከጠራው ፥ ታዲያ
መሲሕ ለዳዊት እንዴት ልጁ ይሆናል?" ብዙ
ሰዎችም በደስታ ይሰሙት ነበር ።

ኢየሱስ "ከሙሴ ሕግ
መምህራን ተጠንቀቁ" አለ
(ማቴ. 23፡1-36፤ ሉቃ. 20፡45-47)

38 ኢየሱስ ሲያስተምር እንዲህ አለ ፥ "ረዣ
ዥም ልብስ ለብሰው ወዲያና ወዲህ መዞርን ፥
በገበያም የክብር ሰላምታ መቀበልን ከሚወዱ
ከሙሴ ሕግ መምህራን ተጠንቀቁ ፤ 39 እንርሱ
በምኩራብ የከበሬታ ወንበር ፥ በግብዣም የክ
ብር ስፍራን ለማግኘት ይሽቀዳደማሉ ። 40 ለታ
ይታ በሚያቀርቡት ረዥም ጸሎት እያመካኙ
የመበለቶችን ቤት ይበዘብዛሉ ፤ ስለዚህ እነርሱ
የባሰ ፍርድ ይደርስባቸዋል ።"

የመበለቲቱ ስጦታ
(ሉቃ. 21፡1-4)

41 ኢየሱስ በምጽዋት መቀበያ ሣጥን ፊት
ለፊት ተቀምጦ ሳለ ሕዝቡ በሣጥኑ ውስጥ ገን
ዘብ ሲጨምሩ ያይ ነበር ፤ ሀብታሞች ብዙ ገን
ዘብ ይጨምሩ ነበር ፤ 42 አንዲት ድኻ መበለ
ትም መጥታ ሁለት ሳንቲም የሚያህል የናስ ገን
ዘብ ሰጠች ። 43 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
ጠርቶ እንዲህ አላቸው ፥ "በእውነት እላችኋ
ለሁ ፥ በሣጥኑ ውስጥ ገንዘብ ከጨመሩት ሰዎች
ሁሉ አብልጣ የሰጠች ይህች ድኻ መበለት
ናት ። 44 ምክንያቱም ሌሎቹ ሁሉ የሰጡት ካላ
ቸው ሀብት የተረፈቸውን ነው ፤ እርስዋ ግን
ድኻ ሆና ሳለች ምንም ሳታስቀር ያላትን ሁሉ
ሰጠች ።"

ምዕራፍ 13

ኢየሱስ ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስ ተነበየ
(ማቴ. 24፡1-2፤ ሉቃ. 21፡5-6)

1 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ሲወጣ ሳለ ከደቀ
መዛሙርቱ አንዱ "መምህር ሆይ! ተመል
ከት ፥ እነዚህ ድንጋዮችና እነዚህ ሕንጻዎች
እንዴት ያምራሉ!" አለው ። 2 ኢየሱስም እን
ዲህ ሲል መለሰለት ፥ "እነዚህን ትልልቅ ሕንጻ
ዎች ታያለህን? እነዚህ ድንጋዮች ሁሉ ይፈር
ሳሉ ፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮ የሚቀር
የለም ።"

ከጌታ መምጣት በፊት ስደትና መከራ ይሆናል
(ማቴ. 24፡3-14፤ ሉቃ. 21፡7-19)

3 ኢየሱስ በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት በደብረ
ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ ጴጥሮስ ፥ ያዕ
ቆብ ፥ ዮሐንስና ፥ እንድርያስ ለብቻቸው ወደ
እርሱ ቀርበው ፥ 4 "ይህ ነገር የሚሆነው መቼ
ነው? ይህስ ሁሉ ሲፈጸም ሲቃረብ ምልክቱ
ምንድን ነው? እስቲ ንገረን" ሲሉ ጠየቁት ።
5 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፥
"ማንም እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ ፤ 6 ብዙ
ዎች 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ በስሜ ይመ
ጣሉ ፤ ብዙ ሰዎችንም ያሳስታሉ ፤ 7 በአቅራቢያ
ችሁ ጦርነት ሲደረግና በሩቅም የጦርነትን ወሬ
ስትሰሙ አትደንግጡ ፤ ይህ ሁሉ ሊሆን ግድ
ነው ፤ ይሁን እንጂ መጨረሻው ገና ነው ።
8 ሕዝብ በሕዝብ ላይ ፥ መንግሥትም በመንግ
ሥት ላይ ጦርነት ያነሣል ፤ በየስፍራው የም
ድር መናወጥና ረሀብ ይሆናል ፤ ይህ ሁሉ እንደ
ምጥ ጣር ያለ የጭንቅ መጀመሪያ ነው ።
9 "እናንተም ራሳችሁ ተጠንቀቁ ፤ ምክንያ
ቱም ሰዎች ለፍርድ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ፤
በየምኩራቡም ይገርፉአችኋል ፤ ምስክር እንድ
ትሆኑኝ በእኔ ምክንያት በገዥዎችና በነገሥ
ታት ፊት ለፍርድ ትቆማላችሁ ። 10 ይህ ሁሉ
ከመሆኑ በፊት ግን የምሥራቹ ቃል ለዓለም
ሕዝብ ሁሉ መጀረስ ይገባዋል ። 11 ሰዎች

12፡32 ፡- ዘዳ. 4፡35 ። 12፡33 ፡- ሆሴዕ 6፡6 ። 12፡36 ፡- መዝ. 110፡1 ። 13፡9-11 ፡- ማቴ. 10፡17-20 ፡ ሉቃ. 12፡11-12 ።

ይዘው ወደ ፍርድ ሲያቀርቡአችሁ ፥ ምን እንና
ገር ይሆን?' በማለት አስቀድማችሁ አትጨ
ነቁ ፤ በዚያን ሰዓት የሚሰጣችሁን ቃል ተና
ገሩ ፤ ምክንያቱም የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ
ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁም ። 12 ወንድም
ወንድሙን ፥ አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ
ይሰጣል ፤ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ በጠላት
ነት ይነሣሉ ፤ ይገድሉአቸዋልም ። 13 በእኔ ምክ
ንያት በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላ
ችሁ ፤ እስከ መጨረሻ በትዕግሥት የሚጸና ግን
ይድናል ።

በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚደርሰው
አሠቃቂ መከራ
(ማቴ. 24፡15-28፤ ሉቃ. 21፡20-24)

14 "ደግሞ [በነቢዩ ዳንኤል እንደተነገረ]
ውንጉፕት በሚይገባው ስፍራ የሚያረክሰውን አስ
ጸያፊ ነገር ታያላችሁ ፤ ይህንንም አንባቢው ያስ
ተውል ፤ በዚያን ጊዜ በይሁዳ አገር ያሉ ወደ
ተራራዎች ይሽሹ ። 15 በቤት ጣራ ላይ ያለ
ወደ ቤቱ ወርዶ ከቤቱ አንዳች ነገር ለመውሰድ
ጊዜ አያጥፋ ፤ 16 በእርሻም ቦታ ያለ ልብሱን
ለመውሰድ ወደ ኋላው አይመለስ ። 17 በዚያን
ጊዜ ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ እመጫቶች
ምኑ ላቸው ። 18 ይህ ሁሉ በክረምት ጊዜ እንዳይ
ሆን ጸልዩ ። 19 በዚያን ወራት እግዚአብሔር
ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን
ድረስ ታይቶ የማይታወቅ መከራና ጭንቅ ይሆ
ናል ፤ ወደ ፊትም እሱን የሚመስል መከራና
ጭንቅ ከቶ አይደርስም ። 20 እግዚአብሔር እነ
ዚያን ቀኖች ባያሳጥርማ ኖሮ ማንም መዳን ባል
ቻለም ነበር ፤ ነገር ግን ለተመረጡት ሰዎች
ሲባል እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ ።
21 "እንግዲህ ማንም ቢሆን 'መሲሕ ይኸው
እዚህ ነው' ወይም 'ያው እዚያ ነው' ቢላችሁ
አትመኑ ። 22 ምክንያቱም ሐሰተኞች መሲሖ
ችና ሐሰተኞች ነቢያት ይመጣሉ ፤ እንርሱ
ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ለማሳሳት ተአ
ምራትና ድንቅ ነገርን ያደርጋሉ ። 23 ሁሉን
አገር አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁና እንግዲህ ተጠ
ንቀቁ ።

የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት
(ማቴ. 24፡29-31፤ ሉቃ. 21፡25-28)

24 "በዚያን ጊዜ ከዚያ ሁሉ መከራ በኋላ
ፀሐይ ትጨልማለች ፤ ጨረቃም ብርሃንዋን አታ
ሳይም ፤ 25 ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ ፤
በሰማይ ያሉ ኀይሎችም ይናወጣሉ ። 26 ከዚ
ያም በኋላ የሰው ልጅ በታላቅ ኀይልና ክብር
በደመና ሲመጣ ይታያል ፥ 27 መላእክቱንም
ይልካል ፤ እንርሱ በአራቱም አቅጣጫ ሄደው
ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ የሚገኙትን
ለእርሱ የተመረጡትን ሰዎች ይሰበስባሉ ።

የጊዜውን መድረስ የምታመለክት የበለስ ዛፍ
(ማቴ. 24፡32-35፤ ሉቃ. 21፡29-33)

28 "የበለስ ዛፍ ምሳሌ ትምህርት ይሁና
ችሁ ፤ ቅርንጫፎችዋ ሲያቈጠቍጡና ቅጠሎች
ዋም ሲለመልሙ ያን ጊዜ ጸደይ እንደቀረበ
ታውቃላችሁ ። 29 እንዲሁም እናንተ ይህ ሁሉ
መሆኑን ስታዩ የሰው ልጅ የሚመጣበት ጊዜ
መቅረቡንና በበር መቆሙን ዕወቁ ፤ 30 በእው
ነት እላችኋለሁ ፥ ይህ ትውልድ ከማለፉ በፊት
ይህ ሁሉ ይፈጸማል ። 31 ሰማይና ምድር ያል
ፋሉ ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ።

የመጨረሻይቱን ቀንና ሰዓት ማንም አያውቅም
(ማቴ. 24፡36-44)

32 "ነገር ግን ስለዚያች ቀንና ስለዚያች
ሰዓት ከአብ በቀር ማንም የሚያውቅ የለም ፤
የሰማይ መላእክትም አያውቁም ፤ ወልድም አያ
ውቅም ። 33 ጊዜው መቼ እንደሚሆን አታውቁ
ምና ተጠንቀቁ ፥ ትጉ ። 34 ይህም ፥ ቤቱን ትቶ
ወደ ሩቅ አገር የሄደውን ሰው ይመስላል ፤ እር
ሱም እያንዳንዱን አገልጋይ በልዩ ልዩ የሥራ
ኀላፊነት ላይ መደበ ፤ ዘበኛውንም ተግቶ እንዲ
ጠብቅ አዘዘው ። 35 ስለዚህ የቤቱ ጌታ የሚመ
ጣበትን ጊዜ አታውቁምና ተጠንቀቁ ፤ ምናልባ
ትም ወደ ማታ ወይም በእኩሌ ሌሊት ወይም
ዶሮ ሲጮኽ ፥ ወይም ጠዋት በማለዳ ይመጣ
ይሆናል ፤ 36 በድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳ
ያገኛችሁ ትጉ ።
37 "ስለናንተ እንደነገርኋችሁ ለሌሎችም
ሁሉ ትጉ እላለሁ ።"

ምዕራፍ 14

በክርስቶስ ላይ የተደረገ ሴራ
(ማቴ. 26፡1-5፤ ሉቃ. 22፡1-2፤ ዮሐ. 11፡45-53)

1 የአይሁዳውያን የፋሲካና የቂጣ በዓል ሊከ
በር ሁለት ቀን ቀርቶት ነበር ፤ የካህናት አለቆ
ችና ሕግ ዐዋቂዎች ኢየሱስን በተንኮል ይዘው
የሚገድሉበትን ዘዴ ይፈልጉ ነበር ። 2 ነገር ግን
ሕዝቡ ሁከት ያነሣሣል በማለት "በበዓል ቀን
ይህን አናደርገውም" አሉ ።

13፡13 ፡- ማቴ. 10፡22 ። 13፡14 ፡- ዳን. 9፡27 ፤ 11፡31 ፤ 12፡11 ። 13፡15-16 ፡- ሉቃ. 17፡31 ። 13፡19 ፡- ዳን. 12፡1 ፤ ራእ. 7፡14 ። 13፡24 ፡- ኢሳ. 13፡10 ፤ ሕዝ. 32፡7 ፤ ኢዩ. 2፡10 ፤ 31 ፤ 3፡15 ፤ ራእ. 6፡12 ። 13፡25 ፡- ኢሳ. 34፡4 ፤ ኢዩ. 2፡10 ፤ ራእ. 6፡13 ። 13፡26 ፡- ዳን. 7፡13 ፤ ራእ. 1፡7 ። 13፡32 ፡- ማቴ. 24፡36 ። 13፡34 ፡- ሉቃ. 12፡36-38 ። 14፡1 ፡- ዘጸ. 12፡1-27 ።

ኢየሱስን ሽቶ የቀባች ሴት
(ማቴ. 26፡6-13፤ ዮሐ. 12፡1-8)

3 ኢየሱስ በቢታንያ ለምጻም በነበረው በስም ዖን ቤት ነበር ። በገበታም ቀርቦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነና የከበረ የናርዶስ ሽቶ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ መጣች ፤ ብልቃጡን ሰብራ ሽቶውን በኢየሱስ ራስ ላይ አፈሰሰችው ። 4 እዚያ ከነበሩት አንዳን ዶቹ በድርጊቱ ተቁጥተው “ይህ ሽቶ በከንቱ መባከኑ ለምንድን ነው? 5 ይህ ሽቶ ከሦስት መቶ ብር በላይ ተሸጦ ገንዘቡ ለድኾች ሊሰጥ ይቻል ነበር እኮ” ተባባሉ ፤ ሴቲቱንም ነቀፉ አት ።

6 ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ ፡ “ተዉአት ፡ ስለ ምን ታስጨንቋአታላችሁ? እርስዋ ለእኔ መል ካም ነገር አድርጋለች ፤ 7 ድኾች ሁልጊዜ ከእና ንተ ጋር ስለሆኑ በፈለጋችሁ ጊዜ ልትረዱአ ቸው ትችላላችሁ ፤ እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እዚህ አልገኝም ፤ 8 ይህች ሴት የተቻላትን አድ ርጋለች ፤ ሥጋዬም ከመቀበሩ በፊት አስቀድማ በሽቶ ቀባችው ። 9 በእውነት እላችኋለሁ ፡ በዓ ለም ሁሉ ይህ ወንጌል በሚሰበክበት በማናቸ ውም ስፍራ ይህ እርስዋ ያደረገችው ለመታሰ ቢያ ይነገርላታል ።”

ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ
(ማቴ. 26፡14-16፡ ሉቃ. 22፡3-6)

10 ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ፡ አስቆሮታዊው ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ወደ ካህ ናት አለቆች ሄደ ። 11 እነርሱም ይህንን ባወቁ ጊዜ ደስ አላቸው ፤ ገንዘብም ሊሰጡት ቃል ገቡለት ። እርሱም ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ምቹ ጊዜ ይፈልግ ነበር ።

ኢየሱስ የፋሲካን ራት ከሐዋርያቱ ጋር በላ
(ማቴ. 26፡17-25፡ ሉቃ. 22፡7-14፡21-23፡ ዮሐ. 13፡21-30)

12 የፋሲካውን በግ በሚያርዱበት በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየ ሱስ ቀርበው “የፋሲካን ራት ለመብላት ወዴት ሄደን እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?” ሲሉ ጠየ ቁት ።

13 እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን እን ዲህ ሲል ላካቸው ፡ “ወደ ከተማ ሂዱ ፤ እዚ ያም የውሃ እንሥራ የተሸከመ ሰው ታገኛላ ችሁ ፤ እርሱን ተከተሉት ፤ 14 ወደሚገባበትም ቤት ሂዱና የቤቱን ጌታ ‘መምህር ፡ ከደቀ መዛ ሙርቴ ጋር የፋሲካን ራት የምበላበት ቤት የት ነው?’ ይላል በሉት ። 15 እርሱም በሰገነት ላይ ያለውን የተዘጋጀውንና የተነጠፈውን ትልቅ አዳራሽ ያሳያችኋል ፤ በዚያ አዘጋጁልን ።”

16 ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከዚያ ወጥተው ወደ ከተማው ሄዱ ፤ ልክ ኢየሱስ እንዳላቸውም አገኙ ፤ የፋሲካንም ራት በዚያ አዘጋጁ ።

17 በመሸ ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር መጣ ፤ 18 በገበታ ቀርበው ሲበሉ ኢየሱስ “በእ ውነት እላችኋለሁ ፡ አሁን ከእኔ ጋር ራት በመ ብላት ላይ የሚገኝኝ ከእናንተ አንዱ ፡ አሳልፎ ይሰጠኛል” አለ ።

19 እነርሱም በዚህ ነገር አዝነው “እኔ እሆ ንን?” እያሉ ተራ በተራ ጠየቁት ።

20 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፡ “ያ ሰው አሁን ከእኔ ጋር በዚህ ሳሕን ውስጥ ወጥ የሚያ ጠቅሰውና ከዐሥራ ሁለታችሁ አንዱ የሆነው ነው ፤ 21 የሰው ልጅ አስቀድሞ በተጻፈው መል ረት ወደ ሞት መሄዱ አይቀርም ፤ ነገር ግን የሰ ውን ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ለዚያ ሰው ወዮ ለት ፤ ያ ሰውስ ቀድሞውኑ ባይወለድ ይሻለው ነበር ።”

የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት (የጌታ ራት)
(ማቴ. 26፡26-30፡ ሉቃ. 22፡14-20፡ 1 ቆሮ. 11፡23-25)

22 እነርሱ በመብላት ላይ ሳሉ ኢየሱስ ኅብ ስት አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ “እንካችሁ ፡ ይህ ሥጋዬ ነው” ብሎ ሰጣቸው ።

23 ጽዋውንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደ ረገ በኋላ ሰጣቸው ፤ ሁሉም ከጽዋው ጠጡ ። 24 እንዲህም አላቸው ፡ “ይህ ስለ ብዙዎች የሚ ፈስ የቃል ኪዳን ደሜ ነው ፤ 25 በእውነት እላችኋለሁ ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አዲ ሱን እስከጠጣ ድረስ ከዚህ ወይን ፍሬ ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም ።”

26 ከዚያም በኋላ መዝሙር ዘምረው ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ወጡ ።

ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ አስቀድሞ ተናገረ
(ማቴ. 26፡31-35፡ ሉቃ. 22፡31-34፡ ዮሐ. 13፡36-38)

27 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ ፡ “‘እረኛውን እመታለሁ ፤ በጎቹም ይበተናሉ’ ተብሎ ተጽፎአልና ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ ፤ ትታችሁኝም ትሸሻላችሁ ፤ 28 ነገር ግን ከሞት ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ ቀድሜአችሁ እሄዳ ለሁ ።”

29 ጴጥሮስ “ሌሎቹ ሁሉ እንኳ ቢክዱህ እኔ ከቶ አልክድህም” አለው ።

14፡3 ፡- ሉቃ. 7፡37-38 ። 14፡7 ፡- ዘዳ. 15፡11 ። 14፡18 ፡- መዝ. 41፡9 ። 14፡24 ፡- ዘጽ. 24፡8 ፡ ኤር. 31፡31-34 ። 14፡27 ፡- ዘካ. 13፡7 ። 14፡28 ፡- ማቴ. 28፡16 ።

30 ኢየሱስም “በእውነት እልሃለሁ ፡ ዛሬ በዚህች ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ከመጮኹ በፊት አንተ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ” አለው ።

31 ጴጥሮስ ግን “መሞት እንኳ ቢያስፈልግ ከእናንተ ጋር እሞታለሁ እንጂ ከቶ አልክድህም” ሲያለ አጠንክሮ ተናገረ ።

የቀሩትም ደቀ መዛሙርት እንዲሁ ይሉ ነበር ።

ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ጸለየ
(ማቴ. 26፡36-46፡ ሉቃ. 22፡39-46)

32 ከዚህም በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል የአት ክልት ስፍራ ሄዱ ፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን “እኔ እዚያ ስጸልይ እናንተ እዚህ ቆዩ” አላ ቸው ። 33 ጴጥሮስንና ያዕቆብን የሐንስንም አስ ከትሎ ሄደ ፤ እዚያም ማዘንና መጨነቅ ጀመረ ። 34 እንዲህም አላቸው ፡ “ነፍሴ በታ ላቅ ሐዘን ለሞት ደርሳለች ፤ እዚህ ቆዩ ፤ ተግታ ችሁም ጠብቁ ።” 35 ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ብሎ ሄደ ፤ ከመሬትም ላይ በግንባሩ ተደፍቶ ፡ የሚ ቻል ቢሆን ያች የመከራ ሰዓት እንድታልፍለት ጸለየ ። 36 እንዲህም አለ ፡ “አባት ሆይ! ሁሉ ነገር ይቻልሃል ፤ ይህን የመከራ ጽዋ ከእኔ አር ቅልኝ ፤ ነገር ግን እንደ አንተ ፈቃድ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ አይሁን ።”

37 ወደ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ተመልሶ በመጣ ጊዜ ተኝተው አገኛቸው ፤ ስለዚህ ጴጥ ሮስን “ስምዖን ሆይ! ተኝተሃልን? አንዳት ዕዓት እንኳ ልትነቃ አልቻልክምን?” አለው ። 38 ቀጥሎ ለሁሉም “ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትግታችሁ ጸልዩ ፤ የሰው መንፈስ ዝግጁ ነው ፤ ሥጋው ግን ደካማ ነው” አለ ።

39 እንደገናም ሄዶ ያንኑ የፈተኛውን ቃል በመናገር ጸለየ ። 40 ደግሞም ተመልሶ በመጣ ጊዜ ዐይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ስለነበ ችኝተው አገኛቸው ፤ የሚመልሱለትንም አያው ቁም ነበር ።

41 ሦስተኛም ጊዜ ወደ እነርሱ መጥቶ እን ዲህ አላቸው ፡ “አሁንም ገና ተኝታችኋልን? አሁንም ዕረፍት ታደርጋላችሁን? እንግዲህስ በቃ ፤ ሰዓቱ ደርሶአል ፤ እነሆ የሰው ልጅ በኃ ጢአተኞች እጅ ተላልፎ ይሰጣል ። 42 በሉ ተነሡ ፤ እንሂድ ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝ ይኸው ቀርቦአል ።”

ኢየሱስ በጠላቶቹ እጅ ተያዘ
(ማቴ. 26፡47-56፡ ሉቃ. 22፡47-53፡ ዮሐ. 18፡3-12)

43 ወዲያውም ኢየሱስ ይህን ሲናገር ሳለ ከዐ ሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ መጣ ፤ ከእር ሱም ጋር ሰይፍና ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎች ነበሩ ፤ እነርሱ ከካህናት አለቆችና ከሙሴ ሕግ መምህራን ከሽማግሌዎችም ዘንድ የተላኩ ነበሩ ። 44 አሳልፎ የሚሰጠውም ይሁዳ “እና ንተ የምትይዙት እኔ ሰላምታ ስጥቼ የምስመ ውን ነው ፤ እርሱን በጥንቃቄ ይዛችሁ ውሰ ዱት” ሲል ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር ።

45 ይሁዳ ወዲያውኑ መጥቶ ወደ ኢየሱስ ቀረበና “መምህር ሆይ!” ብሎ ሳመው ። 46 ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ኢየሱስን ያዙት ። 47 እዚያ ቆመው ከነበሩት ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ ቈረጠ ። 48 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፡ “ሰይፍና ዱላ ይዛችሁ የመጣችሁት እኔን እንደ ወንበዴ ለመያዝ ነውን? 49 በየቀኑ በቤተ መቅ ደስ እያስተማርሁ ስኖር አልያዛችሁኝም ነበር ፤ ነገር ግን ይህ የሆነው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈ ጸም ነው ።”

50 ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ ትተውት ሸሹ ።

51 ነጠላ ብቻ የለበሰ አንድ ወጣት ግን ኢየ ሱስን ይከተል ነበር ፤ ሰዎቹም በያዙት ጊዜ ፡ 52 ነጠላውን ጥሎ ራቁቱን ሸሽቶ አመለጠ ።

ኢየሱስ ወደ ፍርድ ሸንጎ ተወሰደ
(ማቴ. 26፡57-68፡ ሉቃ. 22፡54-55፡63-71፡ ዮሐ. 18፡13-14፡19-24)

53 ኢየሱስን ግን ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት ወሰ ዱት ፤ እዚያ የካህናት አለቆች ፡ ሽማግሌዎችና የሙሴ ሕግ መምህራን ተሰብስበው ነበር ። 54 ጴጥሮስም እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ኢየ ሱስን በሩቅ ይከተለው ነበር ። እዚያም ከሎሌ ዎች ጋር ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር ። 55 የካህ ናት አለቆችና የሸንጎው አባሎች ሁሉ በኢየሱስ ላይ ሞት የሚያስፈርድበት ምስክር ይፈልጉ ነበር ፤ ግን አላገኙም ። 56 ብዙዎችም በሐሰት መስክረውበት ነበር ፤ ሆኖም ቃላቸው ሳይስ ማማ ቀረ ።

57 አንዳንዶቹም ተነሥተው እንዲህ ሲሉ በሐሰት መሰከሩብት ፡ 58 “እኔ ይህን በሰው እጅ የተሠራውን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ውስጥ ሌላ በሰው እጅ ያልተሠራ እሠራለሁ ብሎ ሲናገር ሰምተነዋል ።” 59 ይህም ሆኖ ምስ ክርነታቸው አልተስማማም ።

60 ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ቆሞ “ምንም አትመልስምን? እነዚህ ሰዎች በአንተ ላይ የሚያቀርቡብህ ክስ ምንድን ነው?” ሲል ኢየሱስን ጠየቀው ።

61 ኢየሱስ ግን ዝም አለ እንጂ ምንም መልስ አልሰጠም ። ሊቀ ካህናቱም “የቡሩክ እግዚአብሔር ልጅ መሲሕ አንተ ነህን?” ሲል እንደገና ጠየቀው ።

14፡49 ፡- ሉቃ. 19፡47 ፡ 21፡37 ። 14፡58 ፡- ዮሐ. 2፡19 ።

62ኢየሱስም “አዎ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅ
በኀያሉ እግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ታያላ
ችሁ፤ እንዲሁም በሰማይ ደመና ተመልሶ
ሲመጣ ታያላችሁ” አለ። 63ሊቀ ካህናቱም
በቍጣ ልብሱን ቀደደና “ሌላ ምስክር ምን ያስ
ፈልገናል? 64እነሆ ይህን የስድብ ቃል በእግዚ
አብሔር ላይ ሲሰንዝር ሰምታችኋል፤ ታዲያ
ምን ይመስላችኋል?” አለ።

ሁሉም በእንድ ቃል “ሞት ይገባዋል!”
ብለው ፈረዱበት።
65እንዳንዶችም ምራቃቸውን እንትፍ ይሉ
በት ጀመር፤ ዐይኑንም በጨርቅ ሸፍነው
“እንተ ነቢይ ከሆንህ እስቲ ማን እንደመታህ
ዕወቅ” እያሉ በቡጢ ይመቱት ነበር። ሌሎ
ችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።

ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ
(ማቴ. 26፡69-75፡ ሉቃ. 22፡56-62፡
ዮሐ. 18፡15-18፡25-27)

66ጴጥሮስ ከሊቀ ካህናቱ ቤት በታች በግ
ቢው ውስጥ እንዳለ፥ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች
አንድዋ መጣች፤ 67እርስዋ ጴጥሮስ እሳት
ሲሞቅ አይታ ትኩር ብላ ተመለከተችውና
“አንተም እኮ ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበርህ”
አለችው።
68እርሱ ግን “እኔ አላውቅም፤ አንቺ የምት
ዪውም አይገባኝም” ሲል ካደ። ይህንንም ብሎ
ወደ ደጃፉ እንደወጣ ዶሮ ጮኸ።
69ገረዲትዋም ጴጥሮስን አይታ በዚያ ለቆ
ሙት “ይህም እኮ ከእነርሱ ወገን ነው” ስትል
እንደገና ትናገር ጀመር፤ 70እርሱ ግን እንደገና
ካደ።

ጥቂት ቆየት ብሎም በዚያ የቆሙት ሰዎች
ጴጥሮስን “የገሊላ ሰው ስለሆንህ በእርግጥ ከእነ
ርሱ ወገን ነህ” አሉት።
71እርሱ ግን “ይህን የምትሉትን ሰው አላ
ውቀውም” እያለ ራሱን መራገምና መማል
ጀመረ።
72ወዲያውኑ ዶሮ ሁለተኛ ጊዜ ጮኸ፤ ጴጥ
ሮስም “ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ፥ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ” ሲል ኢየሱስ የተናገረው ቃል ትዝ
አለውና ምርር ብሎ አለቀሰ።

ምዕራፍ 15

ኢየሱስ ወደ ጲላጦስ ተወሰደ
(ማቴ. 27፡1-2፡11-14፡ ሉቃ. 23፡1-5፡
ዮሐ. 18፡28-38)

1ጠዋት በማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌ
ዎች፥ ከመሴ ሕግ መምህራን፥ ከሸንጎውም
አባሎች ሁሉ ጋር ተገናኝተው ተማከሩ፤ ከዚ
ያም በኋላ ኢየሱስን አስረው ወሰዱትና ለጲላ
ጦስ አሳልፈው ሰጡት። 2ጲላጦስም “አንተ
የአይሁድ ንጉሥ ነህን?” ሲል ጠየቀው።

ኢየሱስም “አንተ እንዳልከው ነኝ” አለው።
3የካህናት አለቆች ግን ኢየሱስን በብዙ ይወ
ነጅሉት ነበር። 4ስለዚህ ጲላጦስ “በስንት ነገር
እንደሚከሱህ ተመልከት፤ ከቶ ምንም መልስ
አትሰጥምን?” ሲል እንደገና ጠየቀው።
5ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ አሁንም ኢየሱስ
ምንም መልስ አልሰጠም።

ኢየሱስ የሞት ፍርድ ተፈረደበት
(ማቴ. 27፡15-26፡ ሉቃ. 23፡13-25፡
ዮሐ. 18፡39-40፡ 19፡1-16)

6ጲላጦስ በየዓመቱ በአይሁድ ፋሲካ በዓል
ጊዜ እንዲፈታላቸው ሰዎች የጠየቁትን አንድ
እስረኛ ይለቅላቸው ነበር። 7በዚያን ጊዜ በመን
ግሥት ላይ ተነሣሥተው ሰው በመግደል ወህኒ
ቤት የገቡ ዐመፀኞች ነበሩ፤ ከነዚህም ዐመፀ
ኞች አንዱ በርባን የሚባለው ሰው ነበር።
8ሰዎቹም ወደ ጲላጦስ ቀርበው የተለመደውን
ምሕረት እንዲያደርግላቸው ጠየቁት። 9እር
ሱም “የአይሁድን ንጉሥ ፈትቼ እንድለቅቅላ
ችሁ ትፈልጋላችሁን?” ሲል ጠየቃቸው።
10ይህንንም ያለው የካህናት አለቆች ኢየሱስን
አሳልፈው የሰጡት በቅንአት መሆኑን ያውቅ
ስለነበር ነው።
11የካህናት አለቆች ግን “በርባን ይፈታልን
እንጂ ኢየሱስ አይፈታ” ብለው ጲላጦስን እንዲ
ጠይቁ ሰዎቹን አነሣሡ። 12ጲላጦስም “ታዲያ
ይህን የአይሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን ላድር
ገው?” ሲል ሰዎቹን እንደገና ጠየቀ።
13እነርሱም “ስቀለው!” እያሉ እንደገና
ጮኹ።
14ጲላጦስም “ያደረገው በደል ምንድን
ነው?” አላቸው።

እነርሱም “ስቀለው!” እያሉ አብዝተው
ጮኹ።
15ጲላጦስ ሰዎቹን ደስ ለማሰኘት ብሎ በር
ባንን ፈትቶ ለቀቀላቸው፤ ኢየሱስን ግን አስገረ
ፈውና እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠው።

ወታደሮቹ በኢየሱስ አፌዙበት
(ማቴ. 27፡27-31፡ ዮሐ. 19፡2-3)

16ወታደሮቹ ኢየሱስን ወደ አገረ ገዥው
ግቢ ወሰዱት፤ የቀሩትንም ወታደሮች ሁሉ
ጠሩ፤ 17ቀይ ልብስም አለበሱት፤ የእሾኽ አክ
ሊልም ጐንጉነው በራሱ ላይ ደፉበትና፥
18“የአይሁድ ንጉሥ ሆይ! ሰላም ለአንተ
ይሁን” እያሉ በማፈዝ እጅ ይነሡት ነበር።

14፡62 ፡- ዳን. 7፡13። 14፡64 ፡- ዘሌ. 24፡16።

19በመቃ ራስ ራሱን ይመቱት ነበር፤ ምራቃቸ
ውንም እንትፍ ይሉበት ነበር፤ በፊቱም በማላ
ገጥ እየተንበረከኩ ይሰግዱለት ነበር። 20ካፈዙ
ቡትም በኋላ ቀዩን ልብስ አውልቀው የራሱን
ልብስ አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

ኢየሱስ ተሰቀለ
(ማቴ. 27፡32-44፡ ሉቃ. 23፡26-43፡
ዮሐ. 19፡17-27)

21ሲሄዱም ሳሉ የቀሬና ሰው የሆነውን የእ
ስክንድርንና የሩፎስን አባት ስምዖንን ከገጠር
ወደ ከተማ ሲገባ አገኙት፤ የኢየሱስን መስቀል
ይንዲሸከም አስገደዱት። 22ከዚያም በኋላ ኢየ
ሱስን የራስ ቅል እየተባለ ወደሚጠራው ስፍራ
ወደ ጎልጎታ ወሰዱት። 23እዚያም በደረሰ ጊዜ
ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ
ሰጡት፤ እርሱ ግን አልጠጣም። 24ከዚህም
በኋላ ሰቀሉት፤ ልብሶቹንም ዕጣ ተጣጥለው
ተከፋፈሉት። 25ኢየሱስን ሲሰቅሉት ጊዜው
ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ነበረ። 26ወንጀሉንም
ለማመልከት “የአይሁድ ንጉሥ” የሚል
ጽሑፍ ተጽፎ ነበር። 27ከኢየሱስም ጋር ሁለት
ወንበዴዎችን አምጥተው አንዱን በቀኙ፥ አን
ዱንም በግራው ሰቀሉ። [28በዚህም ሁኔታ
ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ” የሚለው የትንቢት
ቃል ተፈጸመ።]**
29በአጠገቡ ያልፉ የነበሩትም ሰዎች ራሳቸ
ውን በንቀት እየነቀነቁ እንዲህ ይሉ ነበር፥
“አዬ! አንተ ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት
ቀን የምትሠራው! 30እስቲ አሁን ከመስቀል
ውረድና ራስህን አድን!”
31በዚህ ዐይነት የካህናት አለቆችና የመሴ
ሕግ መምህራንም እንዲህ እያሉ ይዘባበቱበት
ነበር፥ “ሌሎችን አድኖአል፤ ራሱን ግን ማዳን
እይችልም። 32እርሱ መሲሑ የእስራኤል
ንጉሥ ከሆነ እስቲ አሁን ከመስቀል ይውረድ፤
እኛም እንይና እንመን!”
እንዲሁም ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴ
ዎች ይሰድቡት ነበር።

ኢየሱስ ሞተ
(ማቴ. 27፡45-56፡ ሉቃ. 23፡44-49፡
ዮሐ. 19፡28-30)

33ከቀኑም ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
34ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ኢየሱስ “ኤሎሄ!
ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ!” ብሎ በታላቅ ድምፅ
ጮኸ። ትርጓሜውም “አምላኬ አምላኬ!
ለምን ተውኸኝ?” ማለት ነው።
35በዚያም ቆመው ከነበሩት ሰዎች አንዳን
ዶቹ የእርሱን ጩኸት ሰምተው “እነሆ ኤልያ
ስን ይጠራል!” አሉ። 36ከእነርሱም አንዱ
ሮጠና ሆምጣጤ በእስፖንጅ ሞላ፤ እንዲጠጣ
ውም በመቃ ላይ አድርጎ ለኢየሱስ ሰጠውና
“ቆይ እስቲ ኤልያስ መጥቶ ያወርደው እንደ
ሆን እንይ” አለ።
37ከዚህም በኋላ ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ
ጮኸ፤ ነፍሱም ከሥጋው ተለየች።
38የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች
ተቀዶ ከሁለት ተከፈለ። 39በመስቀሉ ፊት
ለፊት ቆሞ የነበረ የመቶ አለቃ ኢየሱስ እን
ዲት [ጮኾ] እንደሞተ እይቶ “ይህ ሰው በእር
ግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር” አለ።

በጎልጎታ የነበሩ ሴቶች
(ማቴ. 27፡55-56፡ ዮሐ. 19፡25-27)

40በሩቅ ሆነው የሚመለከቱ አንዳንድ ሴቶ
ችም በዚያ ነበሩ። ከእነርሱም መካከል መግደ
ላዊት ማርያም፥ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት
ማርያም፥ ሰሎሜም ይገኙ ነበር። 41እነርሱ
ኢየሱስ በገሊላ በነበረበት ጊዜ ይከተሉትና ያገ
ለግሉት ነበር። እንዲሁም ከኢየሱስ ጋር ወደ
ኢየሩሳሌም የመጡ ብዙ ሌሎች ሴቶች ነበሩ።

ኢየሱስ ተቀበረ
(ማቴ. 27፡57-61፡ ሉቃ. 23፡50-56፡
ዮሐ. 19፡38-42)

42ቀኑ መሽቶ ስለነበር የሰንበት ዋዜማና የዝ
ግጅትም ጊዜ ሆነ፤ 43በዚያኑ ጊዜ የአይሁዳው
ያን ሸንጎ አባል የነበረ ዮሴፍ የሚባል የተከበረ
የአርማትያስ ሰው መጣ። እርሱም የእግዚአብ
ሔርን መንግሥት በተስፋ የሚጠባበቅ ሰው
ነበር። በድፍረት ወደ ጲላጦስ ፊት ቀረበና የኢ
የሱስ አስከሬን እንዲሰጠው ለመነ። 44ጲላጦ
ስም “እንዴት እንዲህ በቶሎ ሞተ?” ብሎ
ተደነቀ። የመቶ አለቃውንም ጠርቶ “በእርግጥ
ከሞተ ቆይቶአልን?” ሲል ጠየቀው። 45የኢየ
ሱስን መሞት ከመቶ አለቃው ከሰማ በኋላ አስከ
ሬኑን እንዲወስድ ለዮሴፍ ፈቀደለት። 46ዮሴፍ
አዲስ የከፈን ልብስ ገዝና የኢየሱስን አስከሬን
ከመስቀል አውርዶ ገነዘው፤ ከአለት ተወቅሮ
በተዘጋጀ መቃብር ውስጥ ቀበረው። ትልቅ
ድንጋይም አንከባሎ መቃብሩን ዘጋ። 47መግደ
ላዊት ማርያምና የዮሳ እናት ማርያም ኢየሱስን
የት እንደቀበሩት ይመለከቱ ነበር።

** 15፡28 አንዳንድ ቅጂዎች ቍ. 28 ይጨምራሉ፤ ታትሞ በሱታ. 22፡37 ያለውን ይመስላል።
15፡21 ፡- ሮም 16፡13። 15፡24 ፡- መዝ. 22፡18። 15፡28 ፡- ኢሳ. 53፡12። 15፡29 ፡- መዝ. 22፡7፤ 109፡25፤ ማር. 14፡58፤ ዮሐ. 2፡19። 15፡34 ፡- መዝ. 22፡1። 15፡36 ፡- መዝ. 69፡21። 15፡38 ፡- ዘጸ. 26፡31-33። 15፡40-41 ፡- ሉቃ. 8፡2-3።

ምዕራፍ 16

ኢየሱስ ከሞት ተነሣ

(ማቴ. 28፡1-8፤ ሉቃ. 24፡1-12፤ ዮሐ. 20፡1-10)

1 የሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማር
ያም ፥ የያዕቆብ እናት ማርያም ፥ ሰሎሜም
ሆነው የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት ሽቶ ገዙ ።
2 እሑድ ጠዋት በማለዳ ልክ ፀሐይ ስትወጣ ወደ
መቃብሩ ሄዱ ። 3 እነርሱ "ድንጋዩን ከመቃብሩ
ደጃፍ ማን አንከባሎ ይከፍትልናል" በማለት እየ
ተነጋገሩ ይሄዱ ነበር ። 4 ምክንያቱም መቃብሩ
የተዘጋበት ድንጋይ እጅግ ትልቅ ስለነበረ ነው ።
ቀና ብለውም በተመለከቱ ጊዜ ድንጋዩ ወደ ጐን
ተንከባሎ አዩት ። 5 ወደ መቃብሩም በገቡ ጊዜ
ነጭ ልብስ የለበሰ ጕልማሳ በስተቀኝ በኩል ተቀ
ምጦ በማየታቸው ደነገጡ ።
6 እርሱ ግን እንዲህ አላቸው ፥ "አይዞአችሁ
አትደንግጡ ፤ እናንተ የምትፈልጉት ተሰቅሎ
የነበረውን የናዝሬቱን ኢየሱስ እንደሆነ ዐውቃ
ለሁ ፤ እርሱ ተነሥቶአል ፤ እዚህ የለም ፤ የተቀ
በረበትም ቦታ ይኸውላችሁ ፥ ተመልከቱ ።
7 አሁንም ሂዱ ፤ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ
ከዚህ በፊት ኢየሱስ እንደነገራችሁ እርሱ ወደ
ገሊላ ቀድሞአችሁ ይሄዳል ፤ በዚያም ታዩታላ
ችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው ።"
8 ሴቶቹም በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ከመቃ
ብር ወጥተው ሸሹ ፤ እጅግ ፈርተው ስለነበር
ምንም ነገር ለማንም አልተናገሩም ።9*

ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ታየ10*

(ማቴ. 28፡9-10፤ ዮሐ. 20፡11-18)

[9 ኢየሱስ እሑድ በማለዳ ከሞት ከተነሣ
በኋላ መጀመሪያ ሰባት አጋንንት ላወጣላት
ለመግደላዊት ማርያም ታየ ። 10 እርስዋ ሄዳ
በሐዘንና በለቅሶ ላይ ለነበሩት ተከታዮቹ ነገ
ረች ። 11 እርስዋ "ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ በሕ
ይወት አለ ፤ እኔም በዐይኔ አይቻዋለሁ" ብላ
ነገረቻቸው ፤ እነርሱ ግን አላመኑአትም ።

ኢየሱስ ለሁለት ደቀ መዛሙርት ታየ

(ሉቃ. 24፡13-35)

12 ከዚያም በኋላ ወደ ገጠር ይሄዱ ለነበሩ
ሁለት ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ በሌላ መልክ
ታያቸው ። 13 እነርሱም ተመልሰው ለቀሩት
ደቀ መዛሙርት ነገሩአቸው ፤ ደቀ መዛሙርቱ
ግን እነዚህንም አላመኑአቸውም ።

ኢየሱስ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ታየ

(ማቴ. 28፡16-20፤ ሉቃ. 24፡36-49፤
ዮሐ. 20፡19-23፥ ሐ.ሥ. 1፡6-8)

14 ከዚያም በኋላ ዐሥራ አንዱ በማእድ ቀር
በው ሲበሉ ኢየሱስ ታያቸው ፤ ባለማመናቸውና
"ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶ በሕይወት አለ ፤ በዐይ
ናችንም አይተነዋል" ብለው የነገሩአቸውንም
ሰዎች ቃል ባለመቀበላቸው ፥ ልባቸውም በመ
ደንደኑ ነቀፋቸው ። 15 እንዲህም አላቸው ፥
"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ፤ ለሰው ሁሉ ወንጌልን
አስተምሩ ። 16 የመነና የተጠመቀ ይድናል ፤
የማያምን ግን ይፈረድበታል ። 17 በእኔ የሚያ
ምኑ ሁሉ እነዚህን ተአምራት የማድረግ ሥል
ጣን ይኖራቸዋል ፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ፤
በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ ፤ 18 እባቦችን ቢይዙ
ወይም የሚገድል መርዝ እንኳ ቢጠጡ አይጐዳ
ቸውም ፤ እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ሲጭኑ
በሽተኞቹ ይድናሉ ።"

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ወጣ

(ሉቃ. 24፡50-53፤ ሐ.ሥ. 1፡9-11)

19 ጌታ ኢየሱስ ይህን ሁሉ ከነገራቸው በኋላ
ወደ ሰማይ ወጣ ። በእግዚአብሔሩም ቀኝ ተቀ
መጠ ። 20 ደቀ መዛሙርቱም በየስፍራው ሁሉ
እየሄዱ አስተማሩ ፤ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ
ነበር ። ተአምራትንም የማድረግ ሥልጣን በመ
ስጠት የትምህርታቸውን እውነተኛነት ያጸና
ነበር ።]

9* 16፡8 በአንዳንድ የጥንት መጻሕፍት በዚህ ምዕራፍ በቍጥር 8 ቀጥሎ ያለው ቃል ይገኛል ፦ "ሴቶቹ ወደ ጴጥሮስና ወደ ጓደኞቹ ሄደው መልእክቱ የነገራቸውን ሁሉ እውሩብኛቸው ፤ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ደኅንነት የሆነውን ፡ የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በደቀ መዛሙርቱ አማካይነት ላከ ።"

10* 16፡9 አንዳንድ ቅጂዎችና የጥንት ትርጉሞች ከቍ. 9-20 ያለውን ከፍል አያጨምሩም ።

16፡7 ፦ ማቴ. 26፡32 ፤ ማር. 14፡28 ። 16፡15 ፦ ሐ.ሥ. 1፡8 ። 16፡19 ፦ ሐ.ሥ. 1፡9-11 ።